# ፅድቅ በእምነት

በአድያምሰገድ ወልደማርያም

የወንጌል ፀጋ አገልግሎት © የመጀመሪያ ዕትም ነሃሴ 2000 ዓ.ም

**www.Gospelofgraceministry.com**

## ፅድቅ በእምነት

## የሮሜ መጽሐፍ ጥናት

**©Copyright 2008 - Adiamseged woldemariam**

All rights reserved. This book may not be copied or reprinted for commercial gain or profit. The use of Short quotations for group study and teaching for seminars is permitted. Permission will be granted upon request. The scripture quotations are from **The bible in Amharic 1962 by united bible society.**

የደራሲው መብት የተጠበቀ ነው

በካሊፎርኒያ፤ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ታተመ

Cover Design: By Exodus Christian Web Design & Graphics Studio

# አድያምሰገድ ወልደማርያም

## ፅድቅ በእምነት

« ክርስትና በትንሳኤው ሐይል የህይወት ለውጥ ነው »

ሕይወቴ ተመልሶ እንደገና እንዲያንሰራራ፣ የጸጋው ጉልበት የበለጠ በህይወቴ ይገለጥ ዘንድ ጌታ እንድ አካል አድርጎ ሳጣመረኝ፣ በከፋውና በሻከረው የሕይወት ዘመኔ ብቅ ብላ ለደገፈችኝ የልብ ሰው ለሆነችው ለምወዳት ባለቤቴ እንዲሁም እጅግ ለምወዳቸው ለልጆቼ ይህን መጽሐፍ በገጸ በረከትነት ሳበረክት ታላቅ ደስታ ይሰማኛል።

# ምስጋና

መቼም አንድ መጽሐፍ ሲጻፍ የየራሳቸውን ድርሻ የሚወጡ በርካታ ሰዎች መኖራቸው እሙን ነው:: ይህም መጽሐፍ ለዚህ ቋሚ ምስክር ነው:: የሁሉንም ድርሻና ተሳትፎ በዚህች አጭር ጽሑፍ ለመዳሰስ መሞከር «አባይን በማንኪያ» ይሆናልና አልሞክረውም:: ሆኖም ግን የጎላ ድርሻ ያበረከቱትን አለመጥቀስ ደግሞ ሰውንም እግዚአብሔርንም መበደል ነውና ጥቂቶቹን ልጠቅስ እወዳለሁ:: ከሁሉ አስቀድሞ ግን፣ ሳላውቀው ላወቀኝ፣ ሳልፈልገው ለፈለገኝ፣ ከኃጢአተኞች ዋና የሆንኩትን እኔን በበረሃማው አገር በሱዳን ከተማ ላገኘኝ፣ ዓለምም ሳይፈጠር አስቀድሞ ለወደደኝ፣ ራሱንም ለእኔ በሞት አሳልፎ ለሰጠ ለመድኃኒቴ፣ ለልዑል እግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋናዬ ይድረሰው:: ይህን ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የጻፈውን መጽሐፍ በትምህርት መልክ እንድጽፍ በርካታ ወራቶችንና ዓመታትን ከእኔ ጋር በመሆን በሀዘን፣ በደስታ፣ በለቅሶና በብዙ ፈተና ውስጥ ሳልፍ ላጽናናኝና ላበረታኝ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋናዬ ይድረሰው:: በመጨረሻም ስወድቅ ላነሳኝ እስከዛሬም ፈጽሞ ለተሸከመኝ የሁሉም አባት ለሆነ ለቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬን ይድረሰው::

ይህን መጽሐፍ በኮምፒውተር ለመጀመሪያ ግዜ ታይፕ በማድረግ ለረዳችኝ ቀንና ሌሊት አብራኝ ሳትታክት ለሠራች ለባለቤቴ ለዮዲት አለሙ ምስጋና አቀርባለሁ::

ከዚያም ይህን መጽሐፍ በኮምፒውተር ታይፕ ያደረገች ብዙውን ጊዜዋን መስዋእት ያደረገች ወረቀቶችን በማስተካከል እንደገናም ደጋግማ በማረም ለረዳችኝ ለአስካል መስፍን ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

እጉንት ከእጥንት እንዲጋጠም ጅማት እንደሚያስፈልግ ሁሉ መጽሐፉን ከዓመት በላይ ጊዜ ወስዶ በጥልቀት በማረም፣ ትምህርቱን በማጋጠም፣ በማስተካከል እንዲሁም ከእርማት አልፎ በ የጣልቃው ሊገቡ የሚገባቸውን ማብራሪያዎች በመስጠትና በማስገባት እጅግ ለደከመ ለወንድም አሸቴ በለጠ እንዲሁም የታረመውን ጽሁፍ እንደገና ታይፕ በማድረግ ለረዳችን ለባለቤቱ ለወ/ሮ መሠረት ጥላሁን የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

# ጽድቅ በእምነት

## የሮሜ መጽሐፍ ጥናት

በአድያምሰገድ ወልደማርያም
የወንጌል ጸጋ አገልግሎት

የመጀመሪያ ዕትም ነሃሴ 2000 ዓ.ም.

# አስተዋፅዖ


መግቢያ:- ———————————————— 3

ምዕራፍ አንድ:- በወንጌል አላፍርም———————— 8

ምዕራፍ ሁለት:- አስተማሪ ሆይ! ራስህን አስተምር ——— 40

ምዕራፍ ሦስት:- ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል ———— 53

ምዕራፍ አራት:- አብርሃምም አመነ ————— 75

ምዕራፍ አምስት:- በእግዚአብሔር ጻድቅ
የመባል ፍሬዎች ———— 88

ምዕራፍ ስድስት:- ጸጋ እንዲበዛ ...? ———— 107

ምዕራፍ ሰባት:- ከሕግ መፋታት ———— 123

ምዕራፍ ስምንት:- የልጅነት መንፈስ ———— 137

ምዕራፍ ዘጠኝ:- ለእሥራኤልም ተስፋ አለ ———— 158

ምዕራፍ አሥር:- ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው ———— 177

ምዕራፍ አሥራ አንድ:- ሁሉ ከእርሱና በእርሱ
ለእርሱም ነውና ———— 189

ምዕራፍ አሥራ ሁለት:- ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት —— 205

ምዕራፍ አሥራ ሦስት:- ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ———— 219

ምዕራፍ አሥራ አራት:- እርስ በእርስ መቀባበል ———— 225

ምዕራፍ አሥራ አምስት:- የተጠናቀቀ አገልግሎት ———— 235

ምዕራፍ አሥራ ስድስት: ስንብት ———— 242

# የጸሐፊው ማስታወሻ

የተማረው ቢሆን ያልተማረው፣ ደሃው ቢሆን ሃብታሙ፣ የጽድቅ ጥያቄ የአዳም ዘር ሁሉ ጥያቄ ነው። ልዩነቱ የሚመጣው «ጽድቅ እንዴት ይገኛል?» ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው ምላሽ ላይ ነው።

አንዳንዱ ወገን፣ «ጽድቅ የሚገኘው በሥራ ነው» ብሎ ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቅ ሩጫውን ሲያያዘው፣ የሩጫው ርቀት በጨመረ መጠን ኃጢአቱ ይበልጡኑ ጎልቶ ሲታየው፣ እርሱም ወዮ! ሲል፣ የረዳት ያለህ! ብሎ ሲጮህ፣ ሊጠብቀው ደፋ ቀና የሚልለት ሕግ ለጩኸቱ መልስ ሲነፍገውና ኃጢአትን እምቢ! የሚልበትን ብቃት አልሰጥ ሲለው፣ «እግዚአብሔር ሰው የማይችለውን ከባድ ሸክም በሰው ላይ የጫነ ጨካኝ ፈራጅ ነው»። ብሎ ደምድሞ ሲቀመጥ፣ በራስ የጽድቅ ሩጫ የእግዚአብሔርን ደረጃ ለማሟላት ያደረገው ግስጋሴ ከጫፍ አሳደርስ ብሎት ተስፋ ሲቆርጥ ይስተዋላል። ሌላው ወገን ደግሞ፣ «ጽድቅ የሚገኘው የሃይማኖትን ወግና ሥርዓት ጥንቅቅ አድርጎ በመፈጸም ነው»። ብሎ ያንንም ለመፈጸም ደፋ ቀና ሲል፣ መንገዱም አልገፋ ሲለው፣ አንዳንዴም ሲሳካለት ዘና ሲል፣ ወዲያው ሲያቅተው ደግሞ ራሱን ሲኮንን፣ ብቻ በሁለቱም ራሱን የከፋ ኃጢአተኛ ሆኖ ሲያገኘው በፍጻሜው «የአዳኝ ያለህ» ሲል ይሰማል።

ሦስተኛው ወገን ደግሞ፣ «በዚህ ምድር ከሰው ጋር ተቀላቅሎ እየኖሩ ጽድቅን ማሰብ ሞኝነት ነው»። ብሎ ሰው ወደሌለበት በመመነን ራሱን ወደ ዱር፣ ገደልና ዋሻ ወስዶ «እፎይ! ከማየውና ከምሰማው ተገላገልሁ» ብሎ ሲያስብ ትቶት ሊሄድ ያልቻለው እኔነቱ ዱር ሳይፈራ፣ ገደል ሳይገድበው አብሮት ተገኝቶ ሃሳቡን ሲያረክሰው፣ በአፉ ያላወጣው፣ ለሰው ያልገለጠው፣ ግን ከህሊናው ሊሰውረው የማይችል የውስጥ

እድፈት ውስጡን ሲሞግተው፣ «እዚህም?...» ብሎ በራሱ ሲገረም፣ ወዲያው መልስ፣ «ታዲያ የት ልሂድ?» ብሎ ሲማጸን ይስተዋላል።

ይህ አይነቱ የጽድቅ ረሃብና ጥማት ብዙ ሩቅ መንገድ ካስኬዳቸው መካከል ጀርመናዊው መነኩሴ ማርቲን ሉተር ተጠቃሽ ነው። ማርቲን ሉተር ከነቤተሰቡ የተዋጣለት ሃይማኖተኛ ነበር። በአንድ ወቅት ግን የሕግ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ትምህርት ቤቱ በጉዞ ላይ እንዳለ መብረቅ በአጠገቡ ወድቆ እርሱንም ገፍትሮ መሬት ጣለው፣ ደግነቱ እርሱ ላይ አልወደቀምና ከሞት ተረፈ። ሆኖም ግን በውስጡ «ዛሬ ሞቼ ቢሆን ኖሮ ነፍሴ የት ትገባ ነበር?» ሲል አሰበ። ስለዚህም ለነፍሱ ጽድቅን ሊገበይላት ያዋጣል ወዳለው ስፍራ መነነ፤ የሚጠበቅበትን ሁሉ ተጠንቅቆ በመፈጸም፣ ራሱንም በጾም በማድከም፣ ሰዓታት የተቆጠሩበትን «ንስሃ» ገባ። ሆኖም የበለጠ ኃጢአተኛ መሆኑን ተረዳ እንጂ የነፍስ ዕረፍት ሊያገኝ አልቻለም። ስለዚህም «እግዚአብሔር ሰው የማይችለውን ነገር እንዲፈጽም በላዩ ላይ የጫነ ጨካኝ ፈራጅ ነው»። የሚል አቋም ያዘ።

አስገራሚው ነገር ግን፣ ሉተር ይህንን አቋሙን እንደያዘ የስነ መለኮት አስተማሪ መሆኑ ነው። በዚሁ ሙያ ተሰልፎ መዝሙረ ዳዊት ሃያ ሁለተኛውን ምዕራፍ ሲያስተምር የያዘውን አቋም የሚያስለውጥ ሞጋች ነገር ገጠመው። ነገሩ እንዲህ ነው:- «እግዚአብሔር ጨካኝ ቢሆን ኖሮ ኃጢአተኛ ውን ለማዳን በአንድ ልጁ ይህንን ያህል አይጨክንበትም ነበር» የሚል። ይህ እውነት ስለ እግዚአብሔር የነበረውን አቋም አስለወጠው። ከጥቂት ጊዜያትም በኋላ የሮሜን መጽሐፍ ሲያስተምር በምዕራፍ አንድ ቁጥር አሥራ ስድስትና አሥራ ሰባት ላይ ጽድቅ የሚገኘው በእምነት መሆኑን የሚያስረዳውን «እፎይ!» የሚያሰኝ ብርሃን አየ ለሉተር የጽድቅ ፀሐይ ወጣችለት። ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ጽድቅ በእምነት በመቀበል ዳግም ተወለደ።
በዚህም ምክንያት የእርሱም የቤተክርስቲያንም ጨለማ ተገፈፈ።

እንግዲያው፣ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለውና መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል የገለጠው እውነት የጽድቅ ጩኸት በውስጡ ያለበት ሕዝብ ሁሉ ሊሰማው የሚገባ እውነት ነው ማለት ነው። ይህ ሃሳብ ብዙ ሊጻፍበት፣ ሰዎች ከጥፋት ሊተርፉበት፣ ከመፍጨርጨርና የራስን ጽድቅ ለማቆም ከሚደረግ የማይሳካ ትግል ለማትረፍ ብርሃኑ የበራለት ሁሉ ሊዘምሩበት የሚገባ የማይሸፈን እውነት ነው። አንድን ጸሐፊ ለመጻፍ የሚያነሳሱት በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም በርካታ ምክንያቶች ይኖሩታል። ዋናው ግን የበራለትን የጽድቅ በእምነት ብርሃን የእርሱ ብቻ አድርጎ በእንቅብ ውስጥ ሊሰውረው አለመቻሉና ለጽድቅ ሲሉ በዱር በገደል የሚንከራተቱ ወገኖችን ለመታደግ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያስቀመጠውን ሸክም ቻል ሊለው አለመቻሉ ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፣ «ጽድቅ በእምነት» መሆኑ ገብቶአቸው በክርስቶስ አምነው የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ወገኖቹ የእግዚአብሔርን ቃል በተብራራ መንገድ ለመረዳት የሚያስችላቸው የጥናት መጽሐፍ በበቂ መንገድ እንዳላገኙ በአገር ቤት ለአገልግሎት ካደረጋቸው ጉዞዎች መረዳቱና በዚህም በውስጡ የተቀጣጠለው እሳት በግ ብሎ መንደዱ ነው።

ይህንን የጥናት መጽሐፍ ለማንበብ እድል የምታገኙ ወገኖች ሁሉ ይህ እሳት በእናንተም እንዲነድና በምድራችን የሚታየውን በቋንቋችን የተዘጋጀ የማገናዘቢያ መጽሐፍት እጥረት ለማስወገድ በኔታ ጸጋ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንደ ክርስቶስ አካል ብቶች የበኩላችንን እንድናደርግ ጸሐፊው ጥሪውን ያቀርባል።

በተፈጥሮ ምግብ ረሃብተኝነት ዘመኑ የተገባደደበት ወገናችን የነፍስ ምግብ ረሃብተኛ ሆኖ አጭሩን ዘመኑን እንዳይጨርስ በሰፊ ገበታ ለመመገብ ዕድሉን ያገኘን ሁሉ ለሕዝባችን አንድ ሁለት የማብራሪያ መጻሕፍት አዘጋጅተን ለማቅረብ እንትጋ። ይህንን ጸሐፊ የረዳ ጌታ ስለእናንተም አይደክምም፤ ከእኛም

በብዙ አስቸጋሪ መንገድ አልፈው ጥሩ የታይፕ ማሽን እንኳዋን ሳይኖር በጌታ ታምነው መሠረት የጣሉ ምስክሮች አሉንና እንበርታ።

ይህችን ትንሽ ዘር እግዚአብሔር ለምድር የምትተርፍ ፍሬ አድርጎ ያብዛት። መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል ወደ ሮሜ ሰዎች ያሰማው፣ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለው እውነት በኢትዮጵያ ዱር ገደሎች፣ ዋሻና ሸንተረሮች ሁሉ ያለከልካይ ያስተጋባ። አሜን!!

ኢየሱስ በክብር ይመጣል!!

አድያምሰገድ ወልደማሪያም

የሮሜ መጽሐፍ እጅግ ጥልቅ የሆነ የደህንነት ሚስጥርን እና ዋና ዋና የእግዚአብሔርን መልካምነት የሚገልፅልን መልእክት ነው። ታዲያ ወንድማችን ብዙ የማገናዘቢያና የማጣቀሻ መፅሐፍቶች በማይገኝበት ሀገራችን ይህንን መጽሐፍ ምእራፍ በምእራፍ፤ በመግቢያ ክፍሎ ግልፅ በሆነ መንገድ ተንትኖ እንዲጠናበት ማቅረቡ ጅማሬውን በማስፋት እንዲቀጥልበት የመንፈስ ቅዱስ ሙሉ እገዛ እንዲረዳው እግዚአብሔር አብዝቶ እንዲባርከው የምድርቱን ህዝብ ወክዬ እባርከዋለሁ!

አቶ ፀጋዬ ሀብቴ

እ.አ.አ. በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መርቲን ሉተር የተባለው ጀርመናዊው መነኩሴና የዩኒቨርሲቲ መምህር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጽድቅ ታስተምርና ትከተል የነበረውን የሕግ መንገድ በመቃወም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እጅግ ወሳኝና ስር - ነቀል የሆነ ተሃድሶአዊ ለውጥ ለማስገኘት የበቃው በሮሜ መልዕክት ውስጥ እንደተጻፈው፣ ጽድቅ የሚገኘው በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው። የሚል የማያወላውል አቋም በመያዝ እንደ ነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል።

ማርቲን ሉተር፣ በአቋሙ ጽኑዕ ሆኖ በጊዜው ኃያል የነበረችውን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቋቋም የቻለው፣ የሮሜ መልዕክት የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሰው የሚቆጠረው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ በእምነት አማካይነት ብቻ ስለሆነ በሥራ ለመጽደቅ የሚጥሩትን ተስፋ ስለሚያስቆርጥ ነው።

ይህንን ለቤተክርስቲያን ተሃድሶና ለውጥ፣ ለማኅበረ ክርስቲያኑም መንፈሳዊ ዕድገት እጅግ ጠቃሚ የሆነውን የሮሜን መልዕክት ወንድም አድያምሰገድ ወ/ማርያም በቅደም ተከተል፣ በቀላሉ ለመረዳት በሚያስችል ስልትና አቀራረብ የተቀነባበረ ገለጻን ያካተተ መጽሐፍ አዘጋጅቶ አቅርቦልናል። የመጽሐፉ ቅንብርና ይዘት ጥራትና ጥልቀት ያለው በመሆኑ ወንድማችን የእግዚአብሔርን ቃል ለወገኖቹ ለማካፈል ያለውን ችሎታና ጉጉት ያሳየናል። ስለዚህ አብያተክርስቲያናት፣ የመንፈሳዊ ትምህርት ተቋሞች፣ ግለሰቦች ወ.ዘ.ተ. መጽሐፉን ገዝተው ቢጠቀሙ በጣም እንደሚባረኩበት አልጠራጠርም።

በተጨማሪም ወንድም አድያም በጀመረው « የወንጌል ጸጋ አገልግሎት» መሣሪያነት በመንፈሳዊ ትምህርቶችና በተዛማጅ ዘርፎች ወገኖቹን በሰፊው ለማገልገል የወሰደውን እርምጃና ጥረት እያደነቅሁ፣ ለአገልግሎቱ መሳካት የሚያስፈልገው ድጋፋችን እንዳይለየው በትህትና አሳስባለሁ።

በአትላንታ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

ፓስተር መስፍን ታደሰ

# መግቢያ

## መልዕክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

መልእክቱ የተጻፈው በክረምት ወራት በቆሮንቶስ ከተማ በሐዋርያው ጳውሎስ ሶስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው እንደሆነ ይታመናል። (የሐሥ 20:3-6፤ ሮሜ 16:2 ፤ 1ቆሮ 1:1) ጊዜውም ከ55-60 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት እንደሆነ በብዙ ሊቃውንት ይታመናል። መልእክቱ በዋና ጸሐፊው በጤርጥዮስ አማካኝነት እንደተጻፈ (ሮሜ 16:22) ያመለክታል። ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ሲነሳ ነው የፃፈው የሚል እምነትም አለ (ሮሜ15:22) ። በሌላ በኩል ደግሞ መልእክቱ ከቆሮንጦስ ከተማ በፊቨን እጅ ተልኳል ተብሎም ይታመናል (ሮሜ 16:1-2) ።

## የመልዕክቱ ጸሐፊና ማንነቱ

የሮሜ መልዕክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፣በጸሐፊነት ጤርጥዮስ እንደረዳው ከዚያው ከመጽሐፉ እናገኛለን (16:22) ።

ጳውሎስ የሚለው ስም ሮማዊ ስም ሲሆን በሮሜ ተወላጅነቱ ያገኘ ው ነው (ሐሥ 22:3፣27-28) ። ጳውሎስ ተወልዶ ያደገው በጠርሴስ ከተማ ሲሆን ስመ ጥር በሆነው በኪልቅያ ዩኒቨርሲቲ ተምሯል (ሐሥ 21:39) ።በወጣትነቱ ዘመን ደግሞ በኢየሩሳሌም ከገማልያል እግር ስር በመሆን የአይሁድን ትምህርት ጠንቅቆ ተምሯል (ሐሥ 22:3) ። የግሪክ ቋንቋ ዕውቀት ስለነበረው የሮሜ መልዕክት በዚያ መልክ እንዲጻፍ ተጽዕኖ አድርጎበታል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በተጨማሪም የድንኳን ስፌት ሙያም ነበረው። ይህንንም ሙያ በአገልግሎቱ አንዳንድ አስቸጋሪ ወቅቶች እንዲጠቀምበት ረድቶታል። በዚያን ዘመን ድንኳን የሚሠራው ከፍየል ቆዳ ነበር።

ጳውሎስ የሮሜን መጽሐፍ የጻፈው ከሃያ ሁለት ዓመታት አገልግሎት በኋላ እንደሆነ ይታመናል። መጽሐፉንም የጻፈበት አንደኛው ምክንያት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ምናልባት በዚያ ወደ ሞት የሚያደርስ መከራ ቢያጋጥመው ወንጌል ግን እንዳይቋረጥ ስለ ወንጌል የጠለቀ ትምህርት ለመስጠት ነበር የሚል ነው። ሮም በወቅቱ የመላው ዓለም ዋና ከተማ ስለነበረች ይህ ጥልቅ መልዕክት ያዘለ ደብዳቤ ለሁሉም አብያተክርስቲያናት ይደርሳል ብሎ በብርቱ ያምን ስለነበረ ነው የሚል አመለካከትም አለ።

በዶክትሪን ትምህርት ቀዳሚ ስፍራ የያዘ ስለሆነ የሮሜ መጽሐፍ ከደብዳቤዎቹ ሁሉ በፊት ቀድሞ ተቀምጦአል:: ሆኖም ግን ከደብዳቤዎቹ ሁሉ ቀድሞ የተጻፈ አይደለም::

## የመልዕክቱ ዋና ሃሳብ

የሮሜ መልዕክት ዋና ሃሳብ «ጽድቅ በእምነት» የሚል ነው:: ከዚህ የጽድቅ መንገድ ውጪ የሆኑት ደግሞ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚጠብቃቸው መሆኑንም የሮሜ መጽሐፍ ያለማወላወል ይገልጻል:: ይህንንም አንባቢዎች ሊስቱት በማይችሉት መንገድ ለማቅረብ ሐዋርያው የተጠቀመው ዘዴ በችሎት ፊት የሚደረገውን የፍትህ ሂደት በምሳሌነት በመጠቀም የሚያነሳቸውን ነጥቦች ለሙግት በሚቀርብ ዓይነት ጥያቄ ያቀርባቸዋል:: ሐዋርያው የተከተለው መደበኛ የሆነውን የሙግት አካሄድ በመሆኑ እንደሰው ልማድ የሚነገሩ ንግግሮችና አስተሳሰቦች ይገኙበታል:: የሮሜን መጽሐፍ ስናጠና ልንጠነቀቅ የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የሚከተለው ነው :: በዚህ መጽሐፍ ጻድቅ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው ፍጹም ሰው ነው፤ የተኮነነው ደግሞ በነገር ሁሉ ትክክለኛ አይደለም ማለት አይደለም:: መግለጥ የተፈለገው በሕግ ዓይን ሰውዬውም ሆነ ሴትዮዋ ሲታዩ ያንን ይመስላሉ የሚለውን ነው:: በዘዳ 25:1 እንደምናነበው ህግ አድርግ አታድርግ ይላል እንጂ ፍጽምናን አያመጣም:: ሕግ የሚመለከተው ትዕዛዞቹ መፈጸም አለመፈጸማቸውን እንጂ የልብን ዝንባሌ አይደለም::

የክርስቶስ ወንጌል የጸጋው ወንጌል ነው:: ይህም ጸጋ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የጽድቅ ሥራ አማካኝነት ኃጢአተኛውን የሰው ዘር ያጸደቀበት፤ የጸደቀውም ሰው በእምነቱ በመጽናት የጽድቅን ሕይወት መምራት የሚችልበት የሕይወት መንፈስ ሕግ የሰጠበት፤ ከዚያም የተነሳ የቅድስናን ሕይወት (sanctification) እንድንኖር የሚያስችለንን ስጦታ የተቀበልንበት ነው:: ይህም ክቡር ስጦታ የጽድቁ ክብር የተገለጠበት ስጦታ ነው (ሮሜ 3:22-24 ፤ 5:2) ::

መዳን የሚባለው እውነትም ይህንን ድንቅ የእግዚአብሔር ቸርነት ያካተተ ነው:: ደህንነት ኃጢአተኛው ሰው በመስቀሉ ሥራ የጸደቀበት ብቻ ሳይሆን ይህንን የጽድቅ ሕይወት መኖር የሚልበትን የእግዚአብሔር ኃይል ያገኘበት ነው (ሮሜ 1:16-17) ::

እንግዲያው ደህንነት የመለኮት ሥራ ነው እንጂ የእኛ አይደለም። ይህ ከሆነ ደግሞ በቅድስና (holiness) ለመኖር የሚያስችለንም በእኛ የጀመረውን መልካም ሥራ (sanctification) የሚፈጽመውም እርሱ ነው። ይህ እውነት በሕይወታችን ተገልጦ እናየው ዘንድ ብልቶቻችንን የጽድቅ መሣሪያ (ሮሜ 6:19) ማድረግና በአዕምሮአችን መታደስ መለወጥ (ሮሜ 12:2) ይገባናል። የሮሜ መልዕክት ይህንን እውነት በግልጽ የሚያስቀምጥ ብርቱ መልዕክት ነው።

የሮሜ መልዕክት በክርስቶስ ሥራ የጸደቁ ቅዱሳን፣ እርስ በእርሳቸው፣ ከማህበረሰቡ ጋር፣ እና ከመንግስት ጋር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ መኖር እንዳለባቸውም ግልጽ መመሪያና ማሳሰቢያ የሚሰጥ ሚዛናዊ መልእክት ያዘለ መጽሐፍ ነው።

ማጠቃለያና ሰላምታ

ሐዋርያው ጳውሎስ በአብዛኞቹ መልዕክቶቹ እንደሚያደርገው ሁሉ የሮሜንም መልዕክቱን የሚደመድመው በስንብት ሰላምታ ነው። በዚህ መጽሐፍ ለበርካታ ሰዎች የራሱን ሰላምታ ከማቅረቡም ባሻገር የአገልግሎት አጋሮቹም በሮሜ ለሚገኙ ቅዱሳን ያስተላለፏቸውን ሰላምታዎች ጨምሮ አስተላልፏል።

ከመልዕክቱ እንደምንረዳው ሐዋርያው ሮሜን ለመጎብኘት ያቀደው እግረመንገዱን ነው። ስለዚህ ቀድሞ ሮም የመሄድ መሻት አልነበረውም ማለት ነው። ዘወትር ግን የሮሜን ሰዎች ለማየት ይጓጓ ነበር። ሆኖም ባሰበው መንገድ ሲጎበኛቸው ባቀደባቸው ስፍራዎች የመሄድ ዕድል አልገጠመውም። በዚህኛው ጉዞውም ሊሄድ ያሰበባት አገር ስፓኝ ነበረች (ሮሜ 15:24) ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ያስተላለፈውን የስንብት ሰላምታ ስንመለከት በጣም በትልቅ ጥንቃቄ ሊታወሱ የሚገባቸውን ሁሉ በማስታወስ እንዳቀረበ እንመለከታለን። ከዚህም የምንረዳው ሐዋርያው ለሚያገለግላቸውና ለአገልግሎት ባልደረቦቹ ምን ያህል ጥንቃቄ እንደሚያደርግና ልቡ ምን ያህል በሸክም የተሞላ መሆኑን ነው። ወደ ሰላምታው ዝርዝር ስንገባም የሚከተሉትን ዝርዝር ሃሳቦች እናገኛለን።

16:1-2 ጳውሎስ የቤተክርስቲያን ተወዳጅ አስተናጋጅ ከሆነው ከጋይዮስ ለሮሜ ሰዎች ሰላምታን አቀርቦአል (16:23)።

ጋይዮስ በጳውሎስ እጅ በቆሮንቶስ ከተማ የተጠመቀ ነበር የሚል የጠበቀ እምነት በመጽሐፉ ምሁራን ዘንድ አለ።

1ኛ ቆሮ 1:14 የከተማው ግምጃ ቤት ሹም የሆነው ኤርስጦስ በቆሮንጦስ የነበረ ሲሆን ጳውሎስ ከእርሱ ጋር እንደኖረ እንረዳለን። በእርሱም ስም ለሮሜ ሰዎች ሰላምታ ያቀርባል። (ሮሜ 16:23 ፣ ሐሥራ19:22) ጳውሎስ ይህን መልእክት በሚጽፍበት ጊዜ ቤተክርስቲያኒቱን እንዳላያት እናውቃለን። (ሮሜ 1:13። ሮሜ 15:23-24) ቤተክርስቲያኒቱ አይሁድ እና ከአህዛብ የተቀላቀሉ አማኞች አሉባት ። ይህች ቤተክርስቲያን ትልቅ ሳትሆን በቤት ውስጥ ያሉ አምስት ቤተክርስቲያናትን ያቀፈች እንደሆነች እንመለከታለን (ሮሜ 16 :5፣ 10፣ 11፣ 14፣ 15) ። ለምሳሌ የቆሮንጦስና የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያናት ትልልቅ ቤተክርስታያናት ስለነበሩ ጳውሎስ በመልእክቱ « ለ-ቤተክርስቲያን » እያለ ጽፎላቸው ነበር (1ኛ ቆሮ 1:2 ፤ 2ኛቆሮ 1:1 ፤ 1ኛተሰ 1:1) ። በዚህችው ቤ/ክ ያመኑትን አይሁድ ጳውሎስ «የእኔ ወንድሞቼ» በማለት ይጠራቸዋል (ሮሜ 9:3) ። እንዲሁም አህዛብ መኖራቸውን የምንመለከተው ደግሞ በምእራፍ 16 ከተጠቀሱት 24 ስሞች ውስጥ ብዙዎቹ የግሪክና የላቲን ስሞች በመሆናቸው ነው። አንዳንድ የመጽሐፉ አስተማሪዎች ምእራፍ 15 እና 16ትን ከሮሜ መልእክት ጋር ለማከተት ከመቸገራቸው ባሻገር አጠያያቂም ሆኖባቸው ነበር። ይሁን እንጂ ሃሳቡ በሮሜ መልእክት ውስጥ እንዲካተት ሊቃውንቱ ወስነዋል።

ጳውሎስ ምንም እንኳ ከሮም አማኞች ጋር በአካል ተገናኝቶ ባያውቅም በሰላምታው የብዙዎችን ስም ያነሳል። ምናልባት ኤፌሶን ሳለ በአገልግሎቱ ያውቁት የነበሩ አማኞች ወደ ሮም ስለሄዱ ነው ተብሎ ይታመናል። ከነዚህም መካከል ጵርስቂላ እና አቂላ ይጠቀሳሉ። ነዋሪነታቸው በኤፌሶን የነበረ ሲሆን በመካከሉ ግን ወደ ሮም በመሄድ የሮም ነዋሪዎች ሆኑ። ከዚያም በኋላ ከሮም ወደ ኤፌሶን እንደገና በመመለስ ኤፌሶን ኖረዋል (1ኛ ቆሮ 16:19 2ኛ ጢሞ 4:19) ። በኢሲያ አገልግሎቱ ጌታን ተቀብሎ ዳግም የተወለደው ሰው አጤኔጦስ በኤፌሶን የታወቀ ስም ሲሆን ጳዎሎስ ለእርሱም ሰላምታ አቅርቦለታል (ሮሜ 16:5) ።

አንዳንድ ሰዎች ቤተክርስቲያንዋ በሐዋርያው ጴጥሮስ የተመሰረተች ናት ብለው ያምናሉ። ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ የቅዱስ ጴጥሮስን ስም በመልእክቱም ሆነ በሰላምታው ሲጠቅስ አናይም። በሌላ ወገን ደግሞ የቤተክርስታያኒቱ ሐዋርያ እና መስራች ሐዋርያው ጳውሎስ ነው የሚሉም ተገኝተዋል። ይህን

አመለካከት ውድቅ የሚያደርገው ሐኪሙ ሉቃስ በሐዋርያት ስራ 28 :14-15 ያሰፈረው እውነት ነው። ጳውሎስ ከመምጣቱ በፊት በሮም ከተማ አማኞች «ዳግም የተወለዱ» እንደነበሩ ጽሁፉ ይገልፃል።

ይህ የሮሜ መጽሐፍ የነፍስ መብል ነው። በየእለቱ ደጋግመን ብናጠናው የበለጠ እርካታ የሚሰጥ የህይወት ውሃ ወንዝ ሆኖ በውስጣችን ይፈልቃል። ከነዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስ ውበት በጌታ ባመኑት ሁሉ ውስጥ ይገለጥ ዘንድ ልኡል እግዚአብሔር በፍትህ ችሎቱ ውሳኔ ያስተላለፈበት የቃል ኪዳን ቃል ነው። ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ ለነፍስዎ ስንቅ ይሆን ዘንድ እነሆ! እንላለን።

# ምዕራፍ አንድ
# በወንጌል አላፍርም!!

*1.1 ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ - - - ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ።*

*ለእግዚአብሔር ወንጌል*

በዚህ ቃል ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ቃሎችን እናገኛለን እነርሱም

= እግዚአብሔር
= ወንጌል የሚሉት ናቸው

ለእግዚአብሔር የሚለው ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ የተለየበትን ምክንያት የሚያስረዳ ሲሆን ተልዕኮው ደግሞ ወንጌል ነው። የተልዕኮው ባለቤትና ላኪው እግዚአብሔር መሆኑንም ያመለክታል።

ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ነው (ኢሳ 61፡1-3፤ሉቃ 4፡17-19)።

*የጌታ የእግዚአብሄር መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች የምስራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሄር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል። የተወደደችውን የእግዚአብሄርን አመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ እግዚአብሄር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ በአመድ ፋንታ አክሊልን በለቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት በሀዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጎናፀፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል (ኢሳ 61:1-3)።*

*ነብዩንም ኢሳያስ መጽሀፍ ሰጡት ፦ መጽሀፉንም በተረተረ ጊዜ ፦ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ፦ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን ለእውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፦ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን አመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል (ሉቃ 4:17-19)።*

የምሥራች ማለት ደግሞ መልካም ዜና ማለት ነው። ደስታ ያለበት፣ ፍስሃ የሞላበት ነፍስን የሚያረካና የሚያረሰርስ መልዕክት ያዘለ ነው።

ወንጌልን መልካም ዜና የሚያስኙት ዋና ዋና ነገሮች ምንድናቸው?

ሀ. ለሁሉ የሚበቃ ጽድቅ በክርስቶስ መዘጋጀቱን ማወጁ (ገላ 3:11-13፤2ቆሮ 5:18-21)።

ለ. የኃጢአት ዕዳ መከፈሉን ማወጁ (ቆላ 2:13-14)።

ሐ. ወደ እግዚአብሔር መግባት የሚቻልበት በር መከፈቱን ማወጁ ነው (ኤፌ 2:14-18)።

*ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና። ማንም በእግዚአብሄር ፊት በህግ እንዳይፀድቅ ግልጥ ነው። ህግም ከእምነት አይደለም ነገር ግን ፦ የሚያደርገው ይኖርበታል ተብሎአል። በእንጨት የሚሰቀል የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከህግ እርግማን ዋጀን (ገላ 3:11-13)።*

*ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሄር ነው፤*

*እግዚአብሄር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሄር በእኛ እንደሚማልድ ስለክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሄር ጋር ታረቁ ብለን ስለክርስቶስ እንለምናለን። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሄር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ሐጢያት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ሐጢያት አደረገው (2ኛ ቆሮ 5:18-21)።*

*እናንተ በበደላችሁና ስጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ ከእርሱ ጋር ህይወትን ሰጣችሁ፤በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የእዳ ጽህፈት ደመሰሰው፤እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል (ቆላ 2:13-14)።*

*እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሀደ በአዋጅ የተነገሩትን የትእዛዛትን ህግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በስጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሄር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ፤በእርሱ ስራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና (ኤፌ 2:14-18)።*

ስለዚህ ይህ መልካም ዜና ሕያውነትን የሚያሳይ ቃል ነው። ሕያውነቱ የሚመነጨውም ባለቤቱ ሕያው ስለሆነ ነው። ምንጩ ሕያው ስለሆነ ውጤቱም ሕያው ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ ለሁሉም ዓለም የሚሆን የምሥራች በመሆኑና ለየትኛውም ትውልድ የሚሠራ ስለሆነ ሕያው ነው።

በዓለማችን በተለያዩ ስፍራዎች የምሥራች ተብለው የሚነገሩ ለሰሚዎች ደስታን የሚሰጡ ነገሮች አሉ። ሁሉም ግን በስፍራ የተወሰኑ ናቸው።

ለምሳሌ «የጤፍ ዋጋ ቀድሞ ከነበረበት 820 ብር ወደ 120 ብር ወረደ» ቢባል ጤፍ ተመጋቢ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን በጣም የሚያስደንቅ ዜና ነው። በቆሎና ቆጮ ተመጋቢ ለሆነው ኢትዮጵያዊ ግን ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም። ለአውሮፓና ለአሜሪካ ነዋሪ ጭራሽ ምንም ትርጉም አይሰጥም።

ስለዚህ በምድር የሚሰሙ የምሥራቾች የተገደቡ ናቸው። የወንጌል የምሥራች ግን ለሁሉ ዘር፣ ለሁሉ ቋንቋ፣ ለሁሉ ቀለም፣ለሁሉ የኑሮ፣ የትምህርትና የዕድሜ ደረጃ ደስ የሚያሰኝ ዓለምን ሁሉ በደስታ የሚያፍለቀልቅ ነው። የዚህም በረከት ተካፋዮች በመሆናችን ደስታችን የላቀ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥቅሉ የተቀመጠ የእግዚአብሔር ቃል አለ። የምሥራቹ ቃል ግን የእግዚአብሔር የማዳኑ ወይም የጸጋው ቃል ነው። በዝርዝር እንመልከት ካልን የእግዚአብሔር ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት እንችላለን። ለምን? ቢባል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉ የበቃውን ጽድቅ ያዘጋጀ፣ የኃጢአትን ዕዳ የከፈለ፣ ወደ እግዚአብሔር መግባት የሚቻልበትን በር የከፈተ ነውና። ስለዚህ ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳኑ ዜና ነው። የወንጌል ማዕከሉ ራሱ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።

ለዚህም ወንጌል ብዙዎች ሕይወታቸውን ሰጥተዋል ሐዋርያው ጳውሎስም ለዚህ ወንጌል አገልጋይ (ባሪያ) ሊሆን የተጠራው በዚህ ግልጽ ምክንያት ነው።

- *ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ*

  = *ሐዋርያነቱ የሚያርፈው በእግዚአብሔር የመጠራቱ ምክንያት ውስጥ ነው።*

- ሐዋርያ ማለት -- የተላከ ማለት ነው። ሰፋ ባለው ፍቺ ስንመለከተው ደግሞ በአንድ ባለሥልጣን ለአንድ የተወሰነ ተልዕኮ የተላከ የሚለውን ሃሳብ ይዞ እናገኘዋለን።

- ብዙዎች የስነመለኮት ሊቆች እንደሚሉት ለሐዋርያነት ከሚፈለጉት መመዘኛዎች አንዱ ከሞት የተነሳውን ክርስቶስን ማየት ነው (1ቆሮ 9:1-2) ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታን ፊት ለፊት አይቷል። ሐዋርያ ሊሆን የተጠራውም በዚያ ጊዜ ነው።

ጥሪው ደግሞ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ አጠራር የሚያመለክት ነው። ጥሪው የሚመሠረተው በክርስቶስ ባገኘው መዳን ላይ ነው። በዚህ ታላቅ ደህንነት ውስጥ የሐዋርያነት አገልግሎትን ሰጠው። ይህንንም ያደረገው ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ፣ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚሠራው ማንነቱ ነው። (ሮሜ 4:17፤ ዘፍ17:1-9 )

*እርሱም ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደተጻፈ ለሙታን ህይወት በሚሠጥ የሌለውንም እንዳለ አድረጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው (ሮሜ 4:17)።*

የእግዚአብሔር ጥሪ ማንነትን ይለውጣል። ለተልዕኮው የሚያስፈልገውን ብቃት ይሰጣል። አብርሃም፣ ሙሴ፣ ጳውሎስ ዓይነተኛ ምሳሌዎቻችን ናቸው።

- ***የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ***

ባሪያ የሚለው ቃል አሽከር ወይም ሎሌ የሚለውን ቃል ያመለክታል። ይህም በዋጋ የተገዛ ወይም በፈቃዱ ራሱን የሰጠ ባሪያ መሆኑን ይገልጣል። ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠቀመበት ባሪያ የሚለው ቃል ለሮሜ ሰዎች ትልቅ ትርጉም የሚሰጥ ነው። ምክንያቱም መልዕክቱን በፃፈበት ዘመን የራሳቸው መብት የሌላቸው ለጌታቸው ፈቃድ ብቻ ለመኖር ራሳቸውን የሰጡ 60 ሚሊዮን ያህል ባሮች በሮሜ ግዛት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ጳውሎስም በገዛ ፈቃዱ ራሱን ለክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠና በዋጋ የተገዛ መሆኑን ለማመልከት ይህንን ቃል ተጠቅሟል።

ሀ. በዋጋ የተገዛ — 1ቆሮ 6:20፤ ኤፌ 1:7
ለ. በነፃነት የሚያገለግል - 1ቆሮ 7:22፤ፊሊ 2:17
ሐሥ 21:13

*በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሰጋችሁ እግዚአብሄርን አክብሩ (1ኛ ቆሮ6:20)።*

*በውድ ልጁም እንደጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት (ኤፌ 1:7)::*

*ባሪያ ሆኖ በጌታ የተጠራ የጌታ ነጻ ነውና፤ እንዲሁም ነጻ ሆኖ የተጠራ የክርስቶስ ባሪያ ነው (1ኛቆሮ 7:22)::*

*ነገር ግን በእምነታችሁ መስዋእትና አገልግሎት ተጨምሬ ህይወቴ እንኳ ቢፈስ ደስ ብሎኛል ከሁላችሁም ጋር አብሬ ደስ ብሎኛል (ፊሊ 2:17)::*

*ጳውሎስ ግን መልሶ፦ እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለጌታ ስለኢየሱስ ስም በእየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቻለሁ እንጂ ለእስራት ብቻ አይደለም አለ (ሐዋ 21:13)::*

- *ተለየ (የተለየ)*

ይህ ቃል በቃጋ ተገዝቶ ወደ ሌላ ቦታ የሄደን ፈቃደኛ ባሪያ ያመለክታል:: ጳውሎስን ቀድሞ ከነበረበት ስፍራ ወደሚፈለገው ስፍራ ለይቶ የወሰደው እግዚአብሔር መሆኑን የሚገልጽ ነው:: ( ቆላ 1:13፤14 ፤ማቴ 13:49፤25:32) የእግዚአብሔር ጥሪ የማፍለስ ጥሪ ነው:: ማለትም ስፍራን የማስለቀቅ ማንነትንና መጠሪያን አድራሻን የመለወጥ ጥሪ ነው::

*እርሱ ከጨለማ ስልጣን አዳነን ቤዛነቱንም እርሱንም የሐጥያትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን (ቆላ 1:13፤14)::*

*በዓለም መጨረሻ እንዲህ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ሐጥያተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል (ማቴ 13:49)::*

*አህዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል (ማቴ 25:32)::*

በመለኮታዊው ጥሪው ጳውሎስን ለራሱ ሥራ እግዚአብሔር ሲለየው የስም ለውጥ አድርጎለታል::

ይህም በችሎቱና በኃይሉ ታላቅነት በመታመን የሚያደርገው የራሱ ሥራ ነው።

የቃሉን ፍቺ ስንመለከት፣ ጳውሎስ ማለት ትንሽ ማለት ነው። ይህንን ትንሽ ሰው በጸጋው ለውጦ ታላቅ ሐዋርያ አደረገው።

**1:2** *- - - በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻህፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው - - - -*

*አስቀድሞ ተስፋ ሰጠ*

ለሮሜ ሰዎች የተጻፈው የምስራቹ ቃል ከነቢያትና ከበጉ ሐዋርያት ቃል የተለየ አለመሆኑን የሚያመለክት ቃል ነው። ይህም ቃል የተስፋ ቃል በመባል ይታወቃል (ሐሥ 13:32፤1ቆሮ9:5)።

*እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምስራቹን ለእናንተ እንሰብካለን (ሐሥ 13:32)።*

*እንደሌሎቹ ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም እህት ሚስቶቻችንን ይዘን ልንዞር መብት የለንምን? (1ኛ ቆሮ 9:5)።*

ስለዚህ የወንጌሉ ቃል ገና ከጥዋቱ በዘፍ 3:15 ጀምሮ በብሉይ ኪዳን የተነገረው የእግዚአብሔር ተስፋ ፍጻሜ ነው ማለት ነው። ነቢዩ ኢሳይያስም ይህንን ወንጌል በምዕ 1:18 ፤ ምዕ 53 እና 55 ላይ በግልጽ ሰብኮታል። እኛ በረከቱን ያገኘነው ወንጌል በነቢያቱ የተሰበከ ነበር። ነቢያቱ ግን ሙሉ በሙሉ ሳይረዱት በእምነት አርቀው እያዩ ተናገሩት እኛ ግን የተስፋውን ቃል ሙላት አገኘን።

**1:3** *ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ - - - ሆኖ*

*በስጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ — ሆኖ (ስለሆነ)*

ይህ ቃል ወንጌሉ የማን ታሪክ መሆኑንና የታሪኩ ባለቤት ወይም የወንጌሉ ማዕከል ስለሆነው ስለክርስቶስ ማንነት

ያወሳል፤ ጳውሎስም የሰውን ልጅ አይሁዳዊ ደግሞም የእግዚአብሔር ልጅ በማለት ይገልጠዋል::

በሁለት ዓብይ ነጥቦች ስናስቀምጣቸውም:-

ሀ. በሰብዓዊነቱ የዳዊት ዘር ነው
ሉቃ 1:32፤ ዮሐ 7:42፤ሮሜ 9:5

ይህ መግለጫ ለአይሁዳውያን በጣም ትርጉም የሚሰጥ ነው ምክንያቱም የዳዊት ዙፋን የስልጣንና የክብር መገለጫ ነውና:: ኢየሱስንም ከዳዊት ዘር ተወልዶ የዳዊትን ዙፋን የሚሰጠው መሆኑን ያመለክታል:: (ንጉሥነቱን) ይገልጣል::

ለ. *ሆኖ የሚለው ቃል ደግሞ ሙሉ ሰው መሆኑን እና* አምላክነቱን *ያመለክተናል*
- ዮሐ 1:14 ይህንን ክፍል ስናነብ ሰው ሆኖ የተገለጠው እግዚአብሔር ወልድ አምላክም እንደሆነ እንረዳለን::

ይህ ሀሳብ የሚብራራው በቀጣዩ ነጥብ ነው::

*እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፡- ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል(ሉቃ 1:32 )::*

*ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ዳዊትም ከነበረበት መንደር ከቤተልሔም እንዲመጣ መጽሐፍ አላለምን? አሉ (ዮሐ 7:42)::*

*አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና ከእነርሱም ክርስቶስ በስጋ መጣ :- እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን (ሮሜ 9:5)::*

*ቃልም ስጋ ሆነ ፀጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ :- አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን (ዮሐ 1:14)::*

**1.4 - - - *እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ - - - ስለተገለጠ ስለ ልጁ ነው እርሱም ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ነው::***

*እንደ ቅድስና መንፈስ*

አንዳንድ ቅጂዎች በቅድስናው መንፈስ ይሉታል ይህ ቃል ቅዱስና ከስላሴ አንዱ የሆነውን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን የሚገልጥ ሲሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰው ብቻ ሳይሆን መለኮት መሆኑንም ያመለክታል፡፡ ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስም በመለኮትነቱ መንፈስ ነው፡፡ በባሕርዩም ቅዱስ ነው፡፡

- *ተገለጠ*

  የሚለው ቃል መለኮት የሆነው እግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር ዘለዘለማዊ ፈቃድ ተወስኖ ለእኛ መገለጡን ያሳየናል፡፡ በዚህ ክፍል ልብ ልንለው የሚገባው ነገር ቃሉ የሚለን የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ ነው እንጂ ሆነ አይደለም፡፡ ከዚህ ብርቱ እውነት በመነሳት ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹምም አምላክ ነው ብለን መናገር እንችላለን ነውም፡፡ ከሙታን በመነሳቱ የእርሱ የመለኮትነት ሙላት ለእኛ በኃይል ተገለጠልን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን እጅግ ከበረ፡፡ እንግዲህ ይህ የምሥራች ቃል ወይም ወንጌል ስለዚሁ በኃይል ከሙታን ስለተነሳውና በስጋ ከዳዊት ዘር ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚተርከው የራሱ የማንነቱ መገለጫ ወይም የማዳኑ ዜና ነው ማለት ነው፡፡

## *1.5 በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን*

*የሐዋርያነት ጸጋ፣ (ጸጋንና ሐዋርያነትን) (ለመኖር የሚያስችል ጸጋ)*

1. *የሐዋርያነት ጸጋ -* ይህ ጸጋ ለጳውሎስ የተሰጠው ከእግዚአብሔር የደህንነትን ስጦታ ከተቀበለ በኋላ ነው። የሐዋርያነት ጸጋ ከመዳን ወይም በኢየሱስ አዳኝነት ከማመን በኋላ የሚመጣ ነው።

- *ጸጋ*

ከተቀባዩ ማንነት ጋር (ሁኔታ ጋር) ያልተገናኘ እግዚአብሔር የሚሰጠው ነጻ ስጦታ ነው። ይህ ጸጋ ደስ የሚያሰኝ ፣ ለደካማው ኃይልን የሚሰጥና የሚያስችል ነው።

- *ሐዋርያ*

የተላከ፣ ማለትም ካመነ በኋላ መልዕክተኛ ለመሆን የተመረጠ፣ የተሾመ ፣ ለላኪው እንደ አምባሳደር ሆኖ የሚያገለግል ነው።

እነዚህን ተልዕኮንና ለተልዕኮው ብቁ የሚያደርገውን ኃይል ያጣመሩ ቃላትን ስንመለከት፣ የወንጌል ተልዕኮ በወንጌሉ ማዕከል በክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ እና ከእርሱ በሚመጣ ጥሪ የሚከናወን መሆኑን እንረዳለን።

አምባሳደር ለጌታው (ለላኪው ደስታ እንደሚኖር ሁሉ) ጳውሎስም ለላኪው ደስታ የሚኖር መሆኑን እንገነዘባለን። የላኪው ደስታ የሐዋርያው ደስታ ነው። ይህንንም ገብቶትና ተረድቶ ያደርገዋል። ደስ የሚሰኝበትን የሚለው ቃል የገባው መሆኑን ያስረዳል። ይህ ደስታ ግን የሚመነጨው ለተልዕኮው ብቁ ለማድረግ ከተሰጠው ጸጋ ውስጥ መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ጳውሎስም ሊያሳይ የሚወደው ይህንን እውነት ነው።

2. *ከእምነት የሚነሳ መታዘዝ*

የሐዋርያነት ጸጋ ተሰጥቶት የተላከው ጳውሎስ ከተልዕኮው የሚጠበቅበትን ውጤት የሚገልጥ ቃል ነው።

በሮሜ 16:26 - - - አምነው እንዲታዘዙ የሚለውን ቃል ለማጠናከሪያ ብንመለከት:-

ጳውሎስ በመልዕክቱ ጅማሬ ላይ ተልዕኮው የምሥራቹን (የክርስቶስን የማዳን ዜና) ማድረስ መሆኑን ከገለጠ በኋላ ግቡም የሰሙትን ዜና አምነው ተቀብለው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እየታዘዙት እንዲኖሩ ማስቻል መሆኑን ይናገራል:: ይህም ማስቻል እርሱን ብቃት ከሰጠው ጸጋ የሚመነጭ ስለሆነ ለዚያው ጸጋ አሳልፎ ይሰጣቸዋል::

በዚህ ክፍል ጠንከር ባለ መግለጫ የተልዕኮው ውጤት ሆኖ የተገለጠውን ከእምነት የሚነሳ መታዘዝ ሰፋ አድርገን መመልከቱ አግባብነት ይኖረዋል:: ስለዚህ መታዘዝ ከምን ከምን የተነሳ ሊመጣ እንደሚችል እንመልከት

መታዘዝ በሚከተሉት መንገዶች ሊመጣ ይችላል:-

--- ከፍርሃት ⟶ ኃይለኝነትን፣ ቅጣትን፣በመፍራት መታዘዝ

--- ከጥቅም ፍለጋ ⟶ ዛሬ ብታዘዝ ነገ ብዙ አገኛለሁ በማለት

--- ለታይታ/ ለይሉኝታ ⟶ ከሰዎች መሞገስንና መከበርን ታዛዥ ነው መባልን በማሰብ መታዘዝ

--- አማራጭ ሲጠፋ ⟶ የማያምኑበትን፣ የማይወዱትን፣ የማያከብሩትን ምርጫ ስለሌለ ብቻ መታዘዝ

--- ከማባበል ⟶ ከጉትጎታ፣ከማባበያ ስጦታዎች የተነሳ መታዘዝ

እነዚህ ሁሉ የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ተሰብኮላቸው ሰዎች በሕይወታቸው እንዲፈጠርባቸው የሚፈለገውን የመታዘዝ ደረጃ አያሟሉም:: የክርስቶስ ወንጌል ተሰብኮ ሰዎች ሊደርሱበት የሚገባው መታዘዝ ከእምነት የሚመነጨው መታዘዝ ወይም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚያስቀምጡት የክርስትና የእምነት አቋም መታዘዝ ነውና በዚያው መሠረት መታዘዝ ይሉታል::

የበለጠ ትርጉም የሚሰጠው ግን አምኖ ከእምነት በሚመነጭ መታዘዝ የሚለው ይሆናል።

አስተማማኝ የሆነው እምነት በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ የተመሰረተው እምነት ነው። ውጤት የሚኖረውም ከዚህ እምነት የሚመነጨው መታዘዝ ነው።

- ማመን የሚችሉና የሚታዘዙ ሕያዋን ናቸው (ዮሐ 6:27-35 ፤ ሮሜ 10:16)

- የእግዚአብሔር ታማኝነት የሚገለጥባቸው በርካታ የሕይወት ዘርፎች ቢኖሩም የታማኝነቱ ሙላት ግን የተገለጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው።ኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝና እውነተኛ ተብሎ ተገልጧል (ራዕ 19:11) እኛም ያመንነው ይህንን ታማኝ ነው። የዳንነውም በዚህ እውነትና ታማኝነት ነው።

*ለሚጠፋ መብል አትስሩ ነገር ግን ለዘላለም ህይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ስሩ ፤ እርሱን እግዚአብሄር አትሞታልና። እንግዲህ የእግዚአብሄርን ስራ እንድንሰራ ምን እናድርግ? አሉት። ኢየሱስም መልሶ:- የእግዚአብሄር ስራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው። እንግዲህ:- እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሰራለህ? ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደተፃፈ አባቶቻችን በምድረበዳ መና በሉ አሉት። ኢየሱስም :- እውነት እውነት እላችኋለሁ :- እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ የእግዚአብሄር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለአለምም ህይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው። ስለዚህ:- ጌታ ሆይ :- ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው:- የህይወት እንጀራ እኔ ነኝ ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም (ዮሐ 6:27-35) ።*

*ነገር ግን ሁሉ ለምስራቹ ቃል አልታዘዙም። ኢሳየስ :-- ጌታ ሆይ:- ምስክርነታችንን ማን አመነ? ብሎአልና (ሮሜ 10:16)።*

የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን የእምነታችንን መሠረት፣ «የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ» በማለት ይገልጠዋል (ዕብ12:2፤3:1)። ስለዚህ እምነታችን የተጀመረው በእርሱ ነው፤ ወደ ሙላት የሚደርሰውና የሚፈጸመውም በእርሱ ነው። ስንታዘዝም ከዚሁ እምነት በመነጨ መንገድ ነው እንጂ በማባበልም ፤ በማስፈራራትም መሆን የለበትም።

መታዘዛችን ከፍቅር የመነጨና ለክርስቶስ ኢየሱስ ማንነት ከበሬታን የሚሰጥ ነው ማለት ነው።

## *1.6 በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ።*

*የክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ*

በዚህኛው ክፍል ውስጥ ሁለት ነጥቦችን መመልከቱ አግባብነት ይኖረዋል

1. ***<u>የተጠራችሁ</u>***፡- ይህ ቃል እግዚአብሔር አብ በሉዓላዊ ማንነቱ ያከናወነውን ወይም መሻቱን የገለጠበትን እውነት እንጂ በእኛ ማንነት ላይ ወይም የእኛ ማንነት ብቃት ኖሮት ለመጠራት የቻልን መሆኑን አያመለክትም። ስለዚህ ቃሉ የጠሪውን በጎ ፈቃድና ውሳኔ የሚያመለክት ነው። (ፊሊ 3:14፤ ዕብ 3:1፤ 1ተሰ 2:12)

   በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል መዳን ይሆንልን ዘንድ አብ በሉዓላዊ ፍቃዱ ለእኛ የሰጠውን ፀጋም ያመለክታል።

2. ***<u>የክርስቶስ ልትሆኑ</u>***፡- ይህ ቃል የተጠራንበት ዋነኛ ዓላማ የክርስቶስ ለመሆን መሆኑን ያመለክታል። አብ የጠራን ከክርስቶስ ጋር ሕብረት እንዲኖረን አንድ እንድንሆን ነው።

- ***<u>ጥሪው</u>***፡- የተለየ ጥሪ ነው። የተለየ የሚሆነውም የጌታ የራሱ የፀጋው ችሎታ የተገለጠበት ስለሆነ ነው። የክርስቶስ የሆንነው ከጸጋው በፈሰሰልን ብቃት ወይም የማስቻል ኃይል የተሰበከልንን ወንጌል ማመንና መታዘዝ ስለቻልን ነው።

- የዚህ ጥሪ ፍጻሜ ዘላለማዊ ክብርን መውረስ ነው። ይህም የሆነው ከኛ ብቃት ሳይሆን ጌታ በራሱ ችሎት ስለፈጸመውና ስላከናወነው ነው። (ሮሜ 8:30 ፤ 1ኛቆሮ 1:9 ፤ 2ኛ ጢሞ 1:9)

*አስቀድሞም የወሰናቸው እነዚህን ደግሞ ጠራቸው ፤የጠራቸውን እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው (ሮሜ 8:30)።*

*ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ህብረት የጠራችሁ እግዚአብሄር የታመነ ነው (1ኛ ቆሮ 1:9)።*

*አብረኸኝ መከራን ተቀበል፤ ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሄር ነውና፦ ይህም እንደ ራሱ ሀሳብና ፀጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ስራችን መጠን አይደለም (2ኛ ጢሞ 1:9)።*

ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ለመሆን የተጠራነውን ጥሪ ካመለከተ በኋላ የሚቀጥለው ደግሞ ቅዱሳን ለመሆን መሆኑን በቀጣዩ ቁጥር ያመለክታል።

## *1.7 በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።*

### *በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁ*

- ይህ መወደድ ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድና ምክንያት የለሽ ፍቅር (አጋፔ) የመነጨ እንጂ እኛ የሚወደድ ነገር ስለተገኘብን እንዳልሆነ እንረዳለን። ይህ መወደድ በቀራኒዮ መስቀል እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ በኩል የሠራውን ግሩም አሠራሩን የሚያመለክት ነው።

### *ቅዱሳን*

ይህ ቃል የክርስቶስ የመሆናችንን ውጤትና ትሩፋት ያመለክታል። ጌታም በጸጋው የሰጠው በረከት መሆኑን ያስረዳል (ዮሐ 17:14፤ሐሥ 26:18) ። በረከቱም ከኩነኔ፣ ከሞት፣ ከበሽታ እንዲሁም ከኃጢአት መለየትን ያካትታል።

*እኔ ቃልህን ሰጥቻቸለሁ፤እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው (ዮሐ 17:14)።*

*የሐጥያትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ ፦ከጨለማ ወደ ብርሀን ከሰይጣንም ስልጣን ወደ እግዚአብሄር ዘወር እንዲሉ አይናቸውን ትከፍት ዘንድ ፦ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአህዛብ አድንሀለሁ ( ሐሥ 26:18)።*

የምንኖርበት ዓለም ኃጢአት የሞላበት ከመሆኑ የተነሳ በክርስቶስ ኢየሱስ የመቤዠቱ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ልምምድ በሕይወታችን ቢያልፍም እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በመስቀል ላይ ባከናወነው ሥራ ቤዝዎቱን ፍጹም አድርጎ አስረግጦ አከናውኖታል።

## *ጸጋና ሰላም*

ሐዋርያው በነዚህ ሁለት ጥምር ቃላት ከቁጥር 1-6 የፃፈውንና በዘመኑ የአይሁድና የግሪክ ማህበረሰብ መካከል በሚደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች የሚቀርበውን የሰላምታ አቀራረብ በመከተል ረዘም ያለ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጥበታል። በዕብራውያን ዘንድ ሰላም (ሻሎም) የሚለው ቃል ከተለያየ ጫና፣ ከጭንቀትና ከመረበሽ ነፃ መሆንን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሙሉ በረከት የሚገልጽ ነው። <u>ስለዚህም ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ የሚገልፀው ከጥሪው የተነሳ ቅዱሳን መሆናቸውንና በእግዚአብሔር ያመኑ ሁሉ የእግዚአብሔርን የታማኝነቱን ትሩፋት (በረከት)</u>፦

> ሀ. እንደ ቤተክርስቲያን ሐሥ -- 26:10
> ለ. እንደ ክርስቶስ ቤተሰብ -- 1ቆሮ 1:2
> ሐ. እንደ ግለሰብ — ኤፌ 1:18፤ ቆላ 1:12

ተካፋዮች መሆናቸውን አስረግጦ
ይናገራል ኤፌ 1:4

*ይህንም ደግሞ በኢየሩሳሌም አደረግኩት፤ ከካህናት አለቆችም ስልጣን ተቀብዬ እኔ ከቅዱሳን ብዙዎችን በወህኒ አሳሰርኳቸው፦ ሲገድሉአቸውም አብሬ ተቸሁ (ሐሥ 26:10)።*

*ወንድሙም ሶስቴንስ በቆሮንጦስ ላለች ለእግዚአብሄር ቤተ ክርስቲያን ፦ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት ፦ የእነርሱና የእኛ*

*ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤ (1ኛ ቆሮ 1:2)።*

*ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የሀይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው (ኤፌ 1:18)።*

*በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሄርም እውቀት እያደጋችሁ ፡- ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና መታገስ እንደክብሩ ጉልበት መጠን በሀይል ሁሉ እየበረታችሁ ፡- በቅዱሳንም ርስት በብርሀን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ ፡- በነገር ሁሉ ደስ ሊያሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን ( ቆላ 1:12)።*

*ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን (ኤፌ1:4)።*

***ደህንነት እኛ ለእግዚአብሔር የምንሠራለት ሥራ ውጤት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በጸጋው እኛን የጠራበት የበጎ ፈቃዱ ውጤት ነው (2ተሰ 2:13-14)። በኢየሱስ ስናምን በጸጋው እንድናለን፤ ከዚያም አዕምሮን የሚያልፈው ሰላም ሁለንተናችንን ይሞላናል።***

*እኛ ግን፡- በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፡- ሁል ጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሄርን ልናመሰግን ግድ አለብን እግዚአብሄር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደበኩራት መርጦአችኋልና፤ ስለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ (2ኛ ተሰ 2:13-14)።*

**1:8-15** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ስለሚጽፍላቸው ሰዎች ያለውን ትልቅ ሸክምና ፍቅር በግልጽ አስቀምጦታል። ይህንን በማድረጉም ታላቅ የሆነ የመሪነትን ብቃት የሚገልጽ ድንቅ ትምህርት አስተማሯል። የተዋጣላቸው መሪዎች የሚቀድመውን የሚያስቀድሙ፣ ነገሮች በትክክል መሠራታቸውን (ማኔጅመንት) ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ነገሮች መሠራታቸውን የሚያረጋግጡ መሆኑንም በጥቂት ቃል ገልጦ አልፏል። ባደረገው ድርጊት የመልዕክቱን እውነትነት ገለጠው ማለት ነው።

**1:8** ***እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ።***

***ከሁሉ አስቀድሜ***

- ሐዋርያው በጣም የከበረ ድንቅ መልዕክት ቢኖረውም የሚቀድመውን ማስቀደምና ትክክለኛ ነገር ማከናወንም አግባብ እንደሆነ አምኗል።

  ስለዚህም ሊቀድም የሚገባውን አስቀድሟል። ያም ስለሚጽፍላቸው ቅዱሳን (ስለ ቤተክርስቲያን) ያለውን ሸክም የሚያመለክት ነው።

***አምላኬ :***

ይህ ቃል ሐዋርያው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቅርብ ግንኙነት የሚያመለክት ነው። አንባቢዎቹም ከጌታ ጋር የግል ሕብረት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገልጻል (2ቆሮ 12:21፤ ፊሊ 1:3፤4:19)።

***በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ***

ሐዋርያው አንባቢዎችን በማመስገን የሥራቸውም ውጤት ያመጣውን ተጽዕኖ በግልጥ በማስቀመጥ ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነውንና ጸጋን የሰጣቸውን እግዚአብሔር ያመሰግናል።ምስጋናውንም የሚያቀርበው በክርስቶስ በኩል ነው።ክርስቶስ ኢየሱስ ምስጋናችን ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበት መካከለኛ ሲሆን ምክንያቱም ደህንነትን ያገኘንበት መካከለኛ እርሱ ነውና።

**1:9:10** ***በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ እየለመንሁ ሁልጊዜ ስጸልይ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ አሳስባለሁ***

*በልጁ ወንጌል ... ሁል ጊዜ ስጸልይ*

ይህ ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ መስዋዕትነት የተገኘውን መቤዠት የሚያመለክት ነው። ጳውሎስም የሚሰብከው በልጁ በኩል የተከናወነውን ይህንኑ ወንጌል ነው። ይህ የወንጌል እውነት በሮሜ ሰዎች ሕይወት ውስጥ በግልጽ እንዲገባ ፍሬውም እንዲታይ በርትቶ የሚጸልይ፣ መሆኑንና ፍሬውንም በዓይኑ ለማየት፣ ከዚህ ቀደም በዓይን ያላያቸውን ግን የሚናፍቃቸውን ለማየት የጓጓ መሆኑንም ይገልጣል። ይህም በሐዋርያው ውስጥ ያለውን የእረኛ ልብ ያመለክታል ስለ መንጋው ግድ የሚለው በመሆኑ ያለማቋረጥ ስለእነርሱ ያነባል። ይህም ከእውነተኛ እረኝነት መንፈስ የወጣው አገልግሎት በሐዋርያው ጳውሎስና በሮሜ ምዕመናን መካከል አስገራሚ ትስስር ተፈጥሮአል። ይህንን የመሰለውን ትስስር የመሠረተውም ይኸው የክርስቶስ ወንጌል ነው።

## 1:11 *ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና*

*መንፈሳዊ ስጦታ*

ከላይ በተመለከትነው ክፍል ሐዋርያው የሮሜን ቅዱሳን ለማየት ያለውን ትልቅ ጉጉት አይተናል። የጉጉቱ ዋና ዓላማ ባመኑት የወንጌል እምነት እንዲጸኑ የሚያስችላቸውን መንፈሳዊ ስጦታ ለማካፈል ነው። በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈሳዊ ስጦታ ምንጭ አድርጎ ራሱን እያቀረበ አይደለም። ነገር ግን እሱም እነርሱም በጋራ የተቀበሉትና አንዳቸው ሌላቸውን ለማነጽ፣ እርስበርስ ለመበረታታት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውን፣ በዋጋ የማይገደበውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እያመለከተ ነው።

ይህ ስጦታ:-

- በዋጋ የማይወሰን ነው (1ቆሮ 7:7)

- የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ (charisma) ማለትም ፈውስ፣ ተአምራት፣ በልሳን መናገርን የያዘ ነው። በሌሎች ነገሮችም ለውጥን ያመጣል (1ቆሮ 12:1-11)
- በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ለሆኑ ሁሉ የሚሰጥና ለብዙዎች የሚተርፍ ነው (2ቆሮ 5:17፤ ሮሜ5:15፤ 1ጴጥ 4:10-11)

**1:12** *ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው*

*እናንተና እኔ*

ሐዋርያው በዚህ ንግግሩ በክርስቶስ ኢየሱስ በመካከላቸው የተፈጠረውን የጠነከረና የሚያነፋፍቅ ሕብረት ይገልጣል:- ከላይ እንደተመለከትነው አብዛኞቹን በዓይን አያውቃቸውም ግን በመካከላቸው በክርስቶስ ወንጌል ምክንያት የተፈጠረው ሕብረት ይህንን የመሰለ ቤተሰባዊነት ፈጥሯል።

- አብረን እንድንጽናና / እንድንበረታታ

  ሀ. *አብረን* – ሐዋርያው ይህንን ቃል ሲጠቀም በእርሱና በሚጽፍላቸው መካከል በጸጋ አማካኝነት የተገኘውን ተመሳሳይ የሆነ እምነት የሚገልጽ ሲሆን የአብሮነቱ ውጤት ደግሞ ከታች ተገልጧል።

  ለ. *እንድንጽናና* - በሌሎች ትርጉሞች እንድንበረታታ ይላል በጋራ ከተቀበሉት ጸጋ በተካፈሉት እምነት እርስ በርስ መንፈሳዊ ስጦታ ሲከፋፈሉ በመካከላቸው መበረታታት ከዚህም የተነሳ ደግሞ ደስታ የሚፈጠር መሆኑን ያሳያል። ይህንን የገለጸበት ምክንያት ሐዋርያው በእነርሱ ውስጥ የሚታየው እድገት ደስ የሚያሰኘው ስለሆነ ነው (3 ዮሐ 4) ።

*ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለም (3ኛ ዮሐ:4)።*

***1:13*** ***ወንድሞች ሆይ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደሆን በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ***

*ብዙ ጊዜ እንደተከለከልሁ*

ሐዋርያው በእርሱ አጀንዳ (መሻት) ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘለዘለማዊ ሐሳብ የሚንቀሳቀስ መሆኑን ለማመልከት ደግሞም እነርሱን ማየት ስላልፈለገ ወይም ከሌሎቹ አሳንሷቸው እንዳልሆነ ለማመልከት ይህንን ቃል ተጠቅሟል:: ሰማያዊ (መለኮታዊ) አሠራሩ ግን በዚህ ሁኔታ እንዲከናወን እንዳደረገ ይገልጻል:: ይህም በትንሽዋ እስያ የነበረው የወንጌል ሥራ መበርከት መሆኑን መገንዘብ እንችላለን::

*ወንድሞች*

ብዙ ጊዜ ይህንን ቃል ሰዎች የፆታ ልዩነት የሚያደርግ አድርገው ይወስዱታል:: በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ቃል ግን ፆታን ጨርሶ የሚለይ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቤተሰቦች (በክርስቶስ ያመኑትን ሁሉ) የሚያካትት ነው:: ጌታም በምድር አገልግሎቱ ይህንን ቃል ሲጠቀም የፆታ ልዩነት ለመፍጠር ፈልጎ አልነበረም::

*ፍሬ እንዳገኝ*

ፍሬ የሚለው ቃል ከመከር የሚገኘውን ውጤት የሚያመለክት ሲሆን ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ የአህዛብ ሐዋርያ ሆኖ የተላከ በመሆኑና በማሳውም ላይ የተሰማራ ስለሆነ የአዝመራውን ፍሬ ማየት የሚፈልግ መሆኑን ይገልባል (ዮሐ 4: 36፤ ፊሊ.1:22፤ ቆላ 1:6፤ ሮሜ 7:4-5)::

*የሚያጭድ ደመወዙን ይቀበላል ፣ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል(ዮሐ 4:36)::*

*ነገር ግን በሥጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን ምን እድመርጥ አላስታውቅም (ፊሊጲ 1:22)::*

*እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ፣ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ስጋ ለሕግ ተገድላችኋል ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ ፣ እናንተ ለሌላው ከሙታን ለተነሳው ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ:: በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የሀጢአትን መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሰራ ነበርና ( ሮሜ 7:4-5)::*

## 1:14 *ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ*

### *ዕዳ አለብኝ*

ሐዋርያው ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበለውን ለአህዛብ ወንጌልን የማድረስ አደራ ቸል ሊለው የማይችል እንደሆነ ለማመልከትና ለአገልግሎቱ ያለውን መሰጠት ለማሳየት ይህንን ቃል ተጠቅሟል::

በዘመኑ በነበረው አመለካከት ግሪኮች የእነርሱን ቋንቋ አጥርቶ የማይናገረውን እና ባህላቸውን የማይከተለውን ሰው የተናቀና ጥበብ የጎደለው አድርገው ያስቡ ነበር:: ስለዚህም «ባርባርያን» የሚል ስያሜ ይሰጡ ነበር:: የተናቁ፣ ንግግር የማያውቁ ማለት ነው:: ሐዋርያው ግን ለጥበበኞቹ ለግሪኮችም ሆነ ላልተማሩት ንግግር ለማያውቁትም ዕዳ አለብኝ ይላል::

ትዕዛዙን ለመፈጸም ያለውን ትጋት ለማሳየት ቢጠቀምበትም ዕዳው አራጣ ያለበት ዕዳ አይደለም:: ማለትም በሙላት ባይፈጽመው የሚጫንበት አራጣ የለም:: በብሉይ ኪዳን ለእሥራኤል የተሰጠውን ሕግ ብንመለከትም ዕዳ አራጣ ሊጨመርበት እንደማይገባ ያመለክታል:: ሆኖም ግን ሰዎች አራጣ ይጨምሩበት ነበር (ዘዳ 22:25፤ ዘዳ 23:19-20፤ ሕዝ 18:18)::

### *ሀሳቡን ሰፋ አድርገን ለመመልከት:-*

#### *ሀ. በሙሴ ህግ መሠረት*

ባለ ዕዳ የሆነው ሰው የሚከፍለው ቢያጣ ለመኖር አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶች በመያዣነት እንዲሰጥ አይጠየቅም (ዘዳ 24:6፣ 10-13)::

*የሰውን ነፍስ እንደ መውሰድ ነውና ወፍጮ ወይም መጅ እንደ መያዣ ማንም አይውሰድ (ዘዳግ 24:6)::*

የእስራኤል ሰዎች ዕዳ ሳይከፍሉ ቢቀሩ ሊሸጡ ይችላሉ:: ሆኖም ግን እንደ ባሪያ አይገዙም (ዘሌ 25:39:47 ፤ ኢሳ 50:1) ::

ይህ ሕግ በአግባቡ ካልተተረጎመ በሕዝቡ ላይ መርገም ያስከትላል:: በዳዊት ዘመን በዚህ ጉዳይ ሰዎች ፍትሕ ፍለጋ ወደ ዳዊት ይመጡ እንደነበር ከቃሉ እንመለከታለን (ኤር 15:10፤ 1ሳሙ 22:2) ::

*እናቴ ሆይ ወዮልኝ! ለምድር ሁሉ የክርክርና የጥል ሰው የሆንሁትን ወለድሽኝ ለማንም አላበደርሁም ፤ ማንም ለእኔ አላበደረም ፤ ነገር ግን ሁሉ ይረግሙኛል (ኤር 15:10)::*

*የተጨነቀም ሁሉ ፣ ብድርም ያለበት ሁሉ ፣ የተከፋም ሁሉ ወደ እርሱ ተከማቸ እርሱም በላያቸው አለቃ ሆነ ከእርሱም ጋር አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎች ነበሩ( 1ሳሙ 22:2)::*

## ለ. በአዲስ ኪዳን ትዕዛዝ መሠረት :-

እንድናገለግል ታዘናል:: ሆኖም ግን በሙላት ስላላገለገልን ሲኦል አንገባም:: ሆኖም ግን የተሰጠንን አደራና ትዕዛዝ በማክበር በሚፈለገው መጠን መትጋትና የተሰጠንን አደራ መፈጸም ይጠበቅብናል:: (ማቴ 25:16-27፤ ዮሐ 2:15 ፤ ማቴ18:21-26፣34 ፤ ዮሐ 5:24)

*አምስት መክሊትን የተቀበለው ሂዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ:: አንድ የተቀበለው ግን ሂዶ ምድርን ቆፈረና*

*የጌታውን ገንዘብ ቀበረው ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው:: አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት አስረከበ ጌታ ሆይ አምስት መክሊት ሰጠኸኝ ነበር እነሆ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍኩበት አለው:: ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ በጥቂቱ ታምነሀል በብዙ እሾምሀለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው:: ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ ጌታ ሆይ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር እነሆ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍኩበት አለ:: ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሀል በብዙ እሾምሀለው ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው:: አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ ጌታ ሆይ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበትንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ ፈራሁም ሂጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት እነሆ መክሊትህ አለህ አለ ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው::አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጥ በተገባ ነበር እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር (ማቴ 25:16-27) ::*

*የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው:: የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታቻቸውንም ገለበጠ ፣ እርግብ ሻጮችንም ይህን ከዚህ ውሰዱ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉ አላቸው (ዩሐ 2:15) ::*

*ስለዚህ መንግስተ ሰማያት ባሮቹ እንዲቆጣጠር የወደደ ንጉስ ትመስላለች:: መቆጣጠርን በጀመረ ጊዜ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ:: የሚከፍለው ቢያጣ እርሱና ሚስቱ ልጆችም ያለውን ሁሉ እንዲሸጥ እና እዳውን እንዲከፍል ጌታው አዘዘ:: ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና ጌታ ሆይ ታገሰኝ ሁሉንም እከፍልሀለው አለው የእዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው እዳውንም ተወለት (ማቴ 18:21-27)::*

*ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ:- አንተ ክፉ ባሪያ ስለለመንኸኝ ያንን እዳ ሁሉ ተውሁልህ ፤ እኔ እንደማርሁህ ባልንጀራህን ያሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው አንተስ አይገባህምን? አለው( ማቴ 18:32-33)::*

*እውነት እውነት እላችኋለሁ ፣ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ፣ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም (ዩሐ 5:24)::*

ሐዋርያው ጳውሎስ ዕዳ አለብኝ ብሎ የተናገረውም ችል ሊሰው የማይችል ትልቅ አደራ መሆኑን ለማመልከት ነው። በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ፀጋ ተቀብሎአልና በተቀበለው ጸጋ በትጋት መሥራት እንዳለበት እያመለከተ ነው።

**1:15** ***ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋችቼአለሁ***

*ተዘጋጅቼአለሁ*

አዲሱ መደበኛ ትርጉም ይህንን የሐዋርያውን የአገልግሎት ርሃብ «እጓጓለሁ» በሚል የአጽንዖት ቃል ያስቀምጠዋል። ጳውሎስ በጌታ ፀጋ የተሞላ፣ አደራውን የሚያውቅ ትጉ ሰው ነበር። የሮሜ ሰዎችንም ለማገልገል ዝግጁ ነበር። ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች መሔድ አልቻለም። ስለዚህ ያለውን ዝግጁነትና ናፍቆት ጠንከር አድርጎ ለመግለጽ ይህንን ቃል ተጠቅሟል። የሐዋርያው ጉጉት ሐገር የመጎብኘት፣ አየር የመለወጥ ጉጉት አልነበረም ነፍስ የመማረክ ጉጉት ነበር።

የሮሜ ቅዱሳን ይህንን ጉጉት ሲመለከቱና ለእነርሱ ያለውን ሸክም ሲረዱ እግዚአብሔር ሐዋርያው ጳውሎስን ስለሰጣቸው በጣም ያመሰግኑታል።

**1:16** ***በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።***

*በወንጌል አላፍርም*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል ስለ እፍረት ያነሳበት ምክንያት ይኖረዋል። የሚሰብከው ወንጌል የተቆራኘው ከአንድ ድሃ የአይሁድ አናጢ ጋር ነው። ሮማውያን ደግሞ አይሁዳውያንን በጣም ይንቁ ነበር። በስቅላት መሞት ደግሞ ከሁሉ የከፋና የተዋረደ ሞት ነው። እምነታቸውን በዚህ የተናቀና የተዋረደ ሞት በሞተ ሰው ላይ እንዲያደርጉ ማወጅ ቀላል አይደለም። ሮም በዘመኑ እጅግ የገነነች ከተማ ናት። ወንጌል ደግሞ ከሮም ግዛቶች ሁሉ አነስተኛ ከሆነችው ሀገር ከኢየሩሳሌም የወጣ ነው። ይህንን ትልቅነት ይዞ ከሞት ተነስቷል ብሎ ስለሚነገርለት ሰው መስማትና ማመን ለእነርሱ ቀላል አይደለም። ለጳውሎስም አሳፋሪ ይመስላል። እርሱ ግን አላፍርም አለ (2ኛ ጢሞ 1:8:12 ፤ ማር 8:38)። እርሱ እለማፈሩ ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም ምንባቦች ስንመለከት ከእርሱ ጋር አብረው የወንጌሉ ባልደረባ የሆኑት ሁሉ እፍረት እንዳይሰማቸው በብርቱ ያሳስባል።

*እንግዲህ በጌታችን ምስክርነት ወይም በእስረኛው በእኔ አትፈር ፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን ስለ ወንጌል አብረኸኝ መከራ ተቀበል ( 2ጢሞ 1:8) ።*

*ስለዚህም ምክንያት ይህን መከራ ደግሞ ተቀብያለሁ ነገር ግን አላፍርበትም ያመንኩትን አውቃለሁና የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ ( 2ኛ ጢሞ 1:12) ።*

*በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል (ማር 8:38) ።*

በፊሊጵስዩስ ታስሯል፤በተሰሎንቄ ከከተማ ተባርሯል፣ በኤፌሶን መሳለቂያ ሆኗል ከአውሬም ጋር ታግሏል፣ በቆሮንቶስ ሞኝ ተብሏል ይህም ሁሉ ሆኖ ግን አያፍርበትም! (ሮሜ 5:2፤ፊሊ 3:7፤ ሐሥ 17:32፤1ቆሮ1:18፣23) የማያፍርበትንም ምክንያት በጭብጥ ማስረጃ ያስቀምጠዋል።

*በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ፀጋ በእምነት መግባት አግኝተናል። በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን (ሮሜ 5:2) ።*

*ነገር ግን ለእኔ እረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቆጥሬዋለሁ (ፊሊጲ. 3:7) ::*

*የሙታን ትንሳኤ በሰሙ ጊዜ አኩሌቶች ግን ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሀም አሉት (የሐዋ 17:32) ::*

*የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና (1ኛ ቆሮ 1:18) ::*

*እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስ እንሰብካለን:: ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብ ሞኝነት ነው (1ኛ ቆሮ1:23) ::*

ሐዋርያው በወንጌል አላፍርም ያለባቸው ምክንያቶች እጅግ ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹን መመልከቱ ይጠቅማል::

## *ሀ. የወንጌል ምንጩ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ:-*

በጳውሎስ ዘመን ከቄሳር የሚወጣ ደብዳቤ የሁሉን ትኩረት ይስባል:: ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል ደግሞ ስለሕያው እግዚአብሔር ልጅ የሚተርክ ነው:: ለዚህ ነው ጳውሎስ ገና በመግቢያው ለእግዚአብሔር ወንጌል የሚለውን ቃል የገለጸው:: ስለዚህ ከእግዚአብሔር የወጣና ማዕከሉም ክርስቶስ ኢየሱስ የሆነው ወንጌል አያሳፍርም ይላል::

## *ለ. የሚያንቀሳቅሰው የእግዚአብሔር ኃይል ስለሆነ*

ኃይል -- Dinamo ብርቱ ጉልበት ያለው
የሚፈነዳ ኃይል ::
(1ቆሮ 2:4፤ 4:20 ፤ 1ኛተሰ 1:5)

*እምነታችሁም በእግዚአብሔር ሃይል እንጅ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም (1ኛቆሮ 2:4)::*

*የእግዚአብሔር መንግስት በሃይል ነው እንጅ በቃል አይደለምና (1ኛቆሮ 4:20)::*

*ወንጌላችን በሃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትንም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደነበር ታውቃላችሁ (1ኛ ተሰሎቄ 1:5)::*

የሮሜ መንግሥት ከሚመካባቸው አንዱ የጦር ሰራዊቱ ኃይል ነው። በየቦታው ጉልበታቸውን የሚገልጡ ኃይላት አሉዋቸው። ሐዋርያውም ይህንን የታወቀ ገሃድ እውነት በመንተራስ ወንጌል ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ይህም ኃይል የሰዎችን ሕይወት የመለወጥ ብቃት አለው። ብዙ ጥፋት የሞላባቸውን የቆሮንቶስና የኤፌሶን ከተማ እንደለወጠ ሁሉ የሮምንም ከተማ እንደሚለውጥ እምነት አለው። ስለዚህ ይህንን የሚለውጥ ኃይል ይዤ አላፍርም እያለ ነው።

## ሐ. *የመጨረሻ ወጤቱም ሰዎችን ማዳን ነው*

የእግዚአብሔር ኃይል የሆነው ወንጌል የሚያድነው:-

- ከእግዚአብሔር ቁጣ (ሮሜ 5:9)
  - -- ከሞት (ኤፌ 2:12)
  - -- ከኃጢአት (ማቴ 1:21)
  - -- ከጥፋት (ሉቃ 19:10)
  - -- ከከንቱ ኑሮ (1ኛጴጥ 1:18)
  - -- ከባርነት (ገላ 5:1)

*በዚያን ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ (ኤፌ 2:12)።*

*ልጅም ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ (ማቴ 1:21)።*

*የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው (ሉቃ 19:10)።*

*ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ንሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደ ሌላው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ (1ኛ ጴጥሮስ 1:18)።*

*በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ (ገላ 5:1)።*

ይህም የማዳን ሥራ (የደህንነት ሥራ)

1. የሆነ ነው (ኤፌ 2:5)

2. እየሆነ ያለ ነው (1ቆሮ 1:18፤ 2ቆሮ 2:15)

3. ለወደፊት የሚሆን ነው
(ሮሜ 13:11፤ 1ቆሮ 5:5 ፤
2ኛ ጢሞ 4:18)

*ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን በፀጋ ድናችኋልና (ኤፌ 2:5)።*

*የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና (1ኛ ቆሮ 1:18)።*

*በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና (2ኛ ቆሮ 2:15)።*

*ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰአት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ ባመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና (ሮሜ 13:11)።*

*መንፈሱ በጌታ በእየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለስጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዱ ነው (1ኛ ቆሮ 5:5)።*

*ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊዉም መንግሥት ይጠብቀኛል ለእርሱ ከዘላለም እስከዘላለም ክብር ይሁን (2ኛጢሞ 4:18)።*

***ድነት የሰው ዘር ሁሉ ዋነኛ ፍላጎት ነው (ሮሜ 10:1፣9-10)። ይህም ድነት ከኃጢአትና በዚህ ዓለም በሰው ሕይወት ከሚከሰተው ምግባረ ብልሹነት የመውጫ ጉልበትና የአሸናፊነትን ኃይል ማግኘትን የሚያካትት ብቻ ሳይሆን በመጨረሻውም ዘመን ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቁጣና ፍርድ ማምለጥ የሚያስችል ነው። ወንጌል ደግሞ በራሱ ሰዎችን ሊያድን፣ በደህንነትም ሊጠብቃቸው፣ በመጨረሻም ወደ ክብር ሊያደርሳቸው የሚችል ሙሉ ኃይል አለው።***

1:17 *ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።*

*የእግዚአብሔር ጽድቅ - - - ይገለጣልና*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል እያመለከተ ያለው እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ ያፈሰሰውን ጽድቅ ነው። ከእግዚአብሔር በእምነት ጽድቅን የተቀበለው ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚኖረውን ሁኔታ የሚገልጥ ነው። ወደፊት ገፋ ስናደርግ በምዕ 3:5 የምንመለከተው ጽድቅ የእግዚአብሔር የባሕርዩ መገለጫ የሆነውን ነው። በዚህኛው ቁጥር የተገለጠው ግን በወንጌል ለሰው ልጆች የገለጠውን፣ ለሰው ልጆች ያካፈለውን፣ እኛም የተቀበልነውን ከሥራችን ሳይሆን ከጌታ ሥራ የተነሳ ያገኘነውን የሚያስረዳ ነው።

ጽድቅ የሚለው ቃል በዚህ መጽሐፍ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ስድሳ ጊዜ ተጠቅሷል። ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት ምክንያት እግዚአብሔር ኃጢአትን በመቅጣቱ ተገልጧል። ጽድቁንም ለኃጢአተኛ ው ደህንነት በመስጠት ገልጦታል።

ሆኖም ግን ጻድቁ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በማጽደቅ እንዴት ፍትሐዊ ሊሆን ቻለ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። እግዚአብሔር ግን በልጁ ሞት ኃጢአትን በመቅጣት በትንሣኤው ደግሞ ለሚቹ ኃጢአተኛ ሕይወትን በመስጠት ጻድቅነቱንና ማጽደቁን በጣም ራ አረጋግጧል (ሮሜ 3:26)።

*ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው(ሮሜ 3:26)።*

- *ከእምነት ወደ እምነት:*

በወንጌል የተገለጠው ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ነው። በብሉይ ኪዳን ጽድቅ በሥራ ነበር። ኃጢአተኞቹ ግን ሥራቸው የእግዚአብሔር የጽድቅ ደረጃ ማማሏት እንደማይችሉ ይረዱ ነበር። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በዕንባቆም 2:4 የተጠቀሰውን ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል የሚለውን በመጥቀስ የጽድቅ መገኛው መንገዱ እምነት መሆኑን በብርቱ ገልጧል። የእምነት ሕይወት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የሚዘልቅ እንደሆነም ያሳያል።

| |
|---|
| ጽድቁም:- ለዘላለም የሚኖር፣ ህያው በሆነ እምነት ውስጥም የሚገኝ ነው። ስለዚህ ሰዎች በመዳን የተገኘ ውን ሕይወት እስከ ዘለቄታው መኖር የሚችሉት በጽድቁ ምክንያት በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም። |

ሐዋርያው ይህንን ነጥቡን ለማብራራት ሰፊ ሽፋን ሰጥቶ አስቀምጦታል። የመጀመሪያዎቹን ስምንት ምዕራፎች ስንመለከትም

ሀ. ከሮሜ 1-4 በእግዚአብሔር ታማኝነት በመታመን ጽድቁን በመቀበል በዚያው በተቀበልነው ጽድቅ ምክንያት በመዳናችን ያገኘነውን ሕይወት መኖር እንደምንችል ሲገልጽ

ለ. ከሮሜ 5-8 ያለው ክፍል ደግሞ በዚህ መዳን ሕይወት እንዴት መኖር እንደሚገባን ያመለክታል። ይህ ማለት እኛ አሁን የምንኖረው ኑሮ ሕይወትን ለማግኘ ት የሚደረግ ጥረት ሳይሆን ሕይወትን ስለተቀበልን በሕያውነት የምንኖረውን የሕይወት አቅጣጫ ዝንባሌንና አካሄድን የሚገልጽ ነው። ይህንን ህይወት እንኖረው ዘንድ ከፍርድና ከኩነኔ ነፃ ሆነናል። ስለዚህ የሕይወቱ ፍሬ የሚገለጠው በዚሁ በጸጋው ባገኘነው ሕይወት በመኖር ነው።

በአጭር አገላለጽ ሕያው የሆነ ዛፍ ፍሬ ማፍራቱ የተፈጥሮ ባህርዩ ነው እንደ ማለት ነው።

1:18:19 *እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና እግዚአብሔር ስለገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና*

*ወንጌልን ለማያምኑ የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል*

1. በዚህ ክፍል የተገለጠው ቁጣ ስሜታዊ የሆነውን ቁጣ የሚያመለክት ሳይሆን በቁ 17 እንደተመለከትነው ጽድቁ የመገለጡን ያህል ቁጣውም የሚገለጥ መሆኑን የሚገልጽና መለኮታዊ የሆነ ባሕሪውን የሚያሳይ ነው (ኤፌ 4:31፤ቆላ 3:8፤ዮሐ 3:36፤ ዕብ 3:11፤4:3)።

*መራራነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋትሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ (ኤፌ4:31)።*

*አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቁጣንና ንዴትን ክፋትንም ከአፋችሁም ስድብን የሚሳፍርም ንግግር አስወግዱ (ቆላ3:8)።*

*በልጁ የሚያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም (ዮሐ3:36)።*

*ዘወትር በልባቸው ይስታሉ መንገዴን ግን አላወቁም አልሁ እንዲሁም ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ (ዕብ3:11)።*

*ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም እንዲህ ወደ እረፍቴ አይገቡም ብየ በቁጣዬ ማልሁ (ዕብ4:3)።*

- እግዚአብሔር ወልድ ይህ ባሕርይ አለው -- (ራዕ 6:16)
- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ይህ ባሕር አለው -- (ዘዳ 32:9-10 ፤ መዝ 78:16-18 ፤95:8-10 ፤ 106:20-23 ፤ ዕብ 3:7)

*የምድር ነገስታትና መኳንንትም ሻለቃዎችም ባለጠጋዎችም ሐይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሻችና በተራራች ዓለቶች ተሰወሩ ተራራዎችና አለቶችንም:- በላያችን ውደቁ በዙፋኑም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን፤ ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና (ራዕ 6:16)::*

*እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ ይህ ሕዝብ አየሁት እነሆ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው (ዘፀ 32 9-10)::*

*ውሀን ከጭንጫ አወጣ ውሀንም እንደ ወንዞች አፈሰሰ ነገር ግን ያበድሉት ዘንድ እንደገና ደገሙ ፤ ልኡልንም በመድረ በዳ አስቆጡት ለነፍሳቸው መብልንም ይፈልጉ ዘንድ እግዚአብሔርን በልባቸው ፈተኑት (መዝ 78:16-18)::*

*በምድረ በዳ እንደተፈታተኑት እንዳስቆጡት ጊዜ ፤ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ:: የተፈታተኑኝ አባቶቻችሁ ፈተኑኝ ሥራዬንም አዩ:: ያችን ትውልድ አርባ አመት ተቈጥቻት ነበር:- ሁልጊዜ ልባቸው ይስታል ፤እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልሁ:: ወደ ዕረፍቴም እንዳይገቡ በቍጣዬ ማልሁ (መዝ 95:8-10)::*

*ሣርም በሚበላ በበሬ ምሳሌ ክብራቸውን ለወጡ:: ታላቅ ነገርንም በግብፅ ፤ድንቅንም በካም ምድር ፤ግሩም ነገርንም በኤርትራ ባህር ያደረገውን ያዳናቸውንም እግዚአብሔርን ረሱ:: እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ፤ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ (መዝ 106:20-23)::*

*ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትን አርባ አመትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ (ዕብ 3:7)::*

2. ቁጣው የሚገለጥባቸው ሰዎች:-

   ሀ. የተገለጠውን እውነት የሚያፍኑ፣ ወደኋላ ችል ብለው የሚያስቀሩትና የሚያደርጉ ሁሉ:: በሚከለክሉ ተብሎ የተገለጠው ይህንን ያመለክታል::

ለ. በእግዚአብሔርና በሰዎች ዘንድ ኃጢአትን በሚያደርጉና ለአመፃ ራሳቸውን በሰጡ ሁሉ ላይ ነው።

ሁሉቱን ስናዋህዳቸው :- እውነትን አፍነውና ደብቀው እውነቱን እያወቁ እውነቱን በህይወታቸው እንዳይሠራ በመከልከል ወደኋላ በመጣል ኃጢአትን የሚያደርጉትን አመፃን የሚለማመዱትን ያመለክታል።

3. እውነትን:- ሲል በወንጌል የተገለጠላቸውን የልጁን ሞትና ትንሣኤ መገለጥ ሳይሆን በግኡዛን ፍጥረቱ ላይ በገሃድ የተገለጠውን መለኮታዊ ባህርዩን ያመለክታል (መዝ 19:1)።

የሰው ልጅ ታሪክ እግዚአብሔርን በቅርበት በማምለክ፣ ከእርሱ ጋር በቅርብ ወዳጅነት በመኖርና ድምጹን በመስማት ይጀምራል። ነገር ግን አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ይህ ትልቅ ከፍታና ማዕረግ በኃጢአት (የእግዚአብሔርን ድንበር በመተላለፍ) ምክንያት ወደ ውርደት ይለወጣል። እግዚአብሔር በፍጥረቱ በኩል በይፋ የገለጠውንም የፈጣሪነት ባሕርዩንና ብቃቱንም በመካድ ፈጣሪን ትቶ የተፈጠሩትን ወደ ማምለክ ዘወር ይላል። ይህ እንግዲህ በፍጥረቱ በኩል የተገለጠውን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባህሪ እውነት መካድ ነው።

*1:20-21* *የማይታየው ባህሪይ እርሱም የዘላለም ሐይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሄርን እያወቁ እንደ እግዚአብሄርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ።*

ምንም እንኳን የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት በጨለማ ውስጥ ቢገባም እግዚአብሔር ግን ሲፈጥረው በስሜት ሕዋሳት (መስማት፣ መዳሰስ፣ ማየትና መስማት) ሊገደብ በማይችል መንገድ ክብሩን በፍጥረታቱ ውስጥ አስቀምጦታል:: ይህም ክብሩ ወይም አምላካዊ ባህርዩ ግን በፍጥረታቱ ውስጥ ታውቆና ግልጥ ሆኖ ይታያል:: የሰው ልጅ ግን ይህን የሚታየውን አምላካዊ ባሕርይ ወይም ገሃድ እውነት እንዳላወቀ በመሆን ራሱን በጨለማ ውስጥ ከተተ:: ከሁሉ አስገራሚ የሆነውን የሰው ልጅ የውድቀቱ ክስተት በአንድ አረፍት ማስቀመጥ ይቻላል:: ከእግዚአብሔር የተሰጡትን ተፈጥሮአዊ ስጦታዎች ለመጠቀም የሚፈልገውና በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ስጦታዎች የሚያውቀው የሰው ልጅ ስጦታዎቹን በውስጡ ያስቀመጠውን እግዚአብሔርን ለማወቅ አለመፈለጉና ስለሰጠው ስጦታ ለማመስገን እምቢ ማለቱ አሳዛኙን የክህደት ቁልቁለት ያመለክታል::

ስለዚህ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ለተገለጠው የእግዚአብሔር እውነት (ኢዮ 38:3) እውቅና አልሰጥ ሲል ማለትም በነፍስና በአዕምሮው መረዳት ሳይፈልግ ሲቀር ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ አልቻለም አልወደደም:: ስለዚህ ሃሳባቸው ከንቱ ሆነ ልባቸውም ጨለመ ስለዚህም አምላካዊ ፍርዱ ይህን ጨለማቸውን ወደ ብርሃን በማውጣት ተገለጠ::

*እንግዲህ እንደሰው ወገብህን ታጠቅ እጠይቅሀለሁ አንተም ተናገረኝ (ኢዮ 38:3)::*

**1:22:23 *ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ::***

*ጥበበኞች - ምኞች - ምዉት ሰው - በእንስሳት - ለወጡ*

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጠንከር አድርጎ የሚሰጠው ሀሳብ ሰው ስለ ራሱ ያለው አመለካከት እንኳን ተዛባ የሚል ዓይነት ነው። ማለትም ጥበበኞች ነን ሲሉ ጌታ ሲያያቸው ግን ደንቆሮዎች ሆነው ተገኙ። ይህም ደግሞ ሞኝነትንና ስንፍናን ያመለክታል። (መዝ 14:1፤ኤር 2:5፤ ሐሥ 14:15) የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ ፈጣሪውንም አመሰለ። ራሱን ለኃጢአት ሲያስገዛ ግን አምላኪ የነበረው ሰው ፈላስፋ ሆነ፤ በፍልስፍናውም ጥበበኛ የሆነ ሲመስለው ወደ ድንቁርና ራሱን ዝቅ አደረገና ፍጥረታትን ማምለክ ጀመረ። ይህም ውድቀት ሐዋርያው በሚቀጥለው ቁጥር የሚያነሳውን ምግባረ ብልሹነት (በኃጢአት መዘፈቅን አመጣ)

*እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንሰማ ሰዎች ነን ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይና ምድርን ባህርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን (ሐዋ ሥራ 14:15)።*

**1:24 *ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው***

***አሳልፎ ሰጣቸው***

እግዚአብሔርን እያወቁ ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት አስከፊ የሆነውን ኃጢአት እንዲለማመዱ ለከንቱነት አሳልፎ ሰጣቸው የኃጢአታቸውንም ፍሬ በሉ። በመሠረቱ እግዚአብሔር በባሕርዩ መሐሪ ነው። ምህረት ማድረግንም እጅግ ይወድዳል። ሆኖም ግን የእግዚአብሔርን እውነት እያወቁ አንፈልግህም ያሉትን ግን አምልኩኝ ብሎ አያስገድድም ነገር ግን ለምኞታቸው አሳልፎ ይሰጣቸዋል ምኞታቸውም የሚወልድባቸው የኃጢአትን ፍሬ እንዲበሉም ያደርጋል። ይህንንም የሚያደርገው ሰው የኃጢአትን ፍሬ ከቀመሰ በኋላ እግዚአብሔር ምህረቱን በመግለጥ ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው (ኤፌ 4:19፤ ሮሜ11:32)።

*ርኩሰትን ሁሉ ለማድረግ እራሳቸውን ወደ ሴሴኝነት አሳልፈው ሰጡ (ኤፌ. 4:19)።*

*እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁለን በአለመታዘዝ ዘግቶአልና (ሮሜ 11:32)።*

ሐዋርያው በቁጥር 18 የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል ብሎ ያስቀመጠው ሀሳብ በእነዚህ ቁጥሮች ተብራርቷል። የመጀመሪያ ቁጣው በልባቸው ፍትወት (የጋለ ምኞት) በመቃጠል ለርኩሰት አልፈው እንዲሰጡ ማድረጉ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ስጋቸውን ለውርደት አሳልፈው እንዲሰጡ ማድረግ ነው። ስጋቸውን አዋረዱ የሚለው ቃል ክቡር የሆነው ሰው እጅግ ዝቅተኛ በሆነው አገዛዝ ስር እንዲወድቅ መደረጉን ያመለክታል። ይህ ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ በሆነው ኃጢአት ስር የመውደቃቸውን አሳዛኝ ገጽታ የሚያመለክት ነው (ሮሜ 1:24-27)።

**1:25:** ***ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው አሜን።***

### *እውነትን በሐሰት ለወጡ*

እውነቱን መቀበል አልፈለጉም ስለዚህ ዋሹ። እውነትን አለመቀበላቸው ግን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንዳይገለጥ አይከለክለውም። እግዚአብሔር ውሸታቸውን እንኳን እንደ መንገድ ተጠቅሞበት ጽድቁን ይገልጥበታል (ሮሜ 3:7፤ ኤፌ. 4:21፤24፤5:8-10)።

*እንዲህ ሊሆን እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በጎለም እንዴት ይፈርዳል? (ሮሜ 3:7)።*

*በእርግጥ ሰምታችሁታልና እውነትም በኢየሱስ እንዳለ (ኤፌ. 4:21)።*

*በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ ለእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ (ኤፌ. 4:24)።*

*ቀድሞ በጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ (ኤፌ 5፡8-10)፡፡*

እውነት እንዲገለጥ ሁልጊዜ ውሸት መኖር አለበት ብሎ እግዚአብሔር አሠራሩን በዚያ መንገድ ግን አላደረገውም፡፡ እውነት በጽድቅ ይገለጣልና፡፡ ሰዎች እውነቱን ላለመቀበል ፈቅደው የመረጡት ውሸት የእግዚአብሔርን እውነት ለመግለጥ መንገድ ሆኖ አገልግሏል፡፡ *«ነገር ግን ሀይሌን እገልጥብህ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ላይ ይነገር ዘንድ ስለዚህ አስነሳሁህ »(ዘጸ 9፡16)፡፡* ብዙ ጊዜ ሰው በኃጢአት ሲዘፈቅ፣ በኃጢአትም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ሲገለጽ ሰው ከእግዚአብሔር ቁጣ ለመሸሸ በቶሎ ንስሃ ገብቶ ይመለሳል ብለን ነው የምናስበው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ተገልጦ እንደምናነበው ግን የሆነው ተቃራኒው ነው፡፡ ከቁጥር 26-28 ያሉት ቁጥሮች ይህንን አስከፊ ገጽታ ያመለክቱናል፡፡

***1:26:*** ***ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ስራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ***

*ለሚያስነውር ምኞት*

ለበጎ ነገር ሊገዛና ሊገራ ለማይችለው ከንቱ ምኞት አስነዋሪ ነገር አሳልፎ እንደሰጣቸው ያመለክታል

**1:27:** ***እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ፡፡***

*በፍትወታቸው ተቃጠሉ*

በዚህ ክፍል የተገለጠው ፍትወት፣ ልቅ የሆነውን ሥርዓት ያልጠበቀውን ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረጋቸውን ያመለክታል፡፡

እግዚአብሔር ይህንን የመሰለውን ጥፋት ማድረጋቸውን በቸልታ ስለማይመለከተው ለጥፋታቸው ተገቢውን ብድራት ይቀበላሉ። ሆኖም ግን መከራውን በራሳቸው ላይ ያመጡት ራሳቸው ናቸው።

**1:28:** ***እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው***

***ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው***

አዕምሮአቸው ቅን የሆነውን ሞራላዊ የሕይወት መርህ ወደማይቀበልበት ፣ የተስተካከለ የሕሊና ፍርድ ሊሰጥ ወደማይችልበት ደረጃ ዘቀጡ(አልፈው ተሰጡ)።

***1:29: ዓመፃ ሁሉ ግፍ መመኘት ክፋት ሞላባቸው ቅናትን ነፍስ መግደልን ክርክርን ተንኮልን ክፉ ጠባይን ተሞሉ***

ይህኛው ቁጥር አዕምሮአቸው የተዛባውን አመለካከት ስለያዘና እግዚአብሔርን ማወቅ አይጠቅምም በማለታቸው በምድር ላይ ያለው ክፋት ሁሉ የሞላባቸው መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህም ጎጂ ለሆነው የሥጋ ምኞትና ባህሪ ተገዢ ሆኑ (ሮሜ 13:13፤ 1ቆሮ 5:10-11፤ 2ቆሮ 12:20፤ ገላ 5:19-21) ።

*በቀን እንደሚሆን በአግባብ እንመላለስ በዘፈንና በስካር አይሁን በዝሙትና በመዳራት አይሁን በክርክርና በቅናት አይሁን (ሮሜ 13:13)።*

*በጠቅላላው የዚህ ዓለም ሴሰኞች ወይም ገንዘብ የሚመኙትን ነጣቂችንም ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም ይህ ቢሆን ከአለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንድ ሴሰኛ ወይም ገንዘብ የሚመኝ ወይም ጣዖት የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኃለሁ። እንደዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ(1ኛ ቆሮ 5:10-11)።*

*ስጦጣ እንደምወደው ሳትሆኑ አገኛችሁ ይሆናል እኔም እንደምትወዱት ሳልሆን ታገኙኝ ይሆናል ብዮ እፈራለሁና ምናልባት ክርክር ቅንዓትም ቁጣም አድመኝነትም ሐሜትም ማሾክሾክም ኩራትም ሁከትም ይሆናሉ(2ኛ ቆሮ 12:20)።*

*የስጋ ስራም የተገለጠ ነው እርሱም ዘሙት ርኩሰት ጥል ክርክር ቅንዓት ቁጣ አድመኝነት መለያየት መናፍቅነት ምቀኝነት መግደል ስካር ዘፋኝነት ይህንም የሚመስል ነው አስቀድሜ እንዳልሁህ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም(ገላ 5:19-21)።*

**1:30-33** ***የሚያሾከሹኩ ሐሜተኞች አምላክን የሚጠሉ የሚያንገላቱ ትዕቢተኞች ትምክህተኞች ክፋትን የሚፈላለጉ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ የማያስተውሉ ውል የሚያፈርሱ ፍቅር የሌላቸው ምሕረት ያጡ ናቸው እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።***

በዚህ ምዕራፍ አንድ መደምደሚያ ላይ የተገለጡት ቁጥሮች የሚያመለክቱት ከነዚህ ሁሉ ከንቱ ድርጊቶች የተነሳ ከእግዚአብሔር ሕይወት የራቁ መሆኑን ነው። ከዚህ እውነት በመነሳት የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጥሱ ሁሉ የሚጠብቃቸው ዕጣ ፈንታ ከእግዚአብሔር መለየት ጨርሰም የተጣሉ መሆን ነው የሚለውን መደምደሚያ መስጠት እንችላለን።

ሐዋርያው በዚህ ክፍል በኛ ዘመን በገሃድ የሚታዩ ሃያ አራት ዓይነት የኃጢአት ዝርዝሮችን ወይም የሰው ልጅ ውድቀት ውጤት የሆኑትን ጥፋቶች ይገልፃል። ከሁሉ የሚያስገርመው ግን የሰው ልጅ እነዚህን ኃጢአቶች መለማመድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንዲለማመዱዋቸው ማበረታታቱ ነው። በዚህ ብቻ ቢያበቃ መልካም ነው ሆኖም ግን ሰው እግዚአብሔርን ማምለክ ትቶ ጣዖት አምላኪ ሆነ። የእግዚአብሔር ፍጡር ሁሉ የበላይ የነበረው ሰው፣ ወደ ክፉ አውሬነት ተለወጠ። በዚህም ለእግዚአብሔር ቁጣ ራሱን አሳልፎ ሰጠ።

ሰዎች ይህንን ከመሰለው አስከፊ አዘቅት ሊወጡና ሊድኑ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ ወንጌል ስለሆነ፣ ወንጌልን ለሰው ሁሉ ለመስበክ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ልንነሳ የሚገባን አሁን ነው:: ይህ የተመለከትነው የሮሜ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ይህንኑ አጉልቶ የሚያሳይ ነው::

# ምዕራፍ ሁለት
# አስተማሪ ሆይ! ራስህን አስተምር

የዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበት ነው። ማለትም አንዳንዶቹ ይህ የጳውሎስ ጽሁፍ የሚመለከተው አይሁዳውያንን ነው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ አይደለም በምዕራፍ 1:18-32 የተገለጹትን ኃጢአት የሚያደርጉትን አህዛብን ነው ይላሉ። ምዕራፉን እያየን ወደፊት ስንገፋ ግን ሕግ ስለተሰጣቸው ሰዎች የሚናገር መሆኑን እናገኛለን። እንዲያውም በቁጥር 17 በግልጽ «አንተ ይሁዲ ነኝ» ካልህ ብሎ በግልጽ ያስቀምጠዋል። ስለዚህ ለአይሁዳውያን መልዕክቱን በግልጽ እያስቀመጠ መሆኑን ያመለክተናል።

ስለዚህ ሐዋርያው እሥራኤላውያንን ኃጢአት ሠርታችኋል ብሎ መገሰጽ የሚያስከፍለውን ዋጋ እያወቀ በብዙ ማስረጃ ኃጢአት መሥራታቸውን ሊገልጽ ይጀምራል። ሐዋርያው እያስተላለፈ ያለው መልዕክት የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ለመከራና ለስደት ዳርጓቸዋል። ኢየሱስንም የሰቀሉት በተመሳሳይ ምክንያት ነው።

***2:1 ስለዚህ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ የምታመካኘው የለህም በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና።***

*የምታመካኘው የለህም*

ይህ ቃል የሕግ አዋቂዎች የሚጠቀሙበት ቃል ሲሆን አንድ ሰው በሰራው ጥፋት ክስ ቀርቦበት ተገቢ ምላሽ ወይም አይመለከተኝም ማለት የሚችልበትን በቂ ማስረጃ ማቅረብ አለመቻሉን የሚያመለክት ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ጥያቄም የሚቀርበው በዳኛው ፈቃድ ከዳኛው ወገን ነው እንጂ ከተከሳሹ ወገን ወይም ከጠበቃው አይደለም (2ሳሙ 12:1-6) ።

> *እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከ ወደ እርሱም መጥቶ አለው በአንድ ከተማ አንድ ባለጠጋ አንድም ድሃ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ባለጠጋውም እጅግ ብዙ በግና ላም ነበረው። ለድሀው ግን ከገዛት አንዲት ታናሽ በግ በቀር አንዳች አልነበረውም፤ አሳደጋትም ከልጆችም ጋር በእርሱ ዘንድ አደገች እንጀራውንም ትበላ ከዋንጫውም ትጠጣ በብብቱም ትተኛ ነበር እንደልጅም ነበረች። በባለጠጋውም እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ከዚያ ወደ እርሱ ለመጣው እንግዳ ያዘጋጅለት ዘንድሳሳ የዚያንም የድኃውን ሰው በግ ወስዶ ለዚያ ለመጣው ሰው አዘጋጀ። ዳዊትም በዚያ ሰው ላይ እጅግ ተቆጥቶ ናታንን:- ሕያው እግዚአብሔርን ይህን ያደረገ ሰው የሞት ልጅ ነው። ይህን አድርጓልና አላዘነምና ስለ አንዲቱ በግ አራት ይመልስ አለው (2ኛ ሳሙ 12:1-6) ።*

- ***እነዚያን ታደርጋለህና***

ተከሳሹ እኔን አይመለከተኝም ያለባቸውን ተመሳሳይ ድርጊቶች አልፈጸመ ይሆናል። ሆኖም ለእርሱ ለራሱ የተሰጠውን ወይም የሚጠበቅበትን ግን አላደረገም። ይህ አገላለጽ ለአይሁዳውያን በጣም ግልጽ ነው። ማለትም ከሕግ አንዱን ማጉደል ሁሉን እንደማጉደል ነው። ውጤቱም ከኃጢአት በታች መውደቅ ነው።

***2:2 እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደሆነ እናውቃለን።***

***በሚያደርጉት***

ድርጊታቸው በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ መሆኑን ያመለክታል:: በእግዚአብሔር ፊት ሲመዘንም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድ የሚያመጣባቸው መሆኑን ይገልፃል (ማቴ 5:22) ::

*እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ የገባዋል ደንቆሮ የሚለው ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል (ማቴ 5:22) ::*

- *የእግዚአብሔር ፍርድ*

ለተገለጠው ድርጊት ምላሽ ይሆን ዘንድ ጥያቄውን የሚያቀርበውና የማይዛባ ፍርድን የሚሰጠውም እግዚአብሔር መሆኑንና ፍርዱም እውነተኛ መሆኑን ያመለክታል::

- *እናውቃለን*

ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቶቹ ውስጥ የሚጠቀምባቸው ተመሳሳይ ቃላት አሉ:: ከነዚህም አንዱ ይህ እናውቃለን የሚለው ቃል ነው:: ይህ አነጋገር አንባቢዎቹ እንዲሳተፉ የሚያደርግ ቢሆንም ቃሉ ብቻውን ሙሉ ሥልጣን አለው:: መለኮታዊ ኃይልም አለው:: በሰዎች ሕይወት ይሠራ ዘንድ ግን የሰዎችን ፈቃድ ይጠይቃል (1ኛቆሮ 10:15) ::

ከተደጋጋሚ ንግግሮቹ ለመጥቀስ ያህል:-

ሀ. እናውቃለን 6:6፣7:14፣8:22፣28
ለ. እያወቅን 5:3፣6:9፣13:11
ሐ. አታውቁምን 6:3፣16 ፣7:1፣11:2

**2:3-5** ***አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሀልን? ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግስቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ***

*የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ።*

*ፈራጁ ሰው*

*ሀ. ራሱ መተላለፍን ያደርጋል*
*ለ. የእግዚአብሔርን መቻልና ትዕግሥት ይንቃል።*

ስለዚህ በሌላው ላይ የሚፈርድ ሰው የራሱን ማስተዋል የማይችል፣ የጌታን ቸርነትና ምህረት በሙላት ያልተረዳ ሰው ነው።

- ጌታ ቻይነቱ = ቶሎ አለመፍረዱን ና ለንስሐ ዕድል መስጠቱን ያመለክታል።

- ጌታ ትዕግሥቱ = ቁጣውን ማዘግየቱንና መቆጣጠሩን ያመለክታል።

**እግዚአብሔር ይቆጣል ይገስጻል፣ በመጨረሻው ሊገልጥ የሚፈልገው ባሕርዩ ቸርነቱን ነው። መቻሉና ትዕግሥቱም ይህንኑ የሚገልጡ ናቸው። ይህ ማለት ግን ለኃጢአት ፍርድ አልተወሰነለትም ማለት አይደለም**
**(ሆሴ 6:5፤መክ8:11) የሚፈርደው ከቸርነቱ የተነሳ ነው። (ኢሳ 27:4)**

*ስለዚህ በነቢያት እጅ ቆረጥኋቸው በአፌም ቃል ገደልኋቸው ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል (ሆሴዕ 6:5)።*

*በክፉ ስራ ላይ ፈጥኖ ፍርድ አይፈረድምና ስለዚህ በሰው ልጆች ውስጥ ልባቸው ክፋት ለመስራት ጠነከረ (መጽሐፈ መክ 8:11)።*

*አልቆጣም ፤ እሾህና ኩርንችት በእኔ ላይ ምነው ዘሰልፍ በነበሩ! በእነርሱ ላይ ተራምጄ በአንድነት ባቃጠልኋቸው ነበር (ኢሳ 27:4)።*

አይሁድ ግን ይህን ቸርነቱንና ትዕግሥቱን እያወቁ ፤ ቸርነቱም ወደ ንስሀ ለመምራት መሆኑን እንጂ በአመጻቸው እንዲገፉ አለመሆኑን እያወቁ ያበሳሉ። ከዚህም የተነሳ የአዋቂ አጥፊ

በመሆን የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሳቸው ላይ ያከማቻሉ (ኤር 31:3 ፤ ሆሴዕ 2:14)::

*እርስዋም :- ውሽሞቼ የሰጡኝ ዋጋዬ ይህ ነው ያለችውን ወይንዋንና በለስዋን አጠፋለሁ፤ ዱርም አደርገዋለሁ:- የምድረ በዳም አራዊት ይበሉታል ( ሆሴዕ 2:14)::*

*እግዚአብሄርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ:- በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብኩሽ (ኤር 31:3)::*

## 2:6 እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል

### ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው

በዚህ ክፍል ሥራ ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ከልብ ዝንባሌ የመነጨን ተግባር ያመለክታል:: ጌታ ደግሞ ልብን የመመርመር ብቃት ስላለው የሠራውን እንዳልሰራ አድርጎ ሰው ሊያታልለው አይችልም:: ስለዚህ ሁሉን በማወቅ ባሕርዩና ችሎታው የእያንዳንዱን ሥራ መዝኖ ለሥራው ዋጋውን ይሰጠዋል:: (ምሳ 24:12፤ኤር 17:10)

*እነሆ፤ ይህን አላውቀውም ብትል ልቦችን የሚመረምር እርሱ አያስተውልምን ነፍስህንም የሚመለከት እርሱ አያውቅምን ለሰውስ ሁሉ እንደ ስራው አይመልስለትም (ምሳ 24:12)::*

*እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኩላሊትንም እፈትናለሁ (ኤር 17:10)::*

## 2:7 በበጎ ስራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል

### በጎ የሆነውን ጸንቶ በማድረግ

ጸንቶ የሚለው ቃል በጎ የሆነውን የሚቃወም ክፉ አሰራር ባለበት ዘመን በጎ ለማድረግና በመከራ ለመጽናት የጨከኑ (ውሳኔ ያደረጉ) የሚኖራቸውን የሕይወት አቋም ሲገልጽ፤ ብድራታቸውም የዘላለም ሕይወት ስጦታ መሆኑን

ያመለክታል:: የዘላለም ሕይወት ደግሞ በእግዚአብሔር መገኘት (PRESENCE) ውስጥ የሚገኝ ነው:: በሌላ አገላለጽ ደግሞ በእግዚአብሔር ውስጥ መኖር ማለት ነው::

**2:8-11** *ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሰፍት ይሆንባቸዋል:: ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራ ጭንቀት ይሆንበታል:: አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል:: አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞ ለግሪክ ሰው፤ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አይደለምና::*

*በአይሁድ ክዚያም በአህዛብ*

በእነዚህ ተከታታይ ቁጥሮች ውስጥ የተገለጠው እውነት እግዚአብሔር ለሰው ፊት የማያዳላ መሆኑንና አይሁድም ሆኑ አህዛብ የሥራቸውን ፍሬ፣ ማለትም:- እውነትን ትተው ክፋትን ለተከተሉ ቁጣው ፣ በጎ ለሚሰራው ደግሞ ክብር ሞገስና ሰላም የሚሆንበት መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

**2:12** *ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለሕግ ደግሞ ይጠፋሉና:: ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል*

*ሕግ ሳይኖራቸው - - - ሕግ እያላቸው*

አይሁዳውያን ሕጉን በመቀበላቸውና አህዛብ ደግሞ ሕግ ስለሌላቸው በአህዛብ ላይ በጣም ይመኩ:: አህዛብንም ጣዖት በማምለካቸው በጨለማ ያሉ ብለው ያልበሰሉ ሞኞች ናቸው ይሏቸዋል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ነገሩን በይፋ በመግለጥ ጉዳዩ ሕግ መቀበሉ ሳይሆን ሕግን መፈጸሙ ወይም መታዘዙ ነው:: ሕግ ኖሮአቸው ካልታዘዙት ሕጉ ራሱ ይፈርድባቸዋል በማለት ያሉበትን አደጋ ያሳያቸዋል::

አህዛብም ደግሞ ሕግ አልተሰጠንምና አይፈረድብንም ቢሉ ሊያመልጡ አይችሉም ወደፊት ሐዋርያው ማብራሪያ ይሰጥበታል እዚህ ቦታ ግን ያለ ሕግ ይጠፋሉ ብሎታል። ማለትም በተሰጣቸው ተፈጥሮአዊ የህሊና ብርሐን የተፈጥሮ ሕግ ውስጣቸው አለ በዚያ ሕግ ይፈረድባቸዋል። እግዚአብሔር በሕሊናቸው በኩል ትዕዛዝን ቢያስተላልፍም ትዕዛዙን ለመፈጸም የግል ፈቃደኝነት ይጠበቅባቸዋል።

**2:13** *በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚየደርጉት ይጸድቃሉ እንጅ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና።*

*መስማት*

ሐዋርያው በዚህ ስፍራ አጠንክሮ ማስረዳት የፈለገው «ጻድቅ የሚያደርገው ሕጉን መስማት ሳይሆን ሕጉ የሚያዘውን መፈጸም ነው» የሚለውን እውነት ነው። ብዙ ሰሙ፣ ግን አልታዘዙም። ስለዚህ ጽድቅ አይሆንላቸውም። የሰሙትን ቢታዘዙ ግን ጽድቅን ያገኙ ነበር። አልሆነም እንጂ!

**2:14 -15** *ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸዉ ሕግ ናቸውና ። እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።*

*ሕግ የሌላቸው - ለራሳቸው ሕግ ናቸው*

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ያልደነዘዘውና ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሳይሰጥ በፊት ያለው ሕሊና በሰው ህይወት ውስጥ ያለውን ትልቅ ድርሻና የሚያከናውነውን ትልቅ ሥራ ነው። «ሕሊናችሁ ሲመሰክርላችሁ» ሕሊና የራሱ የሆነ ምስክርነት አለው።

ሕሊናን ስናስብ በሕሊናችን ተጠቅመን ነገሮችን እናመዛዝናለን ሆኖም ግን እኛን ሊገዛን አይገባም።

ሕሊና የመደንዘዝ ምልክት ሊያሳይ ይችላል (1ኛቆሮ 8:7፤10:25፤2ቆሮ5:11) ።

*ነገር ግን ይህ እውቀት በሁሉ ዘንድ አይገኝም አንዳንዶች ግን ጣዖትን እስከ አሁን ድረስ ስለ ለመዱ፡- ለጣዖት የተሰዋ ነው ብለው ይበላሉና ሕሊናቸው ደካማ ስለሆነ ይረክሳሉ (1ኛቆሮ8:7)።*

*እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ። በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከሕሊና የተነሣ ሳትመረምሩ ብሉ ምድርና በእርስዋ የሞላባት ሁሉ የጌታ ነውና (1ኛ ቆሮ 10:25)።*

*እንግዲህ የጌታን ፍርሃት አውቀን ሰዎችን እናስረዳለን ለእግዚአብሔር ግን የተገለጥን ነን በህሊናችሁም ደግሞ የተገለጥን እንደ ሆንን ተስፋ አደርጋለሁ (2ኛቆሮ 5:11)።*

• *አሳባችሁ ሲካሰስ* — ንጹህ ህሊና ተው ሲል ኃጢአት ያሸነፈው ደግሞ አድርግ ሲል የሚፈጠረውን ውስጣዊ ጦርነት ያመለክታል። ይህም የነፍስን ጭንቀት ያመጣል።

እነዚህ ሁለት እውነቶች ተጣምረው አህዛብ የሕግ ትዕዛዝ በልባቸው የተጻፈላቸው መሆኑን ያመለክታሉ። ስለዚህ ሊያመልጡ አይችሉም ማለት ነው።

## 2:17 *አንተ ግን አይሁዳዊ ብትባል በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔርም ብትመካ*

አይሁድ ባላቸው ሕግና ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ግንኙነት የተነሳ ያለ ልክ ይመካሉ። ሆኖም ግን ይህ ድርጊት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ሆነባቸው (ኤር 9:24፤ሚክ 3:11፤አሞጽ 3:2) ።

*ነገር ግን የሚመካው፡- ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ በዚህ ይመካ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና ይላል እግዚአብሔር (ኤር 9:24)።*

*አለቆቿ በጉቦ ይፈርዳሉ ካህናቶቿም በዋጋ ያስተምራሉ ነቢያቶችዋም በገንዘብ ያምዋርታሉ ከዚህም ጋር፡- እግዚአብሔር በመካከላችን አይደለምን ክፉ ነገር ምንም አይመጣብንም እያሉ በእግዚአብሔር ይታመናሉ (ትንቢተ ሚክያስ 3:11)።*

*እንዲህ ብሏል፡- እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቃችኋለሁ ስለዚህ ስለኃጢአታችሁ ሁሉ እበቀላችኋለሁ (አሞፅ 3:2)::*

ልንመካ የሚገባው :-

1. በእግዚአብሔር 5:11
2. በክርስቶስ 15:17፤ ፊሊጵ 3:3
3. በመስቀሉ ገላ 6:14
4. በመከራችን 5:3
5. በድካማችን 2ቆሮ 11:30፤ 12:5:9
6. ሰዎች ዳግም ሲወለዱና የሕይወት ለውጥ ሲያሳዩ 1ተሰ 2:19
7. በክርስቶስ ባገኘነው ማንነት 2ቆሮ 1:14 ፤7:4:14፤9:2-3

*እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስ የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና (ፊሊ 3:3)::*

*ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለአለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከኔ ይራቅ (ገላ 6:14)::*

*ትምክህት የሚያስፈልግ ከሆነ ፣ ከድካሜ በሚሆነው ነገር እመካለሁ (2ኛቆሮ 11:30)::*

*እንደዚህ በላለው እመካለሁ ፣ ስለ ራሴ ግን ከድካሜ በቀር አልመካም (2ኛ ቆሮ 12:5)::*

*እርሱም ፀጋዬ ይበቃኃል ፣ ኃይሌ በድካም ይፈፀማልና አለኝ እንግዲህ የክርስቶስ ሀይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ (2ኛቆሮ 12:9)::*

*ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን እናንተ ክብራችንም ደስታችንም ናችሁና (1ኛተሰ2:19)::*

*ከምታነቡትና ከምታስተውሉት በቀር ሌላ አንጽፍላችሁምና በጌታችን በኢየሱስ ቀን እናንተ ደግሞ ትምክህታችን እንደምትሆኑ እንዲሁ ትምክህታችሁ እንድንሆን በከፊል ስለ እኛ እንዳስተዋላችሁ ፈጽማችሁ ታስተውሉ ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ (1ኛቆሮ 1:14)::*

*ስለ እናንተ እምነቴ ታላቅ ነው ፣ በእናንተ ምክንያት ትምክህቴ ታላቅ ነው መጽናናት ሞልቶብኛል በመከራችን ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል (2ኛቆሮ 7:4)::*

*በመጽናናታችንም ስለ ቲቶ ደስታ አብልጦ ደስ አለን ፣ መንፈሱ በሁላችሁ አርፎአልና ለእርሱ በምንም ስለ እናንተ የተመካሁ እንደሆን አላፈረሁምና ነገር ግን ሁሉን ለእናንተ በእውነት እንደ ተናገርን እንደዚሁ ደግሞ ትምክህታችን በቲቶ ፊት እውነት ሆነ (2ቆሮ 7:13-14)*

*ለቅዱሳን ስለሚሆን አገልግሎት ልጽፍላችሁ አያስፈልገኝምና በጎ ፈቃዳችሁን አውቄአለሁና ስለዚህም አካይያ ከአምና ጀምሮ ተዘጋጅቷል ብዬ ለመቄዶንያ ሰዎች በእናንተ እመካለሁ ቅናታችሁም የሚበዙትን አነሳስቷል:: ነገር ግን ለእነርሱ እንዳልሁ፣ የተዘጋጃችሁ ትሆኑ ዘንድ በዚህም ነገር ስለ እናንተ ያለው ትምክህታችን ከንቱ እንዳይሆን ወንድሞችን እልካለሁ (2ቆሮ 9:2-3)::*

## 2:18 *ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ*

### *ፈቃዱን አውቀህ*

ጌታ ሕግን ለአይሁድ ሲሰጥ ዓላማው ፈቃዱን አውቀው፣ በህይወታቸውም ከፍተኛ ስፍራ ሰጥተውት በተግባር የእርሱ መሆናቸውን እንዲያሳዩ ነበር:: (ፊሊ.1:10) «የሚሻለውን ፈትናችሁ ትወድዱ ዘንድ» ለኛም የተሰጠን ይኸው መመሪያ ነው:: የሚሻለውን አውቆ በፍቅር መታዘዝ::

*ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የፅድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና ያለ ነውር እንድትሆኑ የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እፀልያለሁ (ፊሊ. 1:10)::*

**2:19-20** *በሕግም የእውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ የእውሮች መሪ በጨለማም ላሉ ብርሃን የሰነፎችም አስተማሪ የሕፃናትም መምህር እንደሆንህ በራስ ብትታመን*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል አይሁድ ስለራሳቸው ያላቸውን አመለካከት በማንሳት የሚጠበቅባቸውን ግን መሆን ያቃታቸውን ያሳያቸዋል።

አይሁድ ስለራሳቸው ያላቸው አመለካከት፡-

- መሪ
- በጨለማ ላሉት ብርሃን
- መካሪ
- አስተማሪ

እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች ግን ከትሕትና የሚመነጩ ነበሩ። (ኢሳ 9:2፤ 49:6 ፤60:3)

*በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገርም ለኖረ ብርሃን ወጣላቸው (ኢሳ 9:2)*

*እርሱም የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመልስ ባሪያዬ ትሆን ዘንድ እጅግ ቀላል ነገር ነውና እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል (ኢሳ 49:9)።*

*ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ ነገሥታትም ወደ መውጫሽ ፀዳል ይመጣሉ (ኢሳ 60:3)።*

ስለዚህ እውነተኛ እውቀት አልነበራቸውም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ተሰጥቷቸው ሳለ ኃይሉን ክደው የሃይማኖትን መልክ ብቻ በመያዛቸው ክብሩ በሕይወታቸው ሊንጸባረቅ አልቻለም (2ጢሞ 3:5) የእግዚአብሔርን ሃሳብ በማወቅ ቀዳሚነት ነበራቸው ሆኖም ግን አልተጠቀሙበትም።

*ለእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ የአምልኮት መልክ አላቸው ሀይሉን ግን ክደዋል ስለዚህ ደግሞ ራቅ (2ጢሞ 3:5)።*

**2:21** *እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን?*

*ራስህን አታስተምርምን ?*

አይሁድ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት አለን እያሉ ራሳቸውን ማስተማር አቃታቸው:: ሌሎችን አታድርጉ ይላሉ ራሳቸው ግን ያደርጋሉ:: አህዛብን ጣዖት በማምለካቸው ይንቋቸዋል ነገር ግን እነርሱ ቤተመቅደሱን ይዘርፋሉ::

| *የሚሰብኩትን አለመኖር በጣም አደገኛና ፍጻሜውም የእግዚአብሔርን ስም ማሰደብ ይሆናል::* |
|---|

**2:23** *በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን?*

*እግዚአብሔርን ታዋርዳለህን? (ታሳፍራለህን?)*

በአማርኛችን ይህ ቃል ጠንከር ያለ መልዕክት አለው:: አንድ ሰው እንደተጠበቀው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር በተለይ የኔ ያለው ሰው በጣም ያፍርበታል:: እግዚአብሔርም የኔ ብሎ በመረጠው በእሥራኤል ይህንኑ የመሰለ እፍረት ወይም ውርደት ነው የደረሰበት:: ሁኔታው በእውነትም አሳፋሪ ነው::

**2:24** *በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከ*

*ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ::*

*ይሰደባል*

የአይሁድ ድርጊት እግዚአብሔርን በማሳፈር ብቻ የሚያቆም ሳይሆን በአህዛብ ዘንድ ስሙን የሚያሰድብ ነበር:: ይህ ስድብ የሚለው ቃል ከፍተኛ የሆነን ክስ ያመለክታል::

ክሱ የሚቀርበው ባላመኑ ሰዎች ነው። ለእነርሱ ክስ የአባታቸው የዲያቢሎስ ባሕርይ ስለሆነ በባህርያቸው ያደርጉታል። አደጋው ግን ለክሱ መነሻ ምክንያት ሆኖ የሚገኘው የእግዚአብሔር ወገኖች ስህተት ሆኖ መገኘቱ ነው።

**2:25** *ሕግን ብታደርግ መገረዝስ ይጥቅማል ሕግን ተላላፊ ብትሆን ግን መገረዝህ አለመገረዝ ሆኖአል።*

*ሕግን መተላለፍ - - - እንዳልተገረዙ መሆን*

ሕግን ጠቅሶ ሕግን መተላለፍ ከሕጉ ጋር ተያይዘው ከሚመጡ በረከቶች ያጎድላል። ሕግን የሚተላለፍ አይሁዳዊ መገረዙ አለመገረዝ ይሆንበታል። (ፊሊ. 3:3)

*እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና (ፊሊ. 3:3)።*

መገረዝ የሚጠቅመው ሕጉ እስከተጠበቀ ድረስ ብቻ ነው (ገላ 6:15፤5:3)። እንግዲህ የሚጠቅመው ሕግን መያዙ ሳይሆን አዲስ ፍጥረት መሆኑ ነው። ወደኛም እውነት ስናመጣው በሕይወት ላይ ለውጥ የሚመጣው ቃል ኪዳን በመግባት ብቻ ሳይሆን በገባነው ቃል ኪዳን መሠረት ለመኖር ራሳችንን በመስጠት ነው።

**2:26** *እንግዲህ ያልተገረዘ ሰው የሕግን ሥርአት ቢጠብቅ አለመገረዙ እንደመገረዝ ሆኖ አይቆጠርለትምን?*

*የሕግ ትዕዛዝ ከተጠበቀ - አለመገረዙ እንደመገረዝ ይቆጠራል*

ከፍቅር በመነጨ መንገድ ስንታዘዝ ጌታ የመታዘዝን በረከት ይሰጠናል። (እንደመገረዝ ይቆጠርልናል)። ይህም የሆነበት ምክንያት ዳግም ስንወለድ ጌታ በመንፈሱ የልባችንን ሸለፈት ስለገረዘው ነው (ቆላ 2:11፤ሐሥ 10:34-35)።

*2:27 ከፍጥረቱም ያልተገረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ሳለህ ህግን በምትተላለፈው በአንተ ይፈርድብሀል።*

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር ላይ የመታዘዝንና ያለመታዘዝን ግልጽ ውጤት ያስቀምጣል

- ያልተገረዘው አህዛብ ከጌታ በፍጥረቱ በተቀበለው የሕሊና ሕግ መሠረት ሕግን ሲፈጽም
- ሕግ የተቀበሉት አይሁዳውያን ሕግን ባለመፈጸማቸው ሕጉ ራሱ ይፈርድባቸዋል።

እንዲያውም በማይታዘዙት ላይ ይፈርዳል።

*2:28-29 በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና በግል*
*በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና ዳ*
*ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው መገረዝ*
*በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እን*
*በመጽሐፍ አይደለም የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔ*
*ነው እንጂ ከሰው አይደለም።*

እውነተኛ ግዝረትም ውጫዊና ስጋዊ አይደለም - - - በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር የሚፈጸም መንፈሳዊ ድርጊት ነው።

በውጫዊ ስርዓት አይሁዳዊ መሆን አይቻልም። ይሁዲ የሚኮነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ ነው። ይህም የሚገኘው የልብ ግዝረት በመንፈስ እማካይነት ሲከናወን ነው።

«አይሁድ» የሚለው ቃል «ይሁዳ» ከሚለው የነገድ ስም የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም ምስጋና ማለት ነው።

# ምዕራፍ ሦስት
# ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል

የሮሜ መጽሐፍ ዋነኛ መልዕክት (ማዕከላዊ ሃሳቡ) የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለመገለጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የመረጠውና የተጠቀመበት ዘዴ የሰውን ልጅ ኃጢአተኛ ነት፣ ከጽድቅ መጉደሉንና የረከሰ መሆኑን በማግለጥ መጀመርን ነው። ስለዚህ በሁለቱ ምዕራፎች እንደተመለከትነው በተለይ ከምዕራፍ 1:18 ጀምሮ አሁን በዝርዝር እስከምንመለከተው ምዕራፍ 3:20 ድረስ ሐዋርያው በደለኛ የሆነውን ሰው በሕግ ፊት አቅርቦ እንደሚሟገት አቃቤ ሕግ የመከራከሪያ ነጥቡን ያቀርባል። ነጥቦቹን አያይዘን አሁን ያለንበትን ክፍል ለማጉላት ይረዳን ዘንድ ሐዋርያው ጳውሎስ ደረጃ በደረጃ የሄደባቸውን መንገዶች እንመልከት

## አህዛብ በድለዋል ሮሜ 1:18-32

ሐዋርያው በዚህ ክፍል ስለ ሰው ልጅ ክፋትና በደል ያቀረበው ማስረጃ በጣም ከባድና አስጸያፊ ነው። ባጠቃላይ የሚያመለክተውም ሰው በክብር ጀምሮ በውርደት መዝቀጡን ነው። ለዚህ ሀሳቡ ሐዋርያው ጳውሎስ ማስረጃውን ሲያቀርብ:-

**ከ ቁ 18 - 20** - የከበረው ነገር ተገልጦላቸው ነበር ሊታወቅ የሚቻለው ዕውቀቱ ነበራቸው። በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነበር።

ከ ቁ 21 - 23 - እያወቁ፣ ግን እውቅና ሊሰጡት ወይም
ሊያከብሩት አልፈለጉም።

ከ ቁ 24 - 27 - በልባቸው ፍትወት ተቃጥለው ራሳቸውን
ለአስነዋሪ ድርጊት አሳልፈው ሰጡ።

ከ ቁ 28 - 32 - ለማይረባ አዕምሮ አልፈው ተሰጥተዋል። ስለዚህ
ራሳቸው ክፉ አድራጊ ብቻ ሳይሆኑ ክፉዎችን
ያበረታታሉ ይተባበራሉም።

በእነዚህ ሁሉ ፍጹም የመከራከሪያ መልስ ሊያቀርቡ በማይችሉባቸው ጥፋቶች አህዛብ በድለዋል !

## የጳውሎስ የሙግት ማጠቃለያ !

እግዚአብሔርን የማወቅ ዕውቀት ተሰጥቷቸው ሳለ አውቀው ሊያከብሩት ስላልፈለጉ፣ ይልቁን በልባቸው ፍትወት በመቃጠል ራሳቸውን ለስጋዊ ምኞታቸው አሳልፈው ስለሰጡና አስነዋሪ ድርጊት ስለፈጸሙ እግዚአብሔር ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ አህዛብ በድለዋል። ክቡር ፍርድ ቤቱ የነገሩን ግራና ቀኝ ተመልክቶ የሞት ፍርድ ! ይበይንልኝ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ !

# አይሁድ በድለዋል (ሮሜ 2:1-3:8)

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚያቀርበው የመከራከሪያ ነጥብ በጣም አደገኛ ነው። ምክንያቱም አይሁድ በድለዋል ብሎ መናገር በራሱ ለሞት የሚያበቃ ስለሆነ። እግዚአብሔርን አለመታዘዝ በራሱ ኃጢአት ቢሆንም አይሁድ ግን ይህንን ኃጢአት በድለናል ብለው በግልጽ አልተናዘዙትም። የብሉይ ኪዳን ነቢያት መከራን የተቀበሉት አይሁድን በድላችኋል ብለው በመናገራቸው ነበር።

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ሐዋርያው ጳውሎስ አይሁድን በድለዋል ብሎ ለማለት የሚያቀርበው የራሱ ማስረጃ አለው። ማስረጃዎቹም፦

**3:1-3** = አህዛብን በሚነቅፉበት ነገር ራሳቸው ተላላፊ ሆነው መገኘታቸው::

**3:4-11** = ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ቸርነት ወደ ንስሀ ሊመራቸው ሲገባ እነርሱ ግን በአመጻቸው ስለቀጠሉ ይህም እግዚአብሔርንያለመታዘዛቸው ግልጽ ማስረጃ መሆኑ::

**3:12-24** = ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ሕግ ከመፈጸም ይልቅ ሕጉ ለእነርሱ በመሰጠቱ ብቻ ከአህዛብ የተሻሉ እንደሆኑ በመቁጠር ሕግ ተላላፊዎች መሆናቸው::

**3:25-29** = ውጫዊ ሰውነታቸውን በመገረዝ በልባቸው ግን የእግዚአብሔርን ሕግ ማፍረሳቸው::

በእነዚህ ምክንያቶች አይሁድ እግዚአብሔርን በድለዋል ስለዚህ አሁንም ፍርድ ቤቱ ግራና ቀኝ ተመልክቶ ፍርድ ይሰጥልኝ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ::

እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች መነሻ በማድረግ ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ የሚያነሳቸውን ዋና ሀሳቦች መመልከት እንችላለን::

ሐዋርያው ምዕራፍ ሦስትን ሲጀምር ሊቀርቡ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን የመሟገቻ ጥያቄዎች በማንሳትይጀምራል:: «አይሁድ በድለዋል የምትል ከሆነ ታዲያ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድነው?» በማለት የተቃዋሚዎቹን ጥያቄ በማንሳት ይጀምራል እስኪ ነጥብ በነጥብ እንመልከተው::

**3:1** ***የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድነው? የመገረዝስ ጥቅሙ ምንድነው?***

የጳውሎስ መልስ ብልጫቸው በሁሉ ነገር ነው የሚል ነው::

ይህንን መልሱን ስንመለከተው በመንፈስ መገረዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋናን የሚያስገኝ ከሆነ በስጋ መገረዝ ደግሞ ለአይሁድ ብልጫው በሁሉ ነገር ነው። በሁሉ ነገር የሚለው መግለጫ በቀጣዩ ቁጥር በግልጥ ተብራርቶ ተቀምጧል።

## 3:2 *አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው*

***አስቀድሞ*** - የእግዚአብሔር ሀሳብ ወደ አህዛብ ከመምጣቱ በፊት በቀዳሚነት የተቀበሉ መሆኑን ያመለክታል።ይህም አንዱ የብልጫ ምልክት ነው።

***የእግዚአብሔር ቃላት*** - ለአይሁድ የተሰጠውን የብሉይ ኪዳን መጻህፍትን ያመለክታል (ቲቶ 1:3)

*በዘመኑም ጊዜ ፡-መድሀኒታችን እግዚአብሄር እንዳዘዘ፡- ለእኔ አደራ በሰጠኝ ስብከት ቃሉን ገለጠ፤ (ቲቶ 1:3)።*

***አደራ*** - አደራ የሚሰጠው ለሚታመን ነው። ሲያምናቸው ታማኝ ሆነው አለመገኘታቸው ለራሳቸው ብዙ በረከት ቢቀርባቸውም እግዚአብሔር ግን አምኖ አደራ ሰጥቷቸው ነበር።
(1ቆሮ 9:17፤1ተሰ 2:4፤ ገላ 2:7 )

*ይህን በፈቃዴ ባደርገው ደመወዝ አለኝና፤ ያለፈቃዴ ግን ባደርገው መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል። (1ኛቆሮ 9:17)።*

*ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሄር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን ፡- እንዲሁ እንናገራለን፡-*

*ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሄርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም (1ኛ ተሰ 2:4)።*

*ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው የወንጌል አደራ እንደተሰጠኝ አዩ (ገላ 2:7)።*

ሐዋርያው የእነርሱ አለማመን (ታማኝ ሆኖ አለመገኘት) የእግዚአብሔርን ታማኝነት ሊቀይረው እንደማይችል በቀጣዩ

ቁጥር ያስረዳል ይህንንም በመከራከሪያ ጥያቄ መልክ ያቀርበዋል።

## 3:3 *አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?*

ለዚህ የመከራከሪያ ነጥብ የጳውሎስ ምላሽ ቁርጥ ያለና የማያወላውል ነው። «በፍጹም!» የሚል እንዲያውም ታማኝነቱን የበለጠ ያጸናዋል እንጂ።

ታማኝነቱንም በሁለት መንገድ የበለጠ ያጸናዋል :-

- ለኃጢአተኛው የኃጢአቱን ዋጋ በመስጠት

- ለሚወዱት ደግሞ በረከትን በመስጠት

| |
|---|
| **እንግዲያው እግዚአብሔር በታማኝነቱ እንደጸና ይኖራል በፍርዱም ደግሞ ጻድቅ (ትክክል) ነው።** |

## 3:4 *ሰው - - - ውሸተኛ - - - እግዚአብሔር እውነተኛ*

እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ስንል ባህርዩን መግለጻችን ነው ማለትም እውነት ነው። ባህርዩ ራሱ እውነት ስለሆነ ድርጊቱና ንግግሩም እውነት ነው።

እውነት የስላሴ ባህርይ ነው።

- እግዚአብሔር አብ እውነተኛ ነው (ዮሐ 3:33)
- እግዚአብሔር ወልድ እውነተኛ ነው (ማቴ 22:16፤ ዮሐ 7:18)
- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ነው (ዮሐ 14:17)

*ምስክሩን የተቀበለ እግዚአብሄር እውነተኛ እንደሆነ አተመ (ዮሐ 3:33)።*

*ደቀ መዛሙርታቸውንም ሄሮድስ ወገን ጋር ላኩበት:- እነርሱም :- መምህር ሆይ :- እውነተኛ እንደሆንህ በእውነትም የእግዚአብሄርን*

*መንገድ እንድታስተምር እናውቃለን፡- ለማንምም አታዳላም፡- የሰውን ፊት አትመለከትምና (ማቴ 22:16)::*

*ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እርሱ እውነተኛ ነው በእርሱም አመጻ የለበትም (ዮሐ 7:18)::*

*እርሱም አለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ (ዮሐ 14:17)::*

ስለዚህ የሰው ውሸት ይህንን ባህርዩን ሊያስለውጠው አይችልም እርሱ ዘላለም እውነተኛ ሆኖ ይኖራል::

**3:5-8** ***ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆን ምን እንላለን? ቁጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነውን? እንደ ሰው ልማድ እላለሁ:: እንዲህ አይሁን እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል? በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ስለምን በእኔ ደገሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና:: የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው::***

***ዓመጻችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ስለ ምን መልካም እንዲመጣ ክፉ አናድርግ? - -***

ሦስተኛውና አይሁድ የመከራከሪያ ሀሳብ አድርገው ያቀርቡታል ብሎ ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ያነሳል::

«ኃጢአታችን የእርሱን ጽድቅ የሚገልጠው ከሆነ እንዴት ይፈርድብናል?» የሚል ዓይነት ነው::

ሐዋርያው ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ መልካምን ነገር ከውስጡ ለማግኘት ክፉ መሥራት የለብንም አውቀን የምንሰራ ከሆነ ግን እግዚአብሔር በጽድቁ ይፈርዳል::

በማለት ፍርዱ ራሱ የማይዛባ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጣል:: ይህን ሀሳብ በሚገባ ለመረዳት ትንሽ ተንተን አድርጎ መመልከት ያስፈልጋል::

ሀ. የአዳም ዘር ኃጢአት ከመስራቱ በፊት እግዚአብሔር ክብሩን ገልጦለት ነበር:: ይህም የሆነው ጌታ በማንነቱ ለፈጠረው ሰው ክብሩን መግለጥ ስለፈለገ ከራሱ ከማንነቱ ከጽድቁ የወጣ ነበር እንጂ ሰው ይህንን ለማምጣት የሚያስችል ብቃት ስላለው አልነበረም::

ለ. የሰው ልጅ (የአዳም ዘር) ኃጢአት ከደረገ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር በድካሙ ጣልቃ በመግባትና በማገዝ ክብሩን ገልጧል::

- እግዚአብሔር በሁለቱም መንገድ ጽድቁን ገልጧል
- አዳምና ሔዋን የወሰዱትን እርምጃ ሲወስዱ የነበራቸው ሀሳብ የሰው ክብር ላቅ ያለ ሆኖ ይገኛል የሚል ነበር:: ሆኖም ግን ወደ ውርደት የሚያዘቅጥ ሆነ:: እግዚአብሔር ግን በድካማቸው ጣልቃ በመግባት፣ ከተደበቁበት በማውጣትና የጸጋ ልብስን በማልበስ ክብሩን ገለጠ:: ከድካማቸው ለማውጣት በሠራው የጽድቁ ሥራ ክብሩን ይበልጥ ገለጠ::

«መልካም እንደሆነ አየች» የሚለው ቃል ለአዳምና ለሔዋን በራሳቸው አመለካከት ዘራቸውን ወደ ክብር ለማምጣት የመረጡት የራሳቸው «የእኔ መልካም» እንደ ነበር ያመለክታል:: ጌታ ግን በጸጋው የእነርሱን መልካም አስወገደና የእርሱን መልካምነት ገለጠ::

ይህንን ስንል ግን እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ኃጢአት እንዲሰሩ በመገፋፋት የእርሱን ቸርነትና ክብር ይገልጣል ማለታችን አይደለም:: አይሁድ ግን ያሰቡት ይህንን ይመስላል::

የእግዚአብሔር እውነተኛነት (የመልካምነቱም ሆነ የፍርዱ) ያለ ኃጢአት ሁልጊዜ ሕልውናው ታውቆ ግልጽ ሆኖ ይኖራል:: እግዚአብሔር በመልካምነቱ በሰራቸው ሥራዎቹ ራሱን ገልጧል ዘወትርም ይገልጣል:: ስለዚህ ክብሩና መልካምነቱ እንዲገለጥ የኃጢአት ድጋፍ አያስፈልገውም:: (ያዕ 1:17)

*በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፡- መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሐናት አባት ይወርዳሉ (ያዕ 1:17)::*

ለኃጢአተኛው በሚያሳየው ቸርነት ጸጋው ይገለጣል:: ከዚህም እውነት በመነሳት የጌታ ዘላለማዊ ዓላማ በጸጋው ፍጹማን ባደረጋቸው የክርስቶስ አካል ብልቶች ክብሩን መግለጥ ነው ማለት እንችላለን::

ጌታ ይፈርዳል ስንል የጌታ የልቡ መሻት ነው (ፈቃዱ ነው) ማለታችን አይደለም:: ነገር ግን የሰው ልጆች ኃጢአት በሚያደርጉበት ጊዜ ይህንን ባህርዩን ይገልጣል:: ምክንያቱም ኃጢአትን መቅጣት የጽድቁ መገለጫ ነውና::

ሐዋርያው ከዚህ ቀጥሎ የሚያነሳው የመከራከሪያ ነጥብ፡- አህዛብ ከበደሉ፣ እንግዲያው ዓለም ሁሉ በድሏል:: ስለዚህ በዓለም ሁሉ ላይ ፍርድ ቤቱ ግራና ቀኙን መርምሮና ተመልክቶ ፍርድ ይስጥልኝ! የሚል ነው::

## 3:9-20 *ከሰናቸዋል - - - የሚያስተውል የለም*

ከሰናቸዋል የሚለው ቃል የክሱን ቃል ማስረዳት እንችላለን፣ አይተናል ገብቶናል ተረድተናል ማለት ነው::

የክሱ ምክንያት ደግሞ፡-

ሀ. የሚያስተውሉ አለመሆናቸው፡ ይህ ግድፈት በአዕምሮ የሠሩትን ኃጢአት ያመለክታል

ለ. ጌታን የሚፈልግ ልብ የሌላቸው መሆኑ

ሐ. ፈቃዳቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስፈጸሚያ እንዲሆን አለመፍቀዳቸው ይህ ግድፈት መልካም ነገር ለማድረግ ፈቅዶ አለመፈለጉን (እምቢተኝነት በተግባር) የሚገልጽ ነው።

እንግዲህ ኃጢአተኛው ሰው እግዚአብሔርን መፈለግ ካልቻለ የቀረው ምርጫ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ፍለጋ መምጣቱ ብቻ ነበር። ወደ ኃጢአተኛው ሲመጣ ግን ኃጢአተኛው ፣ ኃጢአትን እምቢ የሚልበትን አቅምና ጉልበት የሚያገኝበትን ጸጋ ይዞ ነው የመጣው። ይህ ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን የሚያስክድ ነው(ቲቶ 2: 11-12)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ጸጋ ዘወትር የሚሻው ኃጢአተኛው ከኃጢአት ርቆ ማየትን ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚሁ መጽሀፍ ከቁ 13-18 ድረስ ለፍርድ ቤቱ የኤክስሬ ምርመራ ውጤት የሚያቀርብ ዓይነት ይመስላል። በቁ 13-14 የተገለጸው ሃሳብ የሰውን የንግግር አካላት የሚያመለክት ነው እነርሱም አንደበት፣ጉሮሮ፣ከንፈር ናቸው።

## ጉሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው

መጽሐፍ ቅዱስ በማቴ 12:34 በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራል ይለናል። ምክንያቱ ምንድነው? ብለን ስንል፣ ኃጢአተኛው በመንፈሱ ሙት ነው። ስለዚህም ከአንደበቱ የሚወጣው የሞት ቃል ነው።

የተከፈተ መቃብር የሚጠብቀውም ሙት አካል ነው፤ ክፍቱን ከተዋችሁትም የሚያወጣው የሞት ሽታ ነው።

## የእባብ መርዝ በአንደበታቸው አለ

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ቃል ሲጠቀም በተምሳሌትነት ሊገልጥ የወደደው እባብ የሚነድፍበትን መርዙን ከሚደብቅበት ከምላሱ ስር ከተሸጎጠው ከረጢት ጋር በማመሳሰል ነው። በከንፈሮቻቸው ስር መርዝን የተሞላ ነገር አለ። ሁኔታ ሲያመች ያወጡታል ይነድፉበታል።

ከዚህም የተነሳ ሰዎች ከአንደበታቸው በሚወጡ መርዛማ ቃሎች ይነደፋሉ:: ይሞታሉም::

ያዕቆብም አንደበት በጣም ትንሽ የሰውነት ክፍል ሆኖ ሳለ ትልቅ ጫካን እንደሚያቃጥለው ትንሽ እሳት ዓይነት አጥፊነቷ የከፋ መሆኑን በመልዕክቱ ም 3:5-6 ጠቅሷል::

ጳውሎስም ይህንኑ በማጠናከር የምላስን አደገኝነት ከእባብ መርዝ ጋር በማያያዝ ጠቅሶታል::

## አፋቸው እርግማንና ምሬት ሞልቶበታል

ሐዋርያው በዚህ ክፍል የገለጠው ሀሳብ እነዚህ ሰዎች የሚታይባቸው ባሕርይ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ሁኔታዎች የማክሰቱ የምሬት ቃላቶችን የማውጣት ሳይሆን አዘውትረው ማድረግን ልማድ ያደረጉና አፋቸውም ይህንን ዘወትር ለማድረግ ያለ እጥረት ሙሉ ሆኖ የሚገኝ መሆኑን ነው::

እስኪ ወገኖች ቆም ብላችሁ አስቡ ከአንደበቱ የሚወጣው ነገር እርግማንና ምሬት ከሆነ ሰው ጋር ምን ያህል ደቂቃ ታግሳችሁ መቆየት ትችላላችሁ? እጅግ አስቸጋሪ ነው::

## በቁ 15-16 የተገለጸው ሃሳብ የሰውን አረማመድ የሚያመለክት ነው

እግሮቻቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው:: የአንድ ሰው አንደበቱ ክፋትን የተሞላ ከሆነ ድርጊቱ ደግሞ አፍራሽና አጥፊ ነው:: በመሠረቱ የክርስቲያኖች እግር ወንጌልን መጫሚያው ያደረገ ነው:: (ኤፌ 6:15) ይህም ወንጌል የሰላም ወንጌል ነው:: ሰላም የሚመጣውም ከሰላሙ ንጉሥ ጋር ከሚኖር የጠበቀ ህብረትና ቁርኝት ነው:: የኃጢአተኞች እግር ግን ለክፋትና ለጥፋት ፈጣን ነው::

የሚሄዱበትም ጎዳና ይህንኑ ጥፋት ያለ ከልካይ ለመፈጸም እጅግ ሰፊ ነው:: (ማቴ 7:13-14) ስለዚህ የሰላምን መንገድ አያውቁም:: (ቁ..17) ሐዋርያው በዚህ ስፍራ ጫን ብሎ ማሳወቅ የፈለገው ነጥብ የነዚህ ሰዎች

ክፋት በአዕምሮ ውስጥ ካለ የጥፋት አቋም አልፎ በድፍረት በተግባር የሚገለጥ ክፋት ነው፡፡ ስለዚህ ከሰላም መንገድ በጣም የራቁና የጥፋት መንገድ የተመቻቸው ናቸው የሚል ብርቱ ሀሳብ ነው፡፡

*እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፡- የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፡- በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ (ኤፌ 6:15)፡፡*

*በሰፊው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ ፡- መንገዱም ትልቅ ነውና፡- ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ ፡- መንገዱም የቀጠነ ነውና፡- የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው (ማቴ 7:13-14)፡፡*

**ኃጢአተኛ የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅም መቀበልም አይፈልግም ይልቁኑ የሰይጣንን ውሸት መቀበል ይቀለዋል፡፡ ይህም አቋሙ እግዚአብሔርን ከመፍራት ይልቅ በትዕቢት በገዛ መንገዱ መሄድን ምርጫው እንዲያደርግ ይገፋዋል፡፡ ጳውሎስም ይህንኑ መግለጫ በማጠናከርና በመዝ 36:1 የተጠቀሰውን «እግዚአብሔርን መፍራት በዓይናቸው ፊት የለም» የሚለውን በመንተራስ እግዚአብሔርን መፍራት ከሌለ ደግሞ ጥበብና ማስተዋል የሌለ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጣል፡፡**

**3:19** ***አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሄር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤***

***እንግዲህ - - - አፍ ሁሉ - - - ዓለም በሙሉ***

ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ መግለጫ ከላይ የዘረዘራቸውን ማስረጃዎች በሙሉ ወደ መደምደሚያ ሊያመጣቸውና ዓለም ሁሉ በድሏል! ብሎ በችሎቱ ፊት ያቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ ጭብጥ ሊያደርገው እንዳሰበ እንዳደረገውም ያመለክታል፡፡

አይሁድ ሕግ አለን ሲሉ ሕጉን በማፍረሳቸው ፤ አህዛብም የጥፋትንና የሞትን መንገድ በመምረጣቸው ሁሉም የሚናገሩት አጡ፡፡ አፋቸው ተዘጋ - - - ጻድቅ ነኝ ብሎ በፊቱ የሚቆምም ጠፋ፡፡ ሁሉ በደለኞች ሆኑ፡፡

*3:20 ይህም የህግን ሥራ በመስራት ሥጋ የለበስ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።*

*ሕግን በመጠበቅ - - - ፃድቅ ሊባል አይችልም*

ሕጉን በሙላት የፈጸመ ሊጸድቅ ይችላል። ነገር ግን ማንም ሰው ሕግን መፈጸም አልቻለም ስለዚህ ማንም ፃድቅ የለም።

1. ሕጉ ኃጢአትን ያሳውቀናል
2. በኃጢአት ተሸንፈን ለፍርድ የተጠበቅን መሆናችንን ያሳወቀናል

ስለዚህ በሙሴ ሕግ ስር ያሉ አይጸድቁም። ምክንያቱም ሊፈጽሙት አልቻሉምና። አቅምም አልነበራቸውምና።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ በኋላ የሚያነሳው ነጥብ፣ እንግዲያው ዓለም ሁሉ በደለኛ ከሆነና በራሱ ሥራ ሊጸድቅ ካልቻለ እግዚአብሔር ይህንን ኃጢአተኛ ሰው ሊያድን የሚችልበት መንገድ መቀየስ ነበረበት። ይህንንም በዘላለም ሃሳቡ ፈጽሞታል ወደሚለው ወሳኝ ሃሳብ የሚያሸጋግር ብርቱ ነጥብ ነው።

*3:21 አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል*

*ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት - - - ተገልጧል።*

1) ሕግና ነቢያት -- እግዚአብሔር ለበደለኛው ዓለም ያዘጋጀው የጽድቅ መንገድ በሕግና በነቢያት ውስጥ የተቀመጠ መሆኑን በግልጥ ለማሳየት ሐዋርያው ይህንን

መግለጫ ተጠቅሟል (ማቴ5:17፤22:40፤ሉቃ 24:27)።

**2) የመሰከሩለት** – እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን የገለጠው የምህረትና የጸጋ እውነት በህግ ውስጥ ተነግሮ ነበር። ይህም እውነት በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ ውስጥ መስዋዕት ይቀርብ በነበረበት ጊዜ በግልጽ ይታይ ነበር። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ሃሳብና አይሁዳውያን የተሳለፉት የቱጋ ነበር? ብለን ስንጠይቅ በግልጽ የተሳሳቱበትን መስመር እንመለከታለን።

እግዚአብሔር ሕግን የሰጣቸው ኃጢአታቸውን እንዲያዩበትና በምህረቱና በጸጋው እንዲታመኑና እርሱን ተስፋ እንዲያደርጉ ነበር። እነርሱ ግን ጌታን ትተው በሕጉ መመካትና ሕጉን ተስፋ ማድረግ ጀመሩ። ስለዚህም ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጨርሶ ራቁ።

ስለዚህ ሐዋርያው የእግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ በሕጉም ሆነ በነቢያት ቃል የተነገረ ነው። ተመስክሮለታል በማለት ማብራሪያውን ያስቀምጣል።

**3) ተገልጧል** - ይህ ቃል ከላይ የተሰጠውን ማስረጃ በአራት ነጥብ የሚያሳርፍ ውብ መደምደሚያ ነው። ሃሳቡም በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ አሁን ተገልጧል። የሚል ኃጢአተኞችን ሁሉ ከሰበብና በራስ ጽድቅ ከመመካት ከማመካኘትና ከከንቱ ተስፋ ወጥተው ወደዚህ ወደተገለጸው ጸጋ እንዲቸኩሉ የሚያደርግ የማረጋገጫ እውነት ነው።

*እኔ ግን ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም (ማቴ 5:17)።*

*እኔ ግን እላችኋለሁ ፡- በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሀነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል(ማቴ 5:22)።*

*ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው (ሉቃ 24:40)።*

ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚሻገረው ወደ መልዕክቱ ሁለተኛ ዋና ሃሳብ ነው። የሚያተኩረውም ዓለም ሁሉ በደለኛ ከሆነ ዓለም ሁሉ ደግሞ መዳን ይገባዋል። ለመዳን ደግሞ እግዚአብሔር መንገድን አዘጋጅቷል የሚል ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ የእግዚአብሔር ጽድቅ መገለጥ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ ማለትም (ሮሜ 3:21-31) ባለው ክፍል ጽድቅን እንዲህ ያብራራዋል። ጽድቅ የተገለጠው፡-

- ከሕግ ውጪ ነው (ቁ. 21)
- በክርስቶስ በማመን ነው (ቁ 22 (ሀ))
- ለሰው ሁሉ ነው (22 (ለ) - 23)
- በጸጋ ነው (24)
- እግዚአብሔር ትልቅ ዋጋ ከፍሎበት ነው (24 (ለ) 25)
- በፍፁም ፍትህዊነት ነው (25 (ሀ) -26)

ሕጉን ዋጋ ቢስ ለማድረግ ሳይሆን ለማጽናት ነው(27-31)

## ከህግ ውጪ የሆነ

ሐዋርያው በዚህ ቃል መግለጥ የፈለገው በክርስቶስ የጸድቅ ሥራ አልቆና ተጠናቆ ለሰው ልጅ የተገለጠው ጽድቅ የሰው ድርሻ የሌለበት መሆኑን ነው። ምክንያቱም በብሉይ ዘመን ጽድቅ የሚገኘው በሰው በጎ ምግባር ነበር (ሕጉን በመጠበቅ) በመሠረቱ ሕጉ የሚገልጠው የእግዚአብሔርን

ጽድቅ ነው። ሕጉ በራሱም ፍጹምና ንጹህ ነው። ሰው ግን ይህንን ንጹህ ነገር በራሱ ሊፈጽመው አልቻለም።

### 3:22 *ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ*

የሆነ የሚለው ቃል ገና የሚሆንን ሳይሆን ሆኖ ያለቀን ነገር የሚያመለክት ነው። ሌላው ይህ ቃል የሚያመለክተን ነገር እምነት ከመድሀኒቱ ጋር የምንገናኝበት መንገድ እንጂ ራሱ መድሀኒቱ አለመሆኑን ነው። በእምነት በኩል ሄደን መድሀኒታችን የሆነውን ክርስቶስን እናገኘዋለን።

«በእምነት በኩል » የሚለውን ቃል በሚገባ ለመረዳት ወደ ቀድሞው አዳማዊ ማንነታችንና ድካማችን መመልከቱ ተገቢ ነው። የቀድሞው አዳማዊ ማንነታችን አለማመን ዋነኛ ባህርያችን ነበር። በዚህም ምክንያት ወደ ጌታ ሊያመጣን የሚችል አንድም ከራሳችን የሆነ በጎ ነገር አልነበረንም የለንምም። አሁን ግን በክርስቶስ ከተገለጠው የሕይወት መንፈስ የተነሳ የሚያምን ልብ ተሰጠን (አዲስ ፍጥረት ሆነን) ይህም የእምነት ስጦታ በእኛ ውስጥ እንዲሰራ ያደረገው ጌታ ነው። የጀመረው እርሱ ነው ወደ ፍጻሜ የሚያደርሰውም እርሱ ነው።

#### የሚገኝ (ተገኝቷል )

ይህ ቃል እኛ ደክመን ባጠን የምናመጣው ሳይሆን በራሱ በተወሰነለት ስፍራ የሚገኝ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መገለጡ ወደ እኛ መጣ እንጂ እኛ መገለጡን አላመጣነውም ማለት ነው። ዓይናችንን ስንከፍተው በስፍራው ሆኖ አገኘነው።

#### በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን

የጽድቁ መገለጥ የተገኘው በክርስቶስ በማመን መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ሥራው የክርስቶስ ታማኝነት ውጤት ነው።

### 3:23 *ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል*

ሕግ እለን የሚሉት አይሁድም ሆኑ፣ ያለ ሕግ የሆኑት አህዛብ ሁሉም በእግዚአብሔር የፍርድ ችሎት ፊት ኃጢአተኞች ሆነው መገኘታቸውንና ፍርድ የሚገባቸው ሆነው መገኘታቸውን ተመልክተናል:: ሐዋርያው አሁን ደግሞ ወደሚቀጥለው የደህንነት ስጦታ ሊሻገር ስለሆነ ለሁሉ ይህ ስጦታ የሚያስፈልግ መሆኑን ለመጥቀስ ይህንን አባባል ተጠቅሟል:: ይህንንም ያደረገው ሁሉ ኃጢአትን ከሰሩ ሁሉም ፍርድ ተመድቦባቸዋል ማለት ከፍርድ ለማምለጥ ደግሞ ብቸኛው መንገድ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የደህንነት ስጦታ አይሁድ ወይም የግሪክ ሰው ሳይባል ሊቀበል እንደሚገባው ማሳየት ስላለበት ነው:: ስናጠቃልለውም ሁሉም ሰው በፊተኛው በአዳም ምክንያት የተኮነነ መሆኑን ይህ ቃል ያመለክታል::

## *የእግዚአብሔር ክብር ጎድሏቸዋል*

ሁሉ ሰው ኃጢአትን ስለሠራ፣ ራሱም ደግሞ ኃጢአትን ስለሰራ በሕይወቱ የተፈጸመው አሳዛኝ ክስተት ከእግዚአብሔር ክብር መጉደል ነው:: የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ውብ የባሕርይ ተካፋይነትና ከእርሱ ጋር ሕብረት ከማድረጉ ቁርኝነት ውስጥ ወጣ:: ከክብሩ ጎደለ::

የሰው ልጅ በፊተኛው አዳም ውስጥ ሆኖ ሊቀበለው አይችልም በሌላ መንገድም ሰው በኃጢአት ውስጥ ሆኖ የጽድቁን ባሕርይ ሊያሳይና ሊያንጸባርቅ አይችልም::

ይህንን ሃሳብ በተብራራ ሁኔታ ለመመልከት ሀሳቦቹን በነጥብ ማስቀመጡ ይጠቅማል::

ሀ. ሰው ሁሉ ኃጢአትን ሠርቷል - በፊተኛው አዳም፣ በራሳችንም ሥራ

ለ. በፊተኛው አዳም ውስጥ ባለንበት ዘመን ሁሉ አንዱ ከሌላው የሚሻል አልነበረም - 2ቆሮ 10:12

ሐ. ሁላችንም ክብር ጎድሎናል

*ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርምና፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ:- ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ:- አያስተውሉም (2ኛ ቆሮ 10፤12)::*

## 3:24 *በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው*

ሐዋርያው ይህንን ቃል ሲጠቀም ማመልከት የፈለገው አንድ ዋነኛ ነገር ኃጢአት የሠራውና ከእግዚአብሔር ክብር የጎደለው ሰው ወደ እግዚአብሔር የክብር ተስፋ ሙላትና ፍጻሜ ሊደርስ የሚችልበትን ብቸኛ መንገድ ነው:: ማለትም « ጻድቃን ናችሁ» ተብሎ የታወጀበትን ምክንያት የሚያመለክት ነው::

- ጥቂት እልፍ ብለን በምዕራፍ 5:2 ላይ ያለውን ሀሳብ ስንመለከት እግዚአብሔር ወደ ክብሩ የመመለስ ተስፋን የሰጠ መሆኑን ያመለክታል::
- ይህ ተስፋ የተፈጸመው ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ታማኝነት ምክንያት ነው (2ቆሮ 4:6፤ 2ቆሮ 3:18፤ 2ተሰ2:14) ::
- አሁን በክርስቶስ ያለን ሁላችን ወደ ክብሩ ገብተናል ማለትም መንግሥቱ ይገዛናል:: (ከጸጋውና ከተስፋው ክብር የተነሳ ወደ ክብሩ ሙላት እንገባለን) (ሮሜ 8:18፤29 ፤ ፊሊ 3:21)::

*በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሄርን የክብሩን እውቀት ብርሀን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ:-- በጨለማ ብርሀን ይብራ ያለ እግዚአብሄር ነውና (2ኛ ቆሮ4:6)::*

*እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደመስታወት እያንጸባረቅን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን( 2ኛ ቆሮ 3:18)::*

*ለዚህም የጌታችንን የእየሱስ ክርስቶስ ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ (2ኛ ተሰ 2:14)::*

*ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን ያሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደል አስባለሁ (ሮሜ 8:18)::*

*ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸዉንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው (ሮሜ 8:29)*

*እኛ ሀገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድሀኒትም እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን እርሱ ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሰራር ክብር ሲጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሲጋችን ይለውጠዋል (ፊሊ 3:21)::*

## ቤዛነት

ቤዛ የሚለው ቃል ቀጥተኛ የአማርኛ ፍቺው «ቀድሞ የራስ የነበረን በአንድ ወቅት ደግሞ በሌላ ወገን የተወሰደን ውድ ነገር ዋጋ ከፍሎ ማስመለስንና የራስ ማድረግ» የሚል ነው:: በዚህ ፍቺ መሠረት የኃጢአት ባሪያ የሆነው ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም መፍሰስ ምክንያት ዋጋ ተከፍሎ መገዛቱን በክብሩ ውስጥ ለመኖር ብቃት ማግኘ ቱን እንመለከታለን::

## እንዲያው

እንዲያው የሚለው ቃል ያለ ምክንያት የሚለውን ፍቺ ያመለክታል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐ 15:25 ላይ ይህንን ተጠቅሟል::

ለደህንነታችን እኛ የከፈልነው ዋጋ የለም:: ቢሆንም ግን የተከፈለው ዋጋ ቀላል ዋጋ አልነበረም:: <u>እንዲያው</u> ሲባል ምንም የተከፈለ ዋጋ የለም ማለት አለመሆኑን ልብ ማለት ይገባል::

ለምሳሌ ሁላችንም ወደ ረጃጅም ፎቆች ውስጥ ስንገባ በቀጥታ ወደምንፈልገው ፎቅ ሊያደርሰን የሚችለው ሊፍት በር ላይ ቆመን የመክፈቻ ቁልፎችን ተጭነን እንጠብቃለን:: ሊፍቱም ካለበት ቦታ እኛጋ ሲደርስ በሩን ከፍቶ ያስገባናል ወደ ፈለግነውም ያደርሰናል:: ይህንን አገልግሎት ለማግኘ ት እኛ የተጠየቅነው ዋጋ የለም ሆኖም ግን የፎቁ ባለቤት ያንን ሊፍት ለማስገጠም እጅግ ብዙ ዋጋ ከፍሏል:: እኛ በነጻ ተገለገልንበት እንጂ ዋጋው በጣም ውድ ነበር:: እኛን ለመጠቀም ባለቤቱ ውድን ዋጋ ከፈለ:: ይህም ህንፃውን ሊሰራ ሲያስብ ባስቀመጠው እቅድ መሠረት ያከናወነው ነው:: የደህንነታችንም ነገር እንዲሁ በእግዚአብሔር የዘላለም እቅድ ውስጥ የነበረና የተፈጸመ ጉዳይ ነው::

## በጸጋው

ይህም ማለት የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ማለት ነው:: በሌላ አነጋገርም በጎ ፈቃዱንና አሠራሩን መግለጡን እኛም ወደ ክብሩ ለመመለስ ብቃት ያገኘንበት አሠራር ያሳያል::

## 3:25 *ማስተሰርያ*

እግዚአብሔር በባህርዩ በኃጢአት ላይ ይቆጣል ይቀጣልም ይህም ፍትሐዊነቱን ያሳያል:: ነገር ግን የሰውን ልጅ ለማዳን ባለው የዘላለም እቅድ መሠረት ይህ ባህርዩ ቁጣው ሳይገለጽ ሊያድነው ስለወደደ የልጁን ደም ማካካሻ አድርጎ ማቅረቡን ያመለክታል::

***አቆመው*** - ይህ ቃል ቀጥተኛ ፍቺው :- ገለጠው ፣ ይፋ አደረገው፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ማለት ነው::

> እግዚአብሔር በዘላለም ሃሳቡ ክርስቶስ መከራ ይቀበል ዘንድ ደሙንም ያፈስስ ዘንድ ወስኖ ነበር:: (ዘፀ 29:36፤ ዘሌ 16:10፤)

> *ለአሮንም ክህነት የታረደውን የአውራ በግ ፍርምባ ወስደህ ለማወዘውዝ ቁርባን በእግዚአብሔር ፊት ትወዘውዘዋለህ እርሱም ያንተ ወግ ይሆናል (ዘፀ29:36)::*

*የመለቀቅም አጣ የሆነበትን ፍየል ያስተሰርይበት ዘንድ ለመለቀቅም ወደ ምድረ በዳ ይወስደው ዘንድ በሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ያቆመዋል (ዘሌ16:10)::*

የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ለኃጢአተኞች የመፍሰሱና የማስተሰርያው ሂደት ይፋ መሆኑ እጅግ መልካምና ከፍቅር የመነጨ ነገር ለሰው መደረጉን እንጂ ሰው መልካም ከማድረጉ የተነሳ የተደረገለት መሆኑን አያመለክትም(1ዮሐ 2:2፤ 4:10)::

*እርሱ የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለአለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ (1ዩሐ 2:2)::*

*ፍቅርም እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰሪየ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም (1ዩሐ 4:10)::*

የክርስቶስ ኢየሱስ መከራ መቀበልና ደሙን ማፍሰሱ ሁለት ገጽታ አለው::

ሀ/ የጌታን ፍርድ (እውነቱንና ጽድቁን)
ለ/ የጌታን ይቅርታ (ጸጋውንና ምህረቱን)

እነዚህ ሁለቱ ተጣምረው በመስቀል ላይ ተገለጡ በኢየሱስ በኩል ማለት ነው:(መዝ 85:10 ፤ኢሳ 45:21 ፤ ዘካ 9:9) ልጁን በመስቀል እንዲሞት በመፍቀድ ጽድቁን ገለጠ ፍትሃዊነቱን ማለት ነው:: ከልጁ ሥራና ከከፈለው ዋጋ የተነሳ ደግሞ ሞት ለተገባው ኃጢአተኛ ሕይወት ተሰጠ::

*ምህረት እና እውነት ተገናኙ ጽድቅ እና ሰላም ተስማሙ (መዝ 85:10)::*

*ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ፤ ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሄር አይደለሁምን? ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም እኔ ጻድቅ አምላክና መድሀኒት ነኝ ከእኔ በቀር ማንም የለም (ኢሳ 45:21)::*

*አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ አንቺ የእየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በይ፤ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው ትሁትም ሆኖ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል (ዘካ 9:9)::*

ይህንን ድንቅ ሥራ ስንመለከት እግዚአብሔር ግን ይህንን ሁሉ ለምን ማድረግ አስፈለገው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። የሚቀጥለው ሀሳብ ይህንን ያብራራልናል።

## በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት

እስካሁን የተሰጡት ትንታኔዎች ሁሉ በዚህ የቁጥሩ ማሰሪያ ሆኖ በተቀመጠው ሃሳብ ውስጥ ተቋጥረው ተደምድመዋል። በፊተኛው አዳም የተሠራው ኃጢአት፣ እኛም የሰራነው ኃጢአት በአንድነት በእግዚአብሔር ፊት ነበሩ። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር እንዳይባርከንና ከክብሩ እንዳንጠግብ ግርዶሽ ሰርተውብን ነበር። ጌታ በትዕግስቱ (በገዛ ፈቃዱና በባሕርዩ) መድኃኒት አመጣልን ከፍቅሩም የተነሳ ጋርዶን የነበረውን ኃጢአት አስወገደና በረከቱን ሰጠን። መልሼ ገዛሁዋቸው ብሎ ተቤዠን ባረከንም። ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ እርምጃ የወሰደው ከፍቅሩ፣ ከምህረቱና ከጽድቁ የተነሳ ነው ማለት ነው።

## *3:26 በዚህ ዘመን*

ኃጢአት በአሮጌው አዳም ተጀምሮ ጌታ መጥቶ ለኃጢአት ዋጋ እስከ ከፈለበት ዘመን ድረስ ነበር። ሆኖም ግን ጌታ ታግሶ ቆየ። ታግሶ ማለት ግን ረሳ ማለት አይደለም። ስለዚህ የኃጢአትን ዋጋ በዚያ ዘመን ከፈለው።

### ያሳይ ዘንድ

*ይህም ማለት ጽድቁን ይገልጠው ዘንድ ማለት ነው ጽድቁን የገለጠውም፡-*

በክርስቶስ ያመኑትን «ፃድቃን» ብሎ በማወጅ « ክርስቶስ ጽድቃችሁ ነው » ብሎ ለዓለም ሁሉ ይናገር ዘንድ ነው።

**3:27** *ትምክህት ወዴት ነው?*

- ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ከሆነ
- ለኃጢአት ዋጋ የከፈለው ክርስቶስ ከሆነ
- ይህም የእግዚአብሔር የዘላለም እቅድ፣ የፍቅሩና የትዕግስቱ መግለጫ ከሆነ ሰው የሚመካበትን ነገር ሊያገኝ አይችልም።

ጸጋን ጸጋ የሚያደርገው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ መሆኑ ነው፤ የሰው ድርሻ የሌለበት መሆኑ ነው።

በሥራ ሕግ ?

መልሱ አይደለም ነው። ምክንያቱም ሕጉ ተሟላ የሚባለው ሁሉም ያለ መዛነፍ ሲፈጸም ብቻ ነው። በሕግ ሊኖሩ የሚፈልጉ ሁሉን መፈጸም ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህም አይቻልም። ስለዚህ በሕግ ሊመኩ አልቻሉም። አይችሉምም ጎድለው ተገኝተዋልና ። እንግዲያውስ ?

በእምነት ሕግ

ክርስቶስ ኢየሱስ አባቱን ፈጽሞ በመታዘዝ ሁሉን መፈጸሙን በማመን በጸጋው አማካይነት ጽድቅን የተቀበልን መሆኑን ያመለክታል።

ቀርቶ አለ

ይህ ሃሳብ በሕግ ለመጽደቅ የሚሮጥበት የሩጫው መድረክ በሩ መዘጋቱን የሚያመለክት ነው። (ገላ 4:17፤ 6:22) ስለዚህ ዛሬ ትምክህታችን ጌታ ራሱ ብቻ ሆኗል ማለት ነው። (ምሳ 7:2፤ ሕዝ 16:63) ይህም ጌታ ኢየሱስ በሠራው ሥራ የጸደቅን መሆኑን ሳናፍር የምንናገርበትን እውነት ያመለክታል።

## 3:28 *እናረጋግጣለን*

*ይህ ቃል ከላይ የተነገረው እውነት የኛ የሕይወት አቋም መሆኑን አስረግጠን ያለማወላወል የምናውጀው መሆኑን የሚገልጽ ቃል ነው። ይህም ማለት በሃሳቡ ወይም በድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ተውጦ በአዕምሮ አስተውሎና አመዛዝኖ ማረጋገጥ ማለት ነው (ፊሊጵ 4:8፤ ዕብ 11:19፤ ዮሐ 11:50፤ 2ቆሮ 10:11)።*

## 3:29፣30 *አምላክ*

**አምላክ ስንል፡-**

*መለኮታዊ፣የማይቀያየር፣የተለየ፣ የማይሞት፣ የማይጠፋ እና ዘለዓለማዊ ማለታችን ነው።*

*ሐዋርያው ይህን ቃል ሲጠቀም መግለጥ የፈለገው የእግዚአብሔርን አምላክነት ለአይሁድ ብቻ ያደረገው ማነው? የሚል የመከራከሪያ ሃሳብ በማንሳት የአህዛብም አምላክ መሆኑን ለማመልከት ነው። (ዘፍ 18:25፤ መዝ 96:7-8፤ 97:5፤ 98:2-3፤ 100:1-2፤ ኤር 10:7) ይህ አምላክ የተገረዘውን አይሁዳዊ በእምነት፣ ያልተገረዘውን አህዛብ በእምነት ያጸድቃል።*

*እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው የሰውን ልጅም ወደ ጽድቅ የሚያደርሰው በአንድ መንገድ ነው ይኸውም በልጁ ሥራ በማመን ብቻ። ይህ እውነት የእግዚአብሔር የታማኝነቱና አድልዎ የሌለበት አሰራሩ ማረጋገጫ ነው።*

## *3:31 ሕግን እናፀናለን - የጽድቅ አገልጋይ ሆነ*

*በእምነት የመጽደቅ አስተምህሮ በምንም መንገድ የሕግ ተጻራሪ አይደለም። ነገር ግን ሕግን ያጸናል እንጂ። ጥቂት ስናብራራውም፡-*

- *ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን ለመፈጸምም መምጣቱን ገለጸልን ማቴ 5:17*
- *ይህንንም እኛን ወክሎ ፈጸመው (እኛ ያቃተንን እርሱ ፈጸመው)*

*ሕግን እንሽረውም ነገር ግን የመኖሪያ መለኪያችን ወይም ደረጃችን አይሆንም*

- ክርስቶስ በእምነት ሕግ ይገዛናል። ማለትም በእኛ ኖሮ ይለውጠናል ከሕግ በላይ የሆነውን የሕይወት ደረጃ አሟልተን እንድንኖር ያስችለናል።

ስለ ሕግ መሰጠት ስናስብ እግዚአብሔር ኃጢአትን ምን ያህል የሚጠየፈው እንደሆነ እንረዳለን። እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚጠየፈውና ችል ብሎ የማይመለከተው ለምንድነው? ብለን ስንል የሚከተሉትን ምላሾች እናገኛለን:-

ሀ/ አስተሳሰባችንን ስለሚያጨልም (ሮሜ 1:21፤ ኤፌ 4:17-18)
ለ/ አካልን ያረክሳል (ያሳድፋል) (ሮሜ 6:19፤ 7:23)
ሐ/ ባሪያ ስለሚያደርግ (ሮሜ 5:21፤ 6:20፤ 7:14፣23፣25)
መ/ መልካምን እየወደድን ክፉ ስለሚያሰራን (ሮሜ 7:21)
ሠ/ ወደ ሞት ስለሚያደርስ (ስለሚገድል) (ሮሜ 5:21፤ 6:23፤ 8:10፤ 1ቆሮ 15:56፤ሮሜ 7:11)
ረ/ ከአሮጌው ሥጋ ጋር ሕብረት ስላለው (ሮሜ 7:25)

ስለዚህም እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ፍርድን አስተላለፈ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ

ሀ/ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ (1ቆሮ 15:3፤ ገላ 1:4)
ለ/ ኃጢአትን ያላወቀውን ኃጢአት አደረገው (2ቆሮ 5:21)
ሐ/ የመግዛት ጉልበቱን አሳጣው (ሮሜ 6:12-14)
መ/ ከክርስቶስ የተነሳ አማኞች ነፃነትን እንዲያገኙና ነፃ ሕይወት እንዲኖሩ አደረገ (ሮሜ 6:18፣22፤8:2)
ሠ/ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስወገደው (በክርስቶስ ሞት) (ሮሜ 6:10፤ 1ቆሮ 15:3፤ ገላ 1:4)

*እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው (2ቆሮ5:21)*

*እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሰጋችሁ ኃጢአት አይንገስ ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር እቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ እራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር እቃ አድርጋችሁ*

*ለእግዚአብሔር አቅርቡ። ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከህግ በታች አይደላችሁምና (ሮሜ6:12-14)።*

*ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያች ከሆናችሁ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት አይነት ከልባችሁ ስለታዘዛችሁ ከኃጢአትም ዛርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን (ሮሜ6:18)።*

*አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔር ተገዝታችሁ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው (ሮሜ6:22)።*

*በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና (ሮሜ8:2)።*

*መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞተናል በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል (ሮሜ6:10)።*

*እኔ ደግሞ የተቀበልኩትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችው እንዲህ ብዬ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረ መጽሐፍ እንደሚል በሶስተኛውም ቀን ተነሳ (1ቆሮ 15:3)*

*ክፉ ከሆነው ከአሁኑ አለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን እራሱን ሰጠ (ገላ1:4)።*

ሐዋርያው ጳውሎስ በመስቀሉ ላይ የተሰራውን ሥራና መስቀሉ በኃጢአት ላይ ያስገኘውን ውጤትና ድል ከታች በሚከተሉት ሁኔታዎች ገልጦታል።

ከመስቀሉ ሥራ የተነሳ:-

ሀ/ ሕግ የሚጠይቀው ሁሉ በመንፈስ በሚመላለሱ ተፈጸመ (ሮሜ 8:4)
ለ/ አማኞች አዲስ ፍጥረት ሆነን (2ቆሮ 5:17፤ ቆላ 3:10-11)
ሐ/ ለቀድሞው ሕይወት ሙት ለመሆንና ለአዲሱ ሕይወት ሕያዋን ለመሆን በቃን (ሮሜ 6:2-11)
መ/ አዕምሮአችን ታድሶ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት ፈለስን (ሮሜ 12:2፤ቆላ 1:13)

ሠ/ በስጋችን ክርስቶስን ማክበር ቻልን (1ቆሮ 6:19-20) ደካማው ሥጋ ከደሙ የተነሳ ክብር ተዘጋጀለት

ረ/ ለዳንነው ለእኛ መስቀሉ የእግዚአብሔር ኃይል ሆነልን (1ቆሮ 1:23-24)

*ከስጋ የተነሳ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በሀጢአተኛ ስጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጅ እንደ ስጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በስጋ ኮነነ (ሮሜ8:4)::*

*ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል እንሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል (2ቆሮ5:17)::*

*እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና የፈጠረውን ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊው የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጭዋ ሰውም መሆን አልተቻለም ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው በሁሉ ነው (ቆላ3:10-11)::*

*ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን::*

*ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና:: ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና:: መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል:: እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ ግን*

*በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳቹሁን ቁጠሩ (ሮሜ6:2-11)::*

*ለእኛም ይገለጠ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ (ሮሜ 8:18)::*

*አስቀድሞ ደግሞ ወሰኖአልና አስቀድሞም የወሰናቸው እነዚህም ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አፀደቃቸው የፀደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው (ሮሜ 8:30)::*

*ወይስ ሲጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በስጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ (1ኛ ቆሮ 6:19-20)::*

*የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ሀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው (1ኛ ቆሮ 1:23-24)::*

## የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

ከኃጢአት ድነናል ሆኖም ግን በቅድስና ለመኖር ገና ብርቱ ጦርነት ይጠብቀናል:: በዚህ ብርቱ ጦርነት ውስጥ ስናልፍም ሁል ጊዜ ኃጢአት መረታትና ድል መደረግ ይገባዋል:: ኃጢአት ደግሞ መሸነፉን አምኖ አያውቅም:: ዛሬም እኛን ለማታለል ይሞክራል:: ሆኖም ግን እኛ በክርስቶስ አሸናፊ መሆናችን የተረጋገጠ ነው:: ሁሉን እርሱ አሸንፏልና ስለዚህም ዘወትር በአሸናፊነት እንኖራለን:: (ሮሜ 8:18-30) ይህንንም የክርስቶስ አሸናፊነት ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ በኋላ በምንመለከታቸው ምዕራፎች ማለትም ከምዕ 4-8 ድረስ ታላቅ የሆነው የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ ከብሉይ ኪዳን መጻህፍት ጋር ያለ አንዳች እንከን በመስማማት የተፈጸመ መሆኑን አብራርቶ ያሳየናል::

# ምዕራፍ አራት
# አብርሃምም አመነ...

የጳውሎስን « ጽድቅ በእምነት» የሚል አስተምህሮ የሚያነቡት በሮም የሚገኙ አይሁዳውያን « ጋሼ ጳውሎስ ይህ አስተምህሮህ ለመሆኑ ከኛ ታሪክ ጋር እንዴት ይሄዳል? ይህን አስተምህሮ ሕግና ነቢያት አረጋግጠውታል ብለሃል ግን አባታችን አብርሃምስ? የሚል ጥያቄ ማንሳታቸው አይቀርም።»

ጳውሎስም ይህንን ጥያቄ በመቀበል ማብራሪያ ይሰጣል። ጳውሎስ የሚሰጠው ማብራሪያ ግን ከኋላ የተናገራቸውን ነገሮች በሚያጸና መልኩ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። ባለፈው ምዕራፍ ሁሉም በድለዋል ስለዚህ ድነት (መዳን) ለሁሉም ያስፈልጋል ብሎ ነበር። እንዲሁ አሁንም አብርሃምን አስመልክቶ ሲጽፍም ይህንኑ ይጠቀማል።

አብርሃም ለአይሁድ በስጋ አባታቸው ነው። እንዲሁም ደግሞ « ለአመኑት ሁሉ » አባት ነው። ማለትም በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ ማለት ነው (ገላ 3:1-18) ይህንን እውነት በማንሳት የቀድሞ አባቶች እንደ አሁኖቹ አማኞች ሁሉ የጸኑት በእምነት ነው በማለት ብርቱ ማስረጃውን ያቀርባል። ይህም ማስረጃው አብርሃም በእምነት የጸደቀባቸውን ሦስት እውነታዎች ያካተተ ነው።

1. አብርሃም የጸደቀው በእምነት እንጂ በስራ አይደለም (ከቁ 1-8)
2. አብርሃም የጸደቀው በጸጋ እንጂ በሕግ አይደለም (ከቁ 9-17)
3. አብርሃም የጸደቀው በትንሣዔው ኃይል እንጂ በሰው ጥረት (ብርታት) አይደለም (ከቁ 18-25)

## 4:1 እንግዲህ . . . አገኘ . .

እንግዲህ የሚለው ቃል በአይሁዳውያን ዘንድ ስለ አብርሃም የነበረውን አመለካከትና ቀደም ባሉት ምዕራፎች እርሱ ያነሳውን ሃሳብ ለማገናኘትና ማስረጃውን (ጭብጡን) በይፋ ለማስቀመጥ እየተንደረደረ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

*አገኘ*

አብርሃም ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኘውን ዋጋ የሚያመለክት ሲሆን አብርሃም ዋጋውን ያገኘበትን ምክንያት አስመልክቶ በአይሁድና በአብርሃም መካከል በጣም ሰፊ ልዩነት አለ።

አይሁድ አብርሃም ጽድቅን ያገኘው በሥራው ነው ብለው ሲያምኑ ጳውሎስ ግን ምንም ሥራ ሳይሰራና የትኛውንም ሃይማኖታዊ ወግ ሳይፈጽም በጸጋና ከእግዚአብሔር ሞገስ የተነሳ ያገኘ መሆኑን በብርቱ ያምናል።

በዘፍ 18:3 «አግኝቼ ከሆነ » ብሎ አብርሃም ያቀረበው ጥያቄ ፍጹም ትህትና የሞላበት እንጂ ከሥራዬ የተነሳ፣ ከሆነ ከእልህ የተነሳ የይገባኛል ጥያቄ እንዳልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ይስማማሉ። ይህም ማለት መንገድህንና አካሄድህን አውቄው ከሆነ፣ ተረድቼውና ገብቶኝ ከሆነ፣ የጸጋህን ፍለጋ ተከትዬ ከሆነ ባይገባኝም አንተው ሞገሴ ነህና አንተው የሰጠኸኝን ሞገስ አይቶህ ማለቱ ነው።

## *4:2 በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ. . .*

አይሁድ አብርሃም የጸደቀው በሥራ ነው ብለው ያምኑ ነበርና እንደሱማ ቢሆን ኖሮ . . . በማለት የሚከተለውን ወይም በአብርሃም ሕይወት ሊታይ የሚችለውን ነገር ይገልጥላቸዋል።

### *የሚመካበት ነበረው*

የጸደቀው በሥራው ቢሆን ኖሮ ባስመዘገበው የሥራ ውጤት ይመካ ነበር ማለቱ ነው። ጳውሎስ ይህንን ነጥቡን ቀድሞ ካነሳውና « ትምክህት የት አለ? » በማለት ካቀረበው ጋር አያይዞ አጠናክሮ ይገልጠዋል።

አይሁድ አብርሃም ሕግን በመፈጸም ነው የጸደቀው ብለው ሲሉ፡-

- *ሕግ ከመኖሩ በፊት ሕግን ፈጽሞአል ማለታቸው መሆኑን እንዴት ዘነጉት ጳውሎስም በዚህ ትልቅ ስህተታቸው ፊት ለፊት ተጋፍጦ « ጽድቅ በእምነት » ወደሚለው አስተምህሮው ሊያመጣቸው በብርቱ ይጥራል።*

## *4:3 መጽሐፍ እንደሚል*

ሐዋርያው ጳውሎስ አስተምህሮው በእግዚአብሔር ቃል (በብሉይ) የተረጋገጠና የተደገፈ መሆኑን ለማሳሰብ የተጠቀመበት ነው።

### *እግዚአብሔርን አመነ*

ይህ ቃል ከብሉይ የተወሰደ ሲሆን (ዘፍ 15:6) የብሉይም ፍቺውም በእግዚአብሔር አመነ የሚል ነው። ይህም እምነት በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ ማረፍንና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ብቻ መደገፍን የሚያመለክት ነው።

አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት (በዘፍ 15፡6)።

*ተቆጠረለት*

አይሁድ አብርሃም ጽድቅን ያገኘው በመታዘዙ ነው። ስለዚህም የሥራው ውጤት ነው ይላሉ። ጳውሎስ ግን ከሥራ ቢሆን ኖሮ የሚገባው ደመወዝ ተከፈለው ይባል ነበር እንጂ ተቆጠረለት አይባልም። በማለት ማስረጃውን ግልጽ ያደርገዋል።

- *ሥራ ደመወዝ አለው፤የይገባኛል ጥያቄም ማንሳት ይቻላል።*
- *እምነት ግን ምንም ሥራ ስለሌለበት ደመወዝ የለውም ስጦታ ግን ይቀበላል። አብርሃምም አመነና ስጦታውን ተቀበለ።*

> «ተቆጠረለት» የሚለውን ቃል በባንክ የአሠራር ሕግ ብንመለከተው፣ አንድ ሀብታም በራሱ አካውንት የነበረን አንድ ትልቅ ሀብት ምንም ለሌለው ምስኪን በኔ አካውንት የነበረውን ሂሳብ በእርሱ ውስጥ አስቀምጡልኝ ብሎ ትዕዛዝ መስጠቱንና ሰውየውም ያንን ነፃ ስጦታ አሜን እሺ ብሎ አምኖ መቀበሉን ያመለክታል።

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር የራሱን ንብረት በአብርሃም መዝገብ ውስጥ አስገባለት ማለት ነው። ስለዚህ በአብርሃም ውስጥ የተገኘው ጽድቅ የጌታ ንብረት እንጂ የአብርሃም የልፋቱ ውጤት አይደለም።

### *4፡4 ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው*

ጳውሎስ ይህንን ግልጽ ሃሳብ ያነሳው

- *ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እምነቱንና መታዘዙን እንደ ሥራ ይቆጥሩት ስለ ነበር ገልጦ ሊያሳያቸው ነው።*

• *ሥራ ከሆነ ደግሞ ለአብርሃም የልፋቱን ዋጋ ነው የሚሰጠው ስለዚህ ለእግዚአብሔር እንደ ዕዳ ነው የሚቆጠረው ብሎ ለማስረዳት ተጠቅሞበታል::*

**እንደ ስጦታ (ጸጋ) አይቆጠርለትም**

ስጦታ ሰጪው ይመሰገንበታል ደመወዝ ግን ሠራተኛው ይከፈልበታል:: አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ የጸጋው ትሩፋት አይደርሰውም ነበር:: አብርሃም ግን አመነ ስለዚህም የጸጋው ትሩፋት ደረሰው «ጸደቀ »::

***4:5 ነገር ግን ለማይሠራ***

*ይህ ቃል የሙሴን ሕግ የተቀበሉ ነገር ግን ጽድቅ የሚገኘው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በጸጋ ነው ብለው በጸጋው የሚታመኑ ሰዎችን ለማመልከት የገባ ነው::*

***ኃጢአተኛውን በሚያጸድቅ***

*አመጸኛውንና ክፉውን በሚያጸድቅ በእግዚአብሔር ኃጢአተኛ ው ሰው « ጻድቅ » ተብሎ የተነገረበትን አሠራር ያመለክታል:: ይህ ቃል ለአይሁድ ትልቅ ትርጉም የሚሰጥ ነው ምክንያቱም*

*ሀ/ በብሉይ የተሰጠው ሕግ ምህረት አያደርግም ነበር (ዘፀ 23:7):: ይህ ደግሞ የጌታ ባህርይ ነው::*
*ለ/ ከሕግ አንዱን ያፈረሰ ሁሉንም እንዳፈረሰ ይቆጠርበታል:: ስለዚህም ሰው ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቅ አይችልም::*

*እንግዲያው ጽድቅ ከሰው ሊገኝ አይችልም ኃጢአተኛውን ከሚያጸድቅ ከጻድቁ ከእግዚአብሔር እንጂ*

***4:6 - 8 ያለ ሥራ . . . ብፅዕና***

*ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ነጥቡን በአስተማማኝ መሠረት ላይ ለማሳረፍ የዳዊትን ሕይወት ምሳሌ በማድረግ ግሩም ማስረጃ ያቀርባል (መዝ 32:1-2):: ይህ ሃሳብ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ኃጢአት ከሠራ በኋላ በዘመረው መዝሙር ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን ሁለት ዋና ነጥቦችን ዳዊት አስቀምጧል::*

1/ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ይላል፤ የሰው የልፋት ውጤት ያልሆነውንም ጽድቅ ለሰው ይሰጣል።

2/ ኃጢአትን አይቆጥርም - ክርስቲያኖች በኃጢአት ልንወድቅ እንችላለን። በሠራነው ኃጢአትም ንስሀ መግባት አለብን። ነገር ግን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን አይቆጥርም። መልካም ሥራችንን ይመዘግብልናል እንጂ ኃጢአታችንን አይመዘግብብንም። ንስሀ ስንገባ ጨርሶ ያነጻናል።

ሐዋርያው ይህንን ብርቱ ማስረጃ በማንሳት ብፅዕናው ከሰውየው መልካምነት ጋር ያልተገናኘ ነገር ግን እግዚአብሔር በመስቀሉ በኩል ባደረገው ቤዛነት ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው።

ከክርስቶስ ደም የተነሳ
ኃጢአቱ ይቅር የተባለለት
ኃጢአቱ የተከደነለት
ኃጢአቱ የማይቆጠርበት ሰው ብጹዕ ነው።

**የእግዚአብሔርን በረከትና የተትረፈረፈ ደስታ በማግኘት ዳዊር ዘንድ ከክርስቶስ ደም የተነሳ ብቃትን አግኝቷል።**

## *4:9-10 ብፅዕና ስለ መገረዝ ተነገረን?*

በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ሐዋርያው ነገሩን የበለጠ ግልጽ በማድረግ መገረዝ የብፅዕና ምልክት አለመሆኑን ለማሳየት በአብርሃም መገረዝና ጽድቅን በማግኘቱ መካከል ያለውን የጊዜ ገደብ (ቅደም ተከተል) በማንሳት ማስረጃውን ያጠናክራል። ለአብርሃም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ከመገረዙ በፊት ስለሆነ ብፅዕናውም ከመገረዙ ጋር የተገናኘ አይደለም።

## *4:11 ሳይገረዝ በነበረው እምነት*

ሀ. በዘፍ፤ 15:6 ጻድቅ ተባለ
ለ. በዘፍ 16:16 እስማኤል ተወለደ
(ጻድቅ ከተባለ ሰማኒያ ስድስት ዓመት ሆኖ ነበር)
ሐ. በዘፍ 17:24 አብርሃም 99 ዓመት ሆነው ያን ጊዜ ተገረዘ

*አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት (በዘፍ 15:6)።*

*ኢ.ጋር እስማኤልን ለአብራም በወለደችለት ጊዜ አብራም የሰማንያ ስድስት አመት ሰው ነበር (ዘፍ 16:16)።*

*አብርሃምም ልጁን እስማኤልን በቤቱም የተወለዱትን ሁሉ በብሩም የገዛቸውን ሁሉ ከአብርሃም ቤተሰብ ወንዶቹን ሁሉ ወሰደ የቁልፍታቸውንም ስጋ እግዚአብሔር እንዳለው በዚያው ቀን ገረዘ (ዘፍ 17:24)።*

## *ምልክት*

ግርዘት ለአብርሃምና ለዘሩ በሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ቃል ኪዳን እንዳላቸው ለምልክትነት የተሰጠ ውጫዊ ማረጋገጫ ነው። አይሁድ ግን ይህ ምልክት ስላላቸው ብቻ ጻድቃን የሆኑ ወይም ለመጽደቃቸው አስፈላጊ እንደሆነ ያስቡ ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ እግዚአብሔር አብርሃምን እኮ ከመገረዙ ወይም ከምልክቱ በፊት ተቀብሎታል። በማለት እምነቱና በእምነቱ ምክንያት መጽደቁ ከምልክቱ ይቀድማል በማለት ጽድቁን ያመጣው ምልክቱ ሳይሆን ምልክቱ የመጽደቁ ማህተም ነው ብሎ ያስረዳቸዋል።

እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ፡- ይህ ቃል በቀጥታ አህዛብን ያመለክታል። ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ብሎ ሲጠቅስ ለተገረዙት ብቻ ሳይሆን ተገርዘው ላመኑት፣ ሳይገረዙም፣ ላመኑት አባት እንዲሆን ማለቱ ነው።

## *4:12 የእምነቱን ፍለጋ*

*የአብርሃምን የእምነቱን ፍለጋ የተከተልን ሁሉ ጽድቅንና ብፅዕናን ማግኘታችንን ያመለክታል። ይህንን እውነት ሰፋ አድርጎ ለመመልከት ምልክቱና ማህተሙ ያላቸውን ግንኙነት መመልከቱ ከዚያም ከኛ ጋር ያለውን ትስስር ማወቅ ይጠቅማል።*

*መገረዝ እንደ ማህተም*

እግዚአብሔር ተስፋ እንደሰጠውና ተስፋውንም እንደሚፈጽም የሚያስታውሰው ነው። ተመሳሳይ በሆነ መንገድም በዚህ ዘመን የምንኖር አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ማህተም ታትመናል (ኤፌ 1:13-14)። ከዚህም የተነሳ የልብ መገረዝን ተቀብለዋል (ቆላ 2:10-12)። ይህ ድርጊት መለስተኛ የሆነ አካላዊ ቀዶ ጥገና ሳይሆን አሮጌውን ሰው በሞት የማስወገድንና አዲሱን ሰው ለብሶ በትንሣኤ ሕይወት ለመመላለስ መብቃትን የሚያመለክት ነው።

> *እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል( ኤፌ 1:13-14)።*

> *ለአለቅነትና ለስልጣናትም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋልና። የስጋንም ሰውነት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሄር አሰራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ (ቆላ 2:10-12)።*

### *4:13 የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሀምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም።*

ለዘሩ የተባለለት በስጋ ዘሩ የሆኑትንና ሕግን የተቀበሉትን ብቻ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእምነቱን ፍለጋ የተከተሉን ሁሉ ነን (ገላ 3:16፤ ዘፍ 18:18፤ 22:18-19)።

> *ለአብርሃምና ለዘሩ የተስፋው ቃል ተነገረ (ገላ 3:16)።*

> *አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና የምድር አሕዛብም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉና (ዘፍ 18:18)።*

*የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ቃሌንም ሰምተኻልና አብርሃምም ወደ ብላቴኖቹ ተመለሱ ተነስተውም ወደ ቤርሳቤህ አብረው ሄዱ አብርሃምም በቤርሳቤህ ተቀመ (ዘፍ 22:18-19)::*

## *4:14 ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል የተስፋውም ቃል ተሽሮአል፤*

በሕግ የሚኖሩት ወራሾች ከሆኑ እምነት የማይጠቅም ይሆን ነበር:: ተስፋም ከንቱና በሥራው የተሳካለት ብቻ የሚባለው እንጀራ ይሆን ነበር::

## *4:15 ሕጉ መቅሰፍትን ያደርጋልና ነገር ግን ሕግ በሌለበት መተላለፍ የለም::*

ሕግ ሁለት ነገርን እንድንመለከት ተሰጠን

1/ <u>መቅሰፍትን</u> - ፍጹምነት የሌለበት የይስሙላ መታዘዝ በራሱ በሕጉ እንደተገለጠው መርገምን ያመጣል::

2/ <u>መተላለፍን</u> - ኃጢአታችንን እንድንመለከት

ሕግ እነዚህን ሁለቱን እንድንመለከት ቢያደርገንም ከኃጢአት የምናመልጥበትንና የምናሸንፍበትን አቅም አይሰጠንም እንዲያውም አውቀን ባለማድረጋችን ቁጣን ያስከትልብናል::

- ጸጋም በተመሳሳይ ሁኔታ ራሳችንን እንድንመለከት ያደርጋል የጸጋውም ቃል ራሳችንን እንደ መስታወት ያሳየናል ግን በዚያው አያበቃም:: የማይገባውን እንድናስተካክል ኃይልና ጉልበት በክርስቶስ በኩል ይሰጠናል::

## *4:16-17 ስለዚህ ከሕግ ብቻ ሳይሆን ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተስፋው ቃል እንዲጸና እንደ ጸጋ ይሆን ዘንድ በእምነት ነው :: እርሱም ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደተጻፈ ለሙታን ህይወት በሚሠጥ የሌለውንም እንዳለ አድረጎ በሚጠራ ባመነበት በእግዚአብሔር ፊት የሁላችን አባት ነው::*

*የተስፋው ቃል እንዲጸና*

ይህ ክፍል የተስፋውን አስተማማኝነትና ጽናት ። ይህም ጽናትና አስተማማኝነት ከእግዚአብሔር ታማኝነት ውስጥየሚመነጭ መሆኑን በግልጥ ያመለክታል።

ተስፋው በእምነት መጣ ይህም በጸጋ የሆነ ሲሆን ተፈጻሚነቱም ለአብርሃም ዘር ሁሉ ነው። ይህም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በክርስቶስ በኩል ተፈጽሟል።

*ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ*

የሞተውን ሕያው ማድረግ የሚችልበትን የመፍጠር ብቃቱን እና አሠራሩን ያመለክታል።

> ጌታ ፈጣሪነቱን የገለጠው ስጋን ከአፈር በማበጀት ብቻ ሳይሆን፤ በፊተኛው አዳም በተሠራው ኃጢአት ምክንያት ተበላሽቶ የነበረውንና ሙት የነበረውን የሕይወት ምዕራፎችን ዘግቶ አዲስ ምዕራፍ በመክፈት ሕይወትን በመስጠት ጭምር ነው። ከጸጋው የተነሳ ባገኘነው ብቃት መሠረት የቀድሞውን አሮጌ ሰውነት ወዲያ በመጣል አዲስ ፍጥረት በመሆን ከኩነኔ ነፃ ሆነን መኖር ችለናል።

*የሌለውን እንዳለ አድርጎ በሚጠራ*

ይህ ቃል የጌታን መለኮታዊ ባህርይና መለኮታዊ አጠራሩን ያመለክታል።

***4:18** ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ።*

*ተስፋ ባልሆነው ጊዜ*

ተስፋ የሚያደርገውንና በእርሱ ውስጥ ማለትም በማንነቱ ምንም ተስፋ ባልነበረው ጊዜ ማለት ነው።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ የእግዚአብሔርን ተስፋ ማለትም አስተማማኝ ጥበቃን በማሰብ የተናገረውን እንደሚፈጽም በማመን በእርግጠኝነት መጠበቅን ያመለክታል።

*ተስፋ ይዞ አመነ*

አብርሃም ከእርሱ በኩል የሚመጣ ምንም ነገር እንደሌለ በመረዳት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በጽናት መጠበቅን ያመለክታል።

*በስፋት ስንመለከተውም*

- ከዚህ የተነሳ መልካም ይሆንልኛል ብሎ የሚያስበውና የሚመካበት ሥራ ሳይኖረው ጌታ የተናገረውን ይፈጽማል ብሎ ማመኑን ያሳያል።
- በነቢያቱ መጽሐፍቶች እንደምናየው «ተስፋ» በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተሰጠ የክብር ቃል ነው (1ጴጥ 1:21፤ ገላ 5:5፤ ኤፌ 1:18-19፤ ቆላ 1:4-5 ፤ ኤፌ 2:12)። በዚህም መሠረት ጌታ ለተስፋ እንጂ ለቁጣ አልጠራንም (ኤር 29:11፣ 31:17፤ ሆሴ2:17)።

*አለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ ፣ ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ከሙታን ባስነሳው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ (1ኛ ጴጥ1:21)።*

*እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና (ገላ 5:5)።*

*ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ነው (ኤፌ 1:18-19)።*

*ስለ እናንተ ስንጸልይ በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሣ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እምነታችሁ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን ስለዚህም ተስፋ በወንጌል እውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ (ቆላ 1:4-5)።*

*በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግስት ርቃችሁ ለተስፋው ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህ ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ (ኤፌ 2:12)::*

*ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም (ኤር 29:11)::*

*ለፍጻሜሽም ተስፋ አለ ይላል እግዚአብሔር ልጆችሽም ወደ ዳርቻቸው ይመለሳሉ (ኤር 31:17)::*

*ከዚያም የወይን ቦታዋን የተስፋ በርም እንዲሆንላት የአኮርን ሸለቆ እሰጣታለሁ በዚያም ከግብፅ ምድር እንደወጣችበት ቀን እንደ ሕጻንነትዋ ወራት ትዘምራለች (ሆሴ 2:17)::*

አብርሃምን የተፈጥሮ አካሉና በዙሪያው ያሉት ነገሮች ሁሉ «መውለድ አትችልም» የሚሉት ቢሆንም «ይሆንልሃል» የሚለውን የጌታ መለኮታዊ ጥሪ (የተስፋ ቃል) ግን ተቀብሎአል:: ተስፋው ደግሞ ከከበበው ነገር ይበልጣል::

## *4:19 የመቶ አመትም ሽማግሌ ስለሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ስጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ*

### *እያወቀ በእምነቱ አልደከመም*

የራሱ ስጋና የሣራ ማህፀን ልጅ ያስገኛል ብሎ ሳይሆን በጌታ ጸጋ ላይ በመደገፍ አለመድከሙን ያመለክታል::

ተስፋ ያደረገውም የራሱን ስጋና የሳራን ማህጸን ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ብቻ ነው::

## *4:20 ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ*

### *ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ*

ያለበት ሁኔታ እግዚአብሔር የተናገረውን የሚፈጽም ባያስመስልም እንኳን አብርሃም ግን የተስፋ ቃሉን አልተጠራጠረም:: ቃል ኪዳኑንም በማክበር ወንዶቹን ሁሉ ገረዛቸው::

አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ታማኝነት ከመደገፍ የጎደለበት ጊዜ ቢኖርም በአጠቃላይ የሕይወቱ አቅጣጫ ግን እያደገና እየበረታ እግዚአብሔርንም እያስከበረ መምጣቱን ያመለክታል፡፡

*በእምነት በረታ*

በእግዚአብሔር ከመታመኑ የተነሳ እግዚአብሔር እንዳበረታውና እንዳይወላውል እንዳገዘው ያመለክታል፡፡

*በአለማመን አልተጠራጠረም*

የተሰፋው ቃል በጌታ ታማኝነት እንዲደገፍና እንዲሁም እንዳይጠራጠር የማድረግ ብቃት ነበረው፡፡ ዛሬም ይኸው እውነት በኛ ሕይወት በገሃድ ይገለጣል፡፡

ሰው በእምነቱ ሲበረታ ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ግን በእምነታቸው የደከሙ በጌታ ዘንድ ይረሳሉ ማለት አይደለም ቃሉ «የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጤሰውንም የጧፍ ክር አያጠፋም» በማለት ያስተምረናል፡፡ በእምነታቸው ብርቱ የሆኑ ሰዎች በጌታ ብርቱነትና ችሎታ የሚታመኑ ስለሆነ ለጌታ ክብር ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

**4:21** *በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም፡፡*

አጥብቆ እየተረዳ

አብርሃም በእምነቱ፣ በውሳኔውም ጸንቶ ይኖር ነበር ስንል በአዕምሮው የሚያወጣና የሚያወርደው ነገር አልነበረም ማለት አይደለም (ዘፍ 17:17)፡፡

በዘፍ 17:26-27 ተጽፎ እንደምናነበው ሁሉንም ሲገርዛቸው ጊዜያዊ የሆነ ድርጊቱን የሚያሳይ ሳይሆን በእምነት ጀምሮ

በእምነት መመሳሰሉን የሚገልጥ ነው (ሉቃ 1:1፤ ሮሜ 14:5)::

*በዚያ ቀን አብርሃም ተገረዘ ልጁ እስማኤልም በቤት የተወለዱትና በብር ከእንግዶች የተገዙት የቤቱ ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር ተገረዙ (ዘፍ 17:26-27)::*

በዚህ ክፍል «ተስፋ» ተብሎ የተጠቀሰው ቃል አብርሃም በእግዚአብሔር ኃይል ማለትም «ተስፋ» በሆነው በክርስቶስ መታመኑን ያመለክታል (ዕብ 6:13-20)::

> *እግዚአብሄርም ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ በእውነት እየባረክሁ እባርክሃለሁ እያበዛሁ አበዛሃለሁ ብሎ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ በራሱ ማለ፤ እንዲሁም እርሱ ከታገሰ በኋላ ተስፋውን አገኘ:: ሰዎች ከእነርሱ በሚመበልጠው ይምላሉ ለማስረዳትም የሆነው መሀላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል፤ ስለዚህም እግዚአብሄር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለፈቀደ እግዚያብሄር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ በመሐላ መካከል ገባ፤ ይህም ተስፋ እንደነፍስ መልህቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃው ውስጥ የገባ ነው በዚያም ኢየሱስ እንደመልከ ጻዲቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ (ዕብ 6:13-20)::*

መርከብ በመልህቅ እንደሚያዝ ሁሉ ጌታም እኛን እንደ ተስፋ መልህቅ ሆኖ ይዞናል:: አብርሃም"ም በሕይወቱ የተነሳው ወጀብ እንዳያጠፋው የረዳው የእግዚአብሔር አለትነት መልህቅ ስለሆነለት ነው::

## *4:22 ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት*

ይህ ቃል ደጋግሞ የተነሳ ሲሆን በዚህ ስፍራ ሲጠቀስም የእግዚአብሔር ወዳጅ መባሉን (ያዕ 2:23) ያመለክታል::

## *4:23 ነገር ግን ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም ስለ እኛም ነው እንጂ*

በአብርሃም ሕይወት የተገለጠው በእግዚአብሔር የመታመን ሕይወትና ይህም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት መሆኑ ለእኛም ለትምህርታችን ተጽፏል።

***4:24-25 ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ እለው።***

*ከሙታን ባስነሳው ለምናምን*

ይህ የምዕራፉ የማጠቃለያ ሃሳብ፡- ኃጢአታችን በደሙ መደምሰሱን ከሙታን በመነሳቱም መጽደቃችንን ያመለክታል።

<u>አልፎ ተሰጠ</u>

በእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞ የታቀደና ጊዜው ሲደርስ ወደ ሙላት የመጣ መሆኑን ያመለክታል።

# የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

ጽድቅ በእምነት የመገኘቱ አስተምህሮ በሕግና በነቢያት ብቻ የተረጋገጠ ሳይሆን አይሁድ በስጋ አባታችን በሚሉት ላላመኑት ደግሞ የእምነት አባት በሆነው በአብርሃምም ማመንና መጽደቅ የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ አይሁድ ሁሉ ሆይ አንድ ጥያቄ ተጠየቁ «አብርሃም የስጋ አባታችሁ ነው፤ የመንፈስ አባታችሁ ነውን? አብርሃም የጸደቀው በእምነት ነው። ዛሬም ዓለም ሁሉ የሚጸድቀው በክርስቶስ በማመን ነው። ከዚህ እውነት የተለየ አቋራጭም አማራጭም መንገድ የለም።

# ምዕራፍ አምስት
# በእግዚአብሔር ጻድቅ የመባል ፍሬዎች

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ሁሉን በስርዓቱና በቅደም ተከተሉ ፍሰቱን ጠብቆ ማንም ሊያመልጥና ሊያስተባብል በማይችልበት ሁኔታ የእግዚአብሔርን እውነት ሲያስተላልፍ እንመለከተዋለን:: ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተመለከትነውም በመጀመሪያ፣ ሁሉ ኃጢአትን ስለሰሩ ከእግዚአብሔር ክብር መጉደላቸውንና በእግዚአብሔር ቁጣ ስር መሆናቸውን ከዚህም ቁጣ በሕግ ሥራ ሊጸድቁ እንደማይችሉ ገለጠ:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ ሰው ሁሉ ሊጸድቅ የሚችልበት ሌላ መንገድ ተገልጧል እርሱም በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር የጸጋው ውጤት ነው:: ጽድቅ በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም:: በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ከምዕራፍ 5-8 ባሉት ክፍሎች የሚገልጠው በእግዚአብሔር ጻድቅ የመባልን ውጤቶች ነው::

በዚህ ክፍል ውስጥ:-

1/ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ሰላምና የዘላለም ሕይወት እርግጠኛነት (ም5)

2/ አዲስ ሕይወት ከጌታ ጋር (ም6)

3/ ከሕግ ነፃ መሆን (ም7)

4/ መንፈስ ቅዱስና የተረጋገጠ የዘላለም ርስት (ም8)
የሚሉት ዋና ዋና ሃሳቦች ይዳሰሳሉ።

በመጀመሪያ በምዕራፍ አምስት የተዳሰሰውን ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ሰላምና የዘላለም ሕይወት እርግጠኝነት እንመለከታለን።

ነጥቦቹን በተሳካ ሁኔታ ለመዳሰስ ምዕራፍ አምስትን በሁለት ዋና ክፍሎች ከፍለን መመልከታችን ይጠቅማል።

ሀ. የጽድቃችን በረከቶች - 5:1-11
ለ. የጽድቃችን መሠረት - 5:12-21

የአንድ የሚያምርና የሚያጓጓ ቤት ዘላቂነት የሚወሰነው በመሰረቱ ጥንካሬና የአሰራር ብቃቱ እንደሆነ ሁሉ፣ ሐዋርያው ጳውሎስም የሚያነሳው በእምነት የሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚያስገኝልን በረከቶች ዘላቂና አስተማማኝ መሆናቸው የሚረጋገጠው የተገኙበት መሰረት አስተማማኝ ከሆነ ነው። ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ይህንን እውነት በግልጽ ያስቀምጥልናል።

## ሀ. <u>የጽድቃችን በረከቶች (1-11)</u>

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ክፍል መጽደቃችን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረሳችን አስተማማኝ ማረጋገጫ ብቻ ሳይሆን በዚህ በምድርም ስንኖር የሚያስገኝልን ድንቅ በረከቶች አሉት። ስለዚህ ክርስቲያን የመሆንን ዕድል ማግኘት ከሁሉ የላቀ አስደናቂ ስጦታ ነው ይለናል።

***5:1 እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ***

*ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም*

መርገም - እግዚአብሔር እኛን ኃጢአተኞች ብሎ ያወጀው የጦርነት አዋጅ ነው

ጽድቅ - እግዚአብሔር እኛን ጻድቃን ብሎ ያወጀው የሰላም አዋጅ ነው

በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል እውነትና ምህረት በአንድነት ተስማሙ (መዝ 85:10) ስለዚህም ለኛ ሰላም ሆነልን::

ይህን ሃሳብ ሰፋ አድርገን ብንመለከተው:-

ሀ. በክርስቶስ ያመነ አማኝ በዚህ ሰላም ውስጥ ይኖራል::

ይህ ሰላም በክርስቶስ የተገኘው የጽድቅ ውጤት ስለሆነ በዚህ ሰላም ውስጥ ለመኖር ይችል ዘንድ ለአማኙ ብቃትን ይሰጠዋል:: ይህም ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም ህብረት ማድረግን አስችሎታል (ሮሜ 5:10)::

*ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ፣ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በህይወት እንድናለን (ሮሜ 5:10)::*

ለ. ሰው በክርስቶስ ከመዳኑ በፊት ይህን የሰላም ህይወት ለመምራት ወይም ለማግኘት የሚያስችል ብቃት አልነበረውም

ሐ. ሰው ይህንን መዳን ካገኘ በኋላ ከአብ ጋር በሰላም ሊያኖረው የሚያበቃ ቅድስና የለውም ነገር ግን በእግዚአብሔር ታማኝነት በመታመን ሲኖር በሰላም ይኖራል (ቆላ 2:6፤ ዕብ 11:6) ::

*እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ (ቆላ 2:6)::*

*ሳይወስድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና (ዕብ 11:6)::*

- ይህን የሰላም ስጦታ ብዙ ክርስቲያኖች የማይለማመዱት ይህ ሰላም ክርስቶስ ለኛ ደሙን በማፍሰሱ ምክንያት ብቻ የተገኘ የእግዚአብሔር የጸጋ ትሩፋት መሆኑን

**ስለሚዘነጉ ፤ ክርስቶስ ሰላሙ እንደወንዝ እንዲፈስ በእነርሱም ሆኖ ሌሎችን ለመድረስ እንዲሰራ «በእኔነት» ስለሚገደብ ነው፡፡ (ሉቃ 2:14፤ ሮሜ 14:7 ፤15:1-13፤ ኤፌ. 6:15፤ኢሳ 9:6)**

*እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፡- ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ (ሉቃ 2:14)፡፡*

*ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና ለራሱም የሚሞት የለም በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን (ሮሜ 14:7)፡፡*

*እኛም ኃይለኞች የሆነን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም እራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል፡፡ እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ፡፡ ክርስቶስ እራሱን ደስ አላሰኘምና ነገር ግን እናንተን የነቀፈበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሆነበት፡፡ በመጽናናትና መጻህፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና፡፡ በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን ፣ እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ታከብሩ ዘንድ ፣ የትእግስትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ በአንድ ሀሳብ መሆንን ይስጣችሁ ፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ተቀበላችሁ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ፡፡ ለአባቶች የተሰጠውን የተስፋ ቃል ያፀና ዘንድ ደግሞም ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሀለሁ ለስምህም እዘምራለሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ፣ አሕዛብ ስለ ምህረቱ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ፡፡ ደግሞም አሕዛብ ሆይ ከሕዝብ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላል፡፡ ደግሞም እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦችም ሁሉ ይወዱስት ይላል ደግሞም ኢሳይያስ (ሮሜ 15:1-13)፡፡*

*እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የፅድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ (ኤፌ 6:15)፡፡*

*ሕፃን ተወልዷልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነት በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መክር ፣ ኃይል አምላክ ፣ የዘላለም አባት ፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል (ኢሳ 9:6)፡፡*

- ሰላም በክርስቶስ በማመን የምንወርሰው የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ዮሐ14:27) ። ኃጥአን ይህንን ስለማይረዱ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ያላቸው ይመስላቸዋል (ሐሥ 10:36፤ ሮሜ 8:6፤ 10:15 ገላ5:22፤ ኢሳ 32:17) ።

*ሰላምን እተውላችኋለሁ ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ አለም እንደሚሰጥ አይደለም (ዩሐ 14:27)።*

*የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰበከ ይህ ቃል ወደ እስራኤል ልጆች ላከ (ሐዋሥራ 10:36)።*

*ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ፣ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው (ሮሜ 8:6)።*

*ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና (ሮሜ 10:5)።*

*የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ፣ ደስታ ፣ ሰላም ፣ ትዕግስት ፣ ቸርነት ፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት ፣ ራስን መግዛት ነው (ገላ 5:22)።*

*የፅድቅ ስራ ሰላም ፣የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል (ኢሳ 32:17)።*

- ክርስቶስ የዚህ ሰላም ምንጭ ብቻ ሳይሆን ሰላሙ በህይወታችን እንዲገዛና ሁለንተናችንን እንዲቆጣጠር የሚያስችል ኃይል ያገኝንበት ብቃታችንም ነው። ስለዚህ ይህ ሰላም ሕይወታችንን እንዲገዛ እኛም እንድንጠቀምበት ይፈልጋል (ዮሐ 15:13-15፤ ኤፌ 2:14፤ ቆላ 1:26-27፤ ማቴ 21:38፤ ሐሥ 9:31)።

*ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና ወዳጆቼ ግን ብያችኋለሁ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና (ዩሐ 15:13-15)።*

*እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን የዋሐዳ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በስጋው የፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምን ያደርግ ዘንድ ኤፌ 2:14*

***5:2 በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን::***

***(ሀ) በእምነት መግባት (ወደ እግዚአብሔር መቅረብ)***

**በእርሱ በኩል አግኝተናል**

- ይህንን ሰላምና በህብረት መኖርን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው ክርስቶስ ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም መኖር የጀመርነው በክርስቶስ ካመንን ጊዜ አንስቶ ነው::
- አግኝተናል ሲል በክርስቶስ የተከናወነው የአብ ሥራ ለኛ ተገለጠ፣ ደረሰን ማለቱ ነው (ኤፌ 1:11፤ 2ቆሮ 5:19)::

*እንደፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሰራ እንደእርሱ ሀሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን (ኤፌ 1:11)::*

*እግዚአብሄር በክርስቶስ ሆኖ አለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ (2ኛ ቆሮ 5:19)::*

**ወደ ቆምንበት ጸጋ**

- ወደ ቆምንበት ሲል ወደምንመላለስበትና ወደምንኖርበት የሕይወት ደረጃ ወይም ምዕራፍ ማለቱ ነው::
- ሌላው ደግሞ ያለንበትን ደረጃ (Position or state) የክርስቶስ ሕይወት ህይወታችን የሆነበትን እርከን ያሳያል:: ጌታ አስከፊ ሞት የሞተው ይህን የህይወት እርከንና ደረጃ ሊያጎናጽፈን ነው::

- ይህ ጸጋ የማያቋርጥና ዘላለማዊነት ያለው የሚፈስስ ምንጭ ነው::

**ሐዋርያው በዚህ ቁጥር የሚገልጸው ወደ እግዚአብሔር እንድንገባ ከልክሎን የነበረው ግድግዳ ፈርሶ አይሁድንም ለያይቶ የነበረው መጋረጃ ተቀድዶ ወደ እግዚአብሔር መግባትና ከእርሱ ጋር በሰላም መኖር ተችሏል:: ይህም የሆነው በክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ነው የሚል ነው (ኤፌ 2:18) ይህ የጳውሎስ አስተምህሮ የቆምነው በእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑን ነው::**

*(ለ) የተባረከ ተስፋ (የእግዚአብሔርን ክብር ተስፋ ማድረግ)*

ሐዋርያው ጳውሎስ ነጥቦቹን በተቀናጀ መንገድ ያስቀምጣቸዋል ማለትም

- ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ማግኘታችን ያለፈው ጠባችን ተወግዶ ሰላም መፈጠሩን ያመለክታል
- ወደ እግዚአብሔር መግባታችን (መቅረባችን) ደግሞ አሁን ያለንበትን የሕይወት አቋም ይገልጣል
- የክብሩ ተስፋ ደግሞ ወደ ፊት አንድ ቀን የክብሩ ተካፋይ የምንሆንበትን ያመለክታል::

ይህ ትልቅ እውነት በሮሜ 3:23 ላይ ከእግዚአብሔር ክብር ወድቆና ተለይቶ ለነበረው ሰው ምንኛ የምስራች ይሆን? አዎን! በኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ከወደቅንበት ማጥ ወጥተን የክብሩ ተካፋዮች ሆነናል::

***5:3-4*** *ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን መከራ ትዕግስትን እንዲያደርግ ትዕግስትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ አያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን!*

*ክርስቲያናዊ ባሕርይ (የተፈተነ ባሕርይ)*

ጌታ ኢየሱስ (በዮሐ 16:33) እንደገለጠው በዓለም ሳለን መከራ አለብን:: ክርስትና በምድር ሕይወት የሚገጥመን ልዩ ልዩ ፈተናዎች እንዳይደርሱብን ማምለጫ መንገድ አይደለም:: በፈተናዎቹ ውስጥ በጽናት ማለፍ የሚቻልበትን ብቃት ማግኘት እንጂ!

*መከራ ትዕግስትን እንዲያደርግ*

ከክርስቶስ የተቀበልነው ጸጋ በመከራ ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ትዕግሥት እንዲገለጥ ያደርገዋል:: ትዕግሥት በህይወታችን ሲገለጥ የክርስቶስ ጸጋ በህይወታችን ገዢና የበላይ የብቃታችንም ምንጭ መሆኑ በገሃድ ይታያል::

*ትዕግሥት - ጽናትን*

ትዕግሥት በህይወታችን ሲገለጥ የሚደርስብን መከራ ሁሉ ሥፍራ ሳያስለቅቀን በጽናት መቆምን ፤ የስጋ እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብንና እግዚአብሔርን መጠበቅን እንማራለን ይህ የክርስቶስ ህይወት በውስጣችን መኖሩንም ይገልጣል::

*ጽናት - የተፈተነ ባሕርይን*

አማኝ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ በአምላኩ ላይ ተደግፎ በታማኝነቱም ታምኖ ሲጸና የጌታንም ማጽናናት ሲለማመድ (2ቆሮ 1:4) እምነቱ ይፈተናል (ያዕ 1:3) በትዕግሥትም የተፈተነ ማንነቱ ይጎለምሳል በክርስቶስ የሆነው ማንነቱም ይገለጣል::

*የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን*

በዚህ የህይወት መስመር የሚጓዝ ሰው ተስፋው የለመለመና የተስፋው ብሾታ ጠፍቶ ሕያው ሆኖ እየታየው የሚመጣ ያልጨለመበት ሰው ይሆናል:: በጌታ የተገለጠው ጽድቅ የሚያስገኝልን በረከት ይህንን የመሰለ እርግጠኝነት የሞላበት ነው::

***5:5-8*** ***በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም:: ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና:: ስለ ፃድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል:: ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል::***

*የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን መፍሰሱ*

ሐዋርያው ጳውሎስ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን እምነት (5:1) ተስፋ (5:2) ፍቅር (5:5) በውብ ቅንጅት ያስቀምጣቸዋል:: ትዕግሥት (5:3-4) ደግሞ በመከራ በመጽናት የሚገለጥ የባሕርይ ለውጥን ያመጣል ይገልጣል::

*ፍቅሩን በልባችን አፍስሷል*

በልባችን ያፈሰሰው ይህ ፍቅር ተስፋው በሙላት የሚፈጸም ስለመሆኑ ማረጋገጫችን ነው:: (ቲቶ 3:5-7)

> *እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ስራ አይደለም፣ ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ህይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በእየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው:: ቃሉ የታመነ ነው (ቲቶ 3:5-7)::*

እግዚአብሔር ፍቅሩን የገለጠው መች ነበር?

*ገና ደካሞች ሳለን*

እግዚአብሔር እኛን የወደደው ገና ኃጢአተኞች ወይም አቅመ ቢሶች ሳለን ነበር። ጽድቅንና ቅድስናን ለማድረግ ምንም ጉልበት ሳይኖረን ማለት ነው።

ጌታ ባዘጋጀው የዘላለም ሃሳብ መሰረት

- ዘመኑ ሲደረስ - በትክክለኛውና እርሱ በወሰነው ጊዜ (ሮሜ 9:9፤ የሐ 5:4)
- ስለ ኃጢአተኞች - ስለ ሰው ዘር ሁሉ - የሰው ዘር ሁሉ ምትክ ሆኖ መሞቱን ይገልጣል ( 2ቆሮ 5:15)

***ስለ ጽድቅ የሚሞት = የለም***
***ለደግ ሰው የሚሞት = ይገኝ ይሆናል (በጭንቅ)***

በሰው ልጅ ሕይወትና ኑሮ ውስጥ የተለመደው የእንካ በእንካ እንጂ አንዱ ለሌላው የመኖር ነገር አይደለም። ምናልባት አንዳዶች ለባለውለታቸው በተወሰነ መጠን ዋጋ ይከፍላሉ። ለጠላት መሞት ግን አይታሰብም። ጳውሎስ ይህንን ማነጻጸሪያ በመጠቀም ጌታ የሰራውን የጽድቅ ስራና በረከት ያጎላዋል።

*ገና ኃጢአተኞች ሳለን*

ይህ መግለጫ የሚያመለክተው በህይወት (በስጋ) ወደ ዓለም ከመጣንበት ጊዜ ጀምሮ የሰራነውን ኃጢአት ብቻ ሳይሆን በፊተኛው አዳም በእግዚአብሔር አብ ዘላለማዊ እውቀት የታየውን ዘመን ሁሉ ያመለክታል።

**ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና**

ክርስቶስ ስለ እኛ መሞቱ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውንና በእኛ ድርጊት የማይወሰነውን የክብሩን ሥራ ያመለክታል። ይህም የተሰወረ ሳይሆን የተገለጠ ነው።

*5:9-10 ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን። ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን ይህም ብቻ አይደለም*

*ከሚመጣው ቁጣ መዳን*

ጌታ በልጁ ሞት ምክንያት ኃጢአተኛውን «ጻድቅ ነህ!» ብሎ አወጀለት። ይህ ጌታ አሁንም ሕያው ሆኖ ለርሱ ስለሚማልድ ዘወትር ይጠብቀዋል ይህ ብቻ ሳይሆን ከሚመጣውም ቁጣ ያድነዋል። ዘወትር እምነቱን አጽንቶ ጌታን በማመኑ መቀጠል ብቻ ይጠበቅበታል።

*ጠላቶች ሳለን*

ጠላቶች የሆንነው ከኃጢአት የተነሳ ነው። ይህም ጥፋታችን በዳኛው የተረጋገጠ ነው (ኤፌ. 2:14-16)።

> *እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሀደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ህግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምን ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሄር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው (ኤፌ 2፤14-16)።*

*በልጁ ሞት ታረቅን*

የእኛና የእግዚአብሔር ጠብ የተወገደውና የታረቅነው በክርስቶስ ሞት ነው። ከታረቅን በኋላ በወዳጅነት እንኖራለን። ብዙ ክርስቲያን እንደታረቀ ሰው የወዳጅነትን ሕይወት በመኖር አይለማመድም። የዳነው ግን በወዳጅነት ለመኖር ነበር።

*በሕይወቱ እንድናለን*

ይህ ሕይወት በእምነት የምንኖረው ነው። ይህንን ጌታ በራሱ ተማምኖ የጀመረውን ሕይወት ወደ ፍጻሜ የሚያመጣው እርሱ ነው። (ቆላ 3:4፤ ዮሐ 14:19፤

ሮሜ 6:8-9፣ ዕብ 7:25) እርሱን ስንከተልና ከእርሱ ጋር ስንኖር እርሱን እንመስላለን።

*ህይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ (ቆላ 3:4)።*

*ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚያ በኋላ አለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ እኔ ህያው ነኝና እናንተ ደግሞ ህያዋን ትሆናላችሁ (ዮሐ 14:19)።*

*ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን (ሮሜ 6:8-9)።*

*ስለእነርሱም ሊማልድ ዘወትር በህይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል (ዕብ 7:25)።*

***5:11 ነገር ግን አሁን መተረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን።***

*በመታረቃችን ሃሴት ማድረግ*

| |
|---|
| እርቅን ባገኘንበት በክርስቶስ በኩል ሕይወታችን ሃሴት የሞላበት ይሆናል ። የሚዋደዱ ሰዎች ዋጋ ከፍሎ የሚያስታርቃቸው ሲገኝና የዕርቁ ሥራ ሲሳካ የሚሰማቸውን ደስታና ሃሴት ስናስብ በጥቂቱም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቃችን በውስጣችን የሚፈጥረውን ሃሴት ያመለክተናል። መቤዠትንም ያሳያል። |

# ለ. የጽድቃችን መሠረት (5:12-21)

ሐዋርያው የጽድቃችንን መሰረት ጥንካሬና አስተማማኝነት ለማመልከት፣ የውድቀታችንን ጽናት በመግለጥ በአባታችን አዳም በኩል የደረሰብንን ኪሳራ መንደርደሪያ አድርጎ ይጠቀምበታል። ይህ ክፍል ባጭሩ በአዳምና በክርስቶስ መካከል ያለው ልዩነት የተገለጠበት ነው።

**5:12** ***ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ አለም ገባ በኃጢአትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ***

*ኃጢአት ገባ*

ኃጢአት ቀድሞ የነበረው በዲያቢሎስና በጭፍሮቹ ዘንድ ብቻ ነበር። አዳም ኃጢአትን ሲሰራ ግን ወደ ዓለም (የሰው ዘር) ደረሰ - ገባ ይህም የሆነው በአንድ ሰው በኩል ነው።

( ኃጢአት ወደ ዓለም የመግቢያ በር አገኘ።አባታችን አዳም )

*ሞት በኃጢአት በኩል ገባ*

ሞትም መግቢያ በር ያገኘው በኃጢአት በኩል ነው። የሞት በሩ ኃጢአት ነው።

*ሁሉም ኃጢአት ስለ ሰሩ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ*

ኃጢአት ስንሰራ የኃጢአት ኃይል ሕያው ሆነ። እኛም የአዳም ወገን ስለሆንን ደሙ በእኛ ውስጥ ስላለ ባህርዩን ወርሰናል ባህርዩም በኃጢአት የተበላሸ ባህርይ ነው። (ሐሥ 17:26፤ ማቴ 25:15)

*ምናልባት እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሄርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው (ሐሥ 17:26)።*

*ለእየንዳንዱ እንዳቅሙ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱም ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲየው ሄደ (ማቴ 25:15)።*

ይህንን ማብራሪያ ስንሰጥ ግን ሰው መጠንቀቅ አለበት ማለትም:-

ሀ. ኃጢአት የምሰራው ባህርዬ ስላለኝ ነው ስለዚህ ተጠያቂ አይደለሁም ማለት አይቻልም

ለ. በመልካም ስራዬ ከሞት ማምለጥ እችላለሁ ማለት አይችልም።

ይህንን የኃጢአት ባህርይ ከውስጥ ከመሠረቱ የሚገድለው ከልተገኘ ይህ ብቃት አይገኝም።

***5:13 ሕግ እስኪ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቁጠርም፤ ሕግ***

***እስኪመጣ ድረስ - የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ከሕግ በፊት በነበሩት ላይ ሞት ነገሰ***

እነዚህን ሁለት ቁጥሮች ልብ ብሎ በርጋታ መመልከት አግባብነት ይኖረዋል

ሀ. የኃጢአት ህልውና ያለ ህግ የተገለጠና ጌታ በውስጣችን ባስቀመጠው የህሊና ሕግ የታወቀ ነው

ለ. ሕግ ሲመጣ ግን ኃጢአት በኛ ላይ መቆጠር ጀመረ። ምክንያቱም ሕግ ኃጢአትን ገለጠው። ይፋ አደረገው፣ እንዲታወቅ አደረገው ከህግ በፊት የነበሩት ሁሉ ኃጢአት ሰርተዋል። ስለዚህ ሞት አግኝቷቸዋል። ሕግ ከመጣ በኋላ ደግሞ እውቀቱ ስለተገለጠ በኛ ላይ ኃጢአት መቆጠር ጀመረ።

***5:14 ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሰሩት ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።***

*በአዳም መተላለፍ . . . አዳም አምሳሉ ነበረ*

የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የተላለፈው አዳም ነበር። ነገር ግን እኛ የእርሱ አምሳል ስለነበርን በእርሱ የመጣው ሞት በእኛ ደረሰብን ምክንያቱም እኛ እርሱን ስለምንመስል።

*ሞት ኃጢአት ባልሰሩት ላይ ነገሠ*

ይህ መግለጫ የሚሻውን ማድረግን፣ መግዛትና ማስተዳደርን ያመለክታል።

*ለእርሱ አምሳሉ ነው*

ይህ ደግሞ ኋለኛውን አዳም የሚገልጥ ሲሆን ሁለቱም የሰውን ዘር የሚወክሉ መሆኑን ያመለክታል።

(ውክልናቸው ግን እጅግ የሰፋ ልዩነት አለው። አዳም ለሞት፣ ኢየሱስ ለሕይወት) (1ቆሮ 15:45)

> *እንዲሁም ደግሞ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ(1ኛ ቆሮ 15:45)።*

ሐዋርያው ከዚህ በታች በኢየሱስ የተገለጠውን ልዩነት በማነፃፀር ይገልጠዋል።

***5:15*** ***ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።***

*ስጦታው እንደ በደሉ መጠን አይደለም*

ሐዋርያው አሁን የሚያነሳው ማነጻጸሪያ የኃይልና የጉልበት ነው። በአዳም የገባው በደል ዓለምን ሁሉ የማጥለቅለቅ ጉልበት አለው ሆኖም ግን በክርስቶስ የተገለጠው ማዳን (ጽድቅ) በበደሉ ልክ አይደለም ይበልጣል! የሚል ነው። ይህንንም የተጠቀመው የጸጋውን ጉልበት ለማሳየት ነው።

*በአንድ ሰው በደል ምክንያት*

ፊተኛው አዳም ኃጢአት ሲሰራ የኃጢአት ኃይል ሁላችንንም ተቆጣጠረን በእኛ ላይ ነገሰ።

## *የእግዚአብሔር ፀጋ ከዚያ ይልቅ በዛ*

በአንዱ ኃጢአት ሁላችን ኃጢአተኞች ከሆንን በአንዱ ጽድቅ ደግሞ እጅግ በተትረፈረፈ ሁኔታ ሁላችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ እንካፈላለን። ጻድቃን እንሆናለን።

***5:16** አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም ፍርድ ከአንድ ሰው ለኩነኔ መጥቶአልና ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ።*

*አንድ ሰው ኃጢአት በማድረጉ እንደሆነው መጠን*

- ፊተኛው አዳም (ተወካዩ) ክብሩን ተቃውሞ ኃጢአት ሠራ
- ከዚህም የተነሳ ከባድ ፍርድ ተመደበ። ፍርዱም የዘላለም ሞት፣ ሲኦልና በእሳት ባህር መጣል ነው።

*ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ*

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር በንጽጽር እያቀረበ ያለው የአዳምን በደልና ወይም በአዳም ኃጢአት ምክንያ ኩነኔ ወደ ሰው ዘር ሁሉ መግባቱንና በአንዱ በኢየሱስ ጽድቅ ምክንያት በእርሱ ያመነ ሁሉ መጽደቁን ነው።

በብዙ በደል የሚለው ቃል የዓለምን (የሁሉን) ኃጢአት የሚያመለክት ነው። በዚህ ክፍል አጽንኦት ሰጥቶት ማሳሰብ የፈለገው በአንዱ ኩነኔ ከመጣው ሞት ይልቅ በአንዱ መታዘዝ የመጣው ጻድቅ ይበልጣል የሚለውን ነው።

*5:17 በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሰ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሳሉ::*

*የነገሠ ከሆነ . . . አብልጠው በሕይወት እንዴት አይነግሱ*

በዚህኛው ቁጥር ውስጥ ሐዋርያው የመከራከሪያ ነጥቡን ወደ ከፍተኛ እርከን በማሸገር ሁለቱን ንግሥናዎች በማነጻጸር ያቀርባቸዋል:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች « እንደ ንጉሥ ኑር! » የሚል ርዕስ ለምዕራፍ አምስት ይሰጡታል::

ሐዋርያው በዚህ ክፍል አዳምም ኢየሱስ ክርስቶስም በሮች መሆናቸውን ይገልጣል ሆኖም በጣም ትልቅ ልዩነት በመካከላቸው አለ ልዩነቱም

*አዳም - የሞት በር ! ሞት በሰው ላይ እንዲነግሥ ምክንያት ሲሆን ኢየሱስ - የሕይወት በር ፤ ሕይወት ለሰው ዘር ሁሉ እንዲሆንና በሕይወትም ለዘላለም እንዲነግሱ ምክንያት መሆኑ ነው ::*

ስለዚህ ልዩነታቸው ቀላል ሳይሆን የሞትና የሕይወት ልዩነት ነው::

ይህንን የመሰለ ትልቅ ልዩነት በግልፅ ካስቀመጠ በኋላ ሐዋርያው ቁጥሩን የሚዘጋው «እንዴት አይበልጥም ትላላችሁ?» ብሎ በአዳም ኃጢአተኞች የሆኑ በክርስቶስ ጽድቅን ለመቀበል ለምን እንደተጠራጠሩ በመሞገት ነው::

*5:18 እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ::*

. በዚህኛው ቁጥር ደግሞ ለተጠየቀው ጥያቄ ማስተባበያ ሲቀርብበት የማይችለውን ምላሽና እውነት አስረግጦ ይናገራል:: ማስረጃውም:-

1. በአንዱ በደል ምክንያት ኩነኔ ሆኖአል (ፍርድ ተመድቦአል)

በአማርኛችን በደል ተብሎ የተቀመጠው ቃል በእንግሊዝኛው offense የሚለው ነው:: ይህም ማለት Offense means [ trespass – Crossing over the line ]

አዳም እግዚአብሔር ያሰመረለትን መስመር አልፎ ባልተፈቀደለት ስፍራ በመገኘት ባለመታዘዝ ፍርድን ለዘር ዘሩ ሁሉ አመጣ:: የሚል እውነት ያዘለ ነው::

2. በአንዱ ጽድቅ ምክንያት (ሕይወትን የሚሰጥ ጽድቅ)

አንዱ ሲተላለፍ ሁለተኛው ግን ፈጽሞ ታዘዘ ስለዚህም የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገለጠ::

> ይህ ጽድቅ « ጸድቃን » ተብለን በእግዚአብሔር የታወጅንበት የሕይወት አቋም ብቻ ሳይሆን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የጽድቅን ሕይወት ለመኖርና ለመምራት የምንችልበትን ብቃት ያገኘንበት ነው::

በነጥቦች ስናስቀምጠው:-

- የእግዚአብሔር ጽድቅ በኃጢአት ላይ በመፍረድ ተገልጧል ሮሜ 3:25
- የእግዚአብሔር ጽድቅ የኃጢአትን ይቅርታ በማስገኘት ተገልጧል ሮሜ 5:16

- የእግዚአብሔር ጽድቅ ወደ ዘላለም ክብር አስገባን:: ይህም ማለት በአዳም በደል ምክንያት ሞት አርቆን የነበርነውን፤ የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ወደ ክብር መለሰን ማለት ነው (ሮሜ 5:18)::

*እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆን ማስተሰሪያ አድርጎ አቆመው ,ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው (ሮሜ 3:25)::*

*በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሳሉ (ሮሜ 5:16)::*

*እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ (ሮሜ 5:18)::*

በነዚህ ቁጥሮች ሐዋርያው በንጽጽር ያስቀመጣቸው መታዘዝና አለመታዘዝ ውጤታቸው እጅግ በጣም ትኩረትን የሚስብ ነው::

አዳም = ትዕዛዙን ጣሰ ተላለፈ = ዘሩ ሁሉ ኃጢአተኞች ሆኑ

ኢየሱስ = ታዘዘ = በእርሱ ያመኑ ሁሉ ጻድቃን ሆኑ

ማለትም በመጀመሪያው ሞት የሁላችን ዕጣ ፈንታ ሆኖ ነበር በሁለተኛው ግን የዘላለም ሕይወት ተሰጠን::

***5:20 በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ***

***ሕግ መጣ . . . ጸጋ ተትረፈረፈ***

የሕግ መምጣት የኃጢአት በምድር ላይ የመብዛቱ ምልክት ነው (ሮሜ 7:3፤13፤20፤)::

ሐዋርያው « ሕግ ገባ »ነው የሚለው ሐዋርያው ይህንን ግልጽ ሲያደርግ ጸጋ ግን ቀድሞም ነበረ የሚለውን ነው።

ሐዋርያው ይህንን ግልጽ ሲያደርግ « ጸጋ » ተትረፈረፈ ነው የሚለው። ክፍሉን በፍጹም እርጋታ ስናጠናው የእግዚአብሔር ጸጋ በእግዚአብሔር ፕላን ላይ የገባ ተጨማሪ ነገር ሳይሆን አስቀድሞውኑ በዕቅዱ ውስጥ የነበረ ነው። እንዴት? ቢባል:-

. ለአዳም ጸጋውን ገልጧል
. ለእምነት አባቶች ጸጋውን ገልጧል
. ለእሥራዔል ሕዝብ ጸጋውን ገልጧል እነዚህ በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

እግዚአብሔር ለሙሴ ሕግን የሰጠው ጸጋን እንዲተካ ሳይሆን የሰው ልጅ ጸጋ ምን ያህል የሚያስፈልገው ኃጢአተኛ መሆኑን እንዲረዳና ወደ ጸጋ እንዲመጣ ለማድረግ ነው።

ሕግ ሲመጣ ኃጢአት እንደ ነገሰ ሁሉ በአንዱ በክርስቶስ ጽድቅ (ጸጋ) ምክንያት ደግሞ ሕይወት ይነግሳል። የዚህም ሕይወት ሙላቱና ፍጻሜው የዘላለም ሕይወት ነው።

የአዳም ኃጢአት የሰውን ልጅ ከገነት አስወጣው የክርስቶስ ኢየሱስ ጽድቅ በመስቀል ላይ ሲገለጥ ወንበዴውንና ለእርሱ ልቡ የተሸነፈውን ሰው «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ! » በማለት በአዳም ሞት ምክንያት ከገነትና ከዘላለም ሕይወት ተባርሮ የነበረውን በደለኛ ወደ ሕይወትና ወደ ዘላለም ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም አብሮ ወደ መኖር አስገባው! በመስቀል ላይ የነበረውና ከጌታ ጋር ወደ ገነት የገባው ወንበዴ በኃጢአት ከእግዚአብሔር ርቀው የነበሩትን ሁሉ ይወክላል።

***5: 21 እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።***

***ይህም የሆነው... ጸጋ በጽድቅ እንዲነግሥ ነው!***

ሞት በኃጢአት ምክንያት እንደነገሰ ሁሉ፤ ጸጋ ደግሞ በጽድቅ ምክንያት አብልጦ እንደሚነግሥ ፤ ክርስቶስም

የሞተው ለዚህ ትልቅ ዓላማ መሆኑን ሐዋርያው በምዕራፉ ማጠቃለያ ላይ በግልጽ ያስቀምጣል::

## ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

ኃጢአት፣ የሞትና የዘላለም ፍርድ በአዳም ምክንያት በእኛ እንደሰራ ሁሉ የሕይወት ፣ ከኩነኔ ነፃ መውጣትና የዘላለም ሕይወት ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ምክንያት ለእኛ ተሰጥቶናል::

ስለዚህ እኛም ይህንን አምነን በመቀበል ይህን ሕይወት በመኖር የጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ በኛ ሕይወት እስከ ዘለቄታው እንዲፈጽመው ልንፈቅድለት ይገባል:: (ዕብ 2:18)

በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ በመደገፍ እርሱ ራሱ ወደ ከፈተው ወደዚህ ሕብረት በመግባት ዘወትር ከአብ ጋር በልጁ በኩል በሕብረት እንኑር::

ይህ ዓለም ሰይጣን የነገሰበት እንደመሆኑ መጠን ክርስቶስ ነግሶብን በጽድቅ ሕይወት እንኑር ስንል ሊመቸን እንደማይችል የታወቀ ነው:: መከራ ይመጣል፤ በመከራው ጸንተን ታግሰን ከጌታ ጋር ስንቆም ግን የክርስቶስ ክብር ተካፋዮች እንሆናለን:: በመከራ የጸናውን አስቡ! መባላችንን እንርሳ (ሮሜ 5:2፤ ቆላ 3:2! ኤፌ 4:18:24)

*እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና (ዕብ 2:18)::*

*በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ፀጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን (ሮሜ 5:2)::*

*በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም (ቆላ 3:2)::*

*እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንዳንነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ ፣ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ (ኤፌ 4:18)::*

*በአእምሮአችሁ መንፈስ ታደሱ ፣ ለእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ (ኤፌ 4:24)::*

# ምዕራፍ ስድስት
# ጸጋ እንዲበዛ...?

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ስለ ጽድቅ ያቀረበውን አስተምህሮ አስመልክቶ የመከራከሪያ ነጥቡን በችሎት ፊት በሚያቀርብ ዓይነት ውብ አካሄድ ገለጸውን ያቀርባል። ሐዋርያው የመከራከሪያ ነጥቦቹን በሶስት ክፍሎ ያቀርባቸዋል

1. ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? (6:1-14)
2. ሕግ በኛ ላይ ስልጣን ከሌለው ወይም በሕግ ስር ካልሆንን እንደልባችን እንሁንን? (6:15-7:6)
3. ሕግ በራሱ ኃጢአት ነውን? (7:7-25)

ሐዋርያው ያነሳቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች ስንመለከት ተደራሲያኑ ሕግንም ሆነ ጸጋን የማያውቁ መሆናቸውን እንረዳለን። ተደራሲያኑ በሁለት የተወጠሩ ጫፎች ወዲያ ወዲህ የሚንገዋለሉ መሆናቸውንም ያስረዳናል። ማለት በአንድ በኩል ሕገኝነት ይጎትታቸዋል በሌላው ጫፍ ደግሞ ገደብ የለሽ ልቅ ኑሮ የመኖር ወይም ለኃጢአት አርነት የመስጠት ሕይወት ይጎትታቸዋል። ዋናውን የዚህን ክፍል ሃሳብ ካያዝነው ሃሳቦቹን ከፋፍለን በየቁጥሮቹ እንመልከታቸው።

## *6:1 ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን?*

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ቁ 1-10 ባለው ክፍል ውስጥ የተሳሳተ አመለካከታቸውን ፍቺያቸው የተመሰረተው ከዕውቀት ማነስ መሆኑን ለተደራሲያኑ በብርቱ ያሳውቃቸዋል ስለዚህ « ዕወቁ » የሚል ማሳሰቢያ ይሰጣቸዋል። የዕውቀት ማነስ በብዙ ስህተት ውስጥ እንደሚያስገባ ሐዋርያው በብርቱ ያሳስባል። ስለ ጽድቅ የቀረበውን የጳውሎስ ትምህርት አንዳንድ ሰዎች ጳውሎስ እኮ ጸጋ እንዲበዛ ከፈለጋችሁ በኃጢአት ግፋበት ብሏል ብለው ያምኑ ነበር። ጳውሎስ ግን ይህንን አላስተማረም። ዛሬም ቃሉ ይህንን አያደፋፍርም በብርቱ ይቃወማል እንጂ።

ገና ከመነሻው ስንመለከት ሰዎች ኃጢአት የሰሩት ጸጋ እንዲበዛ አይደለም።

ጌታም ጸጋውን ያፈሰሰው ኃጢአትን ለማበረታታት አይደለም የኃጢአት ብዛት ዓለምን ስለሸፈነ ብዙዎችን ለማጽደቅ እንጂ። ጌታ በባህርዩ የተትረፈረፈ ጸጋን የተሞላ ነው።

| |
|---|
| ጸጋ የተገለጠው ለኃጢአት ሳይሆን ለኃጢአተኞች ነው። ስለዚህ ለኃጢአተኞች ኃጢአት የማይሰሩበትን አቅም ይሰጣቸዋል እንጂ ኃጢአትን ጉልበተኛ አያደርገውም። ስለዚህ ይህ የተሳሳተ አመለካከት የወጣው ከዕውቀት ማነስ ነውና ተረዱ ይላል ጳውሎስ። ዛሬም ጸጋን ለኃጢአት መሸፈኛና ማስተባበያነት ሊጠቀም ለሚፈልግ የዘመኑ ትውልድ መልዕክቱ አትሳሳቱ፣ ጸጋው ኃጢአትንና ዓለማዊ ምኞትን ለማስካድና ከክርስቶስ ጋር በእርሱ ሕይወት መኖርን ሊያስችለን ነው የመጣው እንጂ በኃጢአት እንድንዘናና ሊያደርገን አይደለም የሚል ነው። |

## *6:2 ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?*

*ለኃጢአት የሞትን እኛ*

ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ ገለጣ በክርስቶስ ኢየሱስ ካመንን ጊዜ ጀምሮ ኃጢአት በኛ ላይ ምንም ኃይል እንደሌለው ያመለክታል። ማለትም ለኃጢአት ሞተናል። በፊተኛው አዳም ምክንያት በሕይወታችን ነግሶ የነበረው የኃጢአት ልምምድ ዙፋኑን ተነጥቋል። ሞተናል ስለዚህ የቀድሞውን ሥራ ለማድረግ ስሜቱ የለንም፣ መሻቱና ፍላጎቱ የለንም የመስራት አቅሙም የለንም።

ስለዚህ ወደፊት የምንኖረው ኃጢአት በሞት በነገሰበት ሕይወት ሳይሆን በሕይወት በነገሰበት በክርስቶስ ውስጥ ነው።

**6:3-4** *ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንዝሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንዝሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንዝሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።*

*አታውቁምን?*

የሐዋርያው የዕውቀት ጉድለት ማመልከቻ ነጥቡ በዚህ ምዕራፍ ብቻ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል (3:6:9) ሁሉም ተደምረው በክርስቶስ ጸጋ የፈሰሰውን የመገለጥ ዕውቀት ማነስ ያሳያሉ።

ታድያ ምንድነው አታውቁምን? የሚላቸው ስንል

*ከሞቱ ጋር አንድ እንድንሆን እንደተጠመቅን።*

የግሪኩ ቃል መጠመቅን በሁለት መንገድ ይፈታዋል

1. የቃል በቃል ፍቺ = መጥለቅ፤ ሙሉ በሙሉ መወረስ (2ኛ ነገ 5:10 ፤ማር 7:4፤ ማር 10:38 ፤ ሐሥ 22:16፤2:38)።

*ሌላሳዕም:-ሂድ፣ በዮርዳኖስም ሰባት ጊዜ ታጠብ ሥጋህም ይፈወሳል አንተም ንፁሕ ትሆናለና ብሎ ወደ እርሱ መልእክተኛ ላከ (2ኛ ነገሥት 5:10)።*

*ሳይታጠቡ አይበሉምና ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም ጽዋንም ማድጋንም የናስ ዕቃንም አልጋንም እንደ ማጠብ ሌላ ነገር ሊጠብቁት የተቀበሉት ብዙ አለ (ማርቆ7:4)::*

*ኢየሱስ ግን የምትለምኑትን አታውቁም እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን አላቸው (ማርቆ10:38)::*

*አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ (ሥራ 22:16)::*

2. **ትእምርታዊ (ምሳሌያዊ) = ህብረትን ፣ አንድነትን ፣ መተባበርን (1ቆሮ 10:2፤ ማር 10:38 )::**

***ሁሉም መሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመና በባህር ተጠመቁ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ (1ኛ ቆሮ10:2)::***

*ኢየሱስ ግን የምትለምኑትን አታውቁም:: እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁ (ማር 10:38)::*

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለቱንም ፍቺዎች በአዕምሮው ይዞ ሙግቱን ያቀርባል:: ስንጠመቅ በአዳም ህይወት ግዛት ስር የነበረው በቁጥጥሩ ስር የነበረው ህይወት አሁን በክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ተወርሷል:: ከእርሱ ጋር አንድ ሆኗል ተባብሯል ከድሮው ግን ተላቋል ማለት ነው::

ከሞቱ ጋር የሚለው ቃል በሞቱ አንድ መሆናችንን ያሳያል:: ይህም እንዴት ተቻለ ቢባል አብ በመለኮታዊ ችሎቱ በወሰነው ውሳኔ በመስቀል ላይ ተፈጸመ:: በዚህ ህይወት ለመኖርም ለሰው ዘር ኃይልና ብቃት ተገኘ::

ተቀበርን የሚለው ቃል ደግሞ ጠልቀን ገብተን ሙሉ በሙሉ መወረሳችንን ያመለክታል::

## *ከሞት እንደተነሳ*

ጌታ ከሞት ሲነሳ በአብ ክብር አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ኑሮ፣ አዲስ ብቃት፣ ለብሶ ለሰው ልጆች ሁሉ ይህንን አዲስ ህይወት ለመስጠት በሚችልበት ብቃት ተነሳ!
እኛም ከሞቱ ጋር ከተባበርን ከመነሳቱም ጋር መተባበር ይገባናል። ይህም ማለት በአዲስ ህይወት መኖር፣ በአዲስ እርከን መመላለስ በአዲስ ተስፋ መመላለስን ያመለክታል።

ጌታ ዛሬ እኛን የሚጋብዘን ይህንን ህይወት እንድንኖረው ነው። ይህም በመፍጨርጨር ሳይሆን በመታመን ነው ። በከፍታም ይሁን በዝቅታ የክብሩን ህይወት መኖር።

***6:5 ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤***

*በሞቱ . . . በትንሳዔው እንተባበራለን።*

መተባበር የሚለው ቃል የጸደቀ ተክል ከግንዱ ጋር ተጣብቆ ከኖረ በግንዱ ያለው ህይወት ሁሉ የሚተላለፍበትን ሕብረት ያመለክታል (ዮሐ 15:1-2፤ ሮሜ 11:17)።

> *እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ ገበሬውም አባቴ ነው። ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል (ዮሐ 15:1-2)።*

> *ነገር ግን ከቅርንጫፎቹ አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንክ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ስር ከሆንህ በቅርንጫፎቹ ላይ አትመካ (ሮሜ 11:17)።*

ጌታ በክርስቶስ የመስቀል ስራ ያስገባን ወደ ሁለት ዋና ዋና የሕይወት አቋሞች ነው። የመጀመሪያው ለአሮጌው ህይወት ሙት መሆኑን (ከክርስቶስ ሞት ጋር መተባበርን) ቀጥሎ

ደግሞ ለአዲሱ ህይወት ህያው ሆኖ መኖርን (ከክርስቶስ ትንሳዔ ጋር መተባበርን) ጌታ የሚፈልገውን ይህንን የክብርና የድል ህይወት እንድንኖረው ነው። ብዙዎች ይህንን ህይወት መኖር አይቻልም ይላሉ። እኛ ደግሞ የራስ ጥረትና የጡንቻ ጉዳይ ሳይሆን በእምነት ለክርስቶስ ቻይነት ራስን በመስጠት እርሱ ይህንን ህይወት በውስጣችን እንዲኖረው በመፍቀድ መኖር ይቻላል እንላለን።

ይህንን እውነት በሚገባ ለመረዳት የኢየሱስ ወዳጅ በነበረው በአልአዛር ህይወት የሆነውን መመልከቱ ይጠቅማል። (ዮሐ 11:14-18፤38-49)

አልዓዛር ሞተ የቀድሞ ህይወቱ አበቃ፣ ተገነዘ መቃብር ገባ ወደ መቃብሩ ኢየሱስ መጣ፣ በቃሉ ኃይልን ሥልጣን ተናገረ ትዕዛዝ ወጣ

ከሞት ተነሳ = አልአዛርን ከሞት ያስነሳው ተፈጥሮአዊ ብቃቱ አይደለም ወደ መቃብሩ መጥቶ የትንሣዔን ቃል ባወጣው በኢየሱስ ጉልበት (ጸጋ) እንጂ

ከመግነዙ ተፈታና ሄደ = መግነዙ መሞቱን የቀደመው ማብቃቱን መራመድ አለመቻሉን ሲያሳይ መፈታቱ ደግሞ አሁን ባገኘው የትንሣኤ ጉልበት በአዲሱ ህይወት ህግ ለመኖር ነፃ መውጣቱን ያሳያል። ከዚያን ቀን ጀምሮ ዓልአዛር በሚወጣበት በሚገባበት ቦታ ሁሉ የሚገልጠው የራሱን ጀግንነት ሳይሆን ከሞት ያስነሳውን ፣ አዲስ የመፈታት ህይወት የሰጠውን የትንሳዔ ጌታ ብቻ ነው።

ከክርስቶስ ጋር በማዕድ ተቀመጠ = አልዓዛር ከጌታ ጋር የተቀመጠው በብቃቱ ሳይሆን በጌታ ነበር አስነስቶት ለራሱ እንዲኖር አልነበረም ከእርሱ ጋር እንዲቀመጥ ነበር። ከአይሁድ ብዙዎች በዚህ ምክንያት ወደ ኢየሱስ መጡ ለምን? ብንል ኢየሱስንና ከሞት ያስነሳውን አልአዛርን ለማየት።

ዛሬ ብዙዎች ክርስቲያኖች በክርስቶስ ያምናሉ ነገር ግን ድል የሞላበትን፣ አሸናፊና የተትረፈረፈ የክርስትና በረከት ያለበትን ህይወት አይኖሩም ከግብጽ ወጥተው በምድረበዳ እንደተንከራተቱት እስራኤላውያን ዓይነት ናቸው።

ይህም ማለት በትንሳዔው ኃይልና ክብር ከክርስቶስ ጋር አይኖሩም ዛሬም ይፍጨረጨራሉ። በትንሣዔው ኃይል ስትመላለስ ከኢየሱስ ጋር ስትሆን ወንጌል ተናጋሪ ብቻ አትሆንም ወንጌል ትሆናለህ! አልአዛር ከኢየሱስ ጋር ተቀመጠ አይሁድ መጡ አዩት አመኑ። ያዩት ከሞት የተነሳውን አልዓዛርን ነው። ያመኑት ግን ከሞት ያስነሳውን ክርስቶስ ኢየሱስን ነው።

ይህ የትንሳዔ ህይወት ለቀድሞው ነገር ሙት መሆናችንን ፣ አሮጌው ህይወት ማለፉን ፣ ከአሮጌው ህይወት ጋር የነበረን ነገር በሙሉ በሞት መቋረጡን ያመለክታል። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን ከክርስቶስ መሞት ጋር መተባበራችንን ከኃጢአት ጋር ካለን ግንኙነት አንፃር ሲፈታው በሚቀጥሉት ሃሳቦች ውስጥ እንመለከታለን።

*6:6-7 ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን*

*የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋል (ነፃ ወጥቷል)*

ይህንን ሃሳብ በግልጽ ለማየት ነጥብ በነጥብ ማብራራቱ ተገቢ ነው:-

1. ከእንግዲህ ወዲህ ለኃጢአት እንዳንገዛ ነፃ ወጥተናል

   ይህም ማለት ኃጢአት በኛ ላይ ሥልጣን እንዳይኖረው፣ ለኃጢአት ባሮች እንዳንሆንና በኛ ላይ ምንም መብት ላይኖረው በሞት ተለያይተናል ማለት ነው። (ስካራም ሰው ከሞተ በኋላ በመጠጥ እንደማይቸገር ሁሉ ማለት ነው)

2. አሮጌው ሰው ከእርሱ ጋር ስለተሰቀለ ነፃ ወጥተናል

   አሮጌው ሰው ሲል = አዳማዊው የህይወት ዘይቤ መኖሪያው ላያደርገው ተለያዩ፣ ተሸነፈ፣ ተወገደ ማለት ነው።

የአልዓዛርን ተፈጥሮአዊ አሠራር ስንመለከትና በዘር ውስጥ የሚከሄደውን እውነታ ስንመለከት አንድ ዘር ይዘራና ውጫዊ አካሉ ሲበሰብስ ሲሞት፣ አድጎም ፍሬ ያፈራል አዲስ የወጣው ግን አሮጌው ሳይሆን አሮጌው ሞቶ አዲሱ ነው።

3. አሮጌው ስጋ ይሻር ዘንድ

ይህም ማለት ኃጢአትን ማገልገል እንዳይችል ፣ ለእርሱ ሥልጣን እንዳይገዛ እንዳይኖርለት።

ሥጋ የምንለው አሮጌውን አዳማዊ ማንነት ሲሆን ይህም ማንነት ይሰለጥንና ይገለጥበት የነበረውን መንፈሳችንን ነፍሳችንን አካላችንን የሚያከትት ነው።

ከአሮጌው አዳማዊ ባሕርይ (ሥጋ) የተነሳ

- መንፈሳችን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ አይችልም
- ነፍሳችን የአብን ፈቃድ መረዳትና ማሰብ አይችልም
- ስጋችን ከኃጢአት ባርነት ለመላቀቅ አቅም የለውም

ይህ አሮጌው ሲሰቀል ግን ነፃ ወጣን። ሞት ለያየን።

***6:8-10*** ***ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል።***

***እናምናለን . . . ለኃጢአት ሞቷል . . . ለእግዚአብሔር ይኖራል***

ሐዋርያው በነዚህ ቁጥሮች የሚያነሳው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለናል ካልን በዚሁ ህይወት በእምነት ጸንተን መኖር ይገባናል።

ከክርስቶስ ጋር ተነስተናል ካልን ደግሞ ክርስቶስ ለአብ ክብር እንደሚኖር እኛም በዚህ እውነት መኖር ይገባናል።

ሐዋርያው በዚህ ክፍል ጠበቅ አድርጎ የሚገልጸው ከዚህ የክብር ሕይወት የሚያጎድለን አለማመን ነው። ስለዚህ ማመን ይገባናል ሞቱ ከሰራ ሕያውነቱም ይሰራል እያለ ነው።

ሞትና ኃጢአት በክርስቶስ ላይ ምንም ስልጣን የላቸውም። እኛ ደግሞ በክርስቶስ ውስጥ ነን ስለዚህ በኛ ላይ ኃጢአትም ሞትም ሥልጣን የላቸውም።

ጌታ ኢየሱስ በመስቀሉ ላይ የኃጢአት ዕዳችንን መክፈል ብቻ ሳይሆን የኃጢአትንም ኃይል ሰብሮታል። ስለዚህ ራሳችሁን ለአዲስ ህይወት አዘጋጁ።

*6፡11 እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታቹሁ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናቹሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናቹሁ ራሳቹሁን ቁጠሩ።*

*ቁጠሩ*

መቁጠር የሚለው ቃል ማሰብ፣ መገመት፣ ማየት፣ ማወጅ ፣ መናገር ማለትንም ሊያጠቃልል ይችላል።

ይህ መቁጠር የሚለው ቃል በሕይወታችን ሊገለጥ የሚችለው ጳውሎስ በቁጥር 6 እንደገለጠው እምነት ሲኖር ነው። ማለትም ልክ አብርሃም እግዚአብሔር ያየለትን ነገር በእምነት እውን እንደሆነ እንዳስተዋለው ዓይነት የእውነት ብርሃን ግልጠት ስናገኝ ነው።

ስለዚህ በክርስቶስ ውስጥ ያለ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ካለው ግንኙነት የተነሳ ለኃጢአት የሞተና ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር ሕያው መሆኑን መቁጠር ያንንም ማወጅ ይኖርበታል።

## *6:12 እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ*

*. . . አታድርጉ*

ሐዋርያው እንግዲያው ራሳችሁን እንደዚያ ከቆጠራችሁ እንዲህ አታድርጉ ብሎ መሠረት ባለው ሁኔታ ግልጽ ያደርገዋል። ምን እናድርግ?

### ኃጢአት እንዲነግሥበት አታድርጉ

ንጉሣችሁ ጽድቅ ሆኗል (ክርስቶስ ሆኗል) እንደሱ ከሆነ ለትልቁ ንጉሥ ተገዝታችኋልና ለተዋረደው ንጉሥ አትገዙ ማለቱ ነው ቀድሞ ስጋ በኛ ላይ ገዢ ንጉሥ ነበር ሞት ንጉሥ ነበር ጌታ ሲመጣ ግን ንግሥናው ተገፈፈ። ንጉሣችንም ተለወጠና ጌታ ኢየሱስ ሆነ (ጽድቅም) በላያችን ሰለጠነ። ስለዚህ አትመለሱ ነው መልዕክቱ።

እንዴት?

ለምኞቱ ባለመታዘዝ - ሁልጊዜ የኃጢአት መነሻው ምኞት ነው። ምኞት የሚታዘዘው ሲያገኝ ኃጢአት ያሠራል። የሚታዘዘው ሲያጣ ግን አቅሙ ይሰበራል።

ለምኞቱ ላለመታዘዝ የስጋን ሟችነት መረዳት ይገባል። ምድራዊው አካልህ ሟች ነው ጠበቃህ ሊሆን አይችልም፣ አቅመ ቢስ ነው ይከዳል። እንግዲያው ሟቹን ሕያው ባደረገ ፣ ደካማውን ባገዘና አቅም በሰጠው ጌታ በመታመን በዚህ ሟች ስጋ ኃጢአት እንዲሰለጥን ምኞቱንም እንዲፈጽም አታድርጉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ነጥቡን ደረጃ በደረጃ በፈርጅ በፈርጁ እያስቀመጠ እዚህ ደርሷል።

ቀደም ብለው የተዳሰሱትን ብንመለከት

የመጀመሪያ መመሪያው *ዕወቁ* የሚል ነው። ይህም ከአዕምሮ ጋር የተገናኘ መረዳትን፣ መገንዘብንና ዕርግጠኝነትን ያመለክታል።

ሁለተኛው ደግሞ *ቁጠሩ* የሚል ነው። ይህም የልብን ዝንባሌ ያመለክታል።

ሦስተኛውና በቁጥር 12 አታድርጉ ብሎ የጀመረውና አድርጉ የሚለውን ለማጽናት የተጠቀመበት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። *አቅርቡ* የሚለው ነው። አቅርቡ የሚለው ቃል ፈቃድን ያመለክታል።

## *6:13-23 አቅርቡ!*

ሐዋርያው ከፈቃድ ጋር የሚገናኘውን ሦስተኛ መመሪያውን አቅርቡ የሚለውን ለማጉላት ያስቀደመው አታቅርቡ የሚለውን ነው። ስለዚህ ይህ አካል ለማን መገኘትና ከማን ደግሞ መጥፋት እንዳለበት ያመለክታል።

## *6:13 ለኃጢአት አታቅርቡ*

1. የአመጻው ማስፈጸሚያ የጦር መሳሪያ አድርጋችሁ አታመቻቹለት። የትኛውንም የሰውነት ክፍላችሁን መሣሪያ አድርጎ እንዲጠቀም አትፍቀዱለት።

2. ለእግዚአብሔር አቅርቡ ሠሪው፣ ሲሠራው ዓላማ ያለው እግዚአብሔር ስለሆነ ለሠራበት ዓላማ እንዲያውለው ለእግዚአብሔር አቅርቡ!

<u>እንዴት?</u>

ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሸጋሩ ሰዎች ብልቶቻችንን የጽድቅ መሣሪያ በማድረግ

በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ሥራ ከሞት ወደ ሕይወት የተሸገርን ሰዎች አካላቶቻችን ለተሰሩበት የእግዚአብሔር ዓላማ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስችል አቅም አግኝተናል። ጽድቅ በላያችን ነግሷል። በላያችን የነገሰው በየትኛውም አካላችን ሊጠቀም የንጉሥነት መብት አለው!

## *6:14 ከጸጋ በታች . . . ከሕግ በታች*

ከጸጋ በታች ስትሆኑ ጸጋ ይገዛችኋል። ጸጋ ሲገዛችሁ ደግሞ ኃጢአት ሊገዛችሁ አይችልም።

ከሕግ በታች ስትሆኑ ሕግ ይገዛችኋል። ለምን?

ኃጢአት የሚታወቀው በሕግ ነው። ሲታወቅ ደግሞ ላወቁት መኖር ግድ ነው።
ለምሳሌ አንድ ሴት እርጉዝ መሆኗን ስታውቅ ለእርግዝናው አስፈላጊ ነገር ማድረግ እንደምትጀምር ዓይነት ማለት ነው።

## *6:15 . . . ከጸጋ በታች በመሆናችን ኃጢአት እንሥራን?*

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር ለዘመናችን የርካሽ ጸጋ ሰባኪዎች ቁርጥ ያለ መልስ ይሰጣል። ከጸጋ በታች መሆን ኃጢአት ለመሥራትና በእግዚአብሔር ምህረት ለመቀለድ ፈቃድ ማግኘት ማለት አይደለም። እንዲያውም ኃጢአትን እምቢ ለማለት አቅም ማግኘት እንጂ።

ከላይ እንዳነሳነው ከጸጋ በታች ስንሆን ገዢያችን ጸጋ እንጂ ኃጢአት አይሆንም። ጸጋ ሲገዛን ኃጢአት ዳግመኛ ላይገዛን ሥልጣኑን (ኃይሉን) ተገፈፈ።

## *6:16 - 17 ራሳችሁን እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ. ..*

ሐዋርያው በነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክተው በክርስቶስ አምነን ከመዳናችን በፊት እና ከዳንን በኋላ ያለውን ፍጹም የሆነ መሰጠትና በቁጥጥር ስር ሆኖ (መታዘዝን) ነው።

ማንኛውም ሰው ወደ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት የኃጢአት ባሪያ ነው:: የኃጢአት ባርነት ደግሞ ደመወዙ የዘላለም ሞት ነው::

ይኸው ሰው ወደ ክርስቶስ ሲመጣ ደግሞ ለኃጢአት ባሪያ እንደነበረ ሁሉ የጽድቅ ባሪያ ይሆናል:: ደመወዙ ደግሞ የዘላለም ሕይወት ነው::

አንድ በሕይወቱ እጅግ አስቸጋሪ የነበረ ሰውና በሚያዩት ሁሉ ዘንድ የክፉዎች አለቃ እስኪባል የደረሰ ሰው እንዲህ አለ « ቀድሞ ቀንደኛ ኃጢአተኛ እንደነበርሁ ሁሉ አሁን ዋና ቅዱስ መሆን አለብኝ » ጥሩ አስቧል አሁን ከቀድሞው ባርነት ነፃ ከወጣሁ:: ነፃ ላወጣኝ ለርሱ ራሴን በፈቃዴ እንደ ባሪያ አደርጋለሁ ማለቱ ነው::

ሐዋርያው በቁጥር 17 እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበትን ሃሳብ ግልጥ ያደርጋል ያም የምስጋናው ምክንያት ቀድሞ የኃጢአት ባሪያ የነበሩ ሰዎች የክርስቶስ የጸጋው ወንጌል ሲደርሳቸው ለሰሙት ትምህርት ራሳቸውን ሲሰጡና ጌታ የበላያቸው ሲሆን ማየቱ ነው::

ለተሰጣችሁለት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወንጌልን ከልብ በመስጠት መቀበላቸውን የሚያመለክት ነው::

**6:18 -20** *ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን:: ስለሰጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ:: ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኩስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ::የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና:: እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁና::*

*ከኃጢአት ነፃ የጽድቅ ባሪያ*

ይህንን ኋላ አድርጎ ለማየት አንድ ሰው በኃጢአት ውስጥ በነበረ ጊዜ ከጽድቅ ነፃ ነው (ጽድቅን ማድረግ አይጠበቅበትም አቅምም የለውም) ወደ ጌታ ሲመጣ ደግሞ ለጽድቅ ባሪያ ስለሚሆን ከኃጢአት ነፃ ነው። (አቅምም የለውም) (ገላ 5:1፤ ሮሜ 8:2፤ 1ቆሮ 7:21-22)

> *በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣ እንግዲህ ፀንታችሁ ቁሙ በባርነት ቀንበር አትያዙ (ገላ 5:1)።*
>
> *በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢያትና ከሞት ህግ አርነት አውጥቶኛልና (ሮሜ 8:2)።*
>
> *ባሪያ ሆነህ ተጠርተን እንደሆነ አይገድህም አርነት ልትወጣ ቢቻልህ ግን አርነት ተቀበል ባሪያ ሆኖ በጌታ የተጠራ የጌታ*
>
> *ነፃ ነውና እንዲሁም ነፃ ሆኖ የተጠራ የክርስቶስ ባሪያ ነው (1ኛ ቆሮ 7:21-22)።*

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ግልጽ እውነት ለማስረዳት ተቀባዮቹ ምን ያህል ደካማ እንደነበሩ ስለገባው ሁለት ቃላትን ተጠሟል።

በተፈጥሮ ደካሞች ስለሆናችሁ።ይህ ድካም መንፈሳዊ ሚስጢርን በብቃት ለመረዳት ያለመቻል ድካም ነው።

በሰው ቋንቋ (እንደ ሰው ልማድ) በሚገባችሁ ምሳሌያዊ አነጋገር ልንገራችሁ ማለቱ ነው። (የሐዋርያው ዋና ትኩረት መልዕክቱን እንዳይስቱበት በሚገባቸው መንገድ ማቅረብ ነው) ይህንን መደርደሪያ ካቀረበ በኋላ አሁን ሊያደርጉ የሚገባቸውን ማመልከት ይጀምራል። ብልቶቻችሁ ለኃጢአት አገልጋይ እንደነበሩ ዛሬ ደግሞ የጽድቅ አገልጋይ አድርጓቸው።

- ቀድሞ« ለአመፃ » ሕግን ለማስተላለፍ መሳሪያ ነበሩ።

• አሁን ደግሞ ለመቀደስ የጽድቅ ባሪያ አድርጋችሁ አቅርቡ ይህ እውነት የእግዚአብሔር አብ በጎ ፈቃድ ነው። (1ተሰ 4:4-8 ፤1ጴጥ 1:15 - 16 ) ስለዚህም ሰውነታችንን ለጌታ ስናቀርብለት በሕይወት ሊያመላልሰን ፤ የቅድስናውን ሥራ በእኛ ሊሰራ ይወዳል። በብልቶቻችንም ፈቃዱን ይፈጽማል። እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ገለጣ (1ቆሮ 1:30) እርሱ ቅድስናችን ሆነ።

*ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ አስቀድመን ደግሞ እንዳልናችሁና እንደ መሰከርንላችሁ ጌታ ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል። ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና። እንግዲህ የሚልጥ ሰውን የጣለ አይደለም መንፈስ ቅዱሱን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ (1ኛተሰ 4:4-8)።*

*ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁሉ ተብሎ እንደ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ (1ኛጴጥ 1:15-16)።*

*የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደተጻፈው ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ፅድቅን ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው (1ኛቆሮ 1:30)።*

ሐዋርያው በቁጥር 20 ላይ የቀድሞውን ደካማነት በብርቱ ቃል ገልጦ ያስቀምጠዋል። በክርስቶስ ደግሞ ያልተወለደ ሰው በፍጥረቱ ኃጢአተኛ ስለሆነ የጌታን ልብ አያውቅም። መልካምና ክፉውን ቢያውቅም ለመልካም ነገር ራሱን ለመስጠትና እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን መልካም ለማድረግ የማይችል፤እንዲያውም ክፉን ማድረግ የሚቀናው መሆኑን ያመለክታል።

ይህንንም በድፍረት የተናገረው አንድ ሰው ወደ ጌታ ሲመጣ ስለ ቀደመው ሕይወቱ የሚሰማውን ቁጭት

እንደ ምሳሌ በማንሳት ነው። ዝርዝሩን ቀጥለን እንመለከተዋለን።

### *6:21 እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ምን ፍሬ ነበራችሁ?*

አንድ ሰው ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ያደርግ የነበረውን ነገር እንደ ድል እንደ ስኬት ይቆጥረው ነበር። ወደ ጌታ ሲመጣ ግን ያ ድርጊት የሚያሳፍርና የሚያሳዝንም ይሆናል። ምክንያቱም የዛን ዘመን ሁሉ ድካማቸው ውጤቱ ባዶ ነው፤ ከሁሉ የከፋው ያለ ክርስቶስ የነበረው የክፋት ሩጫ ዘመን ፍሬው የዘላለም ሞት ነው።

### *6:22 የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆናችኋል . . . መጨረሻውም የዘለዘለም ሕይወት ነው*

የጌታ ባሮች ስንሆን ሕይወታችን በፍሬ ይሞላል። ፍሬውም የቅድስና ፍሬ ነው። ይህም የቅድስና ፍሬ የእግዚአብሔርን የመልካምነት ደረጃ የሚያሟላ ነው።

ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ በዮሐ 15 ላይ ስለ ወይን ግንዱና ቅርንጫፉ ተናግሯል። የወይኑ ግንድ ኢየሱስ ሲሆን ቅርንጫፎቹ ደግሞ በእርሱ ያመኑት ቅዱሳን ናቸው። በዚሁ ክፍል በእርሱ የሚኖሩ ፍሬ እንደሚኖራቸው ፍሬያቸውም የበዛና የተረፈ እንደሚሆን ተናግሯል። ፍሬያቸውን ለማብዛትም የሚያጠራቸው መሆኑ ተገልጧል

ግንዱ = ይሸከማል፣ የሚያስፈልገውን ሁሉ ይሰጣል
ቅርንጫፉ = በግንዱ ይኖራል፣ ተማምኖ ይቀመጣል፣
ራሱን ያቀርባል የግንዱ ሕይወት
ይገለጥበታል።

ከግንዱ ጋር ስንጣበቅ ስንተባበር ፍሬው
በሕይወታችን ይገለጣል።

= የዚህ ፍሬ ዘለቄታው ለዘላለም ነው። ይህም
የዘላለም ሕይወት ነው።

## 6:23 የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው

ሰው በሕይወት ዘመኑ ወዶ ፈቅዶ ራሱን ለሰጠለት ነገር ያገለግላል፣ ይሰራል፣ ይተጋል በመጨረሻም ደመወዙን ይቀበላል። አንድ ሰውም በኃጢአት ሲተጋ ከኖረ ደመወዙ መቀበሉ አይቀርም ደመወዙ ግን ሞት ነው።

በኃጢአት ለመኖር ለወሰኑ ከእግዚአብሔር የፍርድ ችሎት ደመወዝ ተመድቦላቸዋል ያም ደመወዝ ሞት ነው!

## የእግዚአብሔር ስጦታ ግን . . . የዘላለም ሕይወት ነው

ሐዋርያው በዚህ ክፍል የገለጠው እውነት እጅግ ብርቱና መሠረታዊ የክርስትና የሕይወት ደረጃ (እርከን የተገለጠበት) ነው። የኃጢአት ዋጋ ደመወዝ ተብሎ ሲጠቀስ የጻድቅ ዋጋ ግን ሳይሆን ከክርስቶስ ሞት የተነሳ እግዚአብሔር የሰጠን ስጦታ ነው። እኛ የምናደርገው ስጦታውን በእምነት መቀበል ነው።

ይህ ማለት ግን ከኛ ምንም የሚጠበቅ ነገር የለም ማለት አይደለም

- እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በሰጠን በዚህ የዘላለም ሕይወት ስጦታ ውስጥ እንድንኖር አዞናል። ይህም ሕይወት የቅድስና ሕይወት ነው።
- እኛ ራሳችንን ለእርሱ ባቀረብንበት መጠን እርሱ በእኛ መኖር ይጀምራል። በላያችን ገዢ እንዲሆን በፈቀድንበት መጠን ግዛቱ በሕይወታችን ተስፋፍቶ ሙሉ በሙሉ እኛን መቆጣጠሩን ፍሬው አብዝቶ ይገለጣል።

## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? ብለው የጳውሎስን የጽድቅ በእምነት ትምህርት ለማጣጣል ለተነሱ ተቃዋሚዎች «በፍጹም!» የሚል ቁርጥ ያለ መልስ የሰጠው ጳውሎስ በማጠቃለያው ጠንከር ያለና ምክንያት የሚያሳጣ ምላሽ ይሰጣል።

ምላሹም፡- የኃጢአት ባርነት ይሻለናል ካላችሁ ትችላላችሁ። ግን አንድ ነገር እወቁ ራሳችሁን ለሰጣችሁለት ነገር በምታሳዩት ትጋት በመጨረሻ ደመወዝ ይከፈላል። በጸጋ አሳብባችሁ ኃጢአትን የምታዘወትሩ ከሆነ ሞት ደመወዝ ሆኖ ይጠብቃችኋል።

በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በተገለጠው ጸጋ ስር ራሳችሁን አስገዝታችሁ ራሳችሁን የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ የምታቀርቡ ከሆነ ግን ዋጋችሁ ከሞት ነፃ በማውጣት ይጀምርና የበዛና የተረፈ የዘላለምን ሕይወት ታገኛላችሁ። የፀጋው ስጦታ መጨረሻ ውጤቱ የዘላለም ሕይወት ነውና።

# ምዕራፍ ሰባት
# ከሕግ መፋታት

የሰው ዘር ሁሉ በፍጥረቱ አንድ ወደ ጽንፈኝነት የሚጎትተው ነገር ያለ እስኪመስል ድረስ ብዙ ጊዜ ዶንፈኝነት ይጠናወተዋል። ክርስቲያኖችም ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ የተሰጠንን የነፃነት ሕይወት መኖር ያቃተን ከዚህ የተነሳ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፉ ሁለት ጽንፈኞችን ይሟገታል። የመጀመሪያዎቹ በምዕራፍ ስድስት የሞገተቻውና « በጸጋ » ስለዳንን እንደፈለገን መኖር እንችላለን የሚል አቋም ያላቸው ለኃጢአት ፈቃድ (አርነት) የሚሰጡት ናቸው። ሁለተኞቹ ደግሞ በዚህኛው ምዕራፍ ፊት ለፊት የሚጋፈጣቸው « ያለ ምንም ጥርጥር የዳንነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት በሕግ ስር መሆን አለብን (ማለትም የኛ ጥረት መጨመር አለበት) » የሚል የሕገኝነትን ጽንፍ ይዘው ያሉትን ነው።

በዚህ ምዕራፍ ሕግ የሚለው ቃል ሃያ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል። ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ ስድስት ክፉ ስራዎችን እንዴት ማቆም እንደምንችል ገልጦልናል። በዚህኛው ምዕራፍ ደግሞ « ለመጽደቅ ብላችሁ መልካም ሥራ መሥራትን አቁሙ፤ በበጎ ሥራችሁ ጨርሶ ልትቀደሱ አትችሉም! » ይለናል።

ይህ ምዕራፍ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ዘንድ ክርክር የተነሳበት ምዕራፍ ነው። ገና ከመነሻው የተጠቀሰው ምሳሌ በሕይወት ያለችው ሴቷ ሆና የሞተው ባሏ ሆኖ ሳለ ለሕግና ለኃጢአተኛው መጠቀሱን ዋቢ አድርገው የተለያየ ሃሳብ ያቀርባሉ። እኛ እንጂ ሕጉ አይሞትምና። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን በጽኑ ማሳሰብ የፈለገው ይህንኑ ነው።

እኛ ሴቲቱን የምንወክል ከሆነና ወንዱ ሕግን የሚወክል ከሆነ ነገሩ እንዲህ ነው ሴቲቱ ከሞተች መልሳ ባል ለማግባት ከሞት መነሳት አለባት ማለት ነው። ክርስቶስም በመስቀሉ ያደረገው ይህንን ነው።

- ሀ. በሞቱ ቀድሞ ለታሰርንበት ( ለሕግ ) እንድንሞት አደረገ
- ለ. በትንሣኤው ደግሞ ለአዲስ በመንፈስ ኑሮ በሕይወት እንድንኖር አደረገ።

ስለዚህ የሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌ ትክክለኛ፣ ሞትንና ትንሣኤን አጉልቶ የሚገልጥ ነው።

ይህንን አጠቃላይ የምዕራፉን የመግቢያ ሃሳብ ከያዝን በዝርዝር ቁጥር በቁጥር እንመለከተዋለን።

## *7:1 ወንድሞች ሆይ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን?*

*ወንድሞች*

*መልዕክቱ የተጻፈው በክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑት መሆኑን ያመለክታል። ( 6:13 )*

= ሕግን ለሚያውቁ

በዚህ ሃሳብ ሕግ የሚሠራው ለሚያውቁትና ሕያው ለሆኑ ሰዎች መሆኑን ያመለክታል:: ይህን ሲል የሕግ ጠበብቶችንና ሊቃውንቱን ማለቱ ብቻ ሳይሆን ሕጉን የሚያውቁትን ሁሉ ማለቱ ነው::

**ሥልጣን የሚኖረው (እንዲገዛው)**

ይህንን ገለፃ በደንብ ለመቃኘት ምድራዊ ንጉሥን ማየቱ በጣም ያስፈልጋል:: የንጉሥ ንጉሥነቱ የሚረጋገጠው የሚገዛው በሕይወት ያለ ሕዝብ ሲኖር ነው:: የሚገዛው ከሌለ ሥልጣኑን ተግባራዊ ለማድረግ መድረክም የለም:: እንዲሁ ሕግም ሥልጣኑን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገዛው ያስፈልገዋል:: በሕይወት ያለ ለሕግ ንቁ የሆነ ማለት ነው:: ሁሉ ሙት ከሆነ ግን ሕጉ ሥልጣን የለውም ወይም በሙታን ላይ አይሠራም::

ብሉይ ኪዳንን ስናጠና አንዳንዶች ከሕግ የአገዛዝ ሕብረት ለመውጣት ፈልገዋል ግን አልቻሉም ዘመኑ ገና ነበረና:: ( ኢዮ 3:1:16:18 ) ነገሩን ግን በውል የተረዱት ይመስላሉ ምክንያቱም ነፃ ለመውጣት የተመኙት «ሞትን» ነበረና ነው::

*ከዚያም በኋላ እዮብ አፉን ከፍቶ የተወለደበትን ቀን ረገመ (ኢዮብ 3:1)::*

*ወይም እንደ ተቀበረ ጭንጋፍ ፣ ብርሃንም እንዳላዩ ሕፃናት በሆንሁ ነበር (ኢዮብ 3:16)::*

*በዚያ ግዞተኞች በአንድነት ተዘልለው ተቀምጠዋል ያስጨናቂውን ድምጽ አይሰሙም (ኢዮብ 3:18)::*

## 7:2 *ያገባች ሴት*

ይህ ቃል አንድ ሰው ወደ ትዳር ሲመጣ የሚጠብቀውን ጠንከ
ካራና በቀላሉ ሊበጠስ የማይችል ቁርኝት የሚያሳይ ነው። የትዳር ኅብረት የሕይወት ዘመን ሁሉ ሕብረትነው። ይህም ህብረት አካላዊ ሕብረት ነው። ( ዘፍ 2:24 )

> *አዳምም አለ ይህች አጥንት ካጥንቴ ናት ስጋም ከስጋየ ናት እርሷ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ (ዘፍ 2:23-24)።*

### በህግ *ታስራለች*

ግንኙነቱ በውል የታሰረ መሆኑን ያመለክታል። ታስራለች የሚለው ቃል የታሰረችበት ክልተፈታ ምንም መንቀሳቀስ የማትችል መሆኑን ያሳያል። ይህንን ህግ ብትጥስ ቅጣት ይጠብቃታል። ስለዚህ ወደደችም ጠላችም በህጉ አገዛዝ ስር መኖር ይጠበቅባታል።

ባልዋ በህይወት እያለ ይህ ህግ በባልዋ ስር እንድትኖር ያስገድዳታል ሆኖም ያስገድዳታል እንጂ ለእርሱ ሁለንተናዋን ሰጥታ እንድትኖር የማድረግ ብቃት ግን የለውም። ኃይልም የለውም።

- ህግ ትዕዛዝ አለው። ትዕዛዙም ፍትህ የማስፈን ትዕዛዝ ነው። የትዳር ህግም ትዕዛዙ ሴት ለራሷ ልትኖር አይገባትም የሚል ነው።

## 7:3 *. . . ለሌላ ወንድ ብትሆን « አመንዝራ » ትባላለች*

ይህች ሴት እሷም በሕይወት እያለች ባሏም በሕይወት እያለ ሲጋብቻ ሕግ የታሰረች ስለሆነ በምንም ምክንያት ለሌላ ልትሆን አትችልም ብትሆን ግን « አመንዝራ » ትባላለች። ድርጊቷ ሕጋዊ አይደለምና በሕግ ተላላፊነት ትጠየቃለች (ዘኑ 5:20 )።

*ነገር ግን ባልሽን ትተህ ረክሰሽ እንደሆን ከባልሽም ሌላ ከወንድ ጋር ተኝተሽ እንደሆነ ካህኑም ሴቲቱን በመርገም መሃላ ያምላታል(ዘኁ 5:20)።*

## ባልዋ ሲሞት ከህጉ አርነት ወጥታለች

ባልዋ በሚሞትበት ጊዜ የሕግ ትስስሩ ይፈርሳል። ቀደም ብሎ ባለው ቁጥር እንደተመለከትነው ትዳር የሕይወት ዘመን ትስስር ነው። ትስስሩም በሕግ ነው። ደግሞም አካላዊ ነው። አካላዊው ትስስር በሞት ሲፈርስ ሕጉም ይፈርሳል። ምክንያቱም ሕግ በሙት ላይ ስለማይሰራ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ምሳሌ የተጠቀመው ስለ ፍቺ ለማውራት ሳይሆን በኛና በህግ መካከል የነበረው ግንኙነት እንዴት እንደፈረሰ ለማመልከት ነው። ስለዚህም በቀጣይ ቁጥሮች ዘርዘር ባለ ሁኔታ በክርስቶስ ሞት እኛም ከሞቱ ጋር በመተባበራችን ከህግ ጋር የነበረን ቁርኝት መፍረሱን በውብ ገለጻው ያመለክተናል።

***7:4 እንዲሁ ወንድሞቼ ሆይ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ስጋ ለሕግ ተገድላችኋል ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ እናንተ ለሌላው ከሙታን ለተነሳው ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ።***

### *በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ሞታችኋል*

ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ 6 : 4 - 5 ያነሳውን ከክርስቶስ ሞት ጋር መሞታችንን ያረጋገጥንበትን ማስረጃውን መሠረት በማድረግ ከሕግም ጋር የነበረን ትስስር በዚያው ሞት መሠረት መወገዱን ያመለክታል።

## ለምን?

### ከሙታን ለተነሳው ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ

ሐዋርያው በጋብቻ ምሳሌ ያመለከተውን እውነት በእርጋታ በዚህ ስፍራ ደግመን መመልከቱ አግባብነት ይኖረዋል፡፤ በምሳሌው መሰረት የሞተችው ሴቷ ናት ( እኛ ነን ) በህይወት ያለው ደግሞ ወንዱ ነው ( ሕጉ ነው ) የሞተች ሴት እንደ ገና ወደ ትዳር ለመምጣት ከሞት መነሳት አለባት። በእኛም ሕይወት የሆነው ይኸው ነው፡፤ ማለትም ከክርስቶስ ጋር ሞተን ብቻ አልቀረንም በትንሣዔው ደግሞ በመነሳት ለእርሱ ለመኖር ሕያዋን ሆነናል።

### ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ

ይህ ፍሬ በተሰጠን የዘላለም ህይወት በዚያ ለእግዚአብሔር መኖር ያለበት ፍሬ ነው ይህ ፍሬ እግዚአብሔር የሚከብርበት ፍሬ ነው (ኤፌ 2:5 ፤ ገላ 2:19 ፤ ሮሜ 6:4:22 ፤ ገላ 5:22 - 23 )።

> *ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን በፀጋ ድናችኋልና (ኤፌ 2:5)።*

> *እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀቱ ከእርሱ ጋር ተቀበርን (ሮሜ 6:4)።*

> *አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔር ተገዝታችሁ ፣ ልትቀደሱ ፍሬአችሁ በመጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው (ሮሜ 6:22)።*

> *የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም ፣ ትዕግስት፣ ቸርነት ፣ በጎነት ፣ እምነት ፣ የውሃት ፣ ራስን መግዛት ነው (ገላ 5:22-23)።*

***7:5 በስጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና***

*በኃጢአተኛው ተፈጥሮ ቁጥጥር ስር . . . ለሞት ፍሬ*

በቀድሞው አዳማዊና አሮጌው ተፈጥሮ ቁጥጥር ውስጥ ሆነን የምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ፍሬው የሞት እንደነበረ በማሳየት በአዲሱ ሕይወት እየታየብን ያለውን ፍሬ አጉልቶ ለመግለጥ ሐዋርያው ያነሳው እውነት ነው።

*በሥጋ ሳለን*

ይህ ቃል የሚያመለክተው ምድራዊውን አካል ሲሆን ይህም አካል ለክርስቶስ ያልተገዛውና በፍጥረታዊው ማንነት ብቻ የሚኖረውን የሚያመለክት ነው። ይህም ስጋ በውስጡ የኃጢአት መሻት ያለውና ፍሬውም የሞት የሆነ ነው።

**ይሠራ ነበር**

በህግ በኩል ኃጢአት መገለጡን ወይም መታወቁን የሚያመለክት መግለጫ ነው። (7:7)

***7:6 አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን ከሕግ ተፈትተናል ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።***

*አሁን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ስንሆን*

ይህኛው እውነት ከፀጋው በታች ያለንበትን የሕይወት አቋም የሚያመለክት ነው። ከፀጋው በታች ስንሆን ደግሞ ሁለት ነገሮች ተከስተዋል ለቀደመው መሞት ለአዲሱ መኖር።

**ለእርሱ ለታሰርንበት ስለሞትን**

ለእርሱ የሚለው ቃል ለሕግ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ልክ ሴትየዋ ከባልዋ በሞት እንደተለየች ማለት ነው።

• መታሰር የሚለው ቃል በመደበኛ እስር ቤት መታሰርን ሳይሆን በእግር ብረት መታሰርን የሚያሳይ የጠነከረ እውነት ነው ለዚህ ነገር ሞተናል ነው የሚለው

በአዲሱ መንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።

መገዛት የሚለው ቃል ባሪያ የሚኖርበትን የኑሮ ደረጃ ያመለክታል መፈታት የሚለው ደግሞ ነፃ የወጣው የሚኖርበትን የኑሮ ደረጃ ያመለክታል።

• በአሮጌው በፊደል ኑሮ መገዛት

ይህ መግለጫ ለሕግ በመገዛት ስር ያለ ሰው ያለበትን አሳዛኝ ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ሕጉ የሚፈለግበትን ይነግረዋል። የሚፈለግበትን ለማድረግ አቅም ግን አይሰጠውም። ይህ ማለት ግን ሕጉ መንፈሳዊ አይደለም ማለት አይደለም ነገር ግን በሰው ልብ ውስጥ ገብቶ የመሥራት ብቃት የለውም ማለት ነው።

• በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ መገዛት

ይህ አዲሱ ሰው ከጉድለት ሕይወት ወደ ሙልአት የመጣ ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ ሕያውነት የተሸገረ ነው። ሕያው ያደረገው ያ መንፈስ ብቃትን ይሰጠዋል። ስለዚህም በደስታ ያገለግላል።

ይህ አዲሱ ሰው የሚጠበቅበት ብልቶቹን በጠቅላላ ለሞተለትና ሕይወት ለሰጠው ጌታ ማስገዛት ነው። (6:19) በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ ጌታ በሁለንተናው የሚገዛ ይሆናል። መገዛቱም በደስታ የሆነ መገዛት ነው።

በብሉይ ኪዳን ሕጉ የተፃፈው በድንጋይ ላይ ነበር። በጸጋ ግን የጌታ ቃል የተፃፈው ሕያው በሆነው ልባችን ላይ ነው። ሕይወታችን አዲስ ሕይወት ነው አገልግሎታችንም ደግሞ በአዲስ መንፈስ ነው።

ሐዋርያው በህግና በጸጋ መከከል ያለውን ልዩነት ካስረዳ በኋላ ተቃዋሚዎቹ ሊያነሱ ለሚችሉት ማለትም « እንግዲያው ይህ ከሆነ ሕግ ምን ይረባል? ምክንያቱም ይህ አስተምህሮ ሕግ ኃጢአት ነው ወደሚል ይወስዳል » የሚል ነው:: ሐዋርያው ግን ከቁ 7 - 13 ባለው ክፍል « አይደለም » የሚል መሟገቻ ያቀርባል::

## *7:7 ሕግ ኃጢአት ነውን?*

*መልሱ አጭርና ግልጽ ነው « አይደለም »*

*ለምን?*

ኃጢአት መኖሩን ያወቅነው በሕግ ነው:: ሕግ ቆሻሻ የሆነውን የሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያሳይ መስታወት ነው:: በደለኞች መሆናችንን ያወቅነው በሕግ ስለሆነ ሕግ ኃጢአት ሊሆን አይችልም::

ሐዋርያው ይህንን እውነት ለማጉላት ከአስሩ ትእዛዛት ዘጠኙንና በውጫዊ የሚገለጡትን ትቶ 10ኛውና የውስጣዊ ማንነት መገለጫ የሆነውን « አትመኝ » የሚለውን መርጧል:: አትመኝ ባላለ ምኞትን አላውቅም ነበር (ዘዳ 27:17 ፤ ዘዳ 5:21)::

> *የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌዉንም ገረዱንም በሬዉንም አህያዉንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸዉንም አትመኝ (ዘፀ20:17)::*
>
> *የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ የባልንጀራህን ቤት እርሻዉንም ሎሌዉንም ገረዱንም በሬዉንም አህያዉንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸዉንም አትመኝ (ዘዳ5:21)::*

በማርቆስ 10:17 - 27 ያለው ሐብታም ወጣት የሰው ልጅ ያለውን « የአዳኝ ያለህ! » ጩኸት የሚያመለክት ጥሩ ምሳሌ ነው:: ሰውየው ውጫዊውን ሲደረድር ጌታ ደግሞ በልቡ ያለውን ስስት የሚገልጥ ትዕዛዝ ሰጠው « ሽጠህ አካፍል » አዝኖ ሄደ እንጂ ፈቃደኛ አልሆነም ምክንያቱም

ኃጢአቱን ተናዝዞ ስስታምነቱን አምኖ መዳን አልፈለገም የመረጠው ከጌታ መለየትን ነበር።

## 7:8 ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ

ሕግ የመጣው ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነበር። ኃጢአት ደግሞ ኃጢአተኛ መሆኑን ለማሳመንና የኃጢአት ባሪያ ለማድረግ ዕድሉን ተጠቀመበት። ብዙ ጊዜ ሰዎች « አታድርግ » የተባለውን ነገር ለማድረግ በጣም ይጓጓሉ። ምክንያቱም ለምን? የሚል መሻት ውስጣቸው ስለሚቀሰቀስ ነው።

ለምሳሌ አዲስ ቀለም በግድግዳ ላይ ቀብታችሁ « አትንኩት! » የሚል ብትለጥፉ ሰው እንደምንም ይነክዋል። ዓላማው ቀለም እንዳያበላሻችሁ ለማስጠንቀቅ ነበር በውስጣቸው ያለው ምኞት ግን ገፋፍቶ ተጎጂ ያደርጋቸዋል። ኃጢአትም ሕግ ለማትረፍ ያመጣውን ለጥፋት ይጠቀምበታል።

### ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና

በአንድ ተፈጥሮአዊ በሆነ ሰው ውስጥ የኃጢአት ሕያውነት የሚረጋገጠው ሰውየው ሙሉ በሙሉ ሲታዘዘው ነው። ሕግ ሲመጣና ሰውየውን ንቁ ሲያደርገው ኃጢአት መጣና ለኃጢአት የተሸጠ የስጋ እንደሆነ በማሳመን ኃጢአት ከማድረግ በስተቀር ምርጫ የሌለው አስመስሎበት በሰውየው ላይ ሕያው ሆነ። ሕግ ባይኖር ግን ዕውቀቱም መነሳሳቱም የለውም ስለዚህም ሕያው ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

## 7:9 ያለ ሕግ ( ሕጉ ሳይኖር ) ሕያው ነበርሁ

ሐዋርያው ጳውሎስ አሁን በደረሰበት የመረዳት እርከን ላይ ቆሞ የቀደመ ሕይወቱን ይገመግማል። በዚህም የተረዳው ነገር ቢኖር ሕግ ከመምጣቱ በፊት ሕያው እንደሆነ ይሰማው ነበር ሕጉ ሞት የሚጠብቀው መሆኑን ሲያውቅ ግን የተፈረደበት መሆኑን ተረዳ፡

### ትዕዛዝ ከመጣች በኋላ

ጳውሎስ ሕጉን በሚገባ ተረድቶ በሕጉ ያለው መልዕክት ከተረዳና ሙሉ ኃላፊነት ከወሰደ ከ13 ዓመቱ በኋላ ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ነው። ያን ጊዜ ሞት የተፈረደበት መሆኑን ሲረዳ የተሰማውን ስሜት ሲገልጽ « ሞትሁ » ብሎ ጠቀሰው።

***7:10 - 11 ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን ለሞት ሆና አገኘኋት ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታሎኛልና በእርስዋም ገድሎኛል።***

*ለሕይወት የታሰበችው ለሞት*

ሕግ ሲመጣ ለሕይወት እንዲሆን ታስቦ ነበር። ነገር ግን ኃጢአት ክፍተቱን አግኝቶ ከሰው ደካማ ማንነት የተነሳ የራሱን ስራ ስለሰራበትና ለኃጢአት መግቢያ መንገድ ተገኘ ። የኃጢአት ደመወዝ ደግሞ ሞት ነው ።

ሕግን ሙሉ በሙሉ መፈጸም የሚችል ሰው ቢገኝ የሚያገኘው ሕይወት ነው። ግን አልሆነም ( ዘሌ 18:5፤ ሕዝ 20:11፤ ሉቃ 10:26፣28) ሕጉ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን እኛ ደግሞ ኃጢአተኛ መሆናችንን ያመለክታል (2ኛቆሮ 3:9)።

> *የሚሰራቸው ሰው በእነርሱ በህይወት ይኖራልና ስርአቴንና ፍርዴን ጠብቁ(ዘሌ 18:5)።*
>
> *ሰው ቢያደርገው ኖሮ በህይወት የሚኖርበት ስርአቴንም ሰጠኋቸው ፍርዴንም አስታወቅኋቸው (ሕዝ 20:11)።*
>
> *እርሱም በህግ የተፃፈው ምንድነው? እንዴትስ ታነባለህ አለው.. .. እየሱስ እውነት መለስህ ይህን አድርግ በህይወትም ትኖራለህ አለው (ሉቃ 10:26፣28)።*
>
> *የኩነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና (2ኛ ቆሮ 3:9)።*

*7:12 ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት*

*ሕጉ. . . ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም*

- ቅዱስ የሆነው ከቅዱሱ እግዚአብሔር የወጣ ስለሆነ የመለኮቱ ባህርይ መገለጫ ስለሆነ ነው
- ጻድቅ የሆነው « ትክክል » ምንም እንከን የሌለበት በመሆኑ
- መልካም ለበጎ እንጂ ሰውን ለመጉዳት ያልተሰጠ መሆኑን ያመለክታል

ኃጢአት ምንም እንኳን ሕጉን ከተደነገገበት መልካም ዓላማ ውጪ ለማድረግ ለማይረባ ነገር ምክንያት አድርጎ ቢጠቀምበትም ሕጉ በራሱ ግን ንጹህ ( ቅዱስ ) ጻድቅና በጎ ነው።

*7:13 እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝ? አይደለም ነገር ግን ኃጢአት ሆነ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር።*

*ኃጢአት በኃጢአትነቱ ይታወቅ ዘንድ*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል የኃጢአትን ክፋት ለመግለጥና ለማስረዳት መግለጫ ቃል ያጣለት ይመስላል። ከዚህም የተነሳ ለበጎ የተገለጠውን ሕግ ለክፉ ነገሩ መግቢያ አድርጎ በመጠቀሙ የኃጢአት አስነዋሪ ባህርይ ተገለጠ።

ኃጢአት ከነ ሙሉ ክፋቱ ከልተገለጠልን ድካማችን፣ ስህተታችን በማለት ልናቀልለው እንሞክራለን። እኛ ምንም ብናቀልለውም የኃጢአት ደመወዙ ሞት መሆኑን አይቀይረውም። ስለዚህ የሚያዋጣው የኃጢአትን ክፋት መረዳት ሐዋርያው በዚህ ቁጥርም እየገለጸ ያለው ይህንኑ

ነው። ሕጉ ግን ለሕይወት የመጣ ለበጎም የታሰበ ነው። በማለት ለህጉ ያለውን ከበሬታ ከገለጠ በኋላ ሕጉ ግን በሰው ሕይወት ውስጥ ሊያደርግ የማይችላቸውን ነገሮች ከቁ 14 - 25 ባለው ክፍል ይገልጣል።

### *7:14 ሕጉ መንፈሳዊ እንደሆነ*

ይህ ገለፃ ሕጉ ምንም እንከን የማይገኝለትና ክቡር መንፈሳዊም መሆኑን ያመለክታል። ከእግዚአብሔር የመጣ በመሆኑም መለኮታዊ ነው የሕጉ መንፈሳዊነት በዘዳ 10:12 - 13 ተገልጧል።

ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ የተሰጠኝ እኔ ግን ለኃጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ።

ይህ የጳውሎስ ገለጣ ኃጢአትን አወቅሁት ቅዱሱ ሕግ ገለጠልኝ እኔ ግን የኃጢአትን ክፋት ለማሸነፍ አቅም አጣሁ ስለዚህ ባሪያው አደረገኝ ሕጉም ገለጠልኝ እንጂ አልለወጠኝም።

### *7:15 የማደርገውን አላውቅምና*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል በሕይወቱ ውስጥ ያለውን ትግል ለማሳየት የተጠቀመበት እንጂ የምሰራውን የማላውቅ ነኝ ብሎ ማለቱ አይደለም። ምክንያቱም ሲያስረዳ በጎ ለማድረግ ስፈልግ ያ አዳማዊ ባህርይ ደግሞ በኃጢአት እየተቀሰቀሰ ክፉ ያደርጋል። ማለትም የማልፈልገው ይሆናል

የዳነ ሰው ኃጢአትን የመጥላት ብቃት በእግዚአብሔር መንፈስ ተሰጥቶታል። ነገር ግን ክፉ ነገር ዝር አይልበትም የሚጠላው ነገር አይጎበኘውም ማለት አይደለም። ጳውሎስም ማሳየት የፈለገው ይህንኑ ነው።

## *7:16 ሕጉ በጎ እንደሆነ*

ሕጉ በጎ መሆኑን የሚገልጸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው እኔ ሕጉ የሚፈልገውን በጎ ነገር ማድረግ ከድካሜ የተነሳ ቢያቅተኝም ሕጉ በራሱ ግን በጎ ነው። በጎነቱም በኔ ደካማነት ተረጋግጧል ማለቱ ነው፡፡

## *7:17 ያን የማደርገው እኔ አይደለሁም*

ሐዋርያው እዚህ ጋ ኃጢአት ባገኘው በር ተጠቅሞ የቀሰቀሰውን አሮጌ ሰው ለማሳየት ይጥራል፡፡ በስጋው ብልቶቹን መሣሪያ አድርጎ የተጠቀመው ስጋ መሆኑን በጉልህ ያወጣዋል፡፡

## *7:18 በእኔ በስጋዬ . . . አውቃለሁ*

ስጋ ደካማ መሆኑንና በጎ ነገር ለማድረግ ብቃት የሌለው መሆኑን በአጽንኦት የገለጠበት ክፍል ነው፡፡ ፍላጎቱ አለ (ፍቃድ አለኝ) የመፈጸም አቅም ግን የለም፡፡

## *7:19 - 20 የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም። የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደረገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ፡፡*

በነዚህ ሁለት ቁጥሮች የተቀመጡት ሃሳቦች ከላይ ያሉት የተደገሙባቸው ሲሆን የስጋን ድካምና በጎ ለማድረግ ብቃት የሌለው መሆኑን አስመልክቶ ነው፡፡ የማይፈለገው የሚሰራበት ምክንያት ደግሞ ከተሰወረውና ከተቀሰቀሰው አዳማዊ ( ስጋዊ ) ማንነት የመነጨ መሆኑን ለማሳየት የገባ ነው፡፡

## 7:21 ሕግ አገኛለሁ

ይህ መረዳት ከልምምዱ ያገኘው መረዳት ነው:: ይህም ማለት ተፈጥሮአዊውን ሕግ ማለቱ ነው:: በጎ መሥራት እየፈለገ ክፋት ግን አብሮት መኖሩን ይረዳል::

## 7:22 በውስጡ ሰውነቱ

ውስጣዊ ማንነታችን እግዚአብሔርን የሚፈልግና ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የሚያስደስተው መሆኑን ያመለክታል ( 2ቆሮ 4:16፤ ኤፌ 3:16 ):: የዳነ ሰው በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል::

> *ስለዚህም አንታክትም፤ ነገር ግን የዉጭዉ ሰዉነታችን ቢጠፋ እንኳ የዉስጡ ሰዉነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል (2ቆሮ4:16)::*
>
> *በመንፈሱ በዉስጥ ሰዉነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን የሰጣችሁ (ኤፌ 3:16)::*

## 7:23 በብልቶቼ ለሚሰራው . . . ሌላ ሕግ

የውስጡ ሰውነቱ እግዚአብሔርን ሲፈልግ ይህንን የሚዋጋና በብልቶቹ እየሰራ ያለ ህግ መኖሩን ያመለክታል:: ከዚህም የተነሳ ብርቱ ሰልፍ ያለበት መሆኑን ያሳያል::

## 7:24 እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ!

እኔ - ይህ መግለጫ ሐዋርያው ከአማኞች ጋር የሚመሳሰል ባህርይ ያለው መሆኑን ያመለክታል::

ጎስቋላ ሰው - አቅም ያጣ በውጊያና በትግል ውስጥ ያለ ሰው፤ ማን ያድነኛል? - የረዳት ፈላጊ ድምጽ ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበረቱ አባቶች ከሚለዩበት ነገር አንዱ ድካማቸውን የበለጠ መረዳታቸው ነው። የጌታን ቅድስና ባዩት መጠን በሚፈለገው መጠን እንዳልኖሩ ይታያቸዋል። ስለዚህም ለተገለጠላቸው ለመዘርጋት የመጀመሪያ እርምጃቸው ያሉበትን መጠየፍን ወደሚቀጥለው እርከን የሚያሻግራቸውን የሚያዛልቅ ረዳት መፈለግ ነው (ፊሊ. 2:13) ።

*ስለ በጐ ፈቃድ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሰራ እግዚአብሔር ነውና (ፊሊ 2:13)።*

## *7:25 በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን!*

ክርስቲያኖች ጳውሎስን ጨምሮ ምንም እንኳን ደካሞችና በብዙ ትግል የሚያልፉ ቢሆንም በመጨረሻ ግን ድረስልኝ ያሉት ረዳት በሙሉ ብርታቱና ክብሩ ስለሚደርስላቸው የመጨረሻ ውጤታቸው የድል ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተገኘው ድልም የመጨረሻ ውጤቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማምጣት ነው።
( 1ቆሮ 15:57) ይህ ድል እንዲገለጥ ግን ራስን አካልን ሁሉ ለጌታ ማስገዛት ይገባል።

*የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው፤ የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነዉ ነገር ግን በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን (1ቆሮ15:57)።*

## የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ህግ ንጹህ ቅዱስና ፍጹም ነው። ሆኖም ህግን እንዲፈጽም የተሰጠው ሰው ግን ደካማና አቅመ ቢስ ጭራሹንም በውስጡ ለሚሰራውና ብልቶቹን መሣሪያ አድርጎ ከንጹሁ ከእግዚአብሔር ህግ ጋር የሚያጣላው አሮጌ ባህርይ ያለበት ስጋ ነው።

ስለዚህ ይህንን ህግ በራስ ጥረት ለመፈጸም መፍጨርጨር አደጋ አለው ይልቁንም የሚያዋጣው ብቃትና ጉልበት ወደሚሰጠው ወደ ኢየሱስ « የረዳት ያለህ » ብሎ መጮህ ነው።ይህ ሲሆን ምንም ደካማ ትባል ያሰብን ብንሆንም የጌታ ብርታት ያገኘንና መጨረሻችን ድል ይሆናል። ይህም ድል በሕይወታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚሆንን ነገር ያመጣልናል። እኛም ስለረዳን እናመሰግነዋለን። የሚያዩንም «እነርሱን የረዳ» ብለው ስሙን ያከብራሉ።

# ምዕራፍ ስምንት
# የልጅነት መንፈስ

ይህ ምዕራፍ በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘንድ «የነጻነት ምዕራፍ» ተብሎ ይታወቃል። ምክንያቱና ምንጩም በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን መሆኑ ገና ከመነሻው ተጠቅሷል። የዚህ ምዕራፍ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱም በምዕራፉ ውስጥ ለ19 ጊዜ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ጉዳይ ነው። ሐዋርያው በሌላ ቦታ ( 2ቆ 3:17) እንደጠቀሰውም « የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት አርነት አለ » ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል አራት መንፈሳዊ ነፃነቶችን ያመለክተናል።

1. ከኩነኔ ነፃ መሆን - 8:1-4
2. ለስጋ ከመሸነፍ ነፃ መውጣት 8:5-17
3. ከተስፋ መቁረጥ ነፃ መውጣት 8:18-30
4. ከፍርሃት ነፃ መውጣት 8:31-39

***8:1 እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። እንግዲህ. . . አሁን. . . ላሉት. . . ኩነኔ የለባቸውም***

ሐዋርያው እስካሁን ባነሳቸው ነጥቦች ላይ ቀጣይና መሰረት ያለው ነገር ማንሳት ሲፈልግ ለመሸጋገሪያ ከሚጠቀምባቸው ቃላት ይህ በብዙ ቦታ የምናገኘው ቃል ነው። እዚህ ቦታ ያስገባውም የሰው ልጅ ከአዳም ጀምሮ የደረሰበትን ውጣ ውረድ ከአለፈ በኋላ አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘውን ነፃነት ለመግለጽ ሲንደረደርበት እናገኘዋለን።

***አሁን***

ከቀድሞው አዳማዊ ባህርይ ተላቅቆ ያለ ክርስቲያን ያለበትን « የአሁን » የሕይወት እርከንና ደረጃ የሚያመለክት ነው ( ሮሜ 3:21፤ 5:9፤ 6:19፤ 7:6)።

***ላሉት***

በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተባበሩትን ያመለክታል (6:5)

**ኩነኔ የለባቸውም**

| |
|---|
| በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ከኃጢአት ነፃ መሆናቸውንና ለኃጢአትም ከተመደበው ፍርድ ነፃ መውጣታቸውን ያሳያል። ይህ ማለት ግን ከፍርድ (ከኩነኔ) ነፃ ሆንን ማለት እንጂ ኃጢአት ከሚያስከትለው ፍሬ ነጻ ነን ማለት አይደለም። |

*8:2 እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም:: በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና::*

*በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው*

ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ያለውን ህይወት የሆነውንና ህይወት የሚሰጠውን መንፈስ የሚያመለክት ነው:: ይህ መንፈስ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ አውጥቶናል:: ኢየሱስ ሕያው ከሆነ በእርሱ ያመኑትም ሕያዋን ይሆናሉ::

ከኃጢአትና ከሞት ነፃ የመውጣታችን ነገር የቅድስና ተከፋይ መሆናችንን ያመለክታል:: የሙሴ ሕግ መብት አለው ኃይል ግን የለውም:: የኃጢአት ህግ ደግሞ ኃይል አለው መብት ግን የለውም:: የክርስቶስ የህይወት መንፈስ ህግ ግን ኃይልም መብትም አለው:: እኛም በእርሱ ስናምን ይህንን ብቃት አገኘን::

ጌታ ሕያው ስለሆነ እኛም ሕያዋን ነን:: (ቆላ 1:27 ፤ ገላ 2:19) ስለዚህ ሕግ ዛሬ በኛ ላይ የይገባኛል ጥያቄ አያነሳም:: ለሕግ ሞተናል:: ሕያዋን የሆንነው ለሞተልን ብቻ ነው::

> *ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ሚስጥር ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ሊያስታውቅ ወደደ ሚስጥሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው (ቆላ 1:27)::*
>
> *እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበርና (ገላ 2:19)::*

## *8:3 ከስጋ የተነሳ ስለደከመ*

ሲጋችን በተፈጥሮ ማንነቱ ኃጢአትን የመቋቋም ጉልበት የለውም::

**ለሕግ ያልተቻለውን**

ሕግ ዓላማው እንዲፈጸምለት ይፈልጋል። ከፈጻሚው አቅም ማነስ የተነሳ ግን አልተፈጸመለትም።

**እግዚአብሔር የገዛ ልጁን**

ይህ ገለጣ ኢየሱስ ወልድ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል።

**በኃጢአተኛ ስጋ ምሳሌ**

ጌታ ኢየሱስ ስጋ ለብሷል። ሆኖም ያለ ኃጢአት የነበረ ፍጹም ሰው ነበር (ዮሐ 1:14 ዕብ 4:15፤ ዕብ 2:16)።

> *ቃልም ስጋ ሆነ ፀጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን (ዮሐ 1:14)።*
>
> *ከሐጢያት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም (ዕብ 4:15)።*
>
> *የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመልአክትን አይደለም (ዕብ 2:16)።*

**ኃጢአትን በስጋ ኮነነ**

ጌታ ኢየሱስ የሰውን ልጅ ኃጢአት ሁሉ ተሸከመ። እንዲያውም ኃጢአት ሆነ (2ቆሮ 5:21)

*እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው (2ኛቆሮ 5:21)።*

***8:4 እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ስጋ ፈቃድ በማንመላለስ የሕግ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ***

## እንደ መንፈስ ፈቃድ

በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኘነውን ከመንፈስ የሆነውን ሕያውነት ያመለክታል። በዚህ በአዲሱ ሕይወት የምንመላለሰው በኛ ጥረት ሳይሆን ሕይወትን ያገኘንበት ኢየሱስን ከሞት ባስነሳው ሕያው መንፈስ በእርሱ ፈቃድ ነው (1ቆሮ 1:30 ፤ ገላ 2:19 - 20)።

*እኔ ለእግዚአብሔር ህያው ሆኜ እኖር ዘንድ በህግ በኩል ለህግ ሞቼ ነበርና (ገላ 2:19)።*

*ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ህያው ሆኘ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁን በስጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው (ገላ 2:20)።*

በእኛ የሚኖረው የክርስቶስ መንፈስ፤ ይገዛናል ፤ ይቆጣጠረናል ፤ ይሰበናል ማለታችን ነው። በአሮጌው ሰውነት ኃጢአት ህያው ሆኖ ይኖር ዘንድ እንደነበረ አሁን ደግሞ በአዲሱ ሰውነት የህይወት መንፈስ በውስጣችን ይሠራል። ኃይልና ብቃትንም አግኝተናል ( ሮሜ 6:11 ፤ 7:5፤9)።

## የሕግ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ

ሕገኝነትን መቆሚያ ያደረጉ ሰዎች ሕግን በጥረታቸው ለመፈጸምና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት በስጋቸው ይሞክራሉ ግን ይወድቃሉ። የጌታ መንፈስ ግን በክርስቶስ የሆኑትን ቅዱሳን ይረዳል፣ ኃይል ይሰጣቸዋል ስለዚህ ሕጉ የመንፈስ ፍሬ ከሆነው « ፍቅር » የተነሳ ይፈጸማል። (ሮሜ 13:8 - 10)

ሐዋርያው ከዚህ በታች ማለትም ከቁ 5 - 17 ባለው ክፍል ሕይወትን በሦስት ደረጃዎች ከፍሎ ያስቀምጠውና አንባቢዎቹ በከፍተኛው ደረጃ መኖርን ምርጫቸው እንዲያደርጉ ያበረታታል።

## *8:5 እንደ ስጋ ፈቃድ የሚኖሩ. . . እንደ መንፈስ ፈቃድ*

እንደ ስጋ ፈቃድ = ያልዳነ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ የለውም ስለዚህም የሚኖረው እንደ ስጋ ፈቃድ ነው። ስለዚህ የልባቸው ምኞት ና ሃሳብ ሁሉ ስጋዊና ለስጋ ነው። አዕምሮውም ዘወትር የሚሞላው ለስጋ ደስታ በመሳብ ነው።

እንደ መንፈስ ፈቃድ = በክርስቶስ ኢየሱስ ያመነ ክርስቲያን ግን የጌታ መንፈስ በውስጡ አለ ስለዚህም በእርሱ ኃይል የመንፈስን ፍላጎት ለማሟላት ልቡም አካሉም ያንን የመንፈስ ቅዱስ ደስታ ለማሟላት የተሰጠ ይሆናል።

## *8:6 - 7 ስለ ስጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለመንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው ። ስለ ስጋ ማሰብ በእግዚአብሐር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና መገዛትም ተሰኖታል*

### *1/ ሞት . . . ሕይወት*

ስለ ስጋ ማሰብ . . . ሞት = በክርስቶስ ኢየሱስ የሌሉትና ሃሳባቸው ለስጋ የሆነው ሰዎች የሃሳባቸው ፍሬ የሞት ፍሬ ነው። ስለዚህም መንገዳቸውም የሞት መንገድ ነው።

የመንፈስን ነገር ማሰብ . . . ሕይወት = በክርስቶስ የዳኑ ሰዎች ሃሳባቸውና ዝንባሌያቸው በመንፈስ ሕግ ቁጥጥር ስር ስለሆነ ጉዞአቸው የሕይወት ነው። ፍሬያቸውም የዘላለም ሕይወት ነው። ይህ ማለት ግን ጨርሶ አይሳሳቱም ማለት አይደለም ነገር ግን የሚመልስ የሚያቀና ጉልበት የሚሰጥ ኃይል በውስጣቸው ስላለ ይበረታሉ በአዲስ ኃይል ይወጣሉ ለማለት ነው።

### *2/ ከእግዚአብሔር ጋር ጠብ . . . ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም*

የስጋን ፈቃድ የሚፈጽምና በስጋው ቁጥጥር ውስጥ ያለ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው። ሰላም በውስጡ የለም (ኢሳ 48:22)።

*ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሄር (ኢሳ 48:22)።*

በክርስቶስ ያመነ ሰው ግን ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለው (ሮሜ 5:1) ሙት የሆነው ማንነታችን በመንፈሱ ሕያው ሲሆን ሕያው ከሆነው ጌታ ጋር ሰላምን ይፈጥራል።

## *8:8 . . . እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችሉም*

*ይህ መግለጫ እንደ ስጋ ፈቃድ እየኖሩ ጌታን ለማስደሰት የሚጥሩትን ሕገኞች ቁርጣቸውን የሚነግር ነው።* በስጋ ፈቃድ ና ጎዳና ተመላልሶ ጌታን ደስ ማሰኘት አይሞከርም ከንቱ ድካም ብቻ ነው ይላቸዋል።

## *8:9 እናንተ ግን*

በክርስቶስ ያመኑትንና ሕይወት ያገኙትን የእግዚአብሔር ልጆች ያመለክታል።

**የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ቢኖር**

*ይህ መግለጫ* የክርስቶስ *መንፈስ* በእናንተ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ቢኖር የሚል ሳይሆን በስጋ ካሉት ጋር ለማወዳደርና ያገኘነውን አዲስ ህይወት ምንጩን ለማመልከት ነው።

**በስጋ አይደላችሁም**

ከኃጢአትና ከሞት ህግ ነፃ ወጥቶ ለእግዚአብሔር የተገዛውን ማንነትና ያለበትን እርከን የሚያመለክት ነው።

## **8:10** *ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ሲሆን*

የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆናችንንም ያመለክታል።

*ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው*

በኃጢአት ቁጥጥር ስር እያለ ኃጢአት የበላይ ነበር ፍሬውም ሞት ነበር ያለ እግዚአብሔር መንፈስ ዘወትርም ያለው ዕጣ ፈንታ ያው ነው።

በጌታ ከዳንን በኋላም ስጋ ከፍ ከፍ ሊል የሚችለው የኃጢአትን መቆናጠጫ ሲያገኝ ነው።

*መንፈሳችን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው*

ይህንን ሃሳብ በተመለከተ ምሁራን ሁለት ዓይነት አመለካከት አላቸው። ሁለቱንም እናቀርባቸዋለን።

ሀ. « መንፈሳችሁ » የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን መንፈስ ነው። ምክንያቱም ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሚለው ከዚህ ጋር የሚነፃፀር ነው ይላሉ።

ለ. ሌሎቹ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ። ማስረጃቸውም ሕያውነትን ያገኘነው ከክርስቶስ ጽድቅ የተነሳ ስለሆነና የቀድሞው የስጋ ባህርይ እንዳይሰለጥን የሚያደርገው ያው መንፈስ ስለሆነ። ከኛ የሆነውን ሳይሆን ወደ ክብር የመጣንበትን አሁንም በውስጣችን በመኖር የክርስቶስን ጽድቅ የሚገልጠውን የክብር መንፈስ የሳያል የሚል ነው።

## *8:11 ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው*

ይህ ቃል መንፈስ ቅዱስ በስላሴ እውነት መሠረት ከአብ ጋር አንድ መሆኑንና የክርስቶስ መነሳትም በመንፈስ ቅዱስ እንደተደረገ ያመለክታል።

*ለሚሞተው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጠዋል።*

ይኸው ህይወት ሰጪ መንፈስ ለሚሞተው ሰውነታችን ህይወትን ይሰጣል። ስለዚህ የስጋ ኃይሉ ገገርነቱ ተቆጣጣሪነቱ ወደ ሞት የመንዳት አቅሙ ተሰብሮአል ማለት ነው።

## *8:12 ለስጋ አይደለም*

ስጋ እኛን ለመግዛትና ለማስተዳደር የከፈለው ዋጋ የለም ስለዚህ ለእርሱ ልንኖርለት አይገባም:: ሕያዋን የሆንነውም ለስጋ አርነት ለመስጠት አይደለም::

### ግዴታ አለብን

ይህ ግዴታ ለስጋ የመኖር ሳይሆን ህይወት ላገኘንበት ለእግዚአብሔር መንፈስ ለመኖር ነው::

## *8:13 እንደ ስጋ ፈቃድ ብትኖሩ*

ተመልሳችሁ ለኃጢአትና ለሞት ህግ ተገዢ ብትሆኑ፣ የድሮውን ሰው ብትመስሉ የሚጠብቃችሁ ሞት ነው:: በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠረው አዲሱ ሰው በተቀበለው የህይወት መንፈስ እንደሚገባ ባይመላለስ የሞትን ፍሬ ሊያፈራ ይችላል የጌታን ክብርም መግለጥ አይችልም:: ይህም ከፍተኛው ሞት ነው (ኤፌ 5:14 ፣1ጢ.ሞ 5:6)::

> *አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ ክርስቶስም ያበራልሃል ይላል (ኤፌ 5:14)::*
>
> *ሴትና ቀንም በጸምና በፀሎትም ፀንታ ትኖራለች ቅምጥሊቱ ግን በሕይወቷ ሳለች የሞተች ናት (1ኛጢ.ሞ 5:6)::*

### በመንፈስ የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ

ይህ ቃል የመንፈስ ቅዱስን ድርሻና እኛ ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን በመስጠት የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ያመለክታል::

መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ያገኘነውን ማንነታችንን ሲገልጽልን እኛ ደግሞ ለዚህ ለተገለጠው ማንነት ራሳችንን በመስጠት ክርስቶስ የበላይ እንደሆነ እንዲገዛና እንዲቆጣጠር እንፈቅዳለን::

በህይወት ትኖራላችሁ

የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን እንዲሰራ ስንፈቅድ ይህንን የንግስና ህይወት መኖር፣ በክብር መመላለስ እንችላለን።

ከአብ በጎ ፈቃድ የተነሳና በክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም መሰጠት ይህንን ህይወት አግኝተናል። ስለዚህ ስጋ ሞትን በውስጣችን ሊያነግስ አቅሙን አጥቷል የክርስቶስ መንፈስ ህይወትን ሰጥቶናል። የስጋ ብልቶቻችንን ለጌታ ስናቀርብ ጌታ ይከብርባቸዋል። ስለዚህ ያንን ህይወት በሙላት መኖር እንጀምራለን።

## *8:14 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ*

ይህ ሃሳብ አቅጣጫ ማግኘትን ፣ ወደሚያዘልቅ ጎዳናና መንገድ መሳብን፤ ምኞት ወደ ፈቀደው ሳይሆን እግዚአብሔር ወደ ፈቀደው ለመራመድ ብቃት ማግኘትን ፣ ጠቋሚ ፣ ከፊት ቀዳሚ ማግኘትን ያመለክታል። ቀድሞ በአሮጌው ሰውነት በነበርን ዘመን ህይወታችንና አቅጣጫችንን የሚመራው የኃጢአትና የሞት ህግ ነበር ክርስቶስ ሊመጣና ብርሃንን ሊያበራልን ግን አቅጣጫችን ተለወጠ የሕይወት መንገድም ተገለጠልን ወደ ህይወት የሚመራ አገኘን።

*የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው*

ወደ ጌታ ስንመጣ በመንፈስ የመመራትን በረከት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን መብት አግኝተናል። ቤተሰብ ሆነናል። የጌታ መንፈስ የጌታ ሲያደርገን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደ አደገና ሙሉ ሥልጣን እንዳለው ልጅ መመላለስን የህይወታችን ዘይቤ አደረገው ልጆች ሆንን። እርሱም አባታችን ሆነ።

## *8:15 አባ - አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ።*

ይህ ገለጣ ልጅ አባቱን አባ. . . አባባ . . . አባብዬ ብሎ የሚጠራበትን የሚወደድ፣ የሚናፈቅ፣ ጥልቅ ቀርኝትንና ትስስርን የሚገልጥ ነው።

*የልጅነት መንፈስ*

ይህ ቃል እንደ እግዚአብሔር ልጆች በሙላት ለመኖር የምንችልበትን ፣ ብቃት ያገኘንበትን የሕይወት እርከናችን ከፍተኛውን ደረጃ የያዘበትን እውነት የሚገልጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ ልባችንን ወደ አብ ክብር በመሳብ አባ - አባት እያለም በመጮህ ይህንን ሕይወት መኖር እንድንችል በውስጣችን ይቃትታል። ስለዚህ ዓይኖቻችን በእርሱ ላይ ያርፋሉ ልባችንም ይቃጠልብናል፤ የቅድስና ህይወት ለመምራትም ብቃትን እናገኛለን (ኤፌ. 1:11፣14 ፤ 4:30 ፤ 2ቆሮ 3:18፤ ቆላ 3:3)።

> *እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሰራ እንደ እርሱ አሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስት ተቀበልን (ኤፌ 1:11)።*
>
> *በመንፈስ ቅዱስ ታትማችሁ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው ፤ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል (ኤፌ 1:14)።*
>
> *ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱስን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ (ኤፌ 4:30)።*
>
> *እኛ ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስታወት እያበለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን (2ኛቆሮ 3:18)።*
>
> *ሞታችኋልና ፤ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና (ቆላ 3:3)።*

## ለፍርሃት የባርነት መንፈስ አልተቀበላችሁም

የተቀበልነው መንፈስ እንደ ገና የፍርሃት ባሪያ የሚያደርገን ሳይሆን እንደ ልጅ ያለ ፍርሃት ግን በማክበርና በፍቅር መኖር የምንችልበትን ጉልበት የሰጠን ነው።

## *8:16 ይመሰክራል*

የእግዚአብሔር መንፈስ በመንፈሳችን ውስጥ ይህንን ልጅነታችንን ያረጋግጥልናል ይህም በቃል ኪዳን የጸናና ፈጽሞ የማይለወጥ መሆኑን ያጸናልናል ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት የምናይበት እውነት ነው።

## *8:17 ልጆች ወራሾች*

ልጅ ከሚታወቅበት አንዱ የአባቱን ሀብት ሙሉ በሙሉ መውረሱ ነው የጌታም ልጆች ስንሆን ይህንኑ አግኝተናል የእርሱ የሆነውን በሙላት ወርሰናል።

### *አብሮ ለመክበር አብሮ መከራ መቀበል*

ይህ መግለጫ ስለ ክርስቶስ ብለን መከራ መቀበልን ያመለክታል። ክርስቶስ በብዙ መከራ አልፎ በክብር ላይ ክብር እንደተጨመረለት ሁሉ እኛም ወደዚህ ክብር ለመግባትና የክብሩ ተካፋይ ለመሆን የመከራው ተካፋይ መሆን ይጠበቅብናል። ይህ ግን ክብሩን ለማግኘት መከራ ቅድመ ሁኔታ ነው የሚል እንዳልሆነ በውል ማጤን ይገባል። ይልቁኑ በምድር ህይወታችን ልዩ ልዩ ፈተና ቢገጥምም ወደፊት ግን ክብር የሚጠብቀን ስለሆነ የክብሩ ወራሽ መሆናችንን በማሰብ እንድንጸና የሚያበረታን ነው (ዮሐ 17:22፣3 ፤ 14:20፤ ኤፌ 2:18 )። ሐዋርያው ይህንን የሚያበረታ ቃል ለማጽናትና ተስፋ መቁረጥን ለማስወገድ ወደፊት ከሚመጣው ክብር ጋር በማነጻጸር መግለጫውን ያቀርባል።

> *እኛ አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን ፣ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ ፣ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ። እንዲሁም አለም አንተ እንደላከኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደወደድኋቸው ያውቃል (ዩሐ 17:22-23)።*

> *እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታዉቃላችሁ (ዩሐ 14:20)።*

> *በእርሱ ስራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና (ኤፌ2:18)።*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል ውስጥ አሁን ያለውን መከራና ወደፊት የሚመጣውን ክብር በንጽጽር የሚያቀርበው ሴት ልትወልድ ስትል ከሚይዛት ምጥ ጋር ነው፡፡ ምጥ ስቃይ አለው ያስጮሃል ሆኖም ግን ለከንቱ ሳይሆን የሚታቀፍ ልጅ ለማምጣት ነው፡፡

እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር በትልቅ ክብር፣ ለደስታና ለዕረፍት ነበር፡፡ የአዳም ኃጢአት ግን ይህንን ለውጦ ፍጥረት ሁሉ መቃተት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡ ይህ መቃተት ግን ፍሬ ያለውና ዕረፍትና ሰላም የሞላበትን ክብርና ዕረፍት የሚያመጣ ነው፡፡

## 8:18 ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን

ይገለጥ ዘንድ ብሎ ሐዋርያው ያስቀመጠው ሃሳብ በጌታ ዘንድ ተጠብቆልን ያለውን የልጅነት ክብርና ርስት ነው፡፡ ጌታ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በፈሰሰ ጊዜ ይህንን የልጅነት ክብር በትንሹ አሁን ማጣጣም ጀምረናል፡፡ ሆኖም ሙላቱ ገና ወደፊት ይገለጣል፡፡

ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን የሚለው ደግሞ የክብሩ ክብደት ከመከራው ክብደት ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚልቅ መሆኑን ለማሳየት ተጠቅሞበታል፡፡ ክብሩ የላቀ ነው፡፡ ለኛ ግን ወደፊት ይገለጣል፡፡

### የአሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ

<u>የአ</u>ሁኑ ዘመን የሚለው ቃል ከክርስቶስ ትንሣኤ አንስቶ እስከ ንጥቀት ጊዜ ድረስ ያለውን « የጸጋ ዘመን » ያመለክታል፡፡

ምንም <u>እንዳይደለ</u> ከቁጥር የሚገባ በጣም የቀለለ እንደሆነ ይገልጣል (2ቆሮ 4:17)፡፡

*የማይታየዉን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ፣ ቀላል የሆነ የጊዜ መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናል የሚታየው የጊዜው ነውና ፣ የማይታየው ግን የዘላለም ነው (2ኛቆሮ 4:17)።*

<u>እስባለሁ</u> ሲል ሐዋርያው ከእግዚአብሔር በተሰጠው ችሎታ ነገሩን አውቆ ተረድቶ፣ አመዛዝኖ መጨረሻ የደረሰበትን ድምዳሜና በውስጡ ስለጉዳዩ ያለውን ዕውቀት ያሳያል።

## *8:19 ፍጥረት ሁሉ*

ይህ ቃል የሰውን ዘር ሳይጨምር ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ፍጥረታት ሁሉ የሚያከትት ነው።

### *የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቃሉ*

በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑና የእግዚአብሔር ልጅነት መብት የተቀበሉት ሁሉ ሊቀበሉ ያለውን የልጅነት ክብር ሙላትና ኢየሱስን የመምሰልን ህይወት ድምቀት ለማየት የሚመኙ መሆኑን ይገልጣል ( 1ዮሐ 3:2 ) ።

> *ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እፀልያለሁ (1ኛ ዮሐ 3:2)።*

## *8:20 ለከንቱነት ተገዝቷል*

ይህ ቃል ፍጥረት ለባዶነት ፣ ለፍሬቢስነት ፣ ህይወት አልባ ለሆነ ኑሮ የተዳረገ መሆኑን ፣ የፍጥረት ዓላማ መዛባቱን ጥፋት መከሰቱንና ማርጀቱን ያሳያል። ከአዳም ኃጢአት ጀምሮ ምድር ለከንቱነት እንድትገዛ እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጥቷል። ሆኖም ግን ተስፋ ደግሞ አለ።

## *8:21 ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥቶ*

ጌታ ምድሩን የሚያድስና ከባርነት ነፃ የሚያወጣ መሆኑን ያመለክታል ( ኢሳ 11:6 ፤ 35:1-2 ፤ ቆላ 1:20 )።

*ተከላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል ጥጃና የአንበሳ ደቦል ፍሪዳም በአንድነት ያርፋሉ ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል (ኢሳ 11:16)::*

*በምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል በረሀውም ሀሴት ያደርጋል እንደ ፅጌሬዳም ያብባል:: እጅግ ያብባል በደስታና በዝማሬ ሀሴትን ያደርጋል የሊባኖስ ክብር የቀርሜሎስና የሳሮን ግርማ ይሰጠዋል የእግዚአብሔርንም ክብር የአምላካችንንም ግርማ ያያሉ (ኢሳ 35:1-2)::*

*እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና (ቆላ 1:20)::*

## *8:22 አብሮ በመቃተትና በምጥ*

ሴት ልጅ የሚወደድ ሕፃን ከመታቀፏ በፊት በብርቱ ምጥ ውስጥ ታልፋለች:: ሆኖም ያ ሁሉ መከራ አልፎ ልጁ ሲወለድ መከራውና ምጡም ይረሳል::

## 8:23 የመንፈስ በኩራት

ይህ ቃል በእግዚአብሔር የልጅነት መንፈስ በጥቂቱ የቀመስነውን የመንግሥተ ሰማያት ጣዕም ያመለክታል:: በብሉይ ዘመን የመከሩ ዋና ፍሬ ከመበላቱና ከመሰብሰቡ ቀድሞ በኩራቱ ይወሰድና ይቀመሳል ያም የሚያመለክተው ብዙ መከር ወደፊት መኖሩን ነው:: እንዲሁ ደግሞ እኛም ገና በሙላቱ የሚገለጠውን ክብር እዚህ በቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት በጥቂቱ የቀመስን መሆኑን ያሳያል::

## *8:24 በተስፋ ድነናል*

ይህ መግለጫ ቀድሞ የነበረውንና አሁንም ያለውን የህይወት ልምምድ የሚገልጥ ነው:: ( 1ቆሮ 1:18 ፤ ሮሜ 5:8 ) ሆኖም ግን ሙላቱ ገና በተስፋ የምንጠብቀው ነው:: የሚታየውን ተስፋ የሚያደርግ ሰው የለምና:: ሆኖም ጥቂት ምልክት አይቶ ገና የተሻለው ሙሉው እንደሚጠብቀው ሲነገር በተስፋ አሁን ያለበትን ምጥ

እየረሳ ይጠብቃል:: የበለጠ ለመረዳት በተመሳሳይ በምዕራፍ 1:16 ያለውን ይመልከቱ::

*የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና (1ኛቆሮ 1:18)::*

*ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔርም ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳናል (ሮሜ 5:8)::*

## *8:25 በትዕግሥት መጠባበቅ*

ይህ ቃል የሚመጣውን ክብር እጅን አጣምሮ መጠበቅን ነው የሚል ፍቺ ያዘለ ሳይሆን በጦር ሜዳ ውስጥ ያለ ወታደር አሸናፊነቱንና የሚጠብቀውን ሽልማት እያሰበ ብርቱ ጦርነትን በመዋጋት እስከ ድሉ ቀን ድረስ መጽናት እንዳለበት የሚያመለክት ነው::

## *8:26 መንፈስ ድካማችንን ያግዛል*

በምንኖርበት ዘመን የሚገጥመንን ምጥና መቃተት በራሳችን አቅም ልንወጣው አንችልም ብቃትም የለንም:: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግን ያግዘናል:: በእርሱም ዘወትር ብርታትን ፣ ጥበብንና ኃይልን እናገኛለን:: በዚህ ክፍል ድካም የሚለው ቃል ኃጢአትን አያመለክትም ሆኖም ጉልበትና ማስተዋል ማጣትን ያመለክታል::

መንፈስ ቅዱስ የሚያግዝበት ሌላው መንገድ ጸሎት ነው:: በመከራ ውስጥ ለማለፍ ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት የጌታን ሃሳብ ለማግኘት ይረዳናል:: ይህንንም የሚፈጽመው በቃላት ከመግለጥ ያለፈ ፣ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን በመረዳት የሆነ ብርቱ ጩኸት በመጮህ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ በአብ ፊት ይጸልያል:: በገዛ ራሱ ደም አማካይነት በአብ ፊት ይታያል ( ይማልዳል ) መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የቅድስናን ኑሮ

መኖር እንድንችል በእኛ ውስጥ ሆኖ ይቃትታል ( ዕብ 7:25 ፤ 9:24 )።

*ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የመሚጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል (ዕብ 7:25)።*

*ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች ፣ የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባምና ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ (ዕብ 9:24)።*

### 8:27 ልብንም የሚመረምረው . . . ያውቃል

ይህ መግለጫ በእግዚአብሔር አብና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ቅርብና አንድነት የሚያመለክት ነው። መንፈስ የአብን ሃሳብ ስለሚያውቅ ጮክ ብሎ በቃላት መንገር አያስፈልገውም ግን ይቃትታል (1ኛ ቆሮ 2:10-11)።

### እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ . . . ይማልዳል

የመንፈስ ቅዱስ መቃተት እኛ የተመኘነውን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የማስጸደቅ መቃተት አይደለም። ሆኖም ግን ግራና ቀኛችንን የማናውቀውን እኛን በማገዝ የሚበጀንንና የእግዚአብሔር መልካምነት የሚገለጥበትን በጎ ነገር እንድንቀበል ይቃትትልናል።

### 8:28 ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን

በህይወታችን የሚሆን ነገር ሁሉ በራሱ መልካምነት የለውም። ሆኖም ግን ጌታ ያንን ነገር የመልካምነቱ መገለጫ ሲያደርገው በጎ ነገር ይወጣዋል። እግዚአብሔር መልካምነቱን በህይወታችን ለመግለጥ እኛ የምናልፍበትን የትኛውንም ሁኔታ ይጠቀምበታል። ውድቀታችን ቢሆን ስኬታችን የጌታን እጅ የምናይባቸው ክቡር መንገዶች ናቸው።

## *8:29 - 30 ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ*

ጌታን ስንከተል በክርስቶስ ሞትና ትንሣዔ ስለተባበርን ወንድሞቹ ሆነናል:: በመስቀሉ ሥራ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን ማለት ነው:: በውስጣችን የሚሰራውም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ክርስቶስን እንድንመስል የሚያደርግ ነው::

### *አስቀድሞ ያወቃቸውን አስቀድሞ ወስኗል*

ይህ መግለጫ ደህንነት መጀመሪያውና መጨረሻው በእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን የሚያመለክት ቃል ነው::

> እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ እርሱ ይጨርሰዋል:: በዚህም መሠረት በደህንነት ሥራ ውስጥ የእኛ ፈቃደኝነት አስፈላጊ ቢሆንም ነገር ግን ይህ የደህንነት ሥራ በኛ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ምክንያቱም የእኛ ፈቃድ ፍጹምነት የጎደለው ስለሆነ ነው:: ፍቃዳችን ፍጹም የማይሆንበት ዋናው ምክንያት ሁሉን ነገር በሙልአት ለመረዳት አቅም ስለሌለንና ዕውቀቱ ስለሚያንሰን ነው:: እግዚአብሔር አብ ግን ሁሉን ስለሚያውቅ ፍቃዱም ፍጹምና ምሉዕ ነው ውሳኔውም ያልተዛባና በዚህ ፍጹም ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነው::

### *የጠራቸውን*

ይህ ቃል እግዚአብሔር አብ በልጁ በኩል « ናችሁ » ብሎ የሰየመውን ስያሜ የሚያመለክት ቃል ነው:: እግዚአብሔር በቀደመው ዕውቀቱ በእርሱም ዘንድ ያለ እንዳች እንከን ተሠርቶ ባለቀው ሥራ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተቀባይነትን ያገኙና የተጠሩ መሆናቸውን ያመለክታል:: በ1ኛ ቆሮ1:30-31 «የሆናችሁ» የሚለው ነው::

> *ነገር ግን የሚመካ በእግዚአብሄር ይመካ ተብሎ እንደተጻፈ ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሄር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስና ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው(1ኛ ቆሮ1:30-31)::*

*አጸደቃቸው*

በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣዔ የተባበሩ ፣ አዳኝነቱን ያመኑና የተቀበሉ በእግዚአብሔር ፊት ፃድቃን ተብለው መቆጠራቸውን የሚገልጽ የውሳኔ ቃል ነው ( ሮሜ 4:24-25)።

> *ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው (ሮሜ 4:24-25)።*

*አከበራቸው*

ይህ ክብር በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ተሰውሮ ያለ በእኛ ህይወት በጌታ ጸጋ የሚገለጥ ነው። ይህ ክብር በአዳም ምክንያት እንዳጣነው ክብር ሳይሆን የላቀ ነው።

በፊተኛው አዳም ከእግዚአብሔር ክብር ጎደልን ( 3:23 ) የኋለኛው አዳም ግን ከከፈለው መስዋዕትነት የተነሳ ሊነገር የማይቻለውን ክብር ተካፋዮች ሆንን። ይህም የእግዚአብሔር አብ የጸጋው አሠራር ነው እንጂ ከእኛ የሆነ አይደለም(ቆላ 3:3-4 ፤2:10-14፤ ኤፌ 1:7፤ 2:6-7 )።

> *ሞታችኋልና ፣ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ፣ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ (ቆላ 3:3-4)።*

> *በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል (ቆላ 2:10-14)።*

> *በውድ ልጁም ፣ እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት (ኤፌ1:7)።*

> *በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የፀጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ፣ ከእርሱ ጋር አስነሳን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን (ኤፌ 2:6-7)።*

### *8:31 እንግዲህ ምን እንላለን?*

አዲሱ መደበኛ ትርጉም « ምን እንመልሳለን? » ይለዋል። ይህ አገባብ በአብዛኛው በተደረገለት አስገራሚ ሥራ ተገርሞ የሚመልሰውን ያጣ ሰው ንግግር ይመስላል። ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር አብ በገዛ ፈቃዱ ያከናወነው ነገር ሁሉ ለበጎ መሆኑንና የመጨረሻ ዓላማውም በክርስቶስ መክበር የሆነውን የሚያሳርፍን እንከን የለሽ አሠራር ያደንቃል።

### *እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?*

ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ፣ ደግሞም ሙታን ሆነን ሳለን ይቅር ብሎ ካዳነን እና ወደ ክብሩ እንድንደርስና በክብሩም እንድንኖር ከፈቀደ ምን ይቀርብናል? ማንስ ከዚህ ሊያጎድለን ይችላል? ( 5:10 ፤ 11:8:28 ) ይህ ማለት ግን ልዩ ልዩ ፈተናና ውጊያ አይኖርብንም ማለት አይደለም። ይህን የክብር ስፍራ የሰጠንና የክብሩንም ህይወት እንድንኖር ያስቻለን እግዚአብሔር ከኛ ጋር ስላለ ምንም ነገር አያሸንፈንም ማለት ነው።

### *8:32 እንዴት እንዲያው አይሰጠንም*

ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት በዓለም ያለው ሁሉ ለእርሱ ተሰጠ። እኛ ደግሞ የክርስቶስ በመሆናችን ሁሉ የተገባው ጌታ በእርሱ ውስጥ ስላለን ለኛ ሁሉን ሰጠን። ከመስቀሉ የተገኘውን የልጅነት ስልጣን ሰጠን። ልጅም ስለሆንን ወራሾች ደግሞ ነን። ይህም ደግሞ እንዲያው የተሰጠንና እግዚአብሔር በጸጋው ያደረገው ሥራ ነው።

በዓለም ያለውን መከራና ሞት ኢየሱስ አሸንፎታል። ከዚህም የተነሳ ሁሉን ወርሷል። ኃጢአትና ሕግም ኃይላቸው ተገፈፈ። ይህንንም እግዚአብሔር በልጁ በኩል ስለ እኛ አደረገው።

ታድያ ይህንን ሁሉ ድንቅ ስጦታ የሰጠ ጌታ እንዴት የሚያስፈልገንን ነገር ይከለክለናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ ሲያስተምር « እግዚአብሔር ለወፎች እንኳን የሚያስብ አምላክ ነው፡፡ እንዴት ለእናንተ አያስብም? » በማለት በኑሮ ጉዳይ ለሚጨነቁ ብርቱ ትምህርት ሰጥቷል፡፡ ሐዋርያው ደግሞ የተሰጠንንና ይገባኛል የማንልበትን ትልቅ ስጦታ በማንሳት ያንን የሰጠ ጥቃቅኑን አይከለክልም በማለት በእግዚአብሔር እንድንታመን ያሳስበናል፡፡ ( 1ቆሮ 3:21-23 ፤ ቆላ 3:4 ኢሳ 55:1-3 )

> *ስለዚህም ማንም በሰው አይመካ ነገር ሁሉ የእናንተ ነውና ጳውሎስ ቢሆን ኬፋም ቢሆን አለምም ቢሆን ሕይወትም ቢሆን ሞትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ፤ ሁሉ የእናንተ ነውና ፤ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው (1ኛቆሮ 3:21-23)፡፡*
>
> *ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ (ቆላ 3:4)፡፡*

## *8:33 የመረጣቸውን*

የተመረጡት ከመልካምነታቸው የተነሳ ሳይሆን ከአብ ከዘላለም ፍቅሩ የተነሳ ነው ( 5:8 )፡፡

### *ማን ይከሳቸዋል?*

ከዘካርያስ ጊዜ አንስቶ ሰይጣን የጌታን ልጆች ለመክሰስ ይነሳል፡፡ እግዚአብሔር ግን እኛን በክርስቶስ « ጸድቃችኋል!» ብሎ ስላወጀና አዋጁንም ሊሽረው ስለማይችል የሰይጣን ክስ ውድቅ ነው፡፡ በክርስቶስ ደም ከፍርድና ከኩነኔ ነፃ ወጥተናል ( 8:1 ) ፡፡

ሰው በሥራው ሳይሆን በሚያጸድቀው በእግዚአብሔር በማመን፣ በጸጋውም ጉልበት በመታመን፣ ከክርስቶስ ጋር በመሞትና በመነሳት በአብ ፊት በክርስቶስ በኩል ይታያል፡፡

## *8:34 የሞተው*

ስለ ሐጢአተኞች አንድ ጊዜ በመሞት የከፈለውን ዋጋ ያመለክታል። ኃጢአት በተሠራ ቁጥር አይሞትም። አንድ ጊዜና ለመጨረሻ ሁሉንም ዕዳ ከፈለ ( ዕብ 9:26-27 )።

እንዲህ ቢሆንስ ፣ አለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር አሁን ግን በአለም ፍፃሜ ራሱን በመስዋእት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላ ፍርድ እንደተመደበባቸው (ዕብ 9:26-27)።

### *ይልቁንም ከሙታን በመነሳት*

ክርስቶስ በሞቱ ዕዳን መክፈሉ ብቻ ሳይሆን በትንሳኤው ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ሕያው በመሆን ሙታን የነበሩትን ሕያዋን በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀበትን ድንቅ እውነት ይገልጣል። ይህ ያስታረቀን ጌታ ለዘላለም ስለ እኛ በመማለድ በትንሣኤው የተቀዳጀነውን የድል ሕይወት መኖር የምንችልበትን ጸጋ ይሰጠናል።

## *8:35 ማን ይለየናል?*

በዙሪያችን የከበቡን ፈተናዎችና ውጊያዎች ዓላማቸው ከዚህ ፍቅር እኛን ማውጣት ነው። ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ የፍቅሩ መገለጫዎች ፍቅሩንና ጥበቃውን የምንመለከትባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ስለዚህ ከፍቅሩ ሊለዩን አይችሉም። የተወደድነው ገና ኃጢአተኞች ሳለን ነው። ይህንን መውደድ መከራ ሊወስድብን አይችልም!

## *8:36 ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን*

ይህ ቃል በመዝ 44:22 የሚገኝ ቃል ነው በ2ቆሮ 4:11 ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ትንሣኤ ሕያዋን

የሆንን ሁላችን ዘወትር ለሞት አልፈን የምንሰጥ ( ወደ ሞት አፋፍ በሚያደርስ መከራ ውስጥ የምናልፍ ) መሆናችንን ያመለክታል::

*ስለ አንተ ሁልጊዜ ተገድለናል ፣ እንደሚታረዱ በጎች ሆነናል (መዝ 44:22)::*

*የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሲጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሳ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለን (2ኛቆሮ 4:11)::*

## *8:37 በዚህ ሁሉ ግን*

እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን ከእርሱ መውደድ ሊለዩን የማይችሉ መሆናቸውን ያመለክታል::

### *ከአሸናፊዎች እንበልጣለን*

ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን ዙሪያችንን የሚያንዣብቡትን ሁሉ ድል የምናደርግና በአንድ የታወቀ የጦር ሜዳ ተዋግተው ካሸነፉ አርበኞች በበለጠ ማዕረግ አሸናፊነታችን የላቀ መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ግን እግዚአብሔር ስለወደደን፤ ክርስቶስ ያስገኘው ድል የእኛ እንዲሆን በዚያ በድል ሕይወት እንድንኖርም ስላስቻለን እንጂ ከእኛ የሆነ አይደለም::

## *8:38 - 39 በክርስቶስ ኢየሱስ ካለ ፍቅር . . . እንዳይችል*

እግዚአብሔር በልጁ በኩል እኛን የወደደበትን መውደድ ፣ የተረጋገጠውንና ሊሻር የማይችለውን በየትኛውም ጉልበተኛ ሊቀለበስ የማይችለውን ጽናት ያመለክታል::

ሐዋርያው ሲመለከት ዙሪያውን ያሉና ያመኑትን የሚገፈታትሩትን መከራዎች አዋጅ የሚያወጣባቸው ይመስላል « አትችሉም » የሚል:: አዋጅ ማውጣት ብቻ ሳይሆን እንደማይችሉም በፍጹም እርግጠኝነት ተረድቷል::

# የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ በአጽንኦት ማስተላለፍ የፈለገው እግዚአብሔር ፈጽሞ የማይጥለን መሆኑን ነው፡፡ ምንም እንኳን እኛ በታማኝነታችን ባንጸናም እግዚአብሔር ግን የታመነ ሆኖ ይኖራል ፍቅሩም ፍጹም ነው፡፡

ሁለተኛው የሐዋርያው ብርቱ ትምህርት እግዚአብሔር ስለ ወደደን በዚህ ምድር ስንኖር መከራ እንዳይደርስብን የማይከላከል መሆኑን ነው፡፡ (immunity) ኢሚዩኒቲ ወይንም ክትባት አልተሰጠንም፡፡

እንዲያውም የአባትነት ፍቅሩን ፣ ጥበቃውንና የቅርብ ወዳጅነቱን የምንረዳው ስለ ስሙ በመከራ (የመስቀሉ መከራ) ስናልፍ ነው፡፡ በዚያ ውስጥ ያሳልፈናል፡፡ ያሳልፈናል ስንል ማለፋችን የተረጋገጠ ነው፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በተደረገው የመስቀል ላይ ሥራ ምክንያት አሸናፊነታችን የተረጋገጠ ነው፡፡

ኩነኔ የለብንም ፣ ግዴታ የለብንም ፣ ተስፋም አንቆርጥም ከክርስቶስም ፍቅር ሊለየን የሚችል ነገር የለም፡፡ በአንድ ቃል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ለእሥራኤልም ተስፋ አለ

የሮሜን መጽሐፍ በእርጋታ እያጠና የመጣ ሰው ምዕራፍ ዘጠኝ ጋ ሲደርስ ጳውሎስ መልዕክቱን ያዘባረቀው ሊመስለው ይችላል:: ምናልባትም ምን ያገናኘዋል? ብሎ ሊያስብ ይችላል:: ሆኖም ግን ሐዋርያው በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት እጅግ በጣም ውብ በሆነም መሚገቻ ሃሳብና የፍትህ ስርዓትን የተከተለ የመከራከሪያ ነጥብ በዓላማ ከምዕራፍ 9 - 11 ባሉት ክፍሎች የተገለጡትን የአስተምህሮና ለእሥራዔል ህዝብ በግሉ ያለውን ፍቅርና የሚያስብላቸውን ሃሳብ በግልጽ ያስቀምጣል::

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ደህንነት እርግጠኝነትና በፍጹም ስለማይለወጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ያለውን አስተምህሮ በገለጠበት በምዕራፍ ስምንትና ከምዕራፍ 12 - 15 በተገለጡት የክርስቲያናዊ ተግባርና አገልግሎት ዝርዝሮች መካከል ይህንን ያስገባው በዓላማና « ጽድቅ በእምነት » የሚለውን አስተምህሮ ለማጽናት ሆን ብሎ ነው::

ጳውሎስ ለአይሁድ እጅግ አስቸጋሪ ሰው ነበር። ብዙዎቹም የሚጠላቸውና ኃይማኖታቸውን በማዋረድ እንግዳ ትምህርት የሚያስተምር የማያከብራቸውና የሚንቃቸው ይመስላቸው ነበር። ጳውሎስ ግን እስራዔልን አስመልክቶ ይህንን የመሰለ አቋም እንደሌለው ለማሳየት በነዚህ ሦስት ምዕራፎች ድንቅ የግል አቋሙን ገልጧል ፣ፍቅሩንና ምጡንም አሳይቷቸዋል።

አስተምህሮታዊ ወደ ሆነው የጳውሎስ ሀሳብ ስንመለስ ደግሞ ጳውሎስ በምዕራፍ 8 አማኞች በእግዚአብሔር ፈጽሞ የተወደዱና የማይጥላቸው ቃል ኪዳኑም የማይታጠፍ መሆኑን ገልጧል። ተሟጋቾቹ ግን አንድ ከባድ ጥያቄ ያነሱበታል። « ይህ የምትለው እውነት ከሆነ የአይሁዳውያንንስ ጉዳይ እንዴት ታየዋለህ? እንደምትነግረን «እስራዔልን ቸል ብሎ ወደ አህዛብ ፊቱን መለሰ፣ ቤተክርስቲያንን መረጠ» እያልክ ነው። ታድያ እስራዔልን የጣለ ቤተክርስቲያንን እንዴት አይጥልም ትላለህ? »

ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ ሙግቱ መሰረታዊ የሆነ መልስ ለመስጠት በነዚህ ምዕራፎች ድንቅ ሃሳብ ያቀርባል።

= በምዕራፍ 9 ውስጥ ስለ እስራዔል ቀደምት መመረጥ

= በምዕራፍ 10 ውስጥ ደግሞ አሁን ስላለችበት መጣል

= በምዕራፍ 11 ውስጥ ወደፊት ስለሚጠብቃት ተሃድሶ በዝርዝር ይናገራል።

በየትኛውም የታሪክ ዘመን ውስጥ የእስራዔልን ያህል የተሟላ ታሪክ ያለው ሀገር የለም ማለትም ያለፈው ፣ የአሁኑና የወደፊቱ ተነገረለት ምድር የለም። ይህም የእግዚአብሔርን የዘላለም ሀሳብ ያመለክታል።

ሐዋርያው ይህንን የእግዚአብሔር ማንነት በግልጽ ለማስረዳት በምዕራፍ ዘጠኝ ውስጥ አራት የእግዚአብሔር ባሕርይ መገለጫዎችን ያቀርባል።

1. ታማኝነቱን ( ሮሜ 9:1 - 13 )
2. ጽድቁን ( ሮሜ 9: 14 - 18 )
3. ፍትሐዊነቱን ( ሮሜ 9:19 - 29 )
4. ጸጋውን ( ሮሜ 9: 30-36 )

የሮሜ ምዕራፍ 9 ሃሳብ እነዚህን አራት ዋና የእግዚአብሔር ባሕርያት ከእሥራዔል ታሪክ ጋር በማያያዝ የሚገልጽ ድንቅ ማስረጃ ነው።

በምዕራፍ 8 በውስጡ የሚሰማውን ያንን ታላቅ እርግጠኝነትና ደስታ ጽፎ እንዳበቃ በውስጡ ያለውን ምጥና ለቅሶ ወደሚገልጸው የእስራዔል ታሪክ ውስጥ ይገባል። ሐዋርያው ጳውሎስ ቀና ብሎ ኢየሱስን ሲመለከት ደስ ይለዋል። መለስ ብሎ ደግሞ ወገኖቹ የሆኑትንና የሚጠፉትን እስራዔላውያንን ሲመለከት ያለቅሳል እንዲያውም ሙሴ በዘዳ 32:30 - 35 እንደጸለየ ሁሉ እሥራዔል የሚድን ከሆነ እኔ የተረገምሁ ልሁን እስኪል አድርሶታል። ይህም ለሚጠፉት ያለውን ልብና ሸክም ያመለክታል።ሐዋርያው ጳውሎስ የሚድኑትን ለመጥቀም ሲል በምድር መቆየትን ስለሚጠፉት ሲል ደግሞ ወደ ሲዖል መውረድን ይመርጣል ( ፊልጵ 1:22 - 24) ምን ዓይነት አስደናቂ ሰው ነው?

### *9:1 በክርስቶስ . . . ሕሊናዬ. . . መንፈስ ቅዱስ*

ነገር ሁሉ በሦስት ምስክር እንደሚጸና ሁሉ ሐዋርያውም እውነት መሆኑንና ውሸት የሌለበት እንደሆነ አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ክርስቶስን ፣ የራሱን ህሊናና የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት ማስረጃ አድርጎ ያቀርባል ( ዘዳ 17:6 ፤ 19:15 ፤2ቆሮ 13:1)። የሚናገረውም የተረጋገጠና የመሃላ ቃል መሆኑን ያስረዳል ( 2ቆሮ 11:31 ፤ ገላ 1:20 ፤ 1ጢሞ 2:7)። ሐዋርያው ጳውሎስ እውነቱን ከመናገር ውጪ ምርጫ አልነበረውም ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት በብርቱ ያስጠይቀዋልና። ይህ እውነት ግን በጣም አደገኛና ነፍሱን ለሞት የሚያበቃ እውነት ነው። ያው እስራዔል ወንጌልን አለመቀበላቸው ነው።

> *በሁለት ወይም በሶስት ምስክሮች አፍ ሞት የሚገባው ይገደል በአንድ ምስክር አፍ አይገደል (ዘዳ 17:6)።*

*ስለ በደል ሁሉ ፣ ክፉ በማድረግም ስለ ሰራት ኃጢአት ሁሉ በማንም ላይ አንድ ምስክር አይቁም በሁለት ምስክሮች ወይም በሶስት ምስክሮች አፍ ነገር ሁሉ ይፀናል (ዘዳ 19:15)::*

*ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሶስተኛዬ ነው ሁሉ ነገር በሁለትና በሶስት ምስክር አፍ ይፀናል (2ኛ ቆሮ 13:1)::*

*ዘላለም የተባረከ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት እንዳልዋሽ ያውቃል (2ኛ ቆሮ 11:31)::*

*ስለምፅፍላችሁ ነገር እነሆ በእግዚአብሔር ፊት ሐሰት አልናገርም (ገላ 1:20)::*

*ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበር እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ እውነት እናገራለሁ አልዋሽም (1ኛ ጢሞ 2:7)::*

## *9:2 ሁል ጊዜ*

ይህ ቃል የሚያመለክተው ሐዋርያው ዘወትር በጭንቀት የሚኖር መሆኑን ሳይሆን እውነቱንና የሚጠብቃቸውን ባሰበ ቁጥር የልብ ስብራት በውስጡ ስለሚሰማው ያለውን ሸክም ለመግለጥ ነው::

## *9:3 ስለ ወንድሞቼ*

ጌታ ቢፈቅድለት በወንድሞቹ ምትክ ሆኖ ከክርስቶስ ቢለይ እንኳን ይመርጥ እንደነበር ይገልጣል:: ይህ ዓይነቱ ምርጫ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ደስታ የሚሆን አገልግሎት እንደነበረ እንረዳለን:: ( ዘኁ 18:14 ፤ ህዝ 44:19 ፤ 1ቆሮ 4:11) የእግዚአብሔርን ደስታ ለመፈጸም ጨርሶ ራስን መስጠት::

*በእስራኤል ዘንድ እርም የሆነው ሁሉ ለአንተ ይሆናል (ዘኁ 18:14)::*

*የእህሉን ቁርባንና የኃጢያትን መስዋእት የበደልንም መስዋእት ይበላሉ በእስራኤልም ዘንድ እርም የሆነ ነገር ሁሉ ለእርሱ ይሆናል (ሕዝ 44:29)::*

*እስከዚህ ሰአት ድረስ እንራባለን ፣ እንጠማለን ፣ እንራቆታለን ፣ እንጐሰማለን ፣እንከራተታለን (1ኛቆሮ 4:11)::*

## *9:4 - 5 የእሥራኤል ሕዝብ*

ሐዋርያው በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ሕዝበ እስራዔል ከጌታ የተሰጧቸውን በረከቶች በዝርዝር ያነሳል።

1. ልጅነት - ከአንዱ ዘር መውረስ (ዘዳ 4:22 ፤ ኤር 3)

*ፈርኦንም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እስራኤል የበኩር ልጄ ነው (ዘፀ 4:22)።*

*በሰው ዘንድ:- ሰው ሚስቱን ቢፈታ ፣ ከእርሱም ዘንድ ሄዳ ሌላ ወንድ ብታገባ ፣ በውኑ ደግሞ ወደ እርሱ ትመለሳለችን ያች ሴት እጅግ የረከሰች አይደለችምን? ይባላል። አንቺ ከብዙ ውሽሞች ጋር አመንዝረሻል ፣ ወደ እኔም ትመለሻለሽን? ይላል እግዚአብሔር። ዓይንሽን አንሥተሽ ወደ ወናች ኮረብቶች ተመልከቺ ያልተጋደምሽምበት ስፍራ ወዴት አለ? ዓረባዊ በምድረ በዳ እንደሚቀመጥ አንች በመንገድ ላይ ተቀምጠሽ ትጠብቂያቸው ነበር ግን በግልሙትናሽና በኃጢአትሽ ምድሪቱን አረከስሽ። ስለዚህ ካፊያ ተከለከለ ፣ የኋለኛውም ዝናብ ጠፋ የጋለሞታም ሴት ፊት ነበረብሽ ፣ ታፍሪም ዘንድ እንቢ ብለሻል። አሁንም:- አንተ አባቴ ሆይ ፣ የብላቴንነቴ ወዳጅ ነህ ብለሽ አልጮኽሽልኝምን? ለዘላለም ይቈጣልን? እስከ ፍጻሜስ ድረስ ይጠብቀዋልን? እነሆ ፣ እንዲህ ብለሽ ተናገርሽ ፣ እንደ ተቻለሽም መጠን ክፉን ነገር አደረግሽ።*

*እግዚአብሔርም በንጉሡ በኢዮስያስ ዘመን እንዲህ አለኝ:- ከዳተኛይቱ እስራኤል ያደረገችሁን አየህን ወደ ረዘመው ተራራ ሁሉ ከለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች ሄደች በዚያም ጋለሞተች። ይህንም ሁሉ ካደረገች በኋላ ወደ እኔ ትመለሳለች ብዬ ነበር ነገር ግን አልተመለሰችም አታላይ እኅትዋም ይሁዳ አየች። ከዳተኛይቱም እስራኤል ስላመነዘረች ስለዚህ ፈትቻታለሁ የፍችዋንም ወረቀት ሰጥቻታለሁ አታላይ እኅትዋ ይሁዳ ግን እንዳልፈራች እርስዋም ደግሞ ሄዳ እንደገለሞተች አየሁ። በግልሙትናዋም በመቀለልዋም ምድሪቱ ረከሰች እርስዋም ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች። በዚህም ሁሉ አታላይቱ ይሁዳ በሀሰት እንጂ በፍጹም ልብዋ ወደ እኔ አልተመለሰችም።*

*እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ:- ከአታላይቱ ከይሁዳ ይልቅ ከዳተኛይቱ እስራኤል ጸደቀች። ሂድና ይህን ቃል ወደ ሰሜን ተናገር ፣ እንዲህም በል ከዳተኛይቱ እስራኤል ሆይ ፣*

ተመለሽ ፣ ይላል እግዚአብሔር መሐሪ ነኝና ፣ ለዘላለምም አልቈጣምና በእናንተ ላይ ፊቴን አላደርግም ፣ ይላል እግዚአብሔር፡፡ በአምላክህ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመጽሽ መንገድሽንም ከለመለመ ዛፍ ሁሉ በታች ለእንግዶች እንደ ዘረጋሽ ፣ ቃሌንም እንዳልሰማሽ ኃጢአትሽን ብቻ እወቂ ይላል እግዚአብሔር፡፡ ከዳተኞች ልጆች ሆይ ፣ እኔ ባላችሁ ነኝና ተመለሱ ይላል እግዚአብሔር አንዱንም ከአንዲት ከተማ ሁለቱንም ከአንድ ወገን እወስዳችኋለሁ ፣ ወደ ጽዮንም አመጣችኋለሁ እንደ ልቤም በግ ጠባቆችን እሰጣችኋለሁ በእውቀትና በማስተዋልም ይጠብቁአችኋል፡፡ በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ ፣ ይላል እግዚአብሔር ፣ በዚያ ዘመን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም ልብ አያደርጉትም ፣ አያስቡትምም ፣ አይሹትምም ፣ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም፡፡ በዚያም ዘመን ኢየሩሳሌምን የእግዚአብሔር ዙፋን ብለው ይጠሩአታል ፣ አሕዛብም ሁሉ ወደ እርስዋ ይሰበሰባሉ ከእንግዲህም ወዲህ ክፉውን እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሄዱም፡፡ በዚያም ዘመን የይሁዳ ቤት ወደ እስራኤል ቤት ይሄዳል በአንድም ሆነው ከሰሜን ምድር ርስት አድርጌ ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠኋት ምድር ይመጣሉ፡፡

እኔ ግን፡- ከወንዶች ልጆች ጋር እንዴት አደርግሻለሁ ያማረችውንስ ምድር የከበረችውን የአሕዛብን ሠራዊት ርስት እንዴት እሰጥሻለሁ ብዬ ነበር፡፡ ደግሞ አባቴ ብለሽ ትጠሪኛለሽ እኔንም ከመከተል አትመለሽም ብዬ ነበር፡፡ የእስራኤል ቤት ሆይ ፣ ሚስት ባልዋን እንደምታታልል እንዲሁ አታለላችሁኝ ይላል እግዚአብሔር፡፡ የእስራኤል ልጆች መንገዳቸውን አጣምመዋልና፣አምላካቸውንም እግዚአብሔርን ረስተዋልና በወናዎች ኮረብቶች ላይ የልመናቸውና ልቅሶአቸው ድምፅ ተሰማ፡፡

ከዳተኞች ልጆች ሆይ ፣ ተመለሱ ፣ ከዳተኝነታችሁንም እፈውሳለሁ፡፡ እነሆ ፣ አንተ አምላካችን እግዚአብሔር ነህና ወደ አንተ እንመጣለን፡፡ በእውነት የኮረብቶችና የተራሮች ፍጅት ከንቱ ናት በእውነት የእስራኤል መዳን በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ ነገር ግን ከትንሽነታችን ጀምሮ የአባቶቻችን ድካም ፣ በጎቻቸውንና ላሞቻቸውን ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውንም ፣ እፍረት በልቶባቸዋል፡፡ ከትንሽነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኛና አባቶቻችን በአምላካችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርተናልና፣ የአምላካችንንም የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማንምና በእፍረታችን እንጋደም ፣ ውርደታችንም ይክደነን (ኤር፡3)፡፡

2. ክብር - የእግዚአብሔር ታቦት በመካከላቸው ከመሆኑ የተነሳ

3. ኪዳን - ከአብርሃም ጋር እግዚአብሔር የገባው
4. ሕግ - በሙሴ በኩል የተሰጠው
መዝ 119:19 - 20 ፤ዘዳ4:7

*ነፍሴ ሁልጊዜ ፍርድህን እጅግ ናፈቀች (መዝ 119:19-20)*

*አምላካችን እግዚአብሔር በምንጠራው ጊዜ ሁሉ እንደሚቀርብልን ፣ አምላኩ ወደ እርሱ የቀረበው ታላቁ ሕዝብ ማነው? (ዘዳ 4:7)::*

5. የመቅደስ ሥርዓት - ይህም በካህናትና በሌዋውያን የሚሠራው ሥራ ነው ( ዕብ 9:1:6)

*ፊተኛይቱ ደግሞ የአገልግሎት ስርአትና የዚህ አለም የሆነው መቅደስ ነበራት (ዕብ 9:1)::*

*ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ ፣ ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል (ዕብ 9:6)::*

6. የተስፋው ቃል - የመሲሁ መምጣት

7. አባቶች - በጌታ የተወደዱ የእምነት ጀግኖች
( ሮሜ 11:29 )

8. ክርስቶስ በስጋ ከእነርሱ መወለዱ
(የአብርሃም ዘር ሮሜ 2:16)

## *9:6 እግዚአብሔር . . . አልሻረም*

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር በብርቱ የሚያቀርበው የመከራከሪያ ነጥብ እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ቃል አልሻረም የሚል ነው:: ይህ ማለት በስጋ እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ በእግዚአብሔር ዓይን እስራኤላዊ ማለት አለመሆኑን በአጽንኦት ይናገራል:: ይህንን የመሰለ ንግግር መናገር ነፍስን ወደ ሞት በፍጥነት የሚገፈትር ድፍረት ነው::

## *9:7-13 የአብርሃምም ዘር ስለ ሆኑ ሁላቸው ልጆች አይደሉም ነገር ግን በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል ተባለ:: ይህም የተሰፋ ቃል ልጆች ዘር ሆነው ይቈጠራሉ እንጂ*

*እነዚህ የሥጋ ልጆች የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም ማለት ነው። ይህ በዚህ ጊዜ እመጣለሁ ለሳራም ልጅ ይሆንላታል የሚል የተስፋ ቃል ነውና። ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን ርብቃ ደግሞ ከአንዱ ከአባታችን ከይስሐቅ በፀነሰች ጊዜ ልጆች ገና ሳይወለዱ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ ለእርስዋ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት። ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።*

በነዚህ በጣምራ አንድ መልዕክት በያዙ ቁጥሮች ጳውሎስ አብርሃምን ምሳሌ አድርጎ የመከራከሪያ ነጥቡን በማስረጃ አስደግፎ ያቀርባል።

አብርሐም ልጆች ነበሩት። ነገር ግን የተስፋው ቃል የተሰጠው ለይስሐቅ ነበር። ሆኖም «ኤሳውን ጠላው» ማለቱ እግዚአብሔር የጥላቻ ባሕርይ አለው ማለት አይደለም።

ግሪከኛው «ጠላው» የሚለው (mikros (mik-ros') ሲያብራራው (apparently a primary word; small (in size, quantity, number or (figuratively) dignity): **lesser degree of love** አጠቃለን ስንመለከተው እግዚአብሔር ለኤሳው የገለጠለት የፍቅር መጠን ለያዕቆብ ከገለጠው ያነሰ መሆኑን ነው። ፍቅሩ ለአንዳንዶች በበለጠ ይገለጻል።

ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ያለው ፍቅር = ወሰን የሌለው ፍቅር ነው (ኤፌ.3:18-19 )።

> *የእናንተ ስርና መሰረት በፍቅር ይፀና ዘንድ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሄርም ፍጻም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ (ኤፌ.3:18-19 )።*

## *9:14 አድልዎ ያደርጋልን?*

ለዚህ ጥያቄ ምላሹን « በፍጹም » የሚል ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ጻድቅና ፍርዱም ፍጹም ስለሆነ ነው። ለአሰራሩ እንከን አይገኝለትም በፍርድ ችሎትም ተሟግቶ የረታው የለም ( ሮሜ 3:4 ፤ ዘፍ 18:25 ፤ዘዳ 32:4 ፤ 2ዜና19:7 ፤ኢዮብ 8:3 ፤ መዝ 92:15 ፤ 145:17 ፤ራዕ 15:3 ፤ኤር 12 )

*በቃልህ ትፀድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ ተብሎ እንደተጻፈ ፣ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን (ሮሜ 3:4)።*

*ይህ ከአንተ ይራቅ ጻዲቁን ከኃጢያተኛ ጋር ትገድል ዘንድ ፣ ጻዲቁም እንደ ኃጢያተኛ ይሆን ዘንድ ፣እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ (ዘፍ 18:25)።*

*እርሱ አምላክ ነው ስራውም ፍጹም ነው መንገዱም ሁሉ የቀና ነው የታመነ አምላክ ፣ ክፋትም የሌለበት ፣እርሱም እውነተኛና ቅን ነው (ዘዳ 32:4)።*

*አሁንም እግዚአብሔርን መፍራት በእናንተ ላይ ይሁን በአምላካችንም በእግዚአብሔር ዘንድ በደልና ለሰው ፊት ማዳላት ማማለጃ መውሰድ የለምና ሁሉን ተጠንቅቃችሁ አድርጉ (2ኛ ዜና 19:7)።*

*በውኑ እግዚአብሔር ፍርድን ያጣምማልን? ሁሉንም የሚችል አምላክ ጽድቅን ያጣምማልን? (ኢዮብ 8:3)።*

*አምላኬ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ ይነግራሉ ፣ በእርሱም ዘንድ አመጻ የለም (መዝ 92:15)።*

*እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው በስራውም ሁሉ ቸር ነው (መዝ 145:17)።*

*ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ ፣ ስራህ ታላቅና ድንቅ ነው የአሕዛብ ንጉስ ሆይ ፣መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው ጌታ ሆይ ፣ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማነው አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፣ የጽድቅም ሥራህ ስለተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ (ራዕ 15:3)።*

*አቤቱ ከአንተ ጋር በተሟገትሁ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ ነገር ግን ከአንተ ጋር ስለ ፍርድ ልናገር። የኃጢያተኞች መንገድ ስለ ምን ይቀናል በደልንስ የሚያደርጉ ሁሉ ስለ ምን ደህንነት*

*ይሆናል ተክልሀቸው ስር ሰድደዋል አድገዋል አፍርተውማል በአፋቸው አንተ ቅርብ ነህ ፣ ከልባቸው ሩቅ ነህ (ኤር 12:1)::*

***9:15 - 16 ለሙሴ የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና:: እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ::***

***ለሙሴ . . . የምምረውን . . .***

ጳውሎስ ወደኋላ መለስ ብሎ ለሙሴ እግዚአብሔር የተገለጠበትን መንገድ ያሳያቸዋል:: የሚያቀርበውም ትዕይንት ሙሴ እግዚአብሔርን ያየበትን ትዕይንት ነው:: ሙሴ እግዚአብሔርን ሊያይ የቻለው ከእግዚአብሔር ምህረትና ከመልካምነቱ የተነሳ እንጂ ከሙሴ ማንነት አለመሆኑን ያመለክታል:: ሙሴ ማየት የቻለው በሰንጣቃው ዓለት ውስጥ በመቀመጡ ነው:: ያም ዓለት ክርስቶስ ነው:: ይህ የሚያሳየው በጌታ ቸርነትና ፍጹም ምህረት እንጂ የክብሩን በረከት ለመቀበል የሚያበቃን ማንነት በኛ ውስጥ አለመኖሩን ነው:: ( ሚክ 7:18 ፤ ዘዳ 33:19 ፤ ሕዝ 16:6 ፤ ማቴ 20:15 )

*በደልን ይቅር የሚል ፣ የርስቱንም ቅሬታ አመጽ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው? ምህረትን ይወድዳልና ቁጣን ለዘላለም አይጠብቅም (ሚኪያስ 7:18)::*

*እግዚአብሔርም እኔ መልካምነቱን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ ፣ የምምረውንም እምረዋለሁ አለ (ዘፀ 33:19)::*

*በአንቺም ዘንድ ባለፍሁ ግዜ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ ባየሁሽ ጊዜ:- በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ (ሕዝ 16:6)::*

*በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን ወይስ እኔ መልካም ስለ ሆንሁ ዓይንህ ምቀኛ ናትን? (ማቴ 20:15)*

ማንም ሰው ምህረትን እንደ ደመወዝ በይገባኛል ሊቀበል አይችልም። ምክንያቱም ምህረት ለወደደ ወይም ለሮጠ ሳይሆን ከሚምር ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው እንጂ! ብዙ ስለደከምን ስለሮጥን ምህረትን ማግኘት እንችላለን ብሎ ማሰብ ኪሣራ ነው። እኛ ሁላችን ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። በአዳም ኃጢአትም የኃጢአት ባሪያዎች ሆነናል። በዚህ ማንነት የምንሮጠውም ሩጫ እግዚአብሔርን እንደሚያስደስተው ማሰብ የለብንም። ነገር ግን ጌታ ከፍቅሩ ትልቅነት የተነሳ ስለራራልን ፍጥረታችንን ለውጦ እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ሰጠን ስለዚህም ምህረትን ተቀበልን።በዚያውም ጸጋ መሮጥና ማገልገል እንችላለን። ነገር ግን በሩጫችን ምህረትን መቀበል አንችልም
(ሮሜ 8:8፤ 4:4፤መዝ 119:32፤ገላ 1:4፣6 ፤5:7፤ 2ቆሮ 1:5 )።

*ልቤን ባሰፋኸው ጊዜ በትእዛዝህ መንገድ ሮጥሁ (መዝ 119:32)።*

*ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢያታችን ራሱን ሰጠ (ገላ 1:4)።*

*በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ (ገላ 1:6)።*

*በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን እንግዲህ ፀንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ (ገላ5:1)።*

*በመልካም ትሮጡ ነበር ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ? ገላ 5:7*

*የክርስቶስ ስቃይ በእኛ ላይ እንደበዛ ፣ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናል (2ኛቆሮ 1:5)።*

## *9:17 በአንተ . . . እንዲነገር*

*ሐዋርያው ይህንን ነጥቡን አጉልቶ ለማሳየት የስሙን ዝና በዓለም ሁሉ እንዲነገር ለማድረግ ፈርኦንን የተጠቀመ መሆኑን በማንሳት የራሱን የፈቃዱን አሠራር ይገልጣል። የፈርኦንን ልብ በማደንደን የጸጋውን ክንድ ገለጠ ( ዘዳ 9:6 )።*

## *9:18 ለሚወደው ምህረት. . . እንዲደነድን የፈለገውን ያደነድነዋል*

እግዚአብሔር ለሚወደው የሚለው ቃል ሉዓላዊ የሆነ ምርጫውን ያሳያል። ለፈርኦን ደንዳና ልብ ከሰዎች መከከል ለይቶ ሰጠው የሚል ዓይነት ሳይሆን ጽድቁን ለመግለጥ ሲል ልቡን እልከኛ ያደረገው መሆኑን ያመለክታል ይህን መሰረት በማድረግ እግዚአብሔር ኃጢአተኞች በኃጢአታቸው እንዲቀጥሉ በመፍቀድ በፍጻሜው ግን ኃጢአትን በመቅጣት ጽድቁን ይገልጣል ማለት እንችላለን። ፈርኦን ድንጋይ ልብ ነበረው (ዘፀ 7:13፤ 14፤22 ፤ 8:15፤19፤32)። በዚህም እግዚአብሔር ደግሞ ልቡን «እልከኛ» አደረገው (ዘፀ 9:12 ፤11:10፤ 14:8)። በዘላለማዊ እውቀቱና በማይወሰን የማስተዋል ባለጠግነቱና ምርጫው ይህንን ያደርጋል ይህም ደግሞ የሉዓላዊነቱና የመለኮት አሰራሩ ነው ( ሮሜ 1:26 ፤መዝ 105:25 ፤ ኢዮብ 9:12 ፤ ኢሳ 43:13፤ ያዕ 3:4 )።

*እግዚአብሔር እንደተናገረ ፣ የፈርኦን ልብ ጸና አልሰማቸውምም (ዘፀ 7:13)።*

*የእስራኤልም ልጆች በባህር መካከል በየብስ ገቡ ውሀውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው (ዘፀ 14:22)።*

*ፈርኦንም ዕረፍታ እንደሆነ ባየ ጊዜ ልቡን አደነደነ እግዚአብሔርም እንደተናገረ አልሰማቸውም (ዘፀ 8:15)።*

*ጠንቋዩችም ፈርኦንን ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው አሉት የፈርኦን ልብ ግን ፀና ፣ እግዚአብሔርም እንደተናገረ አልሰማቸውም (ዘፀ 8:19)።*

*ፈርዖንም በዚህ ጊዜ ደግሞ ልቡን አደነደነ ፤ ሕዝቡንም አለቀቀም (ዘፀ 8:32)::*

*<u>እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ</u> <u>አፀናው</u> እግዚአብሔርም ለሙሴ እንደተናገረው አልሰማቸውም (ዘፀ 9:12)::*

*ሙሴና አሮንም እነዚህን ታአምራቶች ሁሉ በፈርኦን ልብ አደርጉ እግዚአብሔርም የፈርኦንን ልብ አጸና ፣ የእስራኤል ልጆች ከአገሩ አልለቀቀም (ዘፀ 11:10)::*

*እግዚአብሔርም የግብፅን ንጉሥ የፈርኦንን ልብ አፀና ፤ እርሱም የእስራኤልን ልጆች አሳደደ የእስራኤልንም ልጆች ከፍ ባለች እጅ ወጡ (ዘፀ 14:8)::*

*ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ሴቶቻቸውም ለባህሪያቸው የሚገባውን ሥራ ለባህሪያቸው በማይገባው ለወጡ (ሮሜ 1:26)::*

*ሕዝቡንም ይጠሉ ዘንድ በባሪያዎቹም ላይ ይተነኰሉ ዘንድ ልባቸውን ለወጠ (መዝ 105:25)::*

*እነሆ ፣ ፈጥኖ ቢነጥቅ የሚከለክለው ማነው? እርሱንስ ምን ታደርጋለህ የሚለው ማነው? (ኢዮብ 9:12)*

*ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ ከእጄም የሚያመልጥ የለም እሰራለሁ ፣ የሚከለክልለ ማነው? (ኢሳ 43:13)::*

*እነሆ መርከቦቹ ደግሞ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆን በአውሎ ነፋስም ቢነዱ  የመሪ ፍቃድ ወደ ሚወደው ስፍራ እጅግ ታናሽ በሆን መቅዘፊያ ይመራሉ (ያዕቆ 3:4)::*

***9:19-21** እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው ትለኝ ይሆናል:: ነገር ግን አንተ ሰው ሆይ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ ሥራ ሠሪውን ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን እቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?*

እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር ማንም ሊከራከረውና በሰራውም ሥራ ላይ ለምን ይህንን አደረግህ? ተብሎ ሊጠየቅ በማይችል መንገድ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን ለመግለጥ ጳውሎስ የተጠቀመባቸውን ሃሳቦች ያዘሉ ናቸው። አንድ የሸክላ ስራ ሙያተኛ በእጁ ያለውን ሸክላ በወደደው መንገድ እያፈረሰ እንደገና እያበጃጀ የመሥራት ሥልጣን እንዳለው ሁሉ እግዚአብሔርም በእሥራዔል ላይ ይኸው የማይቀነስና የማይጠየቅ የማይገሰስ ሥልጣን አለው ( ኢሳ 29:16 ፤ 45:9፤64:8፤ ምሳ 16:4 ፤ ኤር 18:3 - 6 ፤ ኢዮብ 10:9 ፤ ዮሐ 15:16 ፤ ይሁዳ 4 ) ።

*እንደ ሸክላ ሰሪ ጭቃ የምትቆጥሩ አይደላችሁም? በውኑ ስራ ሰሪውን አልሰራኸኝም ይለዋልን? ወይስ የተደረገው አድራጊውን አታስተውልም ይለዋልን? (ኢሳ 29:16) ።*

*ከሰሪው ጋር የሚታገል ወዩለት በምድር ሸክላዎች መካከል ያለ ሸክላ ነው (ኢሳ 45:9)።*

*እግዚአብሔር ሁሉን ለእርሱ ለራሱ ፈጠረ ኃጢአን ደግሞ ለክፉ ቀን (ምሳ 16:4)።*

*አሁን ግን አቤቱ ፣ አንተ አባታችን ነህ እኛ ጭቃ ነን አንተም ሰሪያችን ነህ ፣ እኛም ሁላችን የእጅህ ስራ ነን (ኢሳ 64:8)።*

*ወደ ሸክላ ሰሪው ቤትም ወረድሁ ፣ እነሆም ፣ ስራውን በመንኮራኩር ላይ ይሰራ ነበር ከጭቃ ይሰራ የነበረ እቃ በሸክላ ሰሪው እጅ ተበላሸ ፣ ሸክላ ሰሪውም እንደወደደ መልሶ ሌላ እቃ አድርጎ ሰራው። የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። የእስራኤል ቤት ሆይ ፣ ይህ ሸክላ ሰሪ እንደሚሰራ በውኑ እኔ በእናንተ ዘንድ መስራት አይቻለኝምን? እነሆ ፣ ጭቃው በሸክላ ሰሪው እጅ እንዳለ ፣ እንዲሁ እናንተ በእኔ እጅ አላችሁ (ኤር 18:3-6)።*

*እንደ ጭቃ አድርገህ እንደለወሰከኝ አስብ ወደ ትቢያ ትመልሰኛለህን? (ኢዮብ 10:9)።*

*እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፣ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ (ዮሐ 15:16)።*

*ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶቹ ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችን ፀጋ በሴሴኝነት ይለውጣሉ ንጉሳችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ (ይሁዳ 4)።*

***9:22 - 23 ነገር ግን እግዚአብሔር ቁጣውን ሊያሳይ ኃይሉንም ሊገልጥ ወድዶ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃች ላይ የክብሩን ባለጠግነት ይገልጥ ዘንድ ለጥፋት የተዘጋጅቱን የቁጣ ዕቃች በብዙ ትዕግስት ከቻለ እንዴት ነው?***

በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ምህረቱን ለመግለጥም ሆነ ቁጣውን ለማሳየት ጌታ በዚህም በዚያም የሚሰራ መሆኑንና ምህረቱን ለመግለጥ መታገሱን የቁጣውንም ጽናት ለማሳየት አመጸኞችን መታገሱን ያመለክታል። የመጨረሻ ዓላማው ግን የጸጋውን ክብር ማሳየት ነው ( ኢሳ 43:1፣7 )።

*አሁንም ያዕቆብ ሆይ የፈጠረህ ፣ እስራኤል ሆይ የሰራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ በስምህ ጠርቼሀለሁ ፣ አንተ የኔ ነህ (ኢሳ 43:1)።*

*ለሜንን መልሰህ አምጣ ፣ ደብቡንም አትከልክል ወንዶች ልጆቼን ከሩቅ ሴቶች ልጆቼንም ከምድር ዳርቻ ፣ በስሜ የተጠራውን ለክሬም የፈጠርኩትን ፣የሰራሁትንና ያደረኩትን ሁሉ አምጣ እለዋለሁ (ኢሳ 43:7)።*

***9:24 የምሕረቱ ዕቃችም ከአይሁድ ብቻ አይደሉም ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን።***

በዚህ ቁጥር ደግሞ በስጋ ከአብርሃም ዘር ያልሆንነው የአህዛብ ወገኖች በመለኮታዊ ጥሪው፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል « ትሆናላችሁ ! » ብሎ በዘላለማዊ አሰራሩ ፣ በዕውቀቱና በማስተዋሉ የወሰነውን ውሳኔ ያሳያል።በዚህ ክፍል የምናስተውለው ነገር የእግዚአብሔርን ጥሪና ችሎታ ነው። የሰዎች ጥሪ ተጠሪውን የመለወጥ ኃይል የለውም ጌታ ሲጠራ ግን የመለወጥ ፣ የመፍጠርና ከሙታን የማስነሳት ኃይል አለው ( ዘፍ 17: 4 - 6 ፤ ሮሜ 4: 16:17 ) ።

*እነሆ ፣ ቃል ኪዳኔ ከአንተ ጋር ነው ለብዙ አሕዛብ አባት ትሆናለህ። ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ ፣ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሀለሁና። እጅግም አበዛሀለሁ ፣ሕዝብም አደርግሃለሁ ፣ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ (ዘፍ 17:4-6)።*

*ስለዚህ ከህግ ብቻ ሳይሆን ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተሰፋው ቃል እንዲፀና እንደ ፀጋ ይሆን ዘንድ በእምነት ነው እርሱም ለብዙ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደተጻፈ፣ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው (ሮሜ 4:16-17)።*

***9:25 - 26*** ***እንዲሁ ደግሞ በሆሴዕ ፦ ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ ብዬ ያልተወደደችውንም የተወደደችው ብዬ እጠራለሁ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባለላቸውም ስፍራ በዚያ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ ይላል።***

እግዚአብሔር የወደደን በልጅነት መብት ነው። ከፍቅሩ ጽናት የተነሳ በልጁ በኩል ልጆቹ አደረገን። ይህም ምህረትን በተሞላው በእግዚአብሔር ፍቅር ስለታሰበን ነው። ( ሆሴ 2:23) የእግዚአብሔርን ፍቅር « ምህረት » በማለት ይገልጠዋል።

*በምድርም ላይ ለእኔ እዘራታለሁ ምህረትም የሌላትን እምራለሁ ፣ ሕዝቤም ያልሆነውን አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ እርሱም አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል (ሆሴ 2:23)።*

***9:27 - 29*** ***ኢሳይያስም፦ የኢስራኤል ልጆች ቁጥር ምንም እንደ ባህር አሸዋ ቢሆን ቅሬታው ይድናል ጌታ ነገሩን ፈጽሞና ቈርጦ በምድር ላይ ያደርገዋልና ብሎ ስለ እስራኤል ይጮኻል። ኢሳይያስም እንደዚሁ፦ጌታ ፀባዖት ዘር ባላስቀረልን እንደ ሰዶም በሆንን ገሞራንም በመሰልን ነበር ብሎ አስቀድሞ ተናገረ።***

ሐዋርያው በነዚህ ሦስት ቁጥሮች እጅግ አደገኛ የሆነውንና ድፍን እስራኤልን በቁጣ የሚያስነሳውን የእግዚአብሔርን የማይሻር እውነት የሆነውን ሃሳብ ያነሳል።ምንም እንኳን የእስራኤል ህዝብ ብዛት ሊቆጠር በማይችል መጠን ቢበዛም የሚድነው ግን የእግዚአብሔር እስራኤል የሆነው « ትርፉ » ብቻ ነው። በማለት ቁርጡን ይነግራቸዋል። ኢሳያስ ይህንን ሲያውጅ ስሜታዊ ሆኖ ሳይሆን በእውቀትና በማስተዋል እንደ አዋጅ ነጋሪ እንደሆነም በመጥቀስ የእርሱ አዋጅ ተከፋይ መሆኑን ይጠቅሳል ( ኢሳ 10:22)።

*የያዕቆብ ቅሬታ ወደ ኃያል አምላክ ይመለሳሉ (ኢሳ 10:22)።*

***9 : 30 - 32 እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ጽድቅን አገኙ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም። ይህስ ስለምንድር ነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው***

በነዚህ ሦስት ቁጥሮች ደግሞ የመጽሐፉ ዋነኛ ማዕከላዊ ነጥብ የሆነውን « ጽድቅ በእምነት » የሚለውን ሃሳብ አጉልቶ በማስረጃ በማውጣት ይገልጣል

- ለጽድቅ ደፋ ቀና ያላሉ አህዛብ በስብከት ሞኝነት በማመን የሆነውን ጽድቅ ተቀበሉ። በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ላቀረበው ጥሪ በእምነት ምላሽ ስለሰጡ « ጻድቃን » ተብለው ተጠሩ ሆኑም።
-
- ለጽድቅ ደፋ ቀና ሲሉ የኖሩት እስራኤላውያን ግን የሕጉን ማዕከላዊ ሃሳብ በመሳት ፣ በፈሪሳዊነታቸውም በመግፋት ወደ ክርስቶስ የሚያመጣውን ሞግዚት የራሳቸውን ትርጓሜና የተሳሳተ ሚዛን በመስጠት ከመንገድ የሚወጡበት ሆነ። ህጉ የሚላቸው ሳይሆን የሚመቻቸውን በማድረግና በመጨመር የሕጉን አገልግሎት ሳይቀበሉ ቀሩ። ሕግ አለን እያሉ ወደ ክርስቶስ ሳይደርሱ ቀሩ።ህጉ ግን ሞግዚት ሆኖ ለክርስቶስ ሊያቀርባቸው ነበር የተሰጠው። ( ማቴ 15:17 - 18 ፤ገላ 3:2 )

*ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ስጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁእ ነህ። እኔም እልሃለሁ ፣ አንተም ጴጥሮስ ነህ ፣ በዚች አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ ፣ የገሀነም ደጆች አይችሏትም (ማቴ 16:17-18)።*

*ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ በሕግ ስራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስ ተቀበላችሁን? (ገላ 3:2)።*

እስራኤላውያን ህጉን የሳቱበትና የህጉን አገልግሎት ያልተቀበሉበት ምክንያት ጽድቅ በእምነት ሳይሆን ህግን በመጠበቅ በሥራ እንደሚገኝ በመቁጠራቸው ነው። እግዚአብሔር ህግን የሰጣቸው ግን በህጉ ጠቋሚነት ኃጢአታቸውን ተረድተው ወደ እግዚአብሔር ምህረት እንዲመጡ ለማድረግ ነበር።

## 9:33 *እነሆ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት እኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ እንደተፃፈ በእንቅፋት ድንጋይ ተሰናከሉ።*

ይህ የታመኑበትን የማያሳፍርና የሚያድን ዐለት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በርሱ ያመኑትም አያፍሩም። እግዚአብሔር በሉዓላዊ ፈቃዱ የጠራቸውና ሆናችኋል ያላቸው ሁሉ ሆነዋል ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ስመረጠን እኛ ቸል ማለት ተፈቅዶልናል ማለት አይደለም። የጌታን ችሎት ለማሳየትና ሰው በራሱ ሊመካበት የሚችለውና ለመመረጥ ያበቃኛል የሚል የተሳሳተ አቋም እንዳይዝ ለማሳሳብ ነው ( ዳን 12:2፤ ዘፍ 49:24 ፤መዝ 118:22 ፤ ኢሳ 8:14 ፤28:16 ፤ማቴ 21:42 ፤ ሉቃ 20:17 ኘ 18፤ ሐሥ 4:11 ፤ 1ቆሮ 3:11 ፤ ኤፌ 2:20 ፤1ቆሮ 1: 23፣26 ፤ 9:22፣23 )።

*በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ አኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት ፣ እኩሌቶቹ ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና (ዳን 12:2)።*

*ነገር ግን ቀስቱ እንደ ፀና ቀረ የእጆቹም ክንድ በያዕቆብ አምላክ እጅ በረታ ፣በዚያው በጠባቂው በእስራኤል አምድ ፣ (ዘፍ 49:24)።*

*ግንበኞች የናቁት ድንጋይ ፣ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ (መዝ 118:22)።*

*እርሱም ለመቅደስ ይሆናል ነገር ግን ለሁለቱ በእስራኤል ቤቶች ለእንቅፋት ድንጋይና ለማሰናከያ ዓለት በእየሩሳሌምም ለሚኖሩ ለወጥመድና ለአሽክላ ይሆናል (ኢሳ 8:14)።*

*ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እነሆ፣በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ የተፈተነዉን፣ የከበረዉን፣ መሠረቱ የጸናዉን የማእዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም (ኢሳ 28:16)።*

*ኢየሱስም እንዲህ አላቸዉ ፡-ግንበኞች የናቁ ድንጋይ፣ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ ፣ለአይኖቻችንም ድንቅ ነዉ የሚለዉን ከቶ በመጽሐፍ አላነበባችሁም? (ማቴ 21:42)።*

*እርሱ ግን ወደ እነርሱ ተመልክቶ እንግዲህ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዘን ራስ ሆነ ተብሎ የተጻፈዉ ይህ ምንድር ነዉ? በዚያም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይቀጠቀጣል የሚወድቅበትም ሁሉ ግን ይፈጨዋል አለ (ሉቃ 20:17-18)።*

*እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት ፣ የማእዘን ራስ የሆነዉ ይህ ድንጋይ ነዉ (ሐሥ 4:11)።*

*ከተመሰረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና ፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1ኛ ቆሮ 3:11)።*

*በሐዋርያትና በነብያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል ፣ የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው (ኤፌ 2:20)።*

*እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስ እንሰብካለን ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው ፤ (1ኛ ቆሮ 1:23)።*

*ወንድሞቼ ሆይ ፤ መጠራታችሁን ተመልከቱ፡ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች ፣ ኃያላን የሆኑ ብዙዎች ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም (1ኛ ቆሮ 1:26)።*

*ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ ፣ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነእርሱ ሆንሁ:: በወንጌልም ማህበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉ አደርጋለሁ (1ኛ ቆሮ 9:22-23)::*

## *የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ*

ሐዋርያውም በዚህ ምዕራፍ ምጡን ጩኸቱን ያለውን ፍቅር ከገለጠ በኋላ በምንም መንገድ ሊሻሻልና ማስተባበያም ሊቀርብበት የማይችለውን የእግዚአብሔር የጽድቅ አሰራር ይገልጣል:: ይህም « ጽድቅ በእምነት እንጂ በሥራ ወይም ከምርጥ ዘር በመወለድ አይደለም! » የሚል ነው::

እንግዲያው አሁንም በዓለም ያለ ሰው ሁሉ ይህ ሁለት ምርጫና ውሳኔ በፊቱ አለ:: እነዚህም ምርጫዎች ለደህንነታችን መልካም ሥራችንና ፀባየ ሸጋነታችንን መታመን ወይም የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት በእምነት መቀበል:: እግዚአብሔር የሰጠው የደህንነት መንገድ « በእምነት በሚገኘው ጸጋ » እንድንድን ነው ( ኤፌ 2:8 - 9)::

ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታ አክብረን በእምነት በመቀበል በዚያውም ጸንተን በመኖር የእግዚአብሔር ልጅነት መብት ተጠቃሚዎች መሆን ተሰጥቶናል::

# ምዕራፍ አሥር
# ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ማዕከላዊ ሃሳብ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን የደህንነት መንገድ ቸል ማለታቸውን መግለጥ ነው:: ሐዋርያው በምዕራፍ 9 ውስጥ ያነሳውን የማይገረሰስ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ዘግቶ በፍጥነት የሚሻገረው ለዚህ ሉዓላዊነቱ አልገዛ ብለው ራሳቸውን ከክብር ስላጎደሉት ስለ እስራኤላውያን ቸልታ በማውሳት ነው:: እንደምናስታውሰው በምዕራፍ 9:30 - 33 ባለው ክፍል ውስጥ በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ በማንሳት አጽንኦት ሰጥቶት መጻፉን ተመልክተናል:: ከዚያም እስራኤላውያን ከክብር ስለጎደሉበትና የደህንነትን መንገድ ቸል ስላሉባቸው ሦስት ምክንያቶች በዚህኛው ምዕራፍ ውስጥ ያወሳል:: ቀጥሎም ከዚህ ለመውጣት የሚችሉበትን መንገድ ያሳያል:: በዚያውም ቸልታቸው ያመጣባቸውንም ኪሣራ ይገልጣል::

የምዕራፉን አጠቃላይ ሃሳብ በቀላሉ ለመጨበጥ ከታች በተዘረዘረው ሁኔታ ክፋፍሎ ማጥናት ይጠቅማል::

1. የደህንነትን መንገድ ቸል ያሉበት ምክንያት ( 10:1 - 13 )
2. ከዚህ ቸልታ ሊወጡ የሚችሉበት መንገድ ( 10:14 - 17)
3. የቸልተኝነታቸው ውጤቶች (10:18 - 21)

ለአጠቃላይ ጥናት ይረዳ ዘንድ ይህንን ካመለከትን በያንዳንዱ ቁጥር ውስጥ ሐዋርያው ማስተላለፍ የፈለጋቸውን መልዕክቶች ሃሳብ በሃሳብ በመከፋፈልና በመተንተን እንመለከታቸዋለን።

***10:1 ወንድሞች ሆይ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።***

*ወንድሞች*

ሐዋርያው በዚህ መጠሪያ የሚገልፃቸው የእምነት ተካፋይ የሆኑትን ነው። ሊነግራቸው የፈለገውም ስለ እስራዔል ያለውን ምጥና ጸሎት ነው ( 4:24፤1ቆሮ 1:22 - 24)።

> *እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስ እንሰብካለን ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው ፤ (1ኛ ቆሮ 1:23)።*

*የልቤ ፈቃድ . . . ልመናዬ*

ይህ የእግዚአብሔር ሰው እስራዔላውያን በተለያዩ መንገዶች የተሰጣቸውን ዕድል ቸል በማለት ባይጠቀሙበትም የእርሱ ፈቃድ ግን ከዚህ ቸልታ ወጥተው እውነቱን እንዲያውቁ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስም በአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ለአማኞች የሚጸልይ መሆኑን ገልጧል በዚህ ስፍራ ግን ስለ ገዛ ወገኖቹ አጥብቆ በብርቱ የልብ ምጥና የስሜት መነካት ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይ መሆኑን እንረዳለን። ጸሎቱ የእምነት ብቻ ሳይሆን ብርቱ «እንባ» ደግሞም « የልብ መሰበር » ያለበት ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በአባቱ ፊት ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ በአባቱ ፊት በምጥና በብርቱ እንባ ይጸልይ ነበር ይህም በአባቱ ፊት ምን ያህል የከበረ እንደነበረ እንረዳለን ከዚህም የተነሳ ልመናው ተሰምቶለታል ( ዕብ 5:7 ) ይህ ዓይነቱ ከልብ መሰበር የሚወጣ ጩኸት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ የከበረ ነው:: በዓለም ግን ይህ ዓይነቱ የልብ መሰበር የሚደገፍ አይደለም ( ኢሳ 53:3 )::

*የተናቀ ከሰውም የተጣለ ፣ የህመም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው ሰውም ፊቱን እንደሚሰወርበት የተናቀ ነው ፣ እኛም አላከበርነውም (ኢሳ 53:3)::*

### *እንዲድኑ*

ይህ ቃል የሐዋርያው ጳውሎስን ፈቃድና ልመናውን ያሳያል:: ይህንን መሠረት አድርገንም እስራኤላውያን የአብርሃም ዘር በመሆናቸው ብቻ እንዳልዳኑ ነው፤ ለመዳን የሚችሉት በሥራ እንጸድቃለን ከሚለው አስተሳሰባቸው ወጥተው ወደ ጌታ የሚመጡ ከሆነ ብቻ ነው:: ጌታ እግዚአብሔር ዓለም ሁሉ ይድን ዘንድ ልጁን ልኮ የኃጢአት መስዋዕት አድርጓል:: ዓለምም ሁሉ እርሱን በማወቅ ከጥፋት ይድኑ ዘንድ ይወድዳል:: ሰዎች ይህንን ተረድተው አለማመናቸው በዚህም ምክንያት አለመዳናቸው የራሳቸው የምርጫ ውጤት ነው:: እውነቱን ለማወቅ ባልወደዱ መጠን ለማይረባ አዕምሮ አልፈው ይሰጣሉ:: በሉዓላዊነቱ ደግሞ ምህረቱን ለሚወድዳቸው ያሳያል በዚህም አዳላህ ተብሎ ሊወቀስ አይችልም:: የክርስቶስ የማዳን ብርሃን ለሁሉ በርቷል ለመረጣቸውም ብርሃኑን አብዝቶ አብርቶላቸዋል:: ( 2ኛ ቆሮ 4:3፤6፤7፤13 )

## *10:2 ለእግዚአብሔር ቀናተኛ እንደሆኑ*

እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ቀናዒ ነበሩ:: ቅናታቸው ግን በዕውቀት ላይ የተመሰረተና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ያለውን ለመፈጸም የሚያስችል አልነበረም::

ቅንዓታቸው በጸጋው ክብር ባለጠግነት ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን በኃይማኖታዊ ወግና ልማዳቸው ላይ ነበር። ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ የብዙ ሰዎች ቅንዓት ከእስራኤላውያን ጋር ተመሳሳይ ነው። ጸጋን ጥለው በሃይማኖታቸው ወግና በልማዳቸው ይታመናሉ።

***10:3 የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም።***

በዚህ ቁጥር ሐዋርያው ጠንከር አድርጎ የሚገልጸው ሃሳብ እስራኤላውያን የጽድቅ ፍላጎት አልነበራቸውም የሚል ሳይሆን የራሳቸውን ጽድቅ ለማቆም በመጣራቸው የእግዚአብሔርን ጽድቅ መቀበል አቃታቸው። ብሎ ነው።

***10:4 የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።***

*ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ*

ጌታ ኢየሱስ ሕግ የሚጠይቀውን ሁሉ በመፈጸም ለሰው ልጆች ጽድቅን ይሰጥ ዘንድ ከሕግ በታች ሆኖ ተወለደ። ሕግንም ያለ እንከን ፈጸመው። በእርሱም ሥራ ስናምን የእርሱ ጽድቅ ለኛ ተቆጠረልን። ( ጻድቃን ተብለን ተጠራን )። ስለዚህ ህግ ወደ እርሱ የሚያደርሰን ሞግዚታችን እንጂ የጽድቃችን መሠረት አይደለም።

***10:5 ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና።***

ሙሴ ህጉን ሲቀበልና ሲገልጠውም « እነዚህን የሚፈጽም ሰው በህይወት ይኖራል » ብሏል። ይህም ማለት ህጉ የሚጠይቀውን የሚፈጽሙ ይጸድቃሉ ማለቱ ነው።

*10:6 - 7 ከእምነት የሆነ ጽድቅ ግን እንዲህ ይላል በልብህ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል አትበል ይህ ክርስቶስን ለማውረድ ነው ወይም በልብህ ወደ ጥልቁ ማን ይወርዳል አትበል ይህ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ነው።*

ወደ ኋላ መለስ ብለን የእስራኤልን ታሪክ ስናጠና ከነዓንን የወረሱት ያመኑት ብቻ ነበሩ። ይህ ለሙሴ ተነግሮት ነበር፤ ጳውሎስም ለሙሴ የተነገረውን ይህንን ማሳሰቢያ ደግሞ ይጽፈዋል። ( ዘዳ 30:11 - 14) ቃሉን ያመኑና ጌታ የተናገረውን ለመፈጸም ሩቅ አለመሆኑን ያመኑ ተሻግረው ገቡ። ( ዘዳ 8:17፤ 9:4 - 5፤ ሮሜ 9:27 - 29 )

*እግዚአብሔርን እንዳትረሳ በልብህም፦ ጉልበቴ የእጄም ብርታት ይህን ሀብት አመጣልኝ እንዳትል (ዘዳ 8:17)።*

*አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ካወጣቸው በኋላ ስለ ጽድቁ አወርሳት ዘንድ ወደዚህች ምድር እግዚአብሔር አገባኝ ስትል በልብህ አትናገር እነዚህን አሕዛብ ስለ ኃጢአታቸው እግዚአብሔር ከፊትህ ያወጣቸዋል (ዘዳ 9:4-5)።*

*ኢሳይያስም፦ የእስራኤል ልጆች ቁጥር ምንም እንደ ባህር አሸዋ ቢሆን ቅሬታው ይድናል ጌታ ነገሩን ፈጽሞና ቈርጦ በምድር ላይ ያደርገዋልና ብሎ ስለ እስራኤል ይጮኻል። ኢሳያስም እንደዚሁ ጌታ ፀባዖት ዘር ባላስቀረልን እንደ ሰዶም በሆንን ገሞራንም በመሰልን ነበር ብሎ አስቀድሞ ተናገረ (ሮሜ 9:27-29)።*

ክርስቶስ የጽድቅን መንገድ ይዞ መጥቶ አባቱንም ታዝዞ ባይፈጽመው ኖሮ ማን ወደ ሰማይ ሄዶ ጽድቅን መቀበል ይችል ነበር? ጌታ በበጎ ፈቃዱ ልጁን ላከው። ስለዚህ አምነን መቀበል እንጂ ባለማመን ከክብር መጉደል አይገባም። ምክንያቱም ክርስቶስን ወደ ምድር ማውረድ የሚያስችል የጽድቅቀ ስራ ያለው ሰው ማንም የለም። የጌታ ምህረት ብቻ ይህን አድርጓል። ይህም ከፍቅሩ የተነሳ የሆነ ነው። በዚህም ጸጋው ተገልጧል ( ኢዮብ 11:7፤ ኢሳ 9:2፤ ዮሐ 1:1፣5፣14 )።

*የእግዚአብሔርም ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህ? (ኢዮ 11:7)።*

*በጨለማ የሄደ ህዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው (ኢሳ 9:2)።*

*በመጀመሪያው ቃል ነበረ ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር (ዮሐ1:1)።*

*ብርሃንም በጨለማ ይበራል ፣ ጨለማም አላሸነፈውም (ዮሐ 1:5)።*

*ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን (ዮሐ 1:14)።*

ክርስቶስ ኢየሱስ በአሁኑ ወቅት ሁሉን ፈጽሞና አሸንፎ በአብ ቀኝ ተቀምጧል።ነገር ግን ጽድቅን በራሳችን ሥራ ለማምጣት ስንጥር ክርስቶስን ከሰማይ የማውረድ ያህል ይቆጠራል ።

## *10:8 የምንሰብከው. . . በእምነት*

ሐዋርያው እዚህ ቦታ በግልጽ የሚያስቀምጠው የሚሰብከው ቃል ከባድና ሩቅ የሆነ ሳይሆን ቅርብ የሆነና ለመረዳት የማያዳግት ግን በእምነት ብቻ ሊቀበሉት የሚገባ ቃል መሆኑን ነው። እምነት በራሱ መዳን ማለት አይደለም። ሆኖም በእምነት መዳንን እናገኛለን። በእምነት ክርስቶስን እናገኛለን በክርስቶስም በኩል ወደ አብ መግባትን እናገኛለን። የማዳን ሥራ በጌታ በራሱ የተሰራ ሲሆን በእርሱ ያመኑ ሁሉ በአብ ወደተዘጋጀው የክብር ህይወት ይገባሉ ( ሮሜ 5:2፤ ዕብ 10:19 - 20፤ ኤፌ 2:18 )።

*በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ በእርሱ ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ፀጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል በእግዚአብሔር ክብር ተስፋ እንመካለን (ሮሜ 5:2)።*

*እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት*

*በሲጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፤ (ዕብ 10:19-20)::*

*በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና (ኤፌ2:18)::*

## *10:9:10 በአፍህ ብትመሰክር*

የክርስቶስ ኢየሱስ ጌትነት ወይም መለኮታዊነቱን ማወጅ ለእስራኤላውያን እጅግ አዳጋች ነው:: ሐዋርያውም ይህንን ጉድለታቸውን ለመንካት እዚህ ቦታ ያስገባዋል::

*ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን*

ሐዋርያው የጌትነቱን ምስጢር ለመግለጥ ጥልቅ የሆነ የክርስቶስ ኢየሱስን ከሞት የመነሳት ምስጢር አሮጌውንም አዳም ( በእርሱ ያመኑት ) ወደ ክብር ለማምጣት የሄደበትን መንገድ ያሳያል::

ክርስቶስ ኢየሱስ ከስላሴ አንዱ ነው:: በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለም ስለኛ ሊሞት ወደደ:: ሞት ያስፈለገውም የሞትን ዕዳ ለመክፈል ነበር:: እግዚአብሔር ለአዳም ፍጥረቱን ሁሉ እንዲገዛ ሥልጣን ሰጥቶት ነበር:: ሰው ግን በኃጢአት ምክንያት ይህንን ሥልጣኑን አጣ:: ሥልጣኑ የሚሰራው እግዚአብሔር ባስመረለት የሕይወት መስመር ሲሄድ ብቻ ነበር:: ከዚህ መንገድ በኃጢአት ምክንያት ሲወጣ ሞት ተፈረደበት:: ይህንን የሞት ፍርድ ለመሻር ሁለተኛው አዳም ሞተ:: በሞቱም የኃጢአትን ዕዳ ከከፈለ በኋላ በጸጋው በኩል የእግዚአብሔር ህይወት ሥልጣኑም ባመኑት ሁል ላይ እንዲሰራ አደረገ::ጌታ ሁል ጊዜም ባለሥልጣን ነው፣ መለኮታዊ ነው:: ነገር ግን የሰውን ልጆች ወደ ሥልጣን ለመመለስ ሞትን ቀመሰ አባቱም ከሞት አስነሳው:: ለሰው ልጅ ሁሉ ህይወትን ሰጠ ይህንን ያመነ በእርሱ የሆነውን ሥልጣንና ህይወት ይቀበላል ( ቆላ 1:15 - 18 ፤ ሐሥ 2:36 ፤ ኤፌ 2:6 - 7 ፊሊጵ 2:7 - 9 ፤ ዕብ2:6 - 9 )::

*እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታዩት ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ስልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ ለእርሱና በእርሱ ተፈጥረዋል እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥመዋል። እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው እርሱም ከሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው (ቆላ 1:15-18)።*

*እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ (ሐዋሥራ 2:36)።*

*በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የፀጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን (ኤፌ 2:6-7)።*

*ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ ! በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ! ለሞትም ይሔውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ (ፊሊ 2:7-9)።*

*ነገር ግን አንድ በአንድ ስፍራ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ወይስ ትጐበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነስከው የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት በእጆችህም ስራ ላይ ሾምከው ሁሉን ከእግሮችህ በታች አስገዛህለት ብሎ መሰከረ። ሁሉን ከእርሱ በታች ባስገዛህ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና። አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም ነገር ግን በእግዚአብሔር ፀጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሳ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን (ዕብ 2:6-9)።*

**እግዚአብሔር አብ ልጁን ያለ ልክ ከፍ ከፍ ሲያደርገውና ለቤተክርስቲያን ራስ ሲያደርገው አካሉም ከእርሱ ጋር ከፍ ከፍ ይላል። በዚህም ሥልጣን በምድር ትኖራለች። በመጨረሻም የእግዚአብሔር መንግሥት ስትገለጥም ሥልጣኗ በፍጹምነትና በሙላት ይገለጣል በመጨረሻም ሁሉም በመለኮት ክብር ሙላት ይጠቃለላል ( 1ቆሮ 15:20-28) ይህንን ያመነ በአንደበቱም የተናገረ ይጸድቃል ጽድቅ በማመን ነውና።**

*አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷል ሞቱ በሰው በኩል ስለመጣ ትንሳኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአል:: ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ህያዋን ይሆናሉ:: ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉ ስልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፣ ፍፃሜ ይሆናል:: ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግስ ይገባዋልና:: የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና:: ነገር ግን ሁሉ ተገዝቷል ሲል ፣ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው :: ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጅ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል (1ኛ ቆሮ 15:20-28)::*

### ***10:11 - 13 መጽሐፍ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና:: በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና::***

የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ማለት በችሎቱና በጸጋው መታመን ማለት ነው:: እግዚአብሔር የሚሰማቸው በልባቸው የጸጋ ሥራውን አምነው ሲቀበሉ ነው:: የእምነታቸውንም አቋም ጨርሶ ሳይጠራጠሩ ሲገልጹ ይሰማቸዋል ይባርካቸዋልም:: ምክንያቱም የሚደገፉት በእርሱ ችሎትና ጸጋ ስለሆነ የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ልመናቸውን ይሰማል የመጨረሻ ትልቅ በረከቱም የዘላለምን ሐይወት መስጠት ነው ( ኤር 24:7 ፤ 2ቆሮ 4:13 )::

*እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ የሚያውቅ ልብ እሰጣቸዋለሁ በፍጹም ልባቸው ወደ እኔ ይመለሳሉና ህዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ (ኤር 24:7)::*

*ነገር ግን አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ ተብሎ እንደተጻፈ ያው አንድ የእምነት መንፈስ ስላለን ፤ እኛ ደግሞ እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን (2ኛ ቆሮ 4:13)።*

### *10:14 እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?*

**እውነተኛ መጠራት የሚኖረው ማመን ሲኖር ነው። ለማመን ደግሞ ሊታመን ስለተገባው መስማት ይገባል። የሰው ልጆች ሁሉ ይህን የጸጋ ወንጌል እንዲሰሙና አምነው እንዲለምኑ ጌታ ፈቅዷል።ለሰሚዎቹም የማስተዋልን ጸጋ የሚሰጠው የጸጋ ሁሉ አምላክ የሆነው ባለጸጋው ጌታ ነው። ምርጦቹ ይሰሙትና ያስተውሉት ዘንድ ታላቁ መምህር በተለያየ መንገድ ያስተምራቸዋል( ኢሳ 6:9 - 10) ይህንንም በመንፈሱና በልዩ ልዩ መንገዶች በተግባር ደግሞም በምክር ይገልጠዋል ( ዕብ 4:12 - 13:12:7 - 11 )።**

*ሂድ ፤ ይህን ህዝብ መስማት ትሰማላችሁ አታስተውሉምም ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው (ኢሳ 6:9)።*

*በአይናቸው እንዳያዩ ፤ በጆሮአቸው እንዳይሰሙ ፤ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ፤ ተመልሰው እንዳይፈወሱ ፤ የዚህን ህዝብ ልብ አደንድን ፤ ጆሮአቸውንም አደንቁር ፤ አይናቸውንም ጨፍን አለኝ (ኢሳ 6:10)።*

*ለመቀጣት ታገሱ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርጋችኋልና አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። ከዚህም በላይ የቀጡን የስጋችን አባቶች ነበሩን አንፈራቸውም ነበር እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በህይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል (ዕብ 12:7-11)።*

### *10:15 መልካሙን የምስራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?*

የወንጌል ስብከት ሥራ በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ሥራ ነው። ይህንን የከበረ ሥራ ሊሰሩ የሚችሉትም የተላኩ ናቸው። ወንጌልን ይዘው የሚራመዱ እግሮች በብዙ ሻካራ ቦታዎች፣ በእሾህና በቆንጥሩ መካከል አልፈው ስለሚሄዱ ብዙ መከራ ሊገጥማቸው ፣ ሊደሙና ሊቆስሉ ይችላሉ መልዕክቱ ግን እጅግ የከበረ ስለሆነ ከተጎዳና ከተጎሳቆለ ሰው እንደሚሰማ ደካማ መልዕክት ሳይሆን የሰሚዎችን ልብ ሰንጥቆ የሚገባ ደስ የሚያሰኝ ያማረ መልዕክት ነው።

***10:16 ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም።***

ይህ መልዕክት ግን ለብዙዎች ቢነገርም ብዙዎች ግን አይቀበሉትም ይህም በእኛ ዘመን የሚሆን ብቻ ሳይሆን በነቢዩ በኢሳያስ ዘመንም ይከሰት ነበር።

***10:17 እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።***

ሐዋርያው ከላይ ጀምሮ ያሉትን ትንታኔዎቹን በሙሉ የወንጌል ማዕከላዊ ሃሳብ በሆነው በክርስቶስ ላይ ያሳርፈዋል። ሰው ሊያምን የሚችለው ሲሰማ ነው።ሊታመን የሚገባውም ክርስቶስ ነው። ስለዚህ በወንጌል ስብከት ሊነገር የተገባው ክርስቶስ ብቻ ነው።

***10:18 ዳሩ ግን፦ ባይሰሙ ነው ወይ? እላለሁ። በእውነት፦ ድምጻቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ አለም ዳርቻ ወጣ።***

ታድያ ይህ ከሆነ እስራኤል ለመስማታቸው ምን ማረጋገጫ አለህ? የሚል ተሚጋች ከውስጥ የነጠመው ይመስላል ጳውሎስ ግን ብርቱ ምላሽ ይሰጣል። ሰምተዋል። ተፈጥሮ ይናገራል፣ የተሰጣቸውም ቃል ይናገራል። እነርሱ መስማት አልፈለጉም እንጂ ( ሰምተው እንዳልሰማ ሆኑ እንጂ ) ሰምተዋል።

***10:19 - 20*** ***ነገር ግን እስራኤል ባያውቁ ነው ወይ? እላለሁ:: ሙሴ አስቀድሞ:- እኔ ሕዝብ በማይሆነው አስቀናችኋለሁ በማያስተውልም ሕዝብ አስቈጣችኋለሁ ብሎአል:: ኢሳይያስም ደፍሮ :- ሳልፈለጉኝ ተገኘሁ ሳልጠየቁኝም ተገለጥሁ አለ::***

ሐዋርያው ከዚያም ሙሴን በመጥቀስ ሕዝቤ ያልኩት ሊሰማኝ ካልወደደ ሕዝቤ ያላልኩትን ማስተዋል ሰጥቼ አስቀናቸዋለሁ አለ:: አህዛብ የዳኑት በዘር ሳይሆን የተሰበከውን የወንጌል ቃል በማመን ነው:: እስራዔልም የሚድነው በማመን ነው:: እስራዔል ግን ከማስተዋል ይልቅ አህዛብ በመዳናቸው ተቆጡ::

***10:21*** ***ስለ እስራኤል ግን ቀኑን ሁሉ ወደ ማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ ይላል::***

ሐዋርያው የምዕራፍ 10 ሃሳቡን የሚያጠቃልለው የእግዚአብሔርን ሀዘን በሚገልጥ ቃል ነው:: እስራዔል የተዘረጋውን የእግዚአብሔር የምህረት እጅ አልቀበል ብላ ቸል ማለቷን በብርቱ ሀዘን ገልጧል:: ለደህንነት የተዘረጋውን መንገድ ባለመከተላቸው ጥፋቱ የራሳቸው ነው:: እጁን መዘርጋቱ ግን አሁንም ለምህረት ጊዜ ያላቸውና ያላበቃባቸው መሆኑን ፤አሁንም ምላሽ ቢሰጡ የደህንነት ነገር በአጠገባቸው ያለ መሆኑን ያሳያል::

## የምዕራፍ አሥር ማጠቃለያ

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳስተማረን ከእምነት ውጪ የሆነና የእግዚአብሔርን የደህንነት መስመር አዛንፎ የሚከናወን የትኛ ውም የሃይማኖት ቅንዓትና ወግ ወደ እግዚአብሔር ክብር ሙላት አያደርስም። ይልቁኑ ከእግዚአብሔር ክብር ያጎድላል። ስለዚህ በዚህ ዘመን ያለነውም ያለምንም ማመንታት ለጸጋው ወንጌል እጃችንን በመስጠት በእስራኤል የደረሰው ኪሳራ እንዳይደርስብን ራሳችንን በመስመሩ ውስጥ ማስገባት ይገባናል። የሚድነው የጌታን ስም የሚጠራ እንጂ የራሱን ጽድቅ ለማቆም በሚደረገው ጥረት የሚታመን አይደለም።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ
# ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና

ሐዋርያው ዛሬም የተዘረጋቺውን የእግዚአብሔር የምህረት ክንድ የምዕራፍ አስር መደምደሚያ በማድረግ በምዕራፍ 11 ሊገልጠው ለሚያስበው ሃሳብ መንደርደሪያ ያደርጋታል። ምዕራፍ 11 በጠቅላላ እስራኤል አሁንም በእግዚአብሔር ዘንድ ተስፋ እንዳላት የሚያመለክት ነው።

***11:1 እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? እላለሁ። አይደለም እኔ ደግሞ እስራኤላዊና ከአብርሃም ዘር ከብንያምም ወገን ነኝና።***

ሐዋርያው በዚህ ስፍራ የእርሱን በጌታ መመረጥና መዳን ምሳሌ በማድረግ ጌታ ሕዝቡን በዘላለማዊ ፍቅሩ የሚወድድና የማይጥል መሆኑን ይገልጣል( ኤር 31:3 ) ።

*እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲሁም አለኝ በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ (ኤር 31:3)።*

***11:2 እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም። መጽሐፍ ስለ ኤሊያስ በተጻፈው የሚለውን በእግዚአብሔር ፊት እስራኤልን እንዴት እንደሚከስ አታውቁምን?***

ይህ ቁጥር እግዚአብሔር ከቀድሞውኑ ብዙ አመጸኞች መካከል ለራሱ ያላቸው እንዳሉና የአብርሃም ዘር ቅሬታዎች በዘመናት መካከል እንደነበሩት ይገልጣል።

***11: 3 - 4 ጌታ ሆይ ነቢያትህን ገደሉ መሰዊያዎችህንም አፈረሱ እኔም ብቻዬን ቀረሁ ነፍሴንም ይሹአታል። ነገር ግን አምላካዊ መልስ ምን አለው ለበአል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ።***

በዚህ ክፍል ኤልያስ በሕዝቡ በደል ተስፋ ቆርጦ ያቀረበውን ክስ ይገልጣል። በኤልያስ ሃሳብም ብቻውን እንደቀረ የሚያስረዳ ነበር። አባባሉም አንተን ብቻ አምኖ የሚቆም ሰው የለም የሚል ዓይነት ነው።

አምላካዊ የሆነው መልስ ግን ብቸኛ አለመሆኑን እና ሰው ያላወቃቸው ቅሬታዎች እንዳሉ ያመለክታል። ይህም የጸጋው ጉልበትና የእርሱ የብቻው ሥራ መሆኑን ያመለክታል።

***11:5 እንደዚሁም በአሁን ዘመን ደግሞ በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ።***

እግዚአብሔር በዘመናት መካከል የራሱን ቅሬታዎች የማቆየቱ እውነት በአብርሃም ዘመን ብቻ የነበረ ሳይሆን ዛሬም አለ፤ አለም እስክትፈጸምም ይህ እውነት የተጠበቀ ነው።

***11:6 በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል።***

*ጸጋና ሥራ*

1. *ሥራ* ማለት ያለ ጌታ እርዳታ ህግን በመፈጸም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት መጣር እና ለመጽደቅ መሞከር ነው። ስናስተውለው ግን በፍጥረታችን ኃጢአተኞች የሆኑ ሰዎች እንዴት አድርገን ነው እግዚአብሔር የሚፈልገውን የቅድስና ህይወት ልንኖር የምንችለው? ይህ ጥረት እግዚአብሔር የማይቀበለውና ፍሬ አልባ ነው።

   ጸጋ ማለት ግን እግዚአብሔር ብቻውን የሚሠራው ሥራ ሲሆን ከጸጋ ተቀባዩ የሚፈልገው በእምነት ራሱን መስጠትና ክብሩን በላዩ እንዲገልጥበት መፍቀድ ብቻ ነው። በጸጋ ውስጥ ራሱን የሚገልጸው ጌታ ነው ክብሩንም ጠቅልሎ የሚወስደው ራሱ ብቻ ነው። ሥራውን በባለአደራነት ይስጠን እንጂ ሠራተኛው እርሱ ነው።

***11:7 እንግዲህ ምንድር ነው? እስራኤል የሚፈልጉትን አላገኙትም የተመረጡት ግን አገኙት፤ ሌሎቹም ደነዘዙ***

እስራዔላውያን አጥብቀው ፈልገዋል። ግን በድንቁርናና በአለማወቅ መንገድ ነበረና አላገኙትም። ሌሎቹ ደግሞ ጨርሰውኑ ደነዘዙ ልባቸውም ደነደነ። ከነርሱ መካከል ግን በጸጋው ያመኑትና የተደገፉት ይህንን ጽድቅ አገኙ።

ከእስራኤል ወገን ሆነው ያመኑት ጸደቁ:: እነዚህ የተመረጡት ናቸው::

***11:8 እንዲሁም ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ጆሮቻቸውም እንዳይሰሙ እግዚአበሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው ተብሎ ተጽፎአል::***

እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የጽድቅ መንገድ ስላልተቀበሉ ልቦናቸው ጨለመ ደነዘዙ:: ጌታም የእንቅልፍን መንፈስ ላከባቸው ስለዚህም ልባቸው በድንዛዜ ጸና::

***11:9 - 10 ዳዊትም:- ማዕዳቸው ወጥመድና አሽክላ ማሰናከያም ፍዳም ይሁንባቸው ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ ጀርባቸውንም ዘወትር አጉብጥ ብሎአል::***

ንጉሥ ዳዊት በገዛ ወገኖቹ ሲጠላና ሲነቀፍ ፣ የገዛ ህዝቡ የሚሄድበት አስነዋሪ ድርጊት ሲያሳዝነው :: ብርቱ ጸሎት ጸለየ:: እንደ ጸለየውም እንቅፋትና ቅጣት ሆነባቸው እስከሁን ድረስም መንቃት አልሆነላቸውም ( መዝ 35:8፤38:4 )::

***11:11 - 12 እንግዲህ የተሰናከሉ እስኪወድቁ ድረስ ነውን? እላለሁ:: አይደለም ነገር ግን እነርሱን ያስቀናቸው ዘንድ በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ:: ዳሩ ግን በደላቸው ለዓለም ባለጠግነት መሸነፋቸውም ለአሕዛብ ባለ ጠግነት ከሆነ ይልቁንስ መሙላታቸው እንዴት ይሆን?***

ሐዋርያው በነዚህ ሁለት ቁጥሮች አስገራሚ የሆነውን የእግዚአብሔርን ድንቅ አሰራር ራሱን በራሱ በሚጠይቅ ዓይነት መንገድ በማቅረብ መልስ በመስጠት እንድናስተውል ያደርጋል::

የእስራኤል መሰናከል እስከ መጨረሻው ጸንቶ በዐለቱ እስኪፈጩ ድረስ የሚዘልቅ አይደለም:: ሆኖም ግን የኃጢአታቸው ጽናት በራሳቸው ጥረት መነሳት እስከማይችሉበት ድረስ የበረታ መሆኑን ለመግለጥ ነው:: ይህም ማለት በጌታ ጸጋ ሲታመኑ የሚነሱበት ጊዜ አለ ማለት ነው:: መነሳታቸውን ዓለም ሁሉ በጉጉት መጠበቅ እንዳለበት ለማሳየትም ሲልና አህዛብም ትሁታን እንዲሆኑ ለማድረግ የሚከተለውን ገለጣ ይጠቀማል::

የእነርሱ በደል መዳን ለአህዛብም እንዲሆን ካስቻለ ከበደላቸው የሚያነጻቸውና ክርስቶስን ሲቀበሉማ ምን ያህል የተትረፈረፈ በረከት ይሆን? የእነርሱ መመለስ ሁላችንን ወደ ልዩ ልዩ በረከት ሙላት ያስገባናል::

***11:13 - 14*** ***ለእናንተም ለአሕዛብ እናገራለሁ:: እኔ የአሕዛብ ሐዋርያ በሆንሁ መጠን ሥጋዬ የሆኑትን አስቀንቼ ምናልባት ከእነርሱ አንዳንዱን አድን እንደ ሆን አገልግሎቴን አከብራለሁ::***

ሐዋርያው ጳውሎስ ለአህዛብ የተላከ ሐዋርያ መሆኑንና አገልግሎቱንም በእንዴት ዓይነት መንፈስ የሚያከናውን መሆኑን የገለጠበት ቁጥር ነው::

ይህንንም የሚያደርገው የገዛ ወገኖቹ በእርሱ እጅ በተሰበከው የጸጋ ወንጌል የሚድኑትን አህዛብ አይተው፣ በቅንዓት እንዲነሳሱና ወደ ጌታ ዘወር እንዲሉለት ብሎ ነው:: ( ይህ ማለት ለአህዛብ ወንጌል የሚሰብከው ለእነርሱ ፍቅር ሳይኖረው ነው ማለት ግን አይደለም ) በወገኖቹ በጣም ከማዘኑና ይህን የከበረ የማዳን ወንጌል ቸል በማለታቸው ካለው ቁጭት የተነሳ ነው::

***11:15*** ***የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ ከሙታን ከሚመጣ ሕይወት በቀር መመለሳቸው ምን ይሆን?***

ለአህዛብ በረከት ምክንያት አድርጎ እግዚአብሔር እስራኤልን ተጠቀመባቸው:: የደህንነትን መንገድ ተቀብለው ወደ በረከቱ ሲገቡማ የባሰ በረከቱ ከሞት የመነሳት

ያህል እጥፍ ድርብ ደስታና በረከት ያመጣል:: ሐዋርያው በዚህ ስፍራ የእስራኤል ልብ ወደ ጌታ ሲመለስ የሚሆነውን ሙላት ለመግለጥ ቃላት ያጠረው ይመስላል::

***11:16 በኩራቱም ቅዱስ ከሆነ ቡሆው ደግሞ ቅዱስ ነው ስሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው::***

የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያ ክፍል በዘኑ 15:17 - 21 ያለውን ሃሳብ ያመለክታል:: ከእርሻ ከሚገኘው የመጀመሪያ ምርት የሚዘጋጀው የቡሖ ክፍል ለእግዚአብሔር ይቀርብ ነበር:: ያም ቡሖውን በጠቅላላ ይቀድሰዋል በኩር የተባሉት ደግሞ የነገድ አባቶች ናቸው::አብርሃም ይስሃቅና ያዕቆብ በኩራቶቹናቸው::( ዘዳ 23:19 ፤ ዘፀ 34:22 ፤ ዘሌ 2:12፤14 ፤23:10 ፤ ዘኑ 18:12፤ 28:26 ፤ ዘዳ 26:2:10 ) ይህ ማለት ግን እስራኤል ሁሉ ቅዱስ ነው ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም ጽኑ መሆኑን ለማሳየትና ወደ ተስፋቸው የሚመለሱ መኖራቸውን ለማሳየት ነው::

*የተመረጠውን የምድር ፍሬ በኩራት ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጣ ጠቦትን በእናቱ ወተት አትቀቅል (ዘፀ 23:19)::*

*የሰባቱንም ሱባኤ በአል ታደርጋለህ ፤ እርሱም የስንዴ መከር በኩራት ነው በአመቱም ፍፃሜ የመከፈቻ በአል ታደርጋለህ (ዘፀ 34:22)::*

*እነዚህንም የበኩራት ቁርባን አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር ታቀርባላችሁ እንደ ጣፋጭ ሽታ ግን በመሰውያው ላይ አይቀበሉም (ዘሌ2:12)*

*ከበኩራትም የእህል ቁርባን ለእግዚአብሔር ብታቀርብ ስለዚህ ቁርባን በእሳት የተጠበሰና የተፈተነ የእህል እሸት ታቀርባለህና (ዘሌ 2:14)::*

*ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ ፤ መከሩንም ባጨዳችሁ ጊዜ የእናንተን መከር ቡኩራት ነዶ ወደ ካህኑ አምጡ (ዘሌ 23:10)::*

*ለእግዚአብሔር ከሚሰጡት የፍሬ መጀመሪያ ከዘይትና ከወይን እህልም የተመረጠውን ሁሉ ለአንተ ሰጥቻለሁ (ዘኁ 18:12)::*

*ደግሞ በበኩራት ቀን ከሰባቱ ሱባኤ በኋላችሁ አዲሱን የእህል ቁርባን ለእግዚአብሔር ባቀረባችሁ ጊዜ ፣ የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንላችኋል የተግባርን ሥራ ሁሉ አትሥሩበት (ዘኁ 28:26)::*

*አምላክህ እግዚአብሔር ከሚሰጥህ ምድር ከምትሰበስበው ፍሬ ሁሉ በኩራት ውሰድ በእንቅብም አድርገው አምላክህ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ ወደ መረጠውም ስፍራ ይዘህ ሂድ (ዘዳ 26:2)::*

*አሁንም እነሆ አቤቱ አንተ የሰጠኸኝን የምድሪቱን ፍሬ በኩራት አቅርቤአለሁ:: አንተም በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት አኑረው በአምላክህም በእግዚአብሔር ፊት ስገድ (ዘዳ 26:10)::*

## *11:17 ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ በቅርንጫፎች ላይ አትመካ፤*

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጠበብቶች እንደሚሉት ጳውሎስ የወይራ ዛፍ የበለጠ ያፈራ ዘንድ ምን መደረግ እንዳለበት ሙያዊ ዕውቀት ነበረው:: ስለዚህም መልዕክቱን ግልጽ ለማድረግ በዚህ ስፍራ ተጠቅሞበታል ይላሉ::

1. ከቅርንጫፉ መልካሙ የወይራ ዛፍ እስራኤል ስትሆን ግንዱ አባቶች ናቸው:: ቃል ኪዳን የገባው ከአብርሃም ከይስሃቅና ከያዕቆብ ጋር ነበርና ( ኤር 11:16፤ ሮሜ 11:1)::

*እግዚአብሔር ስምሽን በመልካም ፍሬ የተዋበች የለመለመች የወይራ ዛፍ ብሎ ጠራው በድኑ አውሉ ነፋስ ጩኸት እሳትን አነደደባት ፣ ቅርንጫፎችዋም ተሰብረዋል:: (ኤር 11:16)::*

*እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን እላለሁ አይደለም ፣ እኔ ደግሞ እስራኤላዊና ከአብርሃም ዘር ከቢኒያም ወገን ነኝና (ሮሜ 11:1)::*

2. አንዳንዱ ቢሰበር ፦ የወይራ ዛፍ የበለጠ ያፈራ ዘንድ የማያፈራው ቅርንጫፍ ተሰብሮ ወደ እሳት ይጣል ነበር ( ኢሳ 27:11፤ ማቴ 21:43 )::

*ጫፎችዋ በደረቁ ጊዜ ይሰበራሉ ሴቶችም ወጥተው ያቃጥሏቸዋል ፣ የማያስተውል ሕዝብ ነውና ስለዚህ ፈጣሪው አይራራለትም ሰሪውም ምህረት አያደርግለትም (ኢሳ 27:11)::*

*የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ትወሰዳለች ፍሬዋንም ለሚያደርግ ህዝብ ትሰጣለች (ማቴ 21:43)::*

***11:18 - 22*** *ብትመካባቸው ግን ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም:: እንግዲህ እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል:: መልካም እነርሱ ካለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል:: ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ:: እግዚአብሔር እንደ ተፈጥሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና:: እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት ጭከናው በወደቁት ላይ ነው በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቈረጣለህ::*

ሐዋርያው በዚህ ክፍል የወይራን ዛፍ ምሳሌ በማድረግ ገዛድ የሆኑ እውነቶች በማስረጃነት ያቀርባል የዳነውንና ወደ እውነተኛው ግንድ በእምነት የተቀላቀለውን የአህዛብ ወገን በመዳኑ ምክንያት በእስራኤል ላይ እንዳይኮራ ያስጠነቅቃል:: ቀድሞ ለተከለው ያልራራ በኋላ በማዳቀል ለገባኸው ይራራል ብለህ አታስብ:: የሚያዋጣው

በመፍራትና በመንቀጥቀጥ በግንዱ ውስጥ በእምነት መኖር ብቻ ነው:: ያስቀመጣቸውን የተፈጥሮ እውነቶች ብንለከት

- ጥንካሬና ጉልበት ያለው ስሩ እንጂ ቅርንጫፉ አይደለም
- ቅርንጫፉ ምግቡን የሚያገኘው ከስሩ ነው ስለዚህ ቅርንጫፉ የሚመካበት ምንም የለውም:: ይህም ስር በጳውሎስ ገለጣ « አብርሃምም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት » የተባለው በእምነት የተገኘው የአብርሃም ጽድቅ ነው::
- የበረሃ ወይራው ከተፈጥሮው ወይራ ጋር ከተቀየጠ ጊዜ ጀምሮ ልዩነት ተወግዷል::
- የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹ የተሰበሩት ባለማመን ነው
- የበረሃ ቅርንጫፎቹ የገቡት በእምነት ነው:: ገባን ያሉት በእምነታቸው ካልጸኑ « የተሰጣቸውን ጸጋ በጥንቃቄ ካልጠበቁ » ለእነርሱም ዕጣው ተመሳሳይ ይሆናል::

ፍሬ እንጅ የትዕቢትን ነገር አትሰብ:- «ፍሬ» የሚለው ቃል ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ትርጉሜ ሲሆን በሌሎች አዋቂያን ዘንድ «ራስህን ጠብቅ» የሚል ትንታኔ ሰጥተውታል:: ይህም ማለት የተሰጠህን ፀጋ በጥንቃቄ በማክበር መያዝን ያሳያል:: ይህም የባሪያን ፍርሃት ሳይሆን የልጅነት ፍርሃትና አክብሮት ነው:: ልጅ በአባቱ ፍቅር እንደሚኖርና የአባቱን ፍቅር በአክብሮት እንደሚጠብቅ ዓይነት ነው::

ስለዚህ ለሁለቱም ወገን የሚያዋጣው በቸርነቱና በምህረቱ ታምኖ በኪዳኑ ውስጥ መኖር ነው ( ኤር 25:29፤1ዮሐ 1:5፤ ገላ 3:16፤ዮሐ 3:16 - 18፤ ሮሜ5:25፣29፤ዕብ 2:13፤ መዝ 51:8:9:40:9 - 10 )::

*ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተናገረ:: ስለ ብዙዎች እንደሚናገር ለዘሮችም አይልም ስለ አንድ እንደሚናገር ግን ለዘርህም ይላል ፤ እርሱም ክርስቶስ (ገላ 3:16)::*

*በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጠን ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና:: ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና (ዮሐ 3:16-18)::*

*የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሁሉ ከአንድ ናቸውና ስለዚህም ምክንያት ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ በማህበርም መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ ደግሞም እኔ በእርሱ እታመናለሁ፤ ደግሞም፦ እነሆ እኔም እግዚአብሔር የሰጠኝንም ልጆች ሲል ወንድሞች ብሎ ሲጠራቸው አያፍርም (ዕብ 2:13)::*

*እኔስ በእግዚአብሔር ቤት እንደለመለ እንደ ወይራ ዛፍ ነኝ ለዓለም እና ለዘላለም በእግዚአብሔር ምህረት ታመንኩ (መዝ 51:8)::*

*አድርገህልኛልና ለዘላለም አመሰግንሀለሁ ፤ በቅዱሳንህም ዘንድ መልካም ነውና ስምህን ተስፋ አደርጋለሁ (መዝ 51:9)::*

*በታላቅ ጉባኤ ፅድቅንም አወራሁ እነሆ ከንፈሮቼን አልከለክልም አቤቱ አንተ ፤ ጽድቄን ታውቃለህ (መዝ 40:9)::*

*እውነትህንም በልቤ ውስጥ አልሰወርኩም ፤ ማዳንህንም ተናገርኩ ምህረትና እውነትህን ከታላቁ ጉባኤ አልሰወርኩም (መዝ 40:10)::*

***11:23 - 24 እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ እግዚአብሔር መልሶ ሊያገባቸው ይችላልና:: አንተ በፍጥረቱ የበረሀ ከነበረ ወይራ ተቈጥረህ እንደ ፍጥረትህ ሳትሆን በመልካም ወይራ ከገባህ ይልቁንስ እነዚያ በፍጥረታቸው ያሉት ቅርንጫፎች በራሳቸው ወይራ እንዴት አይገቡም?***

ያላመኑት አህዛብ እግዚአብሔር ቸርነቱን አብዝቶላቸው ልባቸውንም አቅንቶ ወደዚህ በረከት ካስገባቸው የአብርሃም ዘር ሆነው ላላመኑትም ይህንኑ ሊያደርግላቸው ይችላል:: ጸጋውን ሰጥቶ እንዲያስተውሉም በማድረግ ወደራሱ ሊያመጣቸው ይችላል:: ( ያዕ 1:17፤ ዘዳ 30:3፤ ሮሜ 11:4፤ ኤር 31:17 ) ልባቸው ወደ እምነት ሲመጣ የበረከቱ ተካፋዮች ይሆናሉ

*በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ (ያዕ 1:17)::*

*አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልሳል ይራራልሀማል አምላክህም እግዚአብሔር አንተን ከበተነበት ከአህዛብም ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሀል (ዘዳ 30:3)::*

*ለበአል ያልሰገዱትን ሰባት ሺ ሰዎች ለእኔ አስቀርቻለሁ (ሮሜ 11:4)::*

*ለፍፃሜሽም ተስፋ አለ ፣ ይላል እግዚአብሔር ፣ ልጆችሽም ወደ ዳርቻቸው ይመለሳሉ (ኤር 31:17)::*

## 11:25 ወንድሞች ሆይ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ ይህን ሚስጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ የአሕዛብ ሙላት እስኪ ገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆኖባቸው፤

### ልባሞች

ይህ ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን እውቀት ሙላት የተቀበሉና የልባቸው ብርሃን የበራላቸውን ሰዎች ነው:: (ጳውሎስ ግን ከእናንተ የሆነና ከእነርሱ የተሻላችሁ እንዳይመስላችሁ ለማለት ለማስጠንቀቂያነት ተጠቅሞበታል::) ይህ ዓይነቱ መገለጥ ሰው በራሱ የሚያመጣው ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ በጸጋው የሚሰራው ሥራ ነው:: ( ኤፌ 3:3፤ 1:17፤6:19 )

*አስቀድሜ በአጭሩ እንደ ጻፍሁ ፣ ይህን ሚስጥር በመግለጥ አስታወቀኝ (ኤፌ 3:3)::*

*የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብን የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ (ኤፌ1:17)::*

*ደግሞም የወንጌል ሚስጥር፡ በግልጥ እንዳስታውቀው አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ (ኤፌ 6፡19)፡፡*

### *የአህዛብ ሙላት እስኪ ገባ ድረስ*

እግዚአብሔር አብ በዘላለማዊ ዕውቀቱ ከአህዛብ ወደ እርሱ የሚመጡትን ቁጥር እስኪሞላ የሚጠብቅ መሆኑን ያሳያል፡፡

### *እስራዔል በከፊል*

ከእስራዔል አንዳንዶቹ የሚቀበሉ ሲሆን በከፊል ደግሞ በድንዳኔ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

## *11፡26 እስራዔል ሁሉ ይድናል*

ከየትውልዱ የተመረጡትን ጠቅላላ ቁጥር ያመለክታል፡፡ የአህዛብ ሙላት ተብሎ የተጠቀሰውም ቃል ከአህዛብ የተመረጡት ቁጥር እስኪሞላ እንደሆነ ሁሉ ማለት ነው፡፡

የመዳናቸው መሠረት ግን የሞተውንና ከሞት የተነሳውን ክርስቶስን ማመን ነው፡፡ « አዳኝ » ወይም « ቤዛ » የሚለው ቃል የተወሰደው ከኢሳ 59፡20 ነው ፡፡

*ለጽዮን ታዳጊ ይመጣል በያዕቆብም ዘንድ ለሚርቁ ይላል እግዚአብሄር (ኢሳ 59፡20)፡፡*

## *11፡27 ኃጢአታቸውንም ስወስድላቸው ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው፡፡*

እግዚአብሔር ከአብርሃም ዘር ጋር የዘላለም ኪዳን ገብቷል፡፡ አሁንም ከኃጢአታቸው ካዳናቸው በኋላ ኪዳኑን ያጸናል፡፡ ( ኢሳ 55፡3፤59፡21 ፤ ኤር 31፡31-34፤32፡38-40 ፤ዕብ 8፡8-12፤10፡16 )

*ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደእኔም ቅረቡ ስሙ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች የታመነችቱን የዳዊትን ምሕረት ፣ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ (ኢሳ 55:3)።*

*ከእነርሱ ጋር ያለው ቃል ኪዳን ይህ ነው ይላል እግዚአብሔር። በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ በአፍህ ውስጥ ያደረኩት ቃሌ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ከአፍህ ከዘርህም አፍ ከዘር ዘርህም አያልፍም ፣ ይላል እግዚአብሔር (ኢሳ 59:21)።*

*እነሆ የእስራኤልን ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምነባበት ቀን ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልፀኑምና ፣ እኔም ቸል አልኋቸው ፣ ይላል እግዚአብሔር። ከነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የገባሁት ቃል ኪዳን ይህ ነውና ፣ ይላል እግዚአብሔር። ህጌን በልቦናቸውም አኖራለሁ ፣ በልቦናቸውም እጽፋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ህዝብ ይሆኑኛል። ኢየንዳንድ ሰው ባልንጀራውን ፣ እያንዳንዱም ወንድሙን እግዚአብሔርን ወርዶ አያስተምርምና ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛል ፣ ይላል እግዚአብሔር። በደላቸውን እምራቸዋለሁና ፣ ኃጢያታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና (ኤር 31:31-34)።*

*እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናችኃለሁ ። ለእነርሱም ከእነርሱም በኃላ ለልጆቻቸዉ መልካም ይሆንላቸዉ ዘንድ ለዘላለም እንዲፈሩኝ አንድ ልብ እና አንድ መንገድ እሰጣቸዋለሁ(ኤር 32:38-40 )።*

*እነርሱን እየነቀፈ ይላቸዋልና ፦ እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል ጌታ ከግብጽ አገር አወጣቸዉ ዘንድ እጃቸውን በየዘሁበት ቀን ከአባቶቻችን ጋር እንደገባሁት ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልፀኑምና፣ እኔም አልኳቸዉ ይላል ጌታ። ከዚህ ወራት በኃላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባዉ ቃል ኪዳን ይህ ነዉና ይላል ጌታ ሕጌን በልቦናቸዉ አኖራለሁ በልባቸዉም እፅፋለሁ ፣ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ህዝብ ይሆኑኛል (ዕብ 8:8-12)።*

*መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናል ከዚህ ወራት በኃላ ከእነርሱ ጋር የምገባዉ ኪዳን ይህ ነዉ ይላል ጌታ በልባቸዉ ሕጌን አኖራለሁ በልቦናቸዉም እጽፈዋለሁ (ዕብ 10:16)።*

## *11:28 በወንጌል በኩል ስለ እናንተ*

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር ስለ እስራኤል ያለውን ሁለት ዘርፍ ያለው አመለካከት ይገልጣል።

እስራኤል ባለማመናቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣላ ፊቱን ወደ አህዛብ ሲያዞር አህዛብ ደግሞ ሲቀበሉ አህዛብ ተጠቀሙ በጠላትነታቸው ለአህዛብ በረከት ሆኑ።ባለማመናቸው ምክንያት ሆኑ እንጂ እግዚአብሔር ጠላቸው ማለት አይደለም።

*ስለ አባቶች*

ስለ አባቶች የሚለው ቃል ከአባቶች የተላለፈ መልካም ነገር አለ ለማለት ሳይሆን ባመኑት ጊዜ የገባውን ቃል ኪዳን ሊያጥፍ የማይችል የታመነ አምላክ በመሆኑ ከዚያ ቃል ኪዳን የተነሳ የሚያስባቸው መሆኑን ያመለክታል።

## *11:29 እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና።*

የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) እግዚአብሔር ኪዳኑንም ሆነ « ልጄ! » ብሎ የጠራበትን ጥሪ አይለውጥም ሕያው ቃሉንም አይሽርም (ዕብ 6:13 )።

> *እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ በእውነት እየባረክሁ እባርክሃለሁ እያበዛሁም አበዛሃለሁ ብሎ ፣ ከእርሱ የሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ ፣በራሱ ማለ (ዕብ 6:13)*

## *11:30 - 32 እናንተም ቀድሞ ለእግዚአብሔር እንዳልታዘዛችሁ አሁን ግን ከአለመታዘዛቸው የተነሳ ምህረት እንዳገኛችሁ እንዲሁ በተመራችሁበት ምሕረት እነርሱ ደግሞ ምሕረትን ያገኙ ዘንድ እነዚህ ደግሞ አሁን አልታዘዙም። እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን በአለመታዘዝ ዘግቶታልና።*

*እናንተም*

ከአህዛብ የዳኑትን ያመለክታል።

- ከእነርሱ አለመታዘዝ የተነሳ እናንተ ምህረትን አገኛችሁ
- እነርሱም ታዝዘው ወደ ምህረት የሚመጡበት ዘመን አለ

***ምህረት የሚገኘው በመታዘዝ ነው። መታዘዝ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሚሆን መታዘዝ ነው። ምህረትን ያገኘነው አምነን ነው። በእርሱ ተስፋ ስላደረግን ነው። ይህ ማለታችን ግን ምህረትን ለማግኘት የሚያስችለን ዋጋ የሆነው መታዘዛችን ነው ማለት አይደለም።ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ ብቁ መሆኑን ስናምን ከዚያም እምነት ተነስተን የመታዘዝን ብቃት በጸጋው አገኘ ን ለማለት ብቻ ነው።***

***11:33 የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።***

የእግዚአብሔር የዕውቀቱ ባለጠግነትና የጥበቡ ጥልቀት ወሰን የለውም ( 1ቆሮ 2:10 ) ይህም ጥበብና ዕውቀት ከምህረቱ ጋር የሚሄድ ነው።

ፍርዱም የማይመረመር ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን ባለመታዘዝ መዝጋቱ የማይመረመር ፍርዱ አንዱ ምልክት ነው።ይህም የእርሱን ዘላለማዊ ዕቅድና ፍትሐዊ ክያኔውን ያሳያል። እኛ ውስን ስለሆንን ይህንን ተረድተን አንጨርሰውም።

*መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው (1ኛቆሮ 2:10)::*

## *11:34 የጌታን ልብ ያወቀ ማን አለ?*

በጌታ ልብ ( አሰምሮ ) ውስጥ ያለውን ያወቀ ጥንትም አሁንም ወደፊትም ማንም የለም:: ጥልቅና ከመረዳት ሁሉ የሚያልፍ ነው::

*አማካሪው ማነው?*

ልዑል እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ውስጥ ያንንና ይህንን አድርግ ብሎ ምክር ሰጥቶት የሚያውቅ ማንም የለም:: ( በመሰረቱ ሁሉን ሠርቶ የጨረሰው የትኛውም ፍጥረት ከመምጣቱ በፊት ስለሆነ ሊያማክረው የሚችል የለም )

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታ የበላይነት ብዙ ቦታ ላይ ጠቅሶ ያስተምረናል ( ኢሳ 40:13 ፤ ኢዮብ 15:1-19 ፤ ኤር 23:18 ):: ይህንንም ትልቅነቱን በልዩ ልዩ ጎዳና ሲገልጽ ቆየና በመጨረሻም ልጁን ላከልን(ዮሐ 1:8 ፤ ዕብ1:1-2 ):: ወደዚህ ትልቅ መረዳት መግባት የምንችለው በጸጋው ብቻ ነው (ኤፌ 1:9-10 ፤ 2ኛ ቆሮ2:9፤12፤16)::

> *የእግዚአብሔርም መንፈስ ያዘዘ ፤ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማነው? ( ኢሳ 40:13)::*

> *ቴማናዊውም ኤልፋዝ መለሰ እንዲህም አለ በውኑ ጠቢብ ሰው እንደ ነፋስ በሆነ እውቀት ይመልሳልን? በሆዱስ የምስራቅን ነፋስ ይሞላልን ከማይረባ ነገር ፤ ወይስ ከማይጠቅም ንግግር ጋር ይዋቀሳልን? አንተም እግዚአብሔርን መፍራት ታፈርሳለህ በእግዚአብሔር ፊት አምልኮን ታስቀራለህ:: በበደልህ አፍህን ያስተምረዋል የተንኰለኞችንም አንደበት ትመርጣለህ የሚፈርድብህ አፍህ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም ከንፈሮችህም ይመሰክሩብሃል:: በውኑ መጀመሪያ የተወለድክ ሰው አንተ ነህን ወይስ ከተራሮች በፊት ተወለድህን? የእግዚአብሔርንስ ምስጥር ሰምተሃልን? ወይስ ጥበብን ለብቻህ አድርገሃልን እኛ*

*የማናውቀው እንተ የምታውቀው ምንድን ነው? ከእኛ ዘንድስ የሌለው የምታስተወለው ምንድን ነው? በእድሜ ከአባትህ የሚበልጡ ሽበትም ያላቸው ሽማግሌዎች ከእኛ ጋር አሉ:: በውኑ እግዚአብሔር ማጽናናት ፣ በየዋህነትም የተነገረ ቃል ጥቂት ነውን? ልብህስ ለምን ይወስድሃል? አይኖችህስ ለምን ይገለጣሉ? በእግዚአብሔር ላይ መንፈስህን እስከ ማንሳት ደርሰህ ይህንም ቃል ከአፍህ እስከማውጣት ደርሰህ ንጹህ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድን ነው? እነሆ ፣ በቅዱሳኑ ስንኳ አይታመንም ሰማያትም በፊቱ ንጹህን አይደሉም:: ይልቁንስ አጸያፊና የረከሰ ፣ ኃጢያትንም እንደ ውሀ የሚጠጣ ምን ያህል ያንስ? ምድሪቱ ለብቻቸው ተሰጥታ ነበር በመካከላቸውም እንግዳ ያላገባችሁ ጠቢባን ከአባቶቻቸው ተቀብለው የተናገሩትን ያልሸሸጉትንም ፣ እገልጥልሀለሁ ፣ ሰማኝ ያየሁትንም እነግርሀለሁ:: (ኢዮብ 151-19)::*

*ሐይሉን ያይና ይሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ምክር የቆመ ማነውና? ቃሉን ያደመጠ የሰማስ ማነው? (ኤር 23:18)::*

*ስለ ብርሀን ሊመሰክር መጣ እንጂ ፣ እርሱ ብርሀን አልነበረም (ዮሐ 1:8)::*

*በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ ሀሳቡ የፈቃዱን ምስጢር አስታውቆናልና (ኤፌ 1:9)::*

## *11:35 ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው?*

እግዚአብሔር የማንም ባለ ዕዳ ሆኖ አያውቅም:: እኛም ፍጥረቱ ስለሆንን የሆነው ሁሉ ከእርሱ የተነሳ ነው:: የምናደርገው የትኛውም ነገር ሁሉ ከእርሱ የተሰጠንና በክርስቶስ የተዘጋጀ ነው:: የጸጋው ባለቤት እርሱ ነውና ከኛ የሆነ ነገር የለም ስለዚህ ይህን አድርጌልሃለሁና ዕዳ አለብህ ሊባል አይችልም ( ኤፌ 2:10፤ 1ቆሮ 3:5፤ 4:7፤ ኢዮብ 4:3 )::

*እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔርን አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ስራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን (ኤፌ 2:10)::*

*አጵሎስ እንግዲህ ምንድር ነው? ጳውሎስ ምንድር ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው ለያንዳንዳቸውም ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግላሉ (1ኛ ቆሮ 3:5)::*

*አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎህል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው? (1ኛ ቆሮ 4:7)።*

*እነሆ ፣ አንተ ብዙዎችን ታስተምር ነበር ፣ የደከሙትንም እጆች ታበረታ ነበር ፣ (ኢዮ 4:3)።*

***11:36 ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን።***

ሐዋርያው ይህንን ድንቅ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አሰራርና ድንቅ ምርጫ ደግሞም ማስጠንቀቂያ ያዘለ ምዕራፍ የሚዘጋው የተፈጠረውም የሆነውም ሊሆን ያለውም ሁሉ ከእርሱ በእርሱና ለእርሱ የፍጻሜ ምስጋናና ክብሩም ተጠቅልሎ ለእርሱ ብቻ ሊሆን እንደሚገባው በመግለጽ ነው ( ኢዮብ 42:2፤ ራዕ 22:13 )።

*ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ ሀሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ (ኢዮ 42:2)።*

*አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ (ራዕ 22:13)።*

## የምዕራፍ አሥራ አንድ ማጠቃለያ

አብርሃም የጸደቀው በእምነት ነው፤ ወገኖቹም ሊጸድቁ የሚችሉት በእምነት ነው። ባለማመናቸው ከወይራው ተገንጥለው ወጡ የበረሃው ወይራ ደግሞ በእምነት ግንዱ ውስጥ ገባ። በመግባቱ ግን ሊኩራ አይገባም ይልቁኑ በፍርሃትና በጥንቃቄ በእምነትም በመጽናት ሊቆይ ይገባዋል። የተቆረጠውም ያመነ ቀን ተመልሶ ይገባል።

ከሰው የሆነ ነገር የለምና ሰው ሁሉ አይመካ ሁሉን ላደረገ ለእርሱ ግን ክብር ምስጋናና ውዳሴ ያምጣ።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት
# ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት

ሐዋርያው ጳውሎስ በአብዛኞቹ መልዕክቶቹ እንደሚያደርገው ሁሉ የመልዕክቱ ማጠቃለያ ምዕራፎች ውስጥ ከዚህ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ያነሳቸው አስተምህሮዎች በተግባር የሚገለጡበትን ተዛምዶአዊ ትምህርቶች ይጽፋል።በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ውስጥ ሊነጣጠሉ የማይችሉ እውነቶች ቢኖሩ አስተምህሮና ተግባራዊነታቸው ናቸው። የተማረውን በተግባር ማዋል ከአንድ የክርስቶስ ተከታይ የሚጠበቅ የሕይወት ክፍል ነው። እምነታችን የተመሠረተበት ነገር ባሕርያችንንም ይቀርጸዋል። ጳውሎስ ያስተማራቸውን አስተምህሮዎች መረዳት ብቻ ሳይሆን በህይወታችንም በተግባር የሚገለጡበትንም ማወቅ ይገባናል። ይህንንም የምናደርግ ከሆነ በእግዚአብሔር ቃል የምንታመን መሆናችንን በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያችን እንገልጣለን። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ሕብረት የሚኖረን ከሆነ ከወንድሞቻችን ጋር ተመሳሳይ ጤነኛ ግንኙነት ይኖረናል፤ ካልሆነ ግን ዮሐንስ በመልዕክቱ እንዳለው ይሆንብናል ( 1ዮሐ 4:20 ) ።

*ማንም ፦ እግዚአብሄርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሄርን ሊወደው እንዴት ይችላል? (1ኛ ዮሐ 4:20)።*

***12:1 እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።***

*እንግዲህ*

ሐዋርያው ይህንን ቃል በመልዕክቱ ለአራተኛ ጊዜ ማንሳቱ ነው። ሁሉም የየራሳቸው አገባብ አላቸው። በአማርኛችን ሁለቱ «ስለዚህ» ሁለቱ ደግሞ «እንግዲህ» ተብለዋል። በእንግሊዝኛው ግን አራቱም « Therefore » ተብለው ነው የተጻፉት።

1. ሮሜ 3:20 = ሁሉ ኃጢአት በመስራታው ምክንያት የተረገሙበትን ማንም ጻድቅ የለም ተብሎ የተኮነነበትን ሁኔታ ለመግለጥ ገብቷል
2. ሮሜ 5:1 = በእምነት መጽደቅን ለማመልከት ገብቷል
3. ሮሜ 8:1 = በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ከኩነኔ ነፃ መሆናቸውን ለማመልከት ገብቷል
4. ሮሜ 12:1 = ራስን ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጎ ማቅረብን ለማመልከት ገብቷል

*ወንድሞች*

ይህ ቃል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የምህረት አሠራር የጸጋው ተካፋይ የሆኑትን ነው።

*ሰውነታችሁን*

ሙሉ መሰጠት ያለበትንና ተመልሶ የራስ ሊሆን የማይችለውን ሁለንተናን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያመለክት ቃል ደረጃውም ለመስዋዕት የሚቀርብ እንስሳ ጨርሶ ለመቃጠል በሚቀርብበት ዓይነት ነው።

*ደስ የሚያሰኝ ሕያውና ቅዱስ*

ይህ እንደ መስዋዕት የምናቀርበው ህይወት ቅዱስ ደግሞ ሙት ያልሆነ ሕያው ሆኖ በእንቅስቃሴ ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሆን ይገባዋል።

*እለምናችኋለሁ*

ጳውሎስ ይህንን የመሰለውን መስጠት እንዲያሳዩ በልመና መልክ ያቀረበበት ምክንያት ግልጽ ነው። ትዕዛዙ የጌታ ትዕዛዝ ቢሆንም ሰው ትዕዛዙን መፈጸም ያለበት በፍጹም ፈቃደኝነት ፣ ገብቶትና ተረድቶ ሊሆን ይገባዋል። ጸጋው ሁሉን የመግዛት ኃላፊነት አለው። ይህ መግዛቱ በተግባር የሚገለጠው ፈቃዱን የሚሰጠውና ሙሉ ለሙሉ ለጸጋው አሠራር ራሱን የሚያቀርብ ሲገኝ ነው። ስለዚህ ከእግዚአብሔር በሆነውና ልብን በሚነካው የርህራሄ መንፈስ መባረካቸውንና እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘታቸውን በሚናፍቅ የአባት ልብ ይለምናቸዋል።

*ለአዕምሮ የሚመች አገልግሎት*

ለአዕምሮ የሚመች አገልግሎት ሊወጣ የሚችለው እግዚአብሔር በቸርነቱና በጸጋው ቅዱሳንና ነውር የሌለብን አድርጎ እንደ ሠራን በማወቅና ከልብም በመረዳት ራስን መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ ሲቻል ነው።

ጌታ ቤተ መቅደሱ ( ቅዱስ ማደሪያው ) አድርጎናል። ከጸጋውም ብርታትና ብቃት የተነሳ በእኛ ይኖራል ይመላለሳልም እንጂ ጌታ በእኛ ውስጥ እንዲሠራ የሚጋብዘው መልካምነት በእኛ ውስጥ የለም። ብቃትን ያገኘነው ከጸጋው የተነሳ ነው። ስለዚህ በእርሱ ብቃት ሥራውን በእኛ ሲሠራ ይህንን የመሰለው አገልግሎት ለአዕምሮ የሚመች አገልግሎት ይሆናል ( 2ኛ ቆሮ 6:16፤ ሮሜ 5:21፤ ሮሜ 8:3 )።

> *የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲህ ሲል:- በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ ፤ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆናሉ (2ኛቆሮ 6:16)::*

***12:2 የእግዚአብሐር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታወቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን አለም አትምሰሉ::***

### *የእግዚአብሐር ፈቃድ*

ሰው የራሱ ፈቃድ አለው:: በሰው ህይወት ውስጥ ግን እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ሥራ ሊሰራ የሚችለው የሰው ፈቃድ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሲገዛ ነው:: ለፈቃዱ ለመገዛት ደግሞ ፈቃዱን መረዳት ያስፈልጋል::

### *ታውቁ ዘንድ*

ሐዋርያው ታውቁ ዘንድ ብሎ ያስቀመጠው ይህ መግለጫ ከአዕምሮ ዕውቀት ያለፈና በህይወት ተፈትኖ ከሚመጣ መረዳት የሚገኘውን ዕውቀተ የሚገልጥ ነው:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ለኛ ዳገት መሆን የለበትም::

ምክንያቱም ክርስቶስ ኢየሱስን ስለሰጠን :: በእርሱም አማካይነት በጸጋው ሥራ የክርስቶስ ልብ ስላለን:: በልባችን በተፃፈ የአዲስ ኪዳን ህግ ስለምንመራ:: ይህም በክርስቶስ ባገኘነው አዲስ ህይወት በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ በመግዛት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በቀላሉ መረዳት እንችላለን ይህ የጸጋው መንፈስ በህይወታችን ስላለ የህይወት አቀጣጫችንና ምርጫችን መንፈሳዊ ሆኗል:: በዚህም መንገድ እያደገ ይሆናል ( ዕብ 8:10 - 11፤ 1ቆሮ 2:16፤ ሮሜ 7:6)::

> *ከዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና ይላል ጌታ ህጌን በልቦናቸው አኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ህዝብ ይሆኑኛል:: እያንዳንዱም ጎረቤቱን እያንዳንዱም ወንድሙን :- ጌታን እወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ያውቁኛልና (ዕብ 8:10-11)::*

*እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን (1ኛ ቆሮ 2:16)።*

*አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን ከሕግ ተፈትተናል ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም (ሮሜ 7:6)።*

## *በልባችሁ መታደስ ተለወጡ*

በአዕምሮ መታደስ የሚገልጥ ሲሆን ይህም ውስጣዊ የሀሊና መንፃትን፣ የአስተሳሰብንና የአመለካከት መለወጥን ያመለክታል፤ ይህ ዓይነቱ ለውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚመጣ ነው። ይህም ህይወት በኛ ዘወትር ይገለጥ ዘንድ ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ህብረት እንድናደርግና የመንፈስ ቅዱስንም ምሪት እንድንከተል ያስፈልጋል ( ሮሜ 6:4፤ 2ቆሮ 3:18 ) ።

*እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን (ሮሜ 6:4)።*

*እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስታወት እያበለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደ ሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን (2ኛ ቆሮ 3:18)።*

## *ይህን ዓለም አትምሰሉ*

ዓለም የራሷ የሆነ የህይወት ዘይቤ አላት። የክርስቶስ የሆኑት ክርስቲያኖች ደግሞ የክርስቶስ የሕይወት ዘይቤ አላቸው። ስለዚህ ባህርያቸውና ስነ - ምግባራቸው የጌታን ፈቃድ የሚያደርግና የክርስቶስን ህይወት የሚገልጥ መሆን ይገባዋል ( ኤፌ 4: 23 - 24 )።

አዲሱ ሰው የተፈጠረው ክርስቶስን እንዲመስል እንጂ ዓለምን እንዲመስል አይደለም።

*12:3 እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ።*

*በሰጣችሁ . . . መጠን*

እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል ብልቶች ሆነን ክርስቶስ ራስ ሆኖ የምንቀሳቀስበትንና የጌታን ፈቃድ የምንፈጽምበትን ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ ሰጥቶኗል። ይህም ስጦታ ለሁሉም እኩል ነው። ሥራው የተለያየ ቢሆንም ከሰጪውና ከስጦታው ጠቀሜታ አንፃር ሚዛናቸው እኩል ነው። ሁሉም ያስፈልጋሉ።

ሐዋርያው በዚህ ስፍራ የሚያመለክተው የሰጠንን አውቀን መስማራት በጣም ጥቅም አለው። ነገር ግን ለራስ ከፍተኛ ግምት መስጠትና የኔ ለየት ያለ ነው ማለት ወይም በተቃራኒው የኔ አይረባም ብሎ በተሰጠው አለመጠቀም ሁለቱንም እግዚአብሔር አይወዳቸውም።

*12:4 - 5 በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።*

*አካል . . . ብዙ ብልቶች. . . አንድ*

አካሉ አንድ ነው ብልቶች ግን ብዙ ናቸው። ሥራቸውም የተለያየ ነው። የሁሉም ግን ለአካሉ ሕያውነት ያስፈልጋሉ። እኛም በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለን ክርስቲያኖች በአካሏ ውስጥ የምናከናውናቸው በርካታ ሥራዎች አሉ። ለተሰጡንም ሥራዎች ባለ አደራዎች ነን።

ብልት ሕያው የሚሆነው በአካሉ ውስጥ ሲሆን ነው የየራሳችን ሥራ ቢኖረንም አንድ ነን። መለያየት አንችልም። ያለ ሌላው አካል ድጋፍ ምንም ለብቻችን የምንሠራው ነገር የለም።

***12: 6 - 8 እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ የሚገዛ በትጋት ይግዛ የሚምር በደስታ ይማር።***

ሐዋርያው በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በአካሏ ውስጥ እግዚአብሔር ለሥራው ማለትም ለቤተክርስቲያን መታነጽና ለቅዱሳን ሕይወት መገንባት የሰጣቸው ልዩ ልዩ ስጦታዎች አሉ። እነዚህ ስጦታዎች ሁሉ ያስፈልጋሉ፣ አንዳቸው ከሌላቸው አይበልጡም።

- የጠባነው መንፈስ አንድ ነው ስጦታው ግን ልዩ ልዩ ነው።
- አገልግሎት ልዩ ልዩ ነው የምናገለግለው ጌታ ግን አንድ ነው።

ስለዚህ ሁላችን አንዱን ጌታ ደስ ለማሰኘት በተሰጠን መጠን በተሰጠን ስፍራና ጸጋ በታማኝነት ያለማበላለጥ እኩል በሆነ ሁኔታ ማገልገል አለብን።

አሁን ባለንበት ዘመን ግን በጸጋ ስጦታዎች መካከል ልዩነት አለ። እንዲያው ለአገልግሎት ሰዎችን ስንጋብዝ እንኳን « የጸጋ አገልጋይ » የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መጠሪያ እንጠቀማለን። ጳውሎስ ግን በዚህ ክፍል ሁሉም ስጦታዎች ከተሰጠን ጸጋ የወጡ « የጸጋ አገልግሎቶች » ናቸው ይለናል።

<u>ትንቢት</u> ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን እንናገር - በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆነ ሁሉ ትንቢት ይናገራል (ይችላል)። ለሁላችን እኩል እምነት እንደተሰጠን እንደዚሁ ስለጌታ አዳኝነት መናገር እንችላለን። በዚህ ክፍል የተገለጠው ትንቢት የነቢያትን ቢሮ አያሳይም ይልቁንም ለማነፅ፣ ለመምከርና ለማፅናናት የሚውለውን አገልግሎት እንጂ። በ1ቆሮ 14:3 የተጠቀሰው ሁሉንም የሚያመለክት ሲሆን የኤፌሶኑ ቢሮን ይገልጻል እነርሱም አንዳንዶች ናቸው (ኤፌ 4:11)።

> *ትንቢት የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰዉ ይናገራል (1ቆሮ 14:3)።*

*እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋሪያት፣ ሌሎችም ነቢየት ፣ሌሎችም ወንጌል ሰባኪዎች ፣ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ (ኤፌ 4:11)።*

«የምክር አገልግሎት» ሁል ጊዜ በቃሉ በማፅናናት መልክ አገልግሎት የሚያቀርቡትን ያመለክታል (ሥራ 13:15 ፣20:2 ) «የሚሰጥ» የልግስና አገልግሎት የሚሰጡትን የሚገልጽ ሲሆን ይህም ምድራዊ የሆነ ንብረትን የሚመለከት ነው። «ማስተዳደር» እነዚህ ሰዎች ከመጋቢነት ጋር አብረው ሊወስዱ ይችላሉ (1ተሰ 5:12፣ 1ጢሞ5:17)። «የሚምር» ሁላችን የይቅርታና የምህረት ህይወት ሊኖረን ሲገባ እነዚህ ሰዎች ግን ከሌሎቻችን የበለጠ አገልግሎት በደስታ የሚሰጡ ናቸው።

«አገልግሎት» የድቁና (ዲያቆናት) አገልግሎት ነው (የሐሥራ 6:2)። «አስተማሪዎች» ሲል ከአምስቱ የአገልግሎት ቢሮዎች መካከል ያለውን የአስተማሪነት ስጦታ (ኤፌ 4:11) አይደለም። ማስተማር የሚችሉ ማናቸውንም ሰዎች የሚያመለክት ነው። ይህም ከጌታ የተሰጠ ስጦታ ነው (ሥራ 18:24)።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን በዚህ ነገር ጥንቃቄ በማድረግ ሁሉም ብልቶች ያለ መበላለጥ የተሰጣቸውን ጸጋ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማስቻል መድረክም ማመቻቸት ይገባታል።( ሮሜ 5:1፤ 1ቆሮ 14:3፤ ኤፌ 4:11፤ የሐሥ 18:24 ) በመድረክ ላይ ቆመው የሚሰብኩትና ቤት ለቤት እየዞሩ ልባቸው ያዘነውን የሚያጽናኑ እኩል ናቸው። ሁለቱም አካሏን ያንፃሉ( ሐሥ 13:15፤ 20:2፤ 1ተሰ 5:12፤ 1ጢሞ 5:17)።

*በወንጉም የእስክንድሪያ ሰዉ የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጵሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰዉ ወደ ኤፊሶን ወረደ እርሱም በመጻፍት እዉቀት የበረታ ነበር (ሥራ 18:24)።*

*ሕግና ነቢየትም ከተነበቡ በኋላ የምኩራቡ አለቆች ወንድሞች ሆይ ህዝብን የሚመክር ቃል እንዳላችሁ ተናገሩ ብለዉ ላኩባቸዉ (ሥራ 13:15)።*

*ያንም አገር እየለፈ በብዙ ቃል ከመከራቸዉ በኋላ ወደ ግሪክ አገር መጣ (ሥራ 20:2)።*

*ወንድሞች ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙችሁን የሚገስጿችሁንም ታውቁ ዘንድ ስለ ሥራቸዉም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሯቸዉ ዘንድ እለምናችኋለሁ (1ኛ ተሰ 5:12)።*

*በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግለዎች፤ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፤ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል (1ጢሞ 5:17)።*

## 12:9 ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፋውን ነገር ተጸየፉት ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ፤

### ግብዝነት የሌለው ፍቅር

- የማስመሰል ያልሆነ በአንደበት የሚነገር በተግባርም የሚገለጥ ። በሥራና በእውነት የሚገለጥ የወንድማማቾች ፍቅር ነው።
- በዚህ ፍቅር ውስጥ እንዳንገባ የሚያደርገን የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ክፉ የሚያመጣቸው ክፉ ነገሮች ናቸው ሐዋርያው መድሐኒቱን ሲነግረን « ክፉውን ተጸየፉት! » ይለናል። ክፉውን ስንጠየፍ ወንድሞቻችንን በክፋት ከመፈለግ ይልቅ በፍቅር እንቀርባቸዋለን፤ በፍቅርም እናገለግላቸዋለን አገልግሎታቸውንም እንቀበላለን (1ጴጥ 1:22፤ 1ዮሐ 3:18)።

*ለእዉነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ (1ኛ ጴጥ 1:22)።*

*ልጆቼ ሆይ፤ በሥራና በእዉነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ (1ኛ ዮሐ3:18)።*

## 12:10 በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤

ሐዋርያው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የመከባበር ደረጃ በዚህ ቁጥር ውስጥ ያስቀምጣል። ይህም አንዱ ከሌላው እንደሚሻል በማሰብ የተሞላ፤ ትህትናና ቅንነት የሞላበት ነው።

ፍቅሩም የአንድ አባት ልጆች የሚታይባቸውን ዓይነት የወንድማማችነትን መዋደድ የሚገልጥ ነው።

### *12:11 በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ ለጌታ ተገዙ፤*

ሐዋርያው በቀደመው ቁጥር ውስጥ አገልግሎታችን መከባበር የሞላበትን በወንድማማች ፍቅር የታጀበ መሆኑን ከገለጠ በኋላ በዚህኛው ቁጥር ደግሞ አገልግሎታችን ሊከናወን የሚገባበትን የግለት መጠን ይገልጣል።

**አገልግሎት በሁለት መንገድ ሊከናወን ይችላል**

1. በዕዳ፣ መቼስ ምን ይደረግ እየተባለ ያለ ደስታና ያለ ኃይል በግፊት። ይህ ዓይነቱ አገልግሎት የሰዎች ፊት እየታየ ታዛቢ እየተፈራ፣ ደግሞም ቀን እስኪወጣ ድረስ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

2. በደስታ ፣ እንደ ትልቅ መታደል እየተቆጠረ ያለ አንዳች ቀስቃሽና ጎትጓች የጌታን ቸርነትና ፍቅር እያሰቡ ያለ መታከት ሊደረግ ይችላል።

እግዚአብሔር የሚፈልገው ሁለተኛውን ነው። ይህን መሰል አገልግሎት ለመስጠት ግን ዘወትር በመንፈስ ግለት ውስጥ መሆን ይገባል።

መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያስደስት እኛንም ከመፍጨርጨር የሚያወጣን ዘወትር የምናደርገው እንቅስቃሴ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላና የታገዘ ሲሆን ነው።

ብዙ ሰዎች በአዲስ ህይወት ውስጥ ባሉ ጊዜ በጌታ መንፈስ ውስጣቸው ይቀጣጠል በነበረ ጊዜ አገልግሎት ደስ ይላቸዋል ያለ መታከትም ያከናውኑታል። ጥቂት ሲቆዩ ግን ያ ግለታቸው ይጠፋል ይቀዘቅዛሉ አገልግሎትም ዳገት ይሆንባቸዋል።

### *12:12 በተስፋ ደስ ይበላችሁ በመከራ ታገሡ በጸሎት ጽኑ፤*

በዚህኛው ቁጥር ውስጥ ደግሞ ሐዋርያው የመንፈስ ግለት የሚያቀዘቅዙ ነገሮችን ይጠቅሳል። እነርሱም በምንኖርባት ዓለም የሚገጥመን የሕይወት ውጣ ውረዶች መገለጫዎች ናቸው።

*በተስፋ ደስ ይበላችሁ*

ክርስቶስን ተስፋ አድርጉ ፣ ከእርሱ ጋር የሚጠብቃችሁን ክብር አስቡ ያን ጊዜ ግለታችሁ አይቀዘቅዝም።

*በመከራ ታገሡ*

መከራ በባህርዩ ትዕግሥት ያሳጣል የመንፈስ ግለት በውስጣችሁ ሲኖር ግን የመንፈስ ፍሬ የሆነው ትዕግሥት ይመጣና ይሸፍናችኋል በትዕግሥትም ታልፋላችሁ።

*በጸሎት ጽኑ*

እግዚአብሔር መልስ እስኪሰጥ ድረስ አለመታከትን ያመለክታል ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት የሚደረግበት የሕይወት ዘይቤ እንጂ ሃይማኖታዊ ስርዓት አይደለም ( ገላ 5:22፤ ኤፌ 6:18)።

> *የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት ፣በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነዉ (ገላ5:22)።*
>
> *በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ በዚህም ሃሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ (ኤፌ6:18)።*

***12:13** ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።*

የወንድማማች ፍቅር በተግባር የሚገለጥ እንጂ የአንደበትና ሞቅ ያለ ሰላምታ ብቻ አይደለም።ሐዋርያው በዚህ ክፍል ፍቅራችሁ ለተቸገሩት ወንድሞች በችግራቸው በመድረስና ካላችሁ በማካፈል ይገለጥ ይላቸዋል።

እንግዶችን በቤታችን ተቀብለን ስናስተናግድም ቤት የእግዚአብሔር ማለታችን ነው። የእግዚአብሔር ቤት ደግሞ የልጆቹ ሁሉ ማረፊያ ነው። ለኔ ቢሰጠኝም በአደራ የአንተም ቤትህ ነውና በነፃነት ተመላለስ ማለት ይገባል። ፈረንጆቹ ይህንን የተረዱት ይመስላሉ « Fell at home » ይላሉ።

***12:14 የሚያሳድዱአችሁን መርቁ መርቁ እንጂ አትርገሙ።***

የሚያሳድዱ ሰዎችን እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው መጸለይ የተለመደ ነው ጳውሎስ ግን የሚያሳድዷችሁን መርቁ ይላል። ልብ ልንለው የሚገባው ነገር ስደት ከውጪ ብቻ ሳይሆን ከውስጥም ሊነሳ ይችላል። ግን ልብ ልንል የሚገባው ነገር ቢኖር ወንድምን መርገም ግን አይፈቀድም። እንኳን መርገም የሚጠላው ነፍሰ ገዳይ ይሆናል።

***12:15 ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ።***

በዚህኛው ቁጥር የተገለጠው ደግሞ በሰዎች ሁኔታ ውስጥ እምነታችን ሳይናጋና አቋማችን ሳይለወጥ የሐዘናቸውና የደስታቸው ተካፋይ መሆን እንደሚገባን ነው።

***12:16 እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ የትዕቢትን ነገር አታስቡ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ።***

ይህ መግለጫ የማይስማሙ የተለያዩ ነገሮች ሊመጡ እንደሚችሉና ከኛ የሚጠበቀው ያልተስማማንበትን ነገር በእግዚአብሔር ብርሃን በቶሎ አስወግደን ተስማምተን መኖር እንደሆነ ያመለክታል። የአንድ አባት ልጆች፣ የአንድ አካል ብልቶች፣ አንዱን መንፈስ የጠጣን አንድ ጌታ ያለን ስለሆነ ሳንስማማ መዝለቅ አንችልም። አለመስማማትን በመንፈሱ ኃይል በማሸነፍ በመስማማት መዝለቅ ይገባናል።

ሐዋርያው በዚህ ስፍራ የኑሮ መበላለጥ የሚፈጥረውን መለያየት በምን መንገድ መፍታት እንደሚገባ በግልጥ አስቀምጧል መፍትሄውም ዝቅ ካሉት ጋር አብሮ ለመኖር መፍቀድና በራስ ስኬትና ሀብት አለመመካት ነው። ዛሬ የታመንንበት ነገር ነገ ጨርሶ ሊከዳን ይችላልና መጠንቀቅ አለብን። በወንድም መኩራት አባትን ማሳዘን ለለውም መሳቂያ መሆን ነው።

***12:17 - 21*** *ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።*

ይህ ክፍል የሚደርስብንን ክፉ ነገር ምን ዓይነት ምላሽ ልንሰጠው እንደሚገባ ነው። ብዙ ሰዎች ይህንን ክፍል በተለያየ መንገድ ይተረጉሙታል። እንዲያውም አንዳንዶቹ « በቀልን ለእግዚአብሔር መተው » ማለት እግዚአብሔር አሳምሮ እንዲቀጣ ለእግዚአብሔር ዱላ የማቀበል ዓይነት ይረዱታል። የክፍሉ ሃሳብ ግን ከዚህ ጨርሶ የተለየ ነው።

*ክፉን በክፉ ለመመለስ ጊዜ አታጥፉ*

ክፉ ለማሰላሰል ጊዜ የለም፡፡ በጎ የሆነውን ለማድረግ ብቻ ነው በክርስቶስ ዳግም የተፈጠርነው፡፡

የሰላሙን ንጉሥ ኢየሱስን ይዘን ከሰው ሁሉ ጋር ( ከማይመቹንም) በሰላም መኖር የሚቻለው የመንፈስ ፍሬ የሆነው ሰላም በውስጣችን ሲሞላ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ራሳቸው በሰላም እየኖሩ ለአካባቢያቸውም ሰላምን የሚያመጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ኢየሱስ « የሚያስተራርቁ ( ሰላም የሚያወርዱ) ብጹዓን ናቸው » ማለቱን መዘንጋት አይገባም ( ማቴ 5:9 )፡፡

*በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና*

የክርስቶስ ፍቅር አስቸጋሪ በሆነው ሁኔታ ውስጥ አስደናቂው የትንሳኤ ሐይል በማያምነው ሰው ላይ ተጽእኖ እንዲመጣ እንደሚያደርግ ያሳያል፡፡ በጥንት ዘመን የከሰል እሳት ያለቀበት ሰው ወደ ጎረቤት በመሄድ የእሳትን ፍም ይለምናል፡፡ ጎረቤቱ ይህን የእሳት ፍም በእራሱ ተሸክሞ ቤቱ ድረስ አምጥቶ ይሰጠዋል፡፡ ይህን አስቸጋሪ ነገር ስላደረገለት ሰውየውን ድርጊቱ ይወቅሰዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ንስሐ ለመግባት ያደረገው ይገፋፋዋል፡፡

በቀል የጌታ ነው ፡፡ ከኛ የሚጠበቀው ጠላቶቻችንን በመልካም ማሸነፍ ነው፡፡ በምድር ከሚገኙ የማሸነፊያ መሣሪያዎች መካከል ወደር ያልተገኘላቸው ክፉን ነገር በመልካም የማሸነፊያ መሣሪያዎች ናቸው ( ዘዳ 32:35፣ ዕብ 10:30፣ ፊሊ 1:9 )፡፡

> *ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ (ፊሊ 1:9)፡፡*
>
> *የጥፋታቸዉ ቀን ቀርቧልና፤ የሚመጣባቸዉም ነገር ይፈጥናልና እግራቸዉ ሲሰነካከል በቀልና ፍርድ የእኔ ነዉ (ዘዳ 32:35)፡፡*

# የምዕራፍ አሥራ ሁለት ማጠቃለያ

የክርስትና ህይወት ሁለንተናን መስዋዕት ተደርጎ ተሰጥቶ የጌታን ፈቃድ ተረድቶ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበት ትልቅ መስጠት ያለበት ህይወት ነው። ፈጽሞ በተለወጠና በታደሰ አዕምሮ የወንድሞችን ጸጋ ተረድቶና ጌታ የሰጣቸውን ስጦታ አክብሮ ፣ የራስንም በሚገባ አውቆ ተቀባብሎ ተከባብሮና ተገጣጥሞ ለአካሏ መታነጽ መትጋት አለበት።

ይህ ሕይወት እውነተኛ የሆነውን በተግባር የሚገለጠው ፍቅር የሚታይበት፣ ከኔ ወንድሜ ይሻላል በመባባል ጠብ ተወግዶ ሰላም የሚሰፍንበት ጠላቶችን እንኳን መልካም በማድረግ ለማሸነፍ የጌታ የማስቻል ጸጋ የሚገለጥበት ህይወት ነው። የተጠራነው ይህንን የመሰለ የሕይወት እርከን ላይ ለመድረስ ጌታን ለማስከበር ነው።

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት
# ፍቅር የሕግ ፍጻሜ

ሐዋርያው በምዕራፍ አስራ ሁለት ውስጥ ከጌታ ጋር ቀጥሎ ደግሞ ከወንድሞች ጋር በሦስተኛ ደረጃም ከጠላቶቻችን ጋር ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነት አስመልክቶ ብርቱ ትምህርት ከሰጠ በኋላ በቀጥታ የሚሻገረው ከባለሥልጣናት ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ነው:: ሐዋርያው በዚህ ክፍል የሥልጣን ምንጭ ማን እንደሆነ ፣ እንዴት መገዛት እንዳለብን ፣ የእንቅስቃሴያችንና የየትኛውም ነገር መለኪያችን ፍቅር ሊሆን እንደሚገባውና የጌታ መመለሻ ቀንም እጅግ በጣም ስለቀረበ በየትኛውም የሕይወታችን ክፍል እንከን ሊገኝብን እንደማይገባ በብርቱ ያሳስባል:: የክርስትና ህይወት በእምነት ጽድቅን ተቀብሎ በዚያው ጽድቅ መስመር እስከ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ድረስ በመዝለቅ የሚጓዙበት የሕይወት ጉዞ መሆኑን ያመለክታል::

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ለባለሥልጣናት መገዛት የሚገባን በሦስት ምክንያት ነው ይለናል

1. ከቅጣት ለመትረፍ = ባለሥልጣናት ጥፋተኛን ለመቅጣት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋልና አለመታዘዝ ራስን ለቅጣት አሳልፎ መስጠት ነው ::

2. ከሕሊና የተነሳ = መንግሥት ያወጣውን ህግ አለማክበር የሕሊና እስረኛ መሆንና ራስን ማስጨነቅ ነው። ግብር መክፈል ያቃተው ሰው ሁልጊዜ በስጋት ይኖራል የሌብነትን ያህልም ይሳቀቃል ( ሌብነትም ነው )

3. ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስንል = ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ ሁሉ የነበረበትን መንግሥት ህግ አክብሮ ኖሯል እኛም ያንኑ ልናደርግ ይጠበቃል። ለመንግሥት ስንገዛ ለመንግሥት ሥልጣንን ለሰጠው ለእግዚአብሔር የመገዛታችን ምልክት ነው።

እነዚህን ዋና የምዕራፉን መልዕክቶች ከያዝን ቁጥር በቁጥር ሃሳቦቹን እንመለከታቸዋለን።

***13:1*** *ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።*

በዚህ ቁጥር የተገለጠው ሃሳብ በግልጥ እንደሚያስቀምጠው ባለሥልጣናትን የሚሾም ጌታ ስለሆነ ጌታን መታዘዛችን ለመግለጥ ቢሮውን ማክበር ይገባናል።

መገዛት የሚለው ቃል ሥልጣኑን መቀበል ሲያመለክት መታዘዝ ደግሞ መተዳደሪ ደንቡንና ሥርዓቱን ማክበርን ይመለከታል። ይህ ማለት የጌታን ልዕልና የሚቃወመውንና የክርስቶስን ክብር የሚጋፋውን ሥርዓትና መመሪያ ሁሉ ያክብር ማለት አይደለም። በዚህ አንጻር ስደት ቢመጣበትም ለስደቱ ራሱን አዘጋጅቶ መቆም ይኖርበታል ( ሐሥ 4:8፣18፣19፣20 ፤ ማቴ 10:17:18 )።

*በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ አላቸዉ እናንተ የህዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች (ሐሥ 4:8)።*

*ጠርተዉም በኢየሱስ ስም ፈጽመዉ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸዉ (ሐሥ 4:18)።*

*ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰዉ እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚያብሔር ፊት የሚገባ እንዳልሆነ ቁረጡ (ሐሥ 4:19)።*

*እኛስ ያየነዉንና የሰማነዉን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸዉ (ሐሥ 4:20)።*

*ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሣልፈዉ ይሰጡአችኋል፣ በምኩራባቻቸዉም የገርፉአችኋልና (ማቴ 10:17)።*

*ከሰዎች ተጠበቁ ለእነርሱና ለአህዛብም መሰከር እንዲሆን ስለ እኔ ወደ ገዥዎች ወደ ነገስታትም ተወሰዳላችሁ (ማቴ 10:18)።*

***13:2 - 4*** ***ስለዚህ ባለስልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሐል ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአበሐር አገልጋይ ነውና።***

ጌታ ለባለ ሥልጣናት ሥልጣንን የሰጠው መልካም አስተዳደርን በምድር እንዲያሰፍኑ ነው። ይህም ማለት ክፉዎችን እንዲቀጡ መልካም የሚያደርጉትን ደግሞ እንዲሸልሙ ማለት ነው። ይህንን ጌታ የሰጣቸውን ድንበር የሚተላለፉ ካሉ ጌታ ይቀጣቸዋል። ለዚህም ምስክር የሚሆኑን የእስራኤሉ ንጉሥ ሳዖልና የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ናቸው(1ሳሙ 13:13 - 14፤ ዳን 4:1 - 37 )።

***13:5 ስለዚህ ስለ ቁጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው::***

ይህ ቁጥር ለባለ ሥልጣናት መገዛት የሚገባን ፍርድን ወይም ቅጣትን በመፍራት ሳሆን ከህሊና ፍርድ ነፃ ለመሆን ጭምር መሆኑን ያመለክታል። ህሊናችን ሁል ጊዜ ለእግዚአብሔር ሥርዓት ተገዢ ስለሆነ ማንንም ሳይፈራ ይሞግተናል:: መዋሸትና ማምለጥም አንችልም::

ስለዚህ እግዚአብሔርን በመፍራት ለባለ ሥልጣናትም በመገዛት በማክበር መኖር ይገባናል ( ሐሥ 24:16፤ ዕብ 13:18 ) ::

> *ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሄርና በሰው ፊት ሁሉ ጊዜ ነውር የሌለባት ህሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ (ሐሥ 24:16)::*
>
> *በልዩልን፤ በነገር ሁሉ በመልካም እንድናር ወደን መልካም ህሊና እንዳለን ተረድተናልና (ዕብ 13:18)::*

***13:6 - 7 ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና:: ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ ግብር ለሚገባው ግብርን ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን መፈራት ለሚገባው መፈራትን ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ::***

እነዚህ ሁለት ቁጥሮች በምድር በምንኖርበት ዘመን ሁሉ የማንም ባለ ዕዳ መሆን እንደማይገባንና የሚፈለግብንን የትኛውንም ነገር በወቅቱ መክፈል እንደሚኖርብን ያመለክታሉ ጌታ ኢየሱስም « የቄሳርን ለቄሳር » በማለት ግብር መክፈል አግባብነት እንዳለው አስተምሯል::

***13:8 እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና::***

በዚህኛው ቁጥር ደግሞ ግለሰባዊ ዕዳን አስመልክቶ ክርስቲያን ዕዳውን በጊዜ መክፈል እንዳለበት ያመለክታል::

ዘወትር በዕዳ ተነክሮ መኖርን የሕወታችን ክፍል ልናደርገው አይገባም:: የተጠራነው በነፃነትና በፍቅር ለመመላለስ እንጂ በዕዳ ታስሮ በመሸማቀቅ ለመኖር አይደለም (ማቴ5:42)::

> *ለሚለምንህ ስጥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል (ማቴ 5:42)::*

በቤተክርስቲያን ፍቅር በሙላት ሲገለጽ አበዳሪና ተበዳሪ አይኖርም ምክንያቱም ያለው ለሌለው ለወንድሙ በቸርነት ይሰጣል እርሱ እየበላ ወንድሙ ጦሙን እንዲያድር አይፈቅድም::

***13:9 - 10*** *አታመንዝር አትግደል አትስረቅ በውሸት አትመስክር አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ:- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል:: ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍፃሜ ነው::*

ሐዋርያው በነዚህ ቁጥሮች የፍቅርን ከፍተኛ ጉልበት ይገለልጣል የአዲስ ኪዳን ትዕዛዝ « እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ » የሚል ነው:: ሐዋርያው ደግሞ « ፍቅር የሕግ መፈጸሚያ ነው » ይላል ፍቅር ካለ እግዚአብሔርንም ሰውንም ማሳዘን የለም:: እንዲያውም ለባልንጀራ መልካም ማድረግ ፣ እግዚአብሔርንም ደስ ለማሰኘት ራስን እንደሚቃጠል መስዋዕት ማቅረብ እንጂ::

በፍቅር ስንመላለስ ህግን ሁሉ እንፈጽማለን:: ማለትም ህግና ነቢያት የተሰቀሉባቸውን ሁለት የአዲስ ኪዳን የሕይውት መርሆዎች በህይወታችን እንፈጽማቸዋለን ማለት ነው::

***13:11*** *ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰአት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና::*

የጌታን ዳግም ምፅዓት ነቅቶ የማይጠብቅ ክርስቲያን በጦር ሜዳ ውስጥ ሆኖ እንደሚያንቀላፋ ወታደር ነው። ( 2ጢሞ 2:3-4 ) ከግራና ከቀኝ የመምጣቱ ምልክቶች እየታዩ ቸል ማለት በጦር ሜዳ ጥፋት ከግራና ከቀኝ እየጮኸ ማንቀላፋት ማለት ነው። ውጤቱም ለሞት ራስን አሳልፎ መስጠት ነው።

> *እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም (2ኛ ጢሞ 2:3-4)።*

***13: 12 - 14 ሌሊቱ አልፎአል ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሐንን ጋሻ ጦር እንልበስ። በቀን እንደምንሆን በአግባብ እንመላለስ በዘፈንና በስካር አይሁን በዝሙትና በመዳራት አይሁን። በክርክርና በቅናት አይሁን ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።***

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር የጨለማውን ሠራዊት ከርቀት የሚስበውንና የሚማርከውን የጨለማ ሥራ (የሥራ ሥራዎች ) ትተን ወይም አውልቀን የብርሃን ልጆች እንደመሆናችን መጠን እንደ ቀን ልጆች ብርሃን የሞላበትን ፤ ያልተሸፋፈነውን ህይወት ልንመራ እንደሚገባን ያሳስበናል።

የጽድቅን ኑሮ የምንኖርና አካሄዳችን የብርሃን ከሆነ የጽድቅን ጦርነት የሚዋጉ የእግዚአብሔር ጦረኞች እንሆናለን። በዚህም የጨለማውን ሥራ እናፈርሳለን የእግዚአብሔርንም የብርሃን መንግሥት በምድር እናመጣለን።

ስለዚህ በዕለት ከዕለት የሕይወታችን እንቅስቃሴ ሁሉ ክርስቶስን ልንገልጠው ይገባል። የለበስነው ልብስ በቀን ውሎአችን በምንቀሳቀስበት ስፍራ ሁሉ መለያችን እንደምን በመንፈሳዊ ህይወታችንም የክርስቶስ ባህሪያት ሊገለጡ ይገባል። ይህንንም ለማድረግ ብቃታችን የሆነው መንፈስ ቅዱስ በሥጋ ላይ የበላይ ሊሆን ይገባል ( 1ቆሮ 9:27 )።

# የምዕራፍ አሥራ ሦስት ማጠቃለያ

የክርስትና ሕይወት ለእግዚአብሔር የመገዛት ብቻ ሳይሆን ጌታ በደሙ ለዋጃቸው ለወንድሞችም ህይወትን መስጠት ለጠላቶችም የጌታን ቸርነት ማሳየትና ጠላቶች ሳለን የወደደንን ጌታ እኛም ለጠላቶቻችን ፍቅርን በማሳየት መግለጥ ነው:: ብዙ ሰው የሚወዱትን ይወዳል ጌታ የገዛው ክርስቲያን ግን የሚጠሉትን ይወዳል:: ከዚህም የተነሳ በምድር ላይ አመፀኛ ለተባሉ መንግሥታት እንኳን ሥልጣን የሰጣቸውን ጌታ እንደሚያከብር እያወቀ ይገዛል:: ይህ ማለት ግን በእምነቱ ጉዳይ ሲመጡበት « እምቢ » አይልም ማለት አይደለም::

ክርስቲያን የሕይወቱ እንቅስቃሴ ሁሉ ከፍቅር የመነጨና ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ዕድፍ ሊያገኝበት በማይችል መንገድ የነፃ የጽድቅ እንቅስቃሴ ነው::የሚኖረውም በጦር ሜዳ እንዳለ ወታደር የጨለማውን ሥራ የብርሃንን ጋሻ ጦር እንደ ልብስ በመልበስ እየተፋለመና የጌታን መንግሥት እያስፋፋ ነው:: አሜን!

# ምዕራፍ አሥራ አራት
# እርስ በርስ መቀባበል

ሐዋርያው በእምነት ጽድቅን የተቀበለ ሕይወት ሊገለጥበት ስለሚገባው በተግባር የሚገለጥ የሕይወት እንቅስቃሴ ከጥቅል ወደ ውሱን ሃሳብ ደረጃ በደረጃ በመውረድ በዚህኛው ምዕራፍ ደግሞ እርስ በርስ እንዳንቀባበል የሚያደርጉንን አበይት ጉዳዮች በማንሳት እነርሱን የማስወገጃ ምክሮች ይለግሳል።

ከጥንት ጀምሮ በክርስቲያኖች መካከል ልዩነቶች ይፈጠራሉ ልዩነቶቹ የሚፈጠሩትም ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት የነበራቸው የሕይወት አቋም ፣ የትውልድ ሀረግ ፣ የኑሮ ደረጃ የትምህርት ደረጃ እና የመሳሰሉት ናቸው። ለምሳሌ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ዘመን አይሁድና አህዛብ ነበሩ ወደ ጌታ የሚመጡት አይሁድ የነበራቸውን ሃይመኖታዊ ልማድ ለመጣል በጣም ሲቸገሩና ጽድቅ በማመን ብቻ በመሆኑ ነገር እየተፈታተናቸው አንዳንድ ጊዜ ወደ ህጉ ጠቀስ ሲያደርጉ ይገኛሉ። ይህ ፈተና ጴጥሮስንም ሞክሮት ነበር ጳውሎስ በግልጽ ገስጾ አተረፈው እንጂ። ጳውሎስም በተራው ከባርናባስ ጋር በማርቆስ የአገልግሎት ባልደረባነት ምክንያት እንዲሁ ተለያይተው ነበር

በአብዛኛው ሁኔታ በክርስቲያን መካከል ልዩነትን የሚፈጥሩት ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ልክ ነው ወይም አይደለም ብሎ መመሪያ ያልሰጠባቸው ሁኔታዎች ናቸው።

ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ትምህርት የሚሰጠው ይህንን አስመልክቶ ነው። ዋና መፍትሄ የሚያደርገውም « መቀባበሉን » ነው። የመቀባበሉ መሠረት ያደረገው የትኛውም ሰው የሚያደርገውን የሚያደርገው ለጌታ ብሎ ነውና ለጌታ ብሎ የሚያደርገው ከሆነ ለአንተ ባይመችህም አትፍረድበት። አንተ ብቻ ልክ እንደሆንክ አታስብ። እርሱንም በልቡ ውስጥ ሆነህ ብታደምጠው አንተን ተሳስተሃል እንደሚልህ አትርሳ።

***14:1 በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት በአሳቡም ላይ አትፍረዱ።***

በዚህ ምዕራፍ በእምነት ስለደከመው ሰውና ስለበረታው ሰው ቀጥተኛ የሆነ የድካምና የብርታት መገለጫ አልተሰጠም ሆኖም ግን የበረታው የደከመውን መቀበል እንዳለበት ተገልጧል።

በሮም ያሉት ደካሞች ለመፅደቅ ስርአትን ሲጨምሩ በገላትያ ያሉት በስርዕት ብቻ የሚጸድቁ ይመስላቸዋል።

ጌታን ስንቀበል « ጽድቅ በእምነት » መሆኑን አምነን ተቀብለናል በአንዳንድ የሕይወት ልምምዳችን ግን ቁርጥ ያለ መመሪያ ባለመገንባታቸው እምነት ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ግን ደከም ብለን እንገኛለን። ስለዚህ ስንደክም በድካማችን የሚፈርድብን ሳይሆን በፍቅር ይዞ የሚያበረታን በደከምንበት በኩል አግዞ አበርትቶን በእካሏ ውስጥ በሙላት በብርታት ወደምንንቀሳቀስበት ህይወት ሊያደርሰን የሚችል ልበ ሰፊ ወገን ስናገኝ ነው።

***14: 2 - 4 ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል።***

ሐዋርያው በነዚህ ቁጥሮች የጠቀሳቸው የልዩነት ምክንያቶች የሚበላና የማይበላውን ከመምረጥ አንፃር የተከሰቱ ናቸው። ስጋ የሚበላው አትክልት የሚበላውን ወይም በተቃራኒው ሁለቱም እርስ በርስ ሳይናናቁ ተቀባብለው መኖር ይገባቸዋል። ሁለቱም ምንም ስህተት የለባቸውም ። ያንን ምርጫ ያደረጉትም ጌታን ደስ ለማሰኘ ት ነው። አደጋው አንዱ በአንዱ ከፈረደና አንዱ ሌላውን ከኰነነው ከናቀውም ነው።

***14: 5 - 6*** *ይህ ሰው አንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል ያ ግን ቀን ሁሉ አንድ እንደ ሆነ ያስባል እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ። ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል የሚበላም እግዚአብሔርን ያመሰግናልና ለጌታ ብሎ ይበላል የማይበላም ለጌታ ብሎ አይበላም እግዚአብሔርንም ያመሰግናል።*

በዚህኛው ደግሞ ቀንን ከቀን ለይቶ ለተወሰነው ልዩ ክብር የመስጠት አዝማሚያ ይታያል። የበረታው ሰው ግን «ቀን ሁሉ እኩል ነው» ሲል ደካማው ደግሞ «ከቀን ተለይቶ የሚከበር አለ» ይላል። የበረታው እንዲገባው ማስተማር እንጂ አስገድዶ ወይም አሳፍሮ የእርሱን አቋም እንዲከተል ማድረግ የለበትም ( ገላ 4:10፤ ቆላ 2:16-17 )።

*ቀንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ። ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜአለሁ ብዬ እፈራላችኋለሁ (ገላ 4:10-11)።*

ሁለቱንም የሚያደርጉት ለጌታ ብለው ነውና ጌታን ለማንገስ የጌታን ፍቅር በማሳየት መተናነጽና መቀባበል ይገባል።

***14: 7 - 9*** *ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና ለራሱም የሚሞት የለም በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን። ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያውም ሆኖአልና።*

እነዚህ ሦስት ቁጥሮች የመኖራችንና የትኛውንም እንቅስቃሴ የማድረጋችንን ምክንያቶች የሚመሩ ደግሞም በኛ ህይወት የበላይ ባለሥልጣንና ባለመብት የሆነው ማን እንደሆነ የሚያመለክቱ ናቸው:: እኛ የምንኖረው ለጌታ ነው ብንሞትም የምንሄደው ወደ ጌታ ነው:: ብንኖር ህይወታችን መስዋዕት ሆኖ እርሱ ብቻ ይጠቀምበታል ብንሞትም ተጠቃልለን ለዘላለም የእርሱ እንሆናለን::

ሞት የህይወት ጠላት ነው:: እኛን ከጌታ መለየት ግን አይችልም:: ብቻ የኛ ህይወት ስለኛ ሞቶ ለተነሳው ጌታ የተገዛ ይሁን! ( 1ኛቆሮ 15:26፤ ሮሜ 8:38፤39፤ ሐሥ 14:15 ፤ ዮሐ 21:19 ፤ ቆላ 3:23 ፤ 1ኛ ተሰ 5:10 )

*የኋለኛዉ ጠላት የሚሻረዉ ሞት ነዉ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአል (1ቆሮ 15:26)::*

*እናንተ ሰዎች ይህን ስለምን ታደርጋላችሁ እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንሰማ ሰዎች ነን ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባህርንም ለእነርስም ያለዉን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያዉ እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌል እንሰብካለን (ሐዋ 14:15)::*

*በምን አይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለዉ ሊያመለክት ይህን አለ (ዮሐ 21:19)*

*ለሰዉ ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉ (ቆላ3:23)::*

*የምንነቃም ብንሆን ፤ የምናንቀላፋም ብንሆን ፤ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ ስለ እኛ ሞተ (1ተሰ 5:10)::*

***14:10 - 13*** ***አንተም በወንድምህ ላይ ስለ ምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለ ምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና::***

***እኔ ሕያው ነኝ ይላል ጌታ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል ምላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና:: እንግዲያስ***

*እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን::*

*እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በርሳችን አንፈራረድ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቁረጡ::*

ሐዋርያው በዚህ ቁጥር ጌታ የሁላችን የበላይ ስለሆነ፣ ሁላችንንም በሞቱና በህይወቱ የገዛን ስለሆነ አንዳችን በሌላችን ላይ መፍረድ እንደማይገባንና ያንን የማድረግ ሥልጣን የተሰጠው ጌታ ብቻ መሆኑን ያመለክታል::

የፍርዱ ወንበር በምድር ባሳለፍነው ህይወትና አገልግሎት መጠን ሁላችንም ስጦታን የምንቀበልበት መድረክ ነው:: በብዙም ሆነ በጥቂት ሁሉም ስጦታ አላቸው:: ይህም በጌታ ፍሬ ስላለን ነው:: ዩሐ 15: 3፣15፣16 በደሙ ክፍያ መሰረት ለኩነኔ ሳይሆን በፊቱ ያለ ፊት መጨማደድና ያለነቀፋ በፍስሐ በክብሩ እንድንኖር በዚያም የፀጋው ክብር ይመስገን ዘንድ ነው እንጂ ቅዱስ ባልሆነ ፍርሀት ጌታ ይፈርድብኛል ብለን እንደ ህገኞች እንድንኖር አይደለም:: አዎ ጌታ ይፈርዳል:: ፍርዱ ግን በደሙ የተመሰረተ የፅድቅ ፍርድ ነው:: ሥራችን ወደ ብርሀን ይወጣል :: የብርሀን ፍሬ ያልሆነው ይቃጠላል የጽድቅ ፍሬ ይቀራል:: በክርስቶስ የብርሐን ልጆች እንደሆንን ብርሀናችን በክብሩ ተውጦ ከእርሱ ጋር እንኖራለን (ኤፌ 1:4፣6፣7፤ 5:8፣25-26):: ፍሬ የሌላቸው (በክርስቶስ ያልሆኑ) ለዚህ እድል ድርሻ የላቸውም (ዩሐ 3:18፣ ራዕ 20:11-15)::

*እናንተ ስለ ነገርኳችሁ ቃል አሁን ንጹህ ናችሁ በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ (ዮሐ 15:3)::*

*ከእንግዲህ ባሮች አልላችሁም ፣ ባሪያ ጌታዉ የሚያደርገዉን አያዉቅምና፣ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፣ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታዉቄአችኋለሁ (ዮሐ 15:15)::*

*እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኳችሁ (ዮሐ 15:16)::*

*በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል (ዮሐ3:18)።*

*ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱ ላይ የተቀመጠዉን አየሁ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸዉም። ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋን ፊት ቆመዉ አየሁ መጻሕፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነዉ ሙታንም በመጽሐፍት ተጽፎ እንደነበር እንደ ስራቸዉ መጠን ተከፈላቸው፤ ባሕርም በእርሱ ወስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ እያንዳንዱ እንደስራው መጠን ተከፈሉ። ሞትና ሰኦልም በእሳት ባህር ዉስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባህር ሁለተኛዉ ሞት ነዉ። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘዉ ማንኛ ዉም በእሳት ባህር ዉስጥ ተጣለ (ራዕይ 20:11-15)።*

በዚህ ምዕራፍ ጳውሎስ ልብ እንድንል የሚያሳስበን ዛሬ እኛ በምድር የፈረድ'ንበትን ጌታ በሰማይ በፍርድ ዙፋኑ ፊት ባይፈርድብትስ? ስለዚህ ፍርድን ለጌታ ትቶ የተሰመረልል'ን የመቀባበልና የመከባበር እርስ በርስ የመደጋገፍ ህይወት መኖር ይገባል።

ጌታን በዚህ ምድር እንድናስከብረው እንቅፋት የሚሆ'ነብንን ሁሉ ህግና ሐጢያት ጭምር በመስቀል ጠርቆ አስወግዶ'ታል። በት'ንሳኤው ህይወት ል'ንኖር ተሰጥቶናል። በክርስ'ቶስ በመደገፍ በዚህ ምድር ሕይወታችንን በቅድስና እንመራ ዘንድ (ገላ2:20) የተከፈለው ዋጋ ቀላል አይደለም።

ሰው ተሳስቷል ካልን ለማረም እንጥራለን የእርምት መንገዳችን ምናልባት ተሳስቷል ያልነውን ሥራ እንዳይሠራ እንቅፋት ማኖር እንዳይሆን ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ስለዚህ በምክራችን ሆነ ለማረም ብለን በየትኛውም እንቅስቃሴ ለሌሎች እንቅፋት ላለመሆን እንጠንቀቅ ( 1ጴጥ 1:18:19፤ ራዕ 5:9 - 10 )።

*ከአባቶቻችኋ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ላይሆን ፤ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ (1ኛጴጥ 1:18-19)።*

*መጽሐፍን ትወስድ ዘንድ ማህተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሀል። ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከህዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ*

*ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው በምድርም ላይ ይነግሣሉ (ራዕ 5:9-10)::*

***14:14 - 20*** ***በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደ ሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ ተረድቼአለሁም ነገር ግን ምንም ርኩስ እንዲሆን ለሚቈጥር ለእርሱ ርኩስ ነው:: ወንድምህንም በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆንህ እንግዲህ በፍቅር አልተመላለስህም:: ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተለትን እርሱን በመብልህ አታጥፋው:: እንግዲህ ለእናንተ ያለው መልካም ነገር አይሰደብ የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና:: እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው:: እንግዲያስ ሰላም የሚቆምበትን እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል:: በመብል ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ:: ሁሉ ንጹሕ ነው በመጠራጠር የተበላ እንደ ሆነ ግን ለዚያ ሰው ክፉ ነው::***

ሐዋርያው በጌታ መንፈስ ሆኖ ሲመለከት ምግብ በራሱ ርኩስ እንዳልሆነ «የረከሰ ምግብ» የሚባል በራሱ እንደሌለ አረጋግጧል ( ማቴ 5:11፤23:25 - 26 )::

*ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው አሳቸው (ማቴ 15:11)::*

*እናንተ ግብዞች ፈሪሣዊያን በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ ወዬላችሁ:: አንተ እውር ፈርሳዊ ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውን የወጭቱን ውስጡን አጥራ (ማቴ 23:25-26)::*

ሆኖም ግን አንዳንድ ሰው ከምግቦች መካከል አንዳንዶቹን ንጹህ እንዳልሆኑ ሊያስብ ይችላል:: የበረታው ደግሞ ሁሉ ንጹህ ነውና ልብላ ሊል ይችላል ግን አንድ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር የወንድማማች ፍቅር ግን ይቀዘቅዛል::ስለዚህ የበረታው ወንድም ፍቅሩን ፍጹም ለማድረግ የወንድሙ ልብ የማይመቸውን ምግብ ባለ

መብላት ራሱን ገዝቶ ወንድሙን ገንዘቡ ሊያደርግ ይገባዋል በመብል ምክንያት ወንድምን ማጣት ኪሣራ ነው። አብሮ መንግሥተ ሰማያት የሚዘልቀው ወንድም እንጂ ሆድ አይደለም ( 1ኛ ቆሮ 6:13፤ ዮሐ 4:9፤6:57፣58 ፤ ዮሐ 11:25፣26 )።

*ሆድም ለመብል ነው እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም ጌታም ለስጋ ነው (1ኛቆሮ 6:13)።*

*ስለዚህ ሳምራዊቲቱ:- አንተ የይሁዳ ሰው ሳትሆን ሣምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ አለችው አይሁድ ከሣምራዊያን ጋር አይተባበሩም ነበርና (ዮሐ 4:9)።*

*ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሳ ህያው እንደምሆን እንዲሁ የላከኝ ደግሞ ከእኔ የተነሳ ህያው ይሆናል። ከሠማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይደለም ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል (ዮሐ 6:57-58)።*

*ኢየሱስም:- ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ህያው ይሆናል ፣ ህያው የሆነም የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ፣ ይህን ታምኛለሽን? አላት። እርሷም:- አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ አምናለሁ አለችው (ዮሐ 11:25-26)።*

**ስለዚህ በፍቅር የምንመላለስ ከሆነ የምንበላውም ሆነ የምንጠጣው ነገር ሁሉ ወንድማችንን እንዳያሰናክለው እንጠነቀቃለን። በምግብ ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ ማፍረስ ተገቢ አይደለም። ስለዚህ የምናደርገው ነገር ሁሉ መተናነጽን የሚያመጣ ሊሆን ይገባዋል ( 1ቆሮ 14:26፤ ቆላ 3:15፤ ኤፌ 4:3፤ 1ቆሮ8:12 ዘፍ 9:3 1ጢሞ 4:4 )።**

*እንግዲህ ፣ ወንድሞች ሆይ ፣ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው ፣ ትምህርት አለው ፣ መግለጥ አለው ፣ በልሳን መናገር አለው መተርጎም አለው ሁሉ ለማነጽ ይሁን (1ኛቆሮ 14:26)።*

*በአንድ አካል የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ የምትመሰገኑም ሁኑ (ቆላ 3:15)።*

*በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ (ኤፌ 4:3)::*

*እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ (1ኛቆሮ 8:12)::*

*ህይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ መብል ይሁናችሁ ሁሉን እንደ ለመለመ ቡቃያ ሠጠኋችሁ (ዘፍ9:3)::*

*እግዘብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ፣ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም (1ኛጢሞ 4:4)::*

***14:21 - 23*** ***ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው:: ለአንተ ያለህ እምነት በእግዚአብሔር ፊት ለራስህ ይሁንልህ:: ፈትኖ መልካም እንዲሆን በሚቈጥረው ነገር በራሱ ላይ የማይፈርድ ብፁዕ ነው:: የሚጠራጠረው ግን ቢበላ በእምነት ስላልሆነ ተኰንኖአል በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው::***

እኛ ክርስቲያኖች ለሰው ማሰናከያ የሚሆን ነገር አናደርግም ምክንያቱም እንደ እምነቱ መጠን ክርስቶስ በርሱ የጀመረውን ሥራ ይፈጽማልና( ቲቶ 2:14፤ 2ቆሮ 11:2 )::

*መድኃኒታችንም ከአመፅ ሁሉ እንዲቤዠን ፣ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናወን ገንዘቡም የሚሆነውን ህዝብ ለራሱ እንዲያነፃ ፣ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል (ቲቶ 2:14)::*

*በእግዚአብሔር ቅንአት እቀናላችኋለሁና ፣ እንደ ንፅህት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና (2ኛ ቆሮ 11:2)::*

እምነታችን ሲጠነክር ሁሉን ከጌታ በንጹህ ሕሊና እንቀበላለን ያለ እንዳች ስጋትም በሁሉም መስክ በጌታ

ነፃነት እንኖራለን ነገር ግን እኛ የደረስንበት የእምነት ደረጃ በእኛና በእግዚአብሔር መከከል የተጠበቀ ሊሆን እንጂ ሌሎችን ለመኮነኛና በእነርሱ ላይ ለመፍረድ መሆን የለበትም።

የሐዋርያው ጳውሎስ የዚህ ምዕራፍ ማጠቃለያ በእምነት ያልተደረገ ሁሉ ኃጢአት ነው። ስለዚህ ከእምነት ጎድለን በኃጢአት ቀንበር ውስጥ እንዳንገባ መጠንቀቅ ይገባናል።

## የምዕራፍ አሥራ አራት ማጠቃለያ

በምድር በምንኖርበት ዘመን የኑሮ ደረጃችን ፣ትውልዳችን ፣ የትምህርት ደረጃችን ወ.ዘ.ተ. እጅግ የተለያዩ ናቸው። በመንፈሳዊውም ዓለም ያለን የእምነት ደረጃ እንዲሁ እጅግ የተለያየ ነው። ሆኖም ግን አንድ እውነት ልብ ማለት ይገባል። ሁላችንን ጌታ ልጆቹ አድርጎናል። ስለዚህ ጌታ የተቀበለን መሆናችንን አውቀን እርስ በርስ መቀባበል፤ አንዳችን በሌላችን ከመፍረድ መቆጠብ ይገባናል። ይህም በሙላት የሚገለጠው የኃጢአትን ብዛት የሚሸፍነው ፍቅር በኛ ሲነግሥ ነው!

# ምዕራፍ አሥራ አምስት
# የተጠናቀቀ አገልግሎት

ሐዋርያው በሮሜ መልዕክቱ የማጠቃለያ ሁለት ምዕራፎች ደጋግሞ የሚያነሳው ስለ አገልጋይነትና ፣ ለአገልግሎት ስለሚቸኩለው ልቡ ነው።

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ በመሸካከምና በመቀባበል ማገልገልን ለራስ መብት ብዙ ሳይሟገቱ ይልቁኑ ለሌሎች ጥቅም ሲባል ማገልገልን ያነሳል።

በዚህ ክፍል አራት ዓይነት አገልግሎቶችን ይጠቅሳል።

1. የክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎት ለአህዛብ
2. የጳውሎስ አገልግሎት ለአይሁድ
3. የአህዛብ አገልግሎት ለአይሁድ
4. የወንድሞች አገልግሎት ለጳውሎስ

እነዚህ ዋና ዋና አገልግሎቶች የተሰጡት በፍጹም መስጠትና ራስን ባለመውደድ ነበር። ለአንባቢዎቹም የሚመክረው ይህንኑ ነው። እርስ በርስ ክርስቶስ እንደተቀበላችሁ በመቀባበል አገልግሉ ይህም ለእግዚአብሔር ምስጋናን ያመጣል የሚል ነው።

*15:1 - 5* *እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል። እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ። ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና ነገር ግን አንተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሆነበት። በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና። በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ታከብሩ ዘንድ*

ብርቱ የሆነው ሰው ደካማውን ከመናቅና ከማጥላላት ወጥቶ ይልቁኑ ሸክሙን ሊያግዘው ይገባል። ክርስቶስ የተወልን ትምህርት ይህ ነው። ባልንጀራን ደስ ለማሰኘት የራስን ጥቅም እንኳን መተው ከጌታ የተቀበልነው ህይወት መገለጫ ነው ( ገላ 6:2 ) ።

ጌታ በመስቀል ላይ እያለ ያደረገው ይህንኑ ነው። መብቱን ተጠቅሞ ከመስቀል አልወረደም። በሰቀሉትም አልፈረደም። እንዲያውም « የሚያደርጉትን አያውቁም » በማለት ኃጢአታቸውን እንኳን ሳይጠቅስ ምህረትን ለመነላቸው። እስጢፋኖስ እንኳን « ይህን ኃጢአት » በማለት ጠቅሶታል ጌታ ግን አልጠቀሰም። ስለዚህ ፍቅሩ ምህረትን የተሞላ ነበር።

*ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ህግ ፈጽሙ (ገላ 6:2)።*

*15: 6 - 7* *የትዕግስትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ። ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ተቀበላችሁ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ።*

ጌታ እኛን የተቀበለን ገና ኃጢአተኞች ሆነን ሳለን ነው።

ከኛም የሚጠብቀው ወንድሞቻችንን በዚያው መንፈስ ተቀብለን እንድናገለግላቸው ነው። ይህ ሲሆን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይበዛል። ይከብራልም( ማቴ 11:28-30፤ሮሜ 5:8፤ ማቴ10:40)።

*እናንተ ደካሞች ሸክም የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ(ማቴ 11:28)።*

*ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና (ማቴ 11:30)።*

*እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ፣ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል (ማቴ 10:40)።*

***15:8 - 13*** ***ለአባቶች የተሰጠውን የተስፋ ቃል ያጸና ዘንድ ደግሞም ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ ለስምህም እዘምራለሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ አሕዛብ ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ። ደግሞም:- አሕዛብ ሆይ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላል። ደግሞም:- እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት ይላል። ደግሞም ኢሳይያስ:- የእሴይ ሥር አሕዛብንም ሊገዛ የሚነሳው ይሆናል በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ:ይላል። የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ።***

እግዚአብሔር ለእስራኤል አባቶች ገብቶት የነበረውን የተስፋ ቃል አህዛብም እንዲያገኙት አደረገ። ይህንንም በረከት ያገኘን እኛ በዚህ ተስፋ በደስታ ልንኖር ይገባል። የማይገባንን አግኝተናልና ( ኤፌ 1:6 )።

*በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ(ኤፌ 1:6)።*

**15:15 - 16** *ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መሥዋዕት ሊሆኑ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ፀጋ ምክንያት ተመልሼ ላስባችሁ ብዬ በአንዳንድ በታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ።*

በብሉይ አገላለጽ አህዛብ ርኩስ ናቸው፤ ስለዚህም መቀደስ ይገባቸዋል። ይህ አገልግሎት ይደርሳቸውና ይቀደሱ ዘንድ ጳውሎስ የአህዛብ ሐዋርያ ( አገልጋይ ሆነ )። አህዛብ የተቀደሱት ግን በአይሁድ ሥርዓት ሳይሆን ከእምነት በሚገኘውና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በተፈጸመው የልብ ግርዛት ነው። ስለዚህም በእግዚአብሔር የተወደደ ቅዱስ መስዋዕት ሆኑ። ሐዋርያውም በአንዳንድ ጉዳዮች የበለጠ ማሳሰቢያ ሊሰጣቸው ፈልጎ ይህንን መልዕክት እንደጻፈላቸው በግልጥ ያስቀምጠዋል (ፊሊ 3:3፤ቆላ 1:1፤ ገላ 2:9) ።

*በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በስጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና (ፊሊ 3:3)።*

*ደግሞ የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው ፣ አዕማድ መስለው የሚታዩ ያዕቆብና ኬፋ ዮሐንስም እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱም ወደ ተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን (ገላ 2:9)።*

**15:17 - 19** *እንግዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሆን ነገር በክርስቶስ ኢየሱስ ትምክህት አለኝ። አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ።*

ሐዋርያው ይህንን ድንቅ አገልግሎት የሰጠው በራሱ ችሎታ ሳይሆን ከጌታ በተቀበለው ጸጋ ነበር። ጌታ በእርሱ አድሮ ሊሰራ በወደደው መጠን ጳውሎስ ራሱን ሰጠ፤ በየከተሞቹም ቤተክርስቲያን መሠረተ እርሱ ጀመረ ሌሎች አገልጋዮች ተቀበሉና ወንጌል ለሰዎች ሁሉ ደረሰ። ጌታ ሁሉን ሠራ እኛ ግን ታዝዘነው ማለቱ ነው እንጂ በጥረታችን ይህን አደረግን ማለቱ አይደለም።

**15:20 - 22** *እንዲሁም በሌላው ሰው መሰረት ላይ እንዳልሰራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ ነገር ግን:- ስለ እርሱ ያልተወራላቸው ያዩት ያልሰሙም ያስተውላሉ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።ስለዚህ ደግሞ ወደ እናንተ እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ።*

ጳውሎስ የሮሜ ሰዎችን ሳይጎበኝ የቀረበትን ምክንያት ያስረዳል። ይኸውም ወንጌልን ላልሰሙ ቅድሚያ ለመስጠት ካለው ቁርጠኝነትና ሸክም የተነሳ ነበር።

**15:23 - 29** *አሁን ግን በዚህ አገር ስፍራ ወደ ፊት ስለ ሌለኝ ከብዙ ዓመትም ጀምሬ ወደ እናንተ ልመጣ ናፍቆት ስላለኝ ወደ እስጳንያ በሄድሁ ጊዜ ሳልፍ እናንተን እንዳይ አስቀድሜም ጥቂት ብጠግባችሁ ወደዚያ በጉዞዬ እንድትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ግን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ። መቄዶንያና አካይያ በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወደዋልና። ወደዋልና የእነርሱም ባለ ዕዳች ናቸዉ አሕዛብ በእነርሱ መንፈሳዊ ነገርን ተካፋዮች ከሆኑ በሥጋዊ ነገር ደግሞ ያገለግሉአቸው ዘንድ ይገባቸዋልና። እንግዲህ ይህን ፈጽሜ ይህን ፍሬ ካተምሁላቸው በኋላ በእናንተ በኩል አልፌ ወደ እስጳንያ እሄዳለሁ*

*ወደ እናንተም ስመጣ በክርስቶስ በረከት ሙላት እንድመጣ አውቃለሁ።*

ሐዋርያው በዚህ ስፍራ ቀጣይ የሆነውን የአገልግሎት እንቅስቃሴውን ያሳውቃቸውና እግረ መንገዱንም ወደ ስፔን ሲሄድ የሮምን ወንድሞች እንደሚጎበኝ ይነግራቸዋል። ይህንን ሁሉ ለማድረግ የሚታመነውም በጌታ ቸርነትና ስጦታ ነበር።

ስለ ጳውሎስ ጉዞ ስናጠና ሁለት የተለያየ አመለካከት አለ። ሁለቱንም እናቀርባለን። አንደኛው ወገን ጳውሎስ በየስፍራው እስራት እንደሚገጥመው መንፈስ ቅዱስ ይገልጥለት እንጂ የመሄዱ ምርጫ የእርሱ ነበር። ይህ ተመሳሳይ ሁኔታ ዳዊት አጋጥሞት አልሄደም ነበር (ሳሙ 23:9-11፣ ሥራ 21:4)። ይሁን እንጂ ጌታ ጣልቃ ገብቶ ለክብሩ ለወጠው የሚል ሲሆን፤ ከሌላው ወገን የሆኑት ደግሞ «በመንፈስ ታስሬ» (ሐሥ 20:23) ትዕዛዝ ነበረ፣ በመታዘዙም በመጨረሻ ለክብሩ መገለጫ ሆነ ይላሉ። (ሮሜ 8:27፣28 )

ይህንን ጉዞ ከማድረጉ በፊት ግን ለአይሁዳውያን ወገኖቹ ከአህዛብ ወንድሞቻቸው እርዳታ ይዞ የመሄድ ዕቅድ ነበረው ዕርዳታውንም ለመሰብሰብ የተጠቀመበትን የማሳመኛ ነጥብ ጠቅሷል። *እስራኤል ለአህዛብ መንፈሳዊ በረከቷን ካካፈለች አህዛብ ደግሞ ከሥጋዊ በረከታቸው ቢያካፍሏት ተገቢ ነው ::* የሚል ነበር።

ይህንን ትልቅ ዓላማ ለመፈጸም ኢየሩሳሌም ሲደርስ ታሰረ። ሮምም እስረኛ ሆኖ ሄደ። እርሱ ቢታሰርም ወንጌል ግን አልታሰረም (ኢሳ66:20 ፤ ዘካ3:10 ፤ 2ኛ ቆሮ 8:1 ፣ 4 ፤ ሐሥ 28:16፣23፣30፣31 )።

***15:30 - 32*** *ወንድሞች ሆይ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ ወደ እናንተ መጥቼ ከእናንተ ጋር እንዳርፍ በይሁዳ ካሉት ከማይታዘዙ እድን*

*ዘንድ ለኢየሩሳሌምም ያለኝ አገልግሎት ቅዱሳንን ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ ጸልዩ።*

በነዚህ ቁጥሮች ሐዋርያው እያቀረበ ያለው ጥያቄ ወንድሞቹ በጸሎት የአገልግሎቱ አጋር እንዲሆኑ የሚጋብዝ ነው። የጸሎቱም ትኩረት ከማያምኑት ሰዎች የክፉት እጅ እንዲድንና አገልግሎቱ በቅዱሳኑ ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ነበር ( ሐሥ 21:17:20 )።

> *ወደ ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ ወንድሞች በደስታ ተቀበሉን (ሐሥ 21:17)።*

እነርሱም በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ አሉትም:- ወንድም ሆይ በአይሁድ መካከል አምነው የነበሩት ስንት አእላፋት እንደሆኑ ታያለህ ሁላቸውም ለህግ የሚቀኑ ናቸው (ሐሥ 21: 20)።

***15:33*** ***የሰላምም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን።***

የጳውሎስ የስንብትና የመዝጊያ ቃላቶች በጣም ጉልበታም የሆኑና ያስተላለፋቸውን መልዕክቶች በጠንካራ ማሰሪያ የሚቋጥሩ ናቸው። ስለ መሸከም፣ ስለ መቀባበል፣ አንዱ ሌላውን ስለማገልገል ሲናገር ይቆይና የሰላም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን ! ይላል። ይህን ማለቱም በሰላም ኑሩ፣ ለወንድሞቻችሁ ኑሩ ማለቱ ነው።

# የምዕራፍ አሥራ አምስት ማጠቃለያ

የበረታው የደከመውን በመርገጥ የሚከሰተውን ሰላም የሚያሳጣ የሕይወት መገለጫ ሰላምን በሚፈጥር ማለት የበረታው የደከመውን ሸክም ያግዘው በማለት የጀመረውን መልዕክት የሰላም አምላክ በመካከላችሁ ሆኖ በሰላም እርስ በርስ የማገልገልን ህይወት ለዘላለም ያዝልቅላችሁ በሚል የበረከት ማሰሪያ ያጠቃልለዋል። አምን! እንደተጻፈው ይሁንልን!

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት
# ሰንበት

ይህ ምዕራፍ ሐዋርያው ለተለያዩ ሰዎች ሰላምታ ያቀረበበትና ለአንዲት እህት ደግሞ ለአገልግሎቷ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እውቅና የሰጠበት ምዕራፍ ነው።

***16:1 በክንክራኦስ ባለች ቤተክርስቲያን አገልጋይ የምትሆን እኅታችንን ፌበንን አደራ ብያችኋለሁ***

በዚህ ቁጥር የተጠቀሰችው እህት ፌቨን የቤተክርስቲያን ዲያቆን እንደሆነች ይነገርላታል። በቤቷም ውስጥ ሴቶችን በማስተማር ታገለግል ነበር። በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ሴቶች የራሳቸው ብቻ የሆነ ህብረት ነበራቸው ( 1ቆሮ 14 ) ፡፡

***16:2 ለቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ ተቀበሉአት እርስዋ ለብዙዎች ለእኔም ለራሴ ደጋፊ ነበረችና ከእናንተም በምትፈልገው በማናቸውም ነገር እርዱአት::***

ሐዋርያው ፌቨንን በምን ዓይነት መንፈስ ሲቀበሏት እንደሚገባ ሲያሳስብ በምዕራፍ 15 ያነሳውን ጌታ እንደተቀበለ የመቀባበል መንፈስ ጌታ እርሷን በተቀበለበት የፍጹም ፍቅርና የመረዳት አቀባበል ተቀበሏት ይላል:: በጉዞዋም ደግሞ የሚያስፈልጋትን በማድረግ እንዲደግፏት ያሳስባል:: ፌቨን ይህንን የሮሜ መልዕክት በሮሜ ላለችው ቤተክርስቲያን አድርሳለች ተብሎም ይታመናል::

**16:3- 5** ***በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ እነርሱም ስለ ነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ:: ከእስያ ለክርስቶስ ቡኩራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ::***

ጵርስቅላና አቂላ ከጳውሎስ ጋር ወዳጆች የሆኑት በድንኳን ስፌት ሥራው አብረውት በነበሩበት ጊዜ ነበር:: እነዚህ ሰዎች ጌታን ከተቀበሉ በኋላ ቤታቸውን ቤተክርስቲያን በማድረግ፣ ብዙዎችንም በማነጽ ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ሆነዋል (ሐሥ 18: 18 - 26)::

> *ከዚህም በኋላ ጳውሎስ እጅግ ቀን ተቀምጦ ወንድሞቹንም ተሰናብቶ በመርከብ ወደ ሶሪያ ሔደ ስለትም ነበረበትና ራሱን በክንክራኦስ ተላጨ ጵርስቅና አቂላም ከእርሱ ጋር ነበሩ (ሐዋሥራ 18:18)::*

> *እርሱም በምኩራብ ገልጦ ይናገር ጀመር ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ ፣ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት (ሐዋሥራ 18:26)::*

***16:6 ስለናንተ ብዙ ለደከመች ለማርያ ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡***

ስለ ማርያም ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በአዲስ ኪዳን በዚህ ስም የተጠሩ ስድስት ሴቶች አሉ፡፡ ይህችኛዋ ግን በዚህ ስፍራ ብቻ የምትገኝ ናት፡፡ ከጳውሎስ ገለጣ እንደምንረዳው ብርቱ አገልጋይ የነበረች ሴት ናት፡፡

***16:7 በሐዋርያት መካከል ስመ ጥሩዎች ለሆኑ ደግሞም ክርስቶስን በማመን ለቀደሙኝ አብረውኝም ለታሰሩ ለዘመዶቼ ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡***

በዚህ ቁጥር የጠቀሳቸው ሰዎች በክርስቶስ በማመን የቀደሙትና በሐዋርያት መካከልም መልካም ምስክርነት የነበራቸው ሰዎች ናቸው፡፡

***16: 8 - 10 በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡ በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራ ለኢሩባኖን ለምወደውም ለስንጣክን ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡ በክርስቶስ መሆኑ ተፈትኖ ለተመሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡ ከአርስጣባሉ ቤተ ሰዎች ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡***

ጵልያጦን የቄሳር ባሮች የሚጠሩበት ስም ነው፡፡ አርስጣባሉ ደግሞ የሄሮድስ የልጅ ልጅ ሊሆን ይችላል፡፡ ( አ.መ.ት )

***16:11 ለዘመዴ ለሄሮድዩና ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡ ከንርቀሱ ቤተ ሰዎች በጌታ ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ፡፡***

ለዘመዴ የሚለው መግለጫ አይሁዳዊ መሆኑን ለማሳወቅ የገባ ይመስላል፡፡ ንርቀሱ ከባርነት ነፃ የወጣና ባለጠጋ የሆነ ክርስቲያን ሲሆን በኔሮ መንግሥት ሞት ተፈርዶበት ነበር ይባላል፡፡

***16:12 - 15*** *በጌታ ሆነው ለሚደክሙ ለፕሮፊሞናና ለጢሮፊሞሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ:: በጌታ እጅግ ለደከመች ለተወደደች ለጠርሲዳ ሰላምታ አቅርቡልኝ:: በጌታ ሆኖ ለታወቀ ለሩፎን ለእኔና ለእርሱም እናት ሰላምታ አቅርቡልኝ:: ለአስቀሬጦንና ለአፍለሶንጰ ለሄርሜንም ለጳጥሮባም ለሄርማንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ:: ለፍሌጎንና ለዩልያ ለኔርያና ለእኅቱም ለአልንጦንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ::*

እነዚህን ሰዎች አስመልክቶ የተለየ ማብራሪያ መስጠት የሚቻልበት ወይም ከታሪክ መጽሀፍ የተገኘ ተጨማሪ ዕውቀት የለም::

***16:16*** *በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ:: የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል::*

**ሐዋርያው በዚህ የሰላም ዝርዝር ውስጥ ይህኛውን ቁጥር ሲያስገባ በዓላማ ያደረገው ይመስላ:: የክርስቲያን ሰላምታ ከእውነት የመነጨና የተቀደሰ ሊሆን ይገባዋል የይስሙላና ግብዝነት የሞላበት ሊሆን ጨርሶ አይገባም:: እንደ የአስቆሮቱ ይሁዳ ዓይነቱ መሳም አደገኛና ገዳይ ነውና ይወገድ:: የተቀደሰው ግን ይጠንክር ይብዛም ( 1ቆሮ 16:20፤ 1ተሰ 5:26፤ሉቃ 22:48 ) ::**

*ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል:: በተቀደሰ አሣሣም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ (1ኛ ቆሮ 16:20)::*

*ከወንድሞች ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ (1ኛ ተሰ 5:26)::*

*ኢየሱስ ግን:- ይሁዳ ሆይ በመሳም የሠውን ልጅ አሳልፈህ ትሠጣለህን? አለው (ሉቃ 22:48)::*

***16:17 - 18*** *ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ:: ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቈላምጥ ንግግርም ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ::*

ሐዋርያው በዚህ ስፍራ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ብርቱ ነው ምክንያቱም የወንጌሉን ዕውቀት ሆን ብለው የሚቃወሙ ሰዎች የሰውን ልብ የመስረቅ ኃይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ መድኃኒቱ ከእነርሱ መራቅ ነው ( 1ቆሮ 5፡6፤ ገላ 3:4 - 5 )::

*መመካታችሁ መልካም አይደለም ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን? (1ኛቆሮ 5:6)::*

*በውኑ ከንቱ እንደሆነስ እንደዚህ ያለ መከራ በከንቱ ተቀበላችሁን? እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ ፣ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማማት ነው? (ገላ 3:4-5)::*

***16:19*** *መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቶአልና እንግዲህ በእናንተ ደስ ይለኛል ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ::*

ክርስቲያን ሊበስል የሚገባው ክፋትን በማወቅ ሳይሆን በጎ ነገርን በማወቅና ጥበበኛ በመሆን መሆኑን በመግለጥ ለዚህ ህይወት የተሰጠን እንድንሆን ያበረታናል ( 1ቆሮ 14:20 )::

*ወንድሞች ሆይ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአእምሮ የበሰሉ ሁኑ (1ኛቆሮ 14:20)::*

***16:20*** *የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።*

እርስ በርሳችን ስንዋደድና በፍቅሩ ስንኖር የሰላም አምላክ በህይወታችን ይነግሳል። ይህ ተግባርም ሴጣንን ከእግራችን በታች የተረገጠ እንዲሆን ያደርገዋል።ይህ ህይወት በሙላት ይገለጥ ዘንድ በክርስቶስ ሰላም ውስጥ መሆን ይገባናል።

***16:22*** *ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ።*

ይህ ሰው ሐዋርያው የተናገረውን ተቀብሎ ይጽፍ የነበረ ሰው ሆኖ ሐዋርያው የእርሱን ሰላምታ እንዲጽፍ ፈቅዶለት ፅፏል ይላሉ።

***16:24*** *የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን።*

በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ላይ ይህ ቁጥር የለም።ምክንያቱም ሃሳቡ በቁጥር 20 ላይ ስለተጠቀሰ ላለመድገም ተፈልጎ ነው ይላሉ። አዋቂዎች።

***16:25 - 26*** *እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ተሰበከ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምስጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው*

ሐዋርያው የመልዕክቱ ማሰሪያ ጋ ሲደርስ ደግሞ የሚያነሳው የሰበከላቸውን ወንጌል ነው። ያም ወንጌል ክርስቶስ ነው። ጳውሎስ የሰበከው ወንጌል ሀዋርያቱ ከሰበኩት የተለየ ወንጌል አይደለም ከእምነት በሚነሳ መታዘዝ ሰዎች ሁሉ ሊኖሩበት የሚችሉበት የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጠበት ሰማያዊ መገለጥ ነው ( 1ቆሮ 15:11 )።

*እንግዲህስ እኔ ብሆን እነርሱም ቢሆኑ እንዲሁ እንሰብካለን እንዲሁም አመናችሁ (1ኛቆሮ 15:11)።*

***16:27 ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን አሜን።***

ሐዋርያው ይህንን ሁሉ የደህንነት ምስጢር፣ የአገልግሎትና የእርስ በርስ መቀባበል፣ በመከራ የመጽናትና ጌታን የመጠባበቅን ህይወት ጥልቀት ከገለጠ በኋላ ጥበብ ሁሉ የእርሱ ነው ብቸኛ ጥበበኛም እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ ክብርና ውዳሴ ሁሉ ተጠቅልሎ ለእርሱ ብቻ ይሁን! ብሎ ይዘጋል።

# አሜን ክብር ሁሉ ለጥበብ ምንጭ ለእግዚአብሔር ብቻ ይሁን!!

# ለማጣቀሻ የተወሰዱ

## Bibles


The message// remix bible by Peterson

NIV New (International Version)

NKJV (New King James Version)

New American Standard Bible Updated edition

King James Version.

American Standard Version

Amplified Bible

Darby Bible

The Living Bible

New American Standard Bible

New Living Translation

New Revised Standard Version

Today's English Version

## References :

Daniel G. Reid, The IVP Dictionary of the New Testament, the one volume Compendium of Contemporary Biblical Scholarship

Desalegne Demissie, Dewel Evanggelistic traning manual

DR. Douglas Moo, The Epistle to the ROMANS, (The New International commentary on the new testament; 1996)

DR. F.F. Bruce, Bible Commentary, ( NIV translation, 1986)

Earl Radmacher, Ronald B. Allen H., Nelson's New Illustrated Bible Commentary, Wayne House

James Strong, LL.D., S.T.D; edited by Warren Baker, Strong's Complete Word Study Concordance (Expanded edition 2004)

Spiros Zodhiates, Th.D., the Complete Word Study New Testament, Word Study Series 1992

Walter A. Elwell, Backer Commentary on the Bible based on the NIV (edited 2002)

Walter A. Elwell, Backer Theological Dictionary of the Bible edited 2000

W.E. Vine, Vine's C.O.N.C.I.S.E Dictionary of Bible Words. 1999

Warren W Wiresby, Bible Exposition Commentary- V1

Zodhiates, the Complete Word Study Old Testament by Word Study Series 1994

Adam Clarke's Commentary, Electronic Database. Copyright © 1996, 2003, 2005 by Bible soft, Inc.

Barnes' Notes, Electronic Database Copyright © 1997, 2003, 2005 by Bible soft, Inc. All rights reserved.

Bible Knowledge Commentary/Old Testament Copyright © 1983, 2000 Cook Communications Ministries; Bible Knowledge Commentary/New Testament Copyright © 1983, 2000 Cook Communications Ministries.

Geneva Notes, PC Study Bible formatted electronic database Copyright © 2003 Bible soft Inc

Jamieson, Fausset, and Brown Commentary, Electronic Database. Copyright © 1997, 2003, 2005 by Biblesoft, Inc

Keil and Delitzsch, Commentary on the Old Testament: New Updated Edition, Electronic Database. Copyright © 1996 by Hendrickson Publishers, Inc

Matthew Henry's Commentary on the Whole Bible: New Modern Edition, Electronic Database. Copyright © 1991 by Hendrickson Publishers, Inc.

The Wycliffe Bible Commentary, Electronic Database. Copyright © 1962 by Moody Press.

Adam Clarke's Commentary, Electronic Database. Copyright © 1996, 2003, 2005 by Biblesoft, Inc.

Robertson's Word Pictures in the New Testament, Electronic Database. Copyright © 1997, 2003 by Biblesoft, Inc. Robertson's Word Pictures in

the New Testament. Copyright © 1985 by Broadman Press.

UBS New Testament Handbook Series. Copyright © 1961-1997, by United Bible Societies.

Vincent's Word Studies in the New Testament, Electronic Database. Copyright © 1997, 2003, 2005 by Biblesoft, Inc. All rights reserved.

Wuest's Word Studies from the Greek New Testament, Copyright 1940-55 by Wm. B. Eerdmans Publishing Co. Copyrights © renewed 1968-73 by Jeannette I. Wuest. All rights reserved.

Vine's Expository Dictionary of Biblical Words, Copyright © 1985, Thomas Nelson Publishers.)

Biblesoft's New Exhaustive Strong's Numbers and Concordance with Expanded Greek-Hebrew Dictionary. Copyright © 1994, 2003 Biblesoft, Inc. and International Bible Translators, Inc.

Thayer's Greek Lexicon, Electronic Database. Copyright © 2000, 2003 by Biblesoft, Inc. All rights reserved.

Greek-English Lexicon Based on Semantic Domain. Copyright © 1988 United Bible Societies, New York. Used by permission.

Brown-Driver-Briggs Hebrew and English Lexicon, Unabridged, Electronic Database. Copyright © 2002, 2003 by Biblesoft, Inc.

The Online Bible Thayer's Greek Lexicon and Brown Driver & Briggs Hebrew Lexicon, Copyright © 1993,

Woodside Bible Fellowship, Ontario, Canada. Licensed from the Institute for Creation Research.

Theological Wordbook of the Old Testament. Copyright © 1980 by the Moody Bible Institute of Chicago

« ወንጌል ደግሞ በራሱ ሰዎችን ሊያድን ፣ በደህንነትም ሊጠብቃቸው ፣ በመጨረሻም ወደ ክብር ሊያደርሳቸው የሚችል ሙሉ ኃይል አለው » ሮሜ 1:16

# ለቤቱ ከፅድቅህ የተነሳ ክብርህን እንዳስተውል እርዳኝ !